# እምነት ሲመዘን



በስናፍጭ ቅንጣት ሚዛን ሲለካ የሚያስፈልገኝን
የእምነት መጠን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ዶክተር መንግሥቱ ለማ

# እምነት ሲመዘን

በሰናፍጭ ቅንጣት ሚዛን ሲለካ የሚያስፈልገኝን
የእምነት መጠን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ዶክተር መንግሥቱ ለማ

እምነት ሲመዘን

© ጥር 2012 መንግሥቱ ለማ
የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

የሽፋን ዲዛይን
ዮናስ ወልደጻድቅ

ዶ/ር መንግሥቱ ለማ ከረጅም ዓመታት አገልግሎቱ ከአካበተው ልምምዱና ግንዛቤው ይህቺን "እምነት ሲመዘን" የተባለችውን መጽሐፍ አዘጋጅቶ አቅርቦልናል።

እምነት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንነታቸውና ትርጉማቸው ከተሰጡ ጥቂት ነገሮች አንዱ ሲሆን (ዕብ፡11:1) በአማኝ ሕይወት ውስጥ ዋና አስፈላጊ ነገር ነው። ያለ እምነት ደስተኛ ሆኖ መኖር አይቻልም፤ ያለ እምነት የእግዚአብሔርን ልብ የሚነካ ፀሎት መፀለይ አይቻልም፤ ያለ እምነት ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ማድረግ አይቻልም፤ በቃሉም እንደተባለው፥

"ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም" ዕብ. 11፤6።

እምነት መንፈሳዊውን ነገር የምንረዳበትና እግዚአብሔርን ለማየት የምንችልበት ዓይን ነው። እምነትት ጌታን የምንዳስስበትና የልብሱን ጫፍ የምንይዝበት እጅ ነው። እምነት ጌታ ምን ያህል ጣፋጭ እንደሆነ የምንቀምስበት ምላስ ነው። እምነት ወደ ጌታ የምንቀርብበትና በፊቱ የምንራመድበት እግር ነው።

ወንድማችን ዶ/ር መንግሥቱ ለማ በዚህች መጽሐፍ ስለ እምነት ምንነት፤ ስለ እምነት ዓይነቶች፤ እምነት ስለ ሚገጥሙት ተግዳሮቶችና መፍትሄአቸው፤ እና እምነትም ከፈቃዳችን ጋር ስላለው ግንኙነት ያብራራል። ስለዚህ፥ አማኞች ሁሉ ሊያነቡት የተገባ መጽሐፍ ነው።

ፓ/ር፤ ዶ/ር፤ ተስፋ ወርቅነህ

## ለውድ ባለቤቴ ለኤልሲ

የሰናፍጭ ቅንጣት ትንሽ እምነት ይዘሽ
ይሆናል ይሳካል ብለሽ ተከራክርሽ፤
እልፍ አዕላፍ ያህል አድጋ ያቺ እምነትሽ
ይኸውልሽ እንቺ ውጤቷን ላሳይሽ

# ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ታትሞ እንዲወጣ እርዳታና ጥረት ያደረጉ ሰዎች ብዙ ናቸው።

ሄኖክ ግርማ፣ ከመጀመሪያ ጀምሮ ስዕሎቹን በኮምፒውተር በመሳል፤ በአማርኛ ሶፍት ዌር አጠቃቀምና ምርጫ ምክር በመስጠት፤ በኋላም መጽሐፉን አታሚው በሚፈልገው መንገድ እኔ በማላውቀው የኮምፒውተር ፕሮግራም በማዘጋጀት፤ ረጂም ጊዜ በመውሰድ ልክ እንደራሱ ሥራ በጥራትም ጉድለት እንዳይኖረው በመንከባከብ ከጠበኩት በላይ እርዳታ ስላደረገልኝ ባለውለታዬ ነው።

ዮናስ ወልደጻድቅ፣ የሽፋኑን ዲዛይን የሰራልኝ ነው። ገና በመጀመሪያ ይህንን አሳብ ሳካፍለው "it will be my honor" ብሎ ያበረታታኝ ትዝ ይለኛል። ከዚያም የተለያዩ አሳቦች ሰጠው ሁሉንም በማስተናገድ የተለያዩየዲዛይንሥራዎችሰርቶልኝበመጨረሻይህአሁንየቀረበውንሽፋን ሰራልኝ። ዮናስ በስራው ብቻ ሳይሆን በሚያበረታታ ንግግሩም አግዞኛል።

አቢይ ግርማ፣ የሊቶ ማተሚያ ቤት ባለቤት በመጽሐፉ የገጾች አቀራርብና የፊደላት ምርጫ ብቻ ሳይሆን ጥራቱ የተጠበቀ መጽሐፍ እንዲሆን በምክሩ ለጋስ ነበር። ከሁሉም በላይ ግን ገና መጀመሪያ ሄጄ የነጋገርኩት ቀን ነው "መጽሐፉ ይታተማል" የሚል ማረጋገጫ የሰጠኝ። ያ አባባል የእምነት ቃል ሆነልኝ።

ፓስተሬ ዶክተር ተሰፋ ወርቅነህ፣ በተጣበበ የአውድ ዓመት ፕሮግራሙ መካከል አንብቦ መጽሐፉን ለመዘከር ጊዜ ስለሰጠኝ፤ የባለቤቴ አባት አቶ አበበ ጎርፌና ወዳጄና የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ አቤሴሎም ሞገስ አንብበው በእርማትና ማስተካከል ስለረዱኝ የልብ ምስጋና ይገባቸዋል።

## ማውጫ


**ክፍል አንድ** 13

የእምነት ምክንያቶች

ምዕራፍ አንድ እምነት ከእግዚአብሔር እንጻር 15

ምዕራፍ ሁለት ለእምነት የሚያስፈልጉ ግንዛቤዎች 31

**ክፍል ሁለት** 53

የእምነት መንገዶች

ምዕራፍ ሶስት የእምነት አሠራር 55

ምዕራፍ አራት ተግባራዊ ዘዴዎችና ሞዴሎች 79

**ክፍል ሶስት** 107

የእምነት እንቅፋቶች

ምዕራፍ አምስት የባህል ቅርሶች 109

ምዕራፍ ስድስት መንፈሳዊ ውጊያ 131

ምዕራፍ ሰባት የስህተት ትምህርቶች (ኑፋቄ) 157

ምዕራፍ ስምንት መጠራጠር 183

ምዕራፍ ዘጠኝ ብቸኝነት 213

**ክፍል አራት** 227

የእምነት ጥልቅ ጉዳዮች

ምዕራፍ አስር የእምነት ስጦታ 229

ምዕራፍ አስራ አንድ ኦ ነጻነት 241

ምዕራፍ አስራ ሁለት ፈቃድና ፍቅር 251

ምዕራፍ አስራ ሶስት ኑ አብረን! የመጨረሻ ጥሪ 261






## ምናብን ለመኮርኮር
(To Tickle the imagination)

Imagination የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የአማርኛው መዝገበ ቃላት "ምናብ" ብሎ ነው የተረጎመው፣ (በአምስቱ የስሜት አውታሮች ማለትም በማየት፣ በመስማት፤ በማሽተት፤ በመቅመስ እና በመዳሰስ የማይደረስባቸውን ነገሮች በዓይነ ሕሊና እንዲደረስባቸው የሚያደርግ ተፈጥሮአዊ ኃይል) ይህ ትርጉም ስለተስማማኝ ምናብ የሚለውን ቃል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሰፊው ተጠቅሜበታለሁ። በተለይ አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉ ለብቻቸው በሳጥን የተቀመጡ አስራ ሁለት ጥያቄዎች አሉ። ጥያቄው በቀረበበት አካባቢ ለተገለጸው እውነት ከመጽሐፉ ወጣ ብሎ ለማሰብ ታቅዶ የቀረበ ስለ ሆነ ነው "ምናብን ለመኮርኮር" የሚል አረዕስት የተሰጠው።

## መንደርደሪያ

አስተማሪው ዛሬም እንደልማዱ ለተማሪዎቹ ሌላ ታሪክ ነገራቸው። አስተማሪው ብዙ ጊዜ ትምህርቱን በሚያስደንቁና ልብ በሚሰቅሉ ታሪኮች ስለሚጀምር በሙያው ምስጉን ነው። ይህ የአስተማሪው ታሪክ የመንገር ችሎታው ተማሪዎቹን ሁልጊዜ አያጓጓ አፋቸውን ያስከፍታቸው ነበር።

የዛሬውም ሁኔታ ከዚያ የተለየ አልነበረም። ፍርድ በመፈለግ ስለምትዋትት አንዲት የምታሳዝን አሮጊት ሴት እና ከሰው ሁሉ በላይ የሆነ ስለሚመስለው እግዚአብሔርን ስለማይፈራ አንድ ግፈኛ ዳኛ ተረከላቸው። አሮጊቷ ግን ዋዛ አልነበረችም፤ ዳኛው ችላ ቢላትም፤ ቢንቃትም፤ ተስፋ ቢያስቆርጣትም፤ እርሷ ግን ባለማቋረጥ ትወተውተው እንደነበር መምህሩ ተረከላቸው። በመጨረሻም የአሮጊቷ ውትወታ ስለበዛበት ዳኛው እንደፈረደላት ነገራቸው።

ታሪኩ የፀሎት ታሪክ ነበር፣ ተግቶ ሳይታክቱ ስለ መጸለይ የሚያስረዳ ታሪክ ነው። አስተማሪው ግን መጨረሻ ላይ የታሪኩን አቅጣጫ ለወጥ አድርጎ አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው

> *"የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?"*
> *(ሉቃ. 18:8)*

አስተማሪው ጌታ የሱስ ይህንን ጥያቄ የጠየቀው በጊዜ ወደፊት ተሻግሮ እንደገና የሚመለስበትን ጊዜ ተመልክቶ በዚያን ጊዜ የሚኖረው የእምነት ሁኔታ አሳስቦት ይመስለል። ከጥያቄው ሌላ የምንረዳው ነገር ተመልሶ ሲመጣ የሚፈልገው ዋናው ነገር እምነት መሆኑን ነው። ጥያቄው ግን መልሶ በእኛም ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች ያስነሳል።

ለምን ጌታ ይህንን ጥያቄ ጠየቀ?
እምነትስ ለምን እንዲህ አስፈላጊ ነገር ሆነ?





ይህንና ይህንን የመሳሰሉ አሳቦችን ዘርዝርን በዚህ መጽሐፍ ለማየት እንሞክራለን። ባገለገልኩባቸው ቤተ ክርስቲያኖች ወይም ሕብረቶች ያስተዋልኩት አንድ ነገር አለ። ይኸውም የማገኛቸው ሰዎች ስለ እምነት የተለያየ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ነው።

ስለ እምነት ጥሩ ግንዛቤ ያላቸውን ሰዎች ያህል ስለ እምነት በጣም የተዛባ መረዳት ያላቸውም አሉ። "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ እንዳይሆንብኝ ስጨብጠው እምነዋለሁ" የምትል አንዲት እህት አውቃለሁ፤ ይህቺ እህት ታዲያ በእግዚአብሔር ቤት የቆየች ነች።

ስለዚህ በመጽሐፉ የመጀመሪያ ሁለት ክፍሎች ሰዎች ስለ እምነት ያላቸውን አንዳንድ የተዛባ አመለካከት ለማቅናትና ለማጥራት ሙከራ እናደርጋልን። ይህንን እያደረግን ስንሄድ አግረ መንገዳችንን ደግሞ ተግባራዊ የሆኑ የእምነት እርምጃዎችን እንጠቅሳለን። ከዚያም እምነት የሚሰራባቸውን የተለያዩ መንገዶች የሚገልጽ ሁሉ አቀፍ ወደሆነ መረዳት እንመጣለን ብዬ አምናለሁ።

በሶስተኛው ክፍል እምነት ለምን አስቸጋሪ ልምምድ እንደሆነ በመግለጽ እንጀምርና በዚያ ላይ ጨምረን ዛሬ ለእምነት ጠላቶች የሆኑ አንዳንድ ነገሮች ላይ እናተኩራለን። ሚዛናዊ የሆኑ መፍትሄዎችንም አግረ መንገዳችንን እንጠቅሳለን።

አራተኛውና የመጨረሻው የመጽሐፍዋ ክፍል ጠለቅ ባሉ የእምነት አሳቦች ላይ ይውላል።

ይህ መጽሐፍ አንባቢውን ተግባራዊ እምነት እንዲኖረው ይጠይቀዋል፤ ይገዳደረዋል፤ ያበረታታዋል መንገዱንም ያሳየዋል ብዬ አምናለሁ። እምነትን ለመረዳት ላለው መዘበራረቅም ተገቢውን ትኩረት በመስጠት አንባቢው እውነተኛ የእምነትን መንገድ እንዲለማመድ ያደፋፍረዋል፣ የእምነት እርምጃ እንዲወስድም ይገፋፋዋል።

እንግዲህ እምነቴና ጸሎቴ አንባቢው ስለእምነት ላለው ጥያቄም ሆነ አለመረዳት በትንሹም ቢሆን መልስ ያገኛል የሚል ነው። እምነትን በሚመለከት የተዘጋበትንም ምስጢር የሚከፍትለት ቁልፍ ያገኝበታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉ የእምነት አይነቶች በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ። እነኚህን የእምነት አይነቶች ለይቶ ማወቁ በዚህ መጽሐፍ የሚተላለፈውን መልእክት ለመረዳት ስለሚያግዝ እስቲ በአጭሩም ቢሆን እንግለጻቸው።

የመጀመሪያው "እምነት" በቃሉ ብቻ የሚገለጸው የእውነት ስብስብ ነው። ይህም በእንግሊዝኛው "The Faith" የሚሉት ነው። ይህም የሚገልጸው ስለ እግዚአብሔር የምናውቃቸውን የእምነት ስብሳቤዎች ሲሆን ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያኖች ይህንን የመጀመሪያውን የእምነት አይነት "የእምነት አንቀጽ" ወይም "የእምነት ኑዛዜ" ብለው ይጠሩታል። ስለ መሠረተ እምነት (Doctrine) እና ስለ ጭፍን እምነት (Dogma) ያሉትን የእምነት ገለጻዎች በቦታቸው እንመለከታቸዋለን። ለጊዜው ግን "እምነት" ክርስቲያኖች ስለእግዚአብሔር ትክክለኛ እውነት ነው ብለው የተቀበሉትና የሚከተሉት ነው ብለን እንለፈው።

ሁለተኛው "የሚያድን እምነት" "Saving Faith" የሚባለው ነው። ይኸኛው የእምነት አይነት እግዚአብሔር ለሰዎች የሚሰጠው ችሎታ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ዘር ሁሉ የኃጢአትን ዋጋ ስለከፈለ ኃጢአትን ሁሉ ይቅር ማለት የሚችል ጌታ መሆኑን ለማመንና ለመቀበል የሚያስችል፤ ጌታ ኢየሱስን የሕይወት ጌታ አድርጎ በእምነት መቀበልም የዘለአለም ሕይወት ለማግኘት ያበቃል የሚል እምነት ነው።

ሶስተኛው የእምነት ስጦታ "The Gift Faith" ነው። ይህም የታመቀ የእምነት ችሎታ ነው። ከችሎታችንና ከግምታችን በላይ የሆነ፤ ሊሆን የማይችለውን ነገር ይሆናል ብሎ ለመቀበል የሚያስችል የእምነት ችሎታ ነው። ይህንንም ሳብ ለብቻው በአንድ ክፍል እናየዋለን።

አራተኛው እኔ የቀን ተቀን እምነት (Normal Faith) የምለው ነው (ይህ እምነት ከእምነት ስጦታ ጋር ያለውን ልዩነት ለማሳየት በመጽሐፉ ወስጥ አንዳንድ ቦታ ተራ እምነት ብዬ ጠቅሼዋለሁ)። ማንም ሰው በየቀኑ ከእግዚአብሔርም ሆነ





ከአካባቢው ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ያተኮረ እምነት ነው። ይህ አይነቱ እምነት በመጽሐፉ ሌሎች ክፍሎችም ባሉት ሳቦች ውስጥም የተጠቀሰ ስለሆነ ብዙውን የመጽሐፉን ክፍል የያዘ ነው።

እንጋፋው ዘማሪ አዲሱ ወርቁ አንድ የታወቀ የእምነት መዝሙር አለው።

> እንዴ ቆርጠናል!
> ተከትለናል!
> በእምነት ጀምረን!
> በድል እናበቃልን!

እስቲ እኛም `ይህንን መጽሐፍ እግዚአብሔር ስለ እምነት ያስተምረኛል በሚል ቆራጥ ውሳኔ እንጀምረው። እግዚአብሔር ብዙ የእምነት ድሎችን ለእኛ ለመስጠት ግን መጽሐፉን እንብበን እስክናበቃ የሚጠብቅ አይመስለኝም። ስለ እያንዳንዳችሁ ያለኝ ጸሎት ግን መጽሐፉን እንብባችሁ በምትጨርሱበት ጊዜ ልዩ የሆነ የእምነት ድል እንድትቀዳጁ ነው።

መልካም ንባብ !

## ክፍል አንድ
## የእምነት ምክንያቶች

ይህ የመጀመሪያው ክፍል ብዙዎቻችን ስለ እምነት የምናውቀውን ነው በተቀናበረ እና በተደራጀ መልክ የሚያቅርበው። ቀላል ይመስል ይሆናል፤ ግን እምነታችን እንዲሠራ እነኚህ ግንዛቤዎች አስፈላጊ ናቸው። እምነትን እግዚአብሔር እንደሚያየው ለማየት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እናያለን፤ ከዚያም እኛ አማኞች ስለ እምነት ሊኖረን የሚገባውን መረዳቶች እንከልሳለን።

# ምዕራፍ አንድ

## እምነት ከእግዚአብሔር አንጻር

የእኛ እምነት ለእግዚአብሔር ምን ያደርግለታል? ብሎ መጠየቅ ያልተለመደ ጥያቄ ቢመስልም አስፈላጊ ጥያቄ ነው። እምነት ለእኛ ስለሚያደርግልን መልካም ነገር በመማርና በማውራት ብዙ ስለምንያዝ እምነታችን ለእግዚአብሔር ስለሚያደርገው ነገር ብዙ አንመረምርም። መኖራችን ለእግዚአብሔር ክብር መሆኑን ስናውቅ ግን እያንዳንዱ መንፈሳዊ ልምምዳችንም ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔርም የሚያደርገው ነገር እንዳለ እንረዳለን። የኛ መንፈሳዊ ልምምድ የእግዚአብሔርን ሕልውናና ፍጹም በሆነው በበላይነቱ ላይ የሚጨምረው ወይም የሚቀንሰው አለ ለማለት ሳይሆን እግዚአብሔር ከኛ ጋር ባለው ግንኙነት ለራሱ የወሰናቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ ለማለት ነው።

1. እምነታችን እግዚአብሔርን ያስደስተዋል
2. እምነታችን እግዚአብሔርን እንዲያደርግ ይፈታዋል
3. ፍላጎቱን ያሟላዋል
4. ያረካዋል
5. ሥራውን ያሰፋዋል
6. ይገልጸዋል
7. ፍርዱን ይገታዋል

### 1. እምነት ያስደስተዋል

እምነታችን ለእግዚአብሔር የሚያደርገው የመጀመሪያው ነገር ማስደሰት ነው። ዕብራውያን 11:6 ይህንን አሳብ በገልጽ ያስቀምጠዋል *“ደግሞም ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት”* ።ልቡን ከፍቶ ላዳመጠ ሁሉ በዚህ ጥቅስ ውስጥ የእግዚአብሔር የልግስናው ድምጽ

ጎላ ብሎ ይሰማል። ይህ ጥቅስ ጎላ አድርጎ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመባረክ ያለውን ጉጉትና ፍላጎት ነው የሚያሳየው። እግዚአብሔር ሊባርከን አጥብቆ ይፈልጋል። ይህንን ለማድረግ እጁን የሚፈታው ምንድነው? እምነት ! ለዚህ ነው እግዚአብሔር ደስ እንዲሰኝ እምነት አስፈላጊ የሆነው።

የምንከተለውና የምናመልከው አምላክ በቸርነት የተሞላ ስለሆነ ልጆቹን መባረክ ደስ ያሰኘዋል።እግዚአብሔርን በእምነት እንዲባርከን ብንተባበረው እርሱ ሊባርከን ደስተኛ ነው።

ብዙሰዎችለረጂምጊዜየሚያስቸግራቸውየእምነትአይነትበእግዚአብሔርተቀባይነት ማግኘታቸውን ማመን ነው። ሰዎች ራሳቸውን እየናቁ፤ በሰዎች ኢይጭ እየተባሉ ካሉ፤ እግዚአብሔር ወዶ እንደተቀበላቸው ማመን ያቅታቸዋል። እግዚአብሔር ግን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይቀበላቸዋል። እነርሱ ግን የእግዚአብሔርን ተቀባይነት መቀበል ስለሚያስቸግራቸው እግዚአብሔርን ያስከፋታል፤ በእነርሱ ሳይሆን የእርሱን ተቀባይነት እምቢ ማለታቸው ነው የሚያስከፋው።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው ይህንን ራስን የመቀበል ችግር በምሳሌ እንዲህ ብለው ገለጹት። "እግሬን በጣም ዘርግቼ ብራመድ አምስት ጫማ ያህል መራመድ እችላለሁ። ሁለት ረጃጅም ሕንጻዎች የአምስት ጫማ እርቀት ቢኖራቸው ካንዱ ሕንጻ አናት ወደሌላው ሕንጻ አናት መራመድ እችላለሁ። የሁለቱ ሕንጻዎች ርቀት ግን ስድስት ጫማ ቢሆን መራመድ ሳይሆን መዝለል ይኖርብኛል። ራስን መቀበል የስድስቱ ጫማ አይነት ርቀት ነው፤ የሚጠይቀው መራመድ ብቻ ስይሆን መዝለል ነው። ከችሎታችን በላይ አይደለም ግን የበለጠ እንድናደርግ ይጠይቀናል። መዝለል ያስፈልገናል። እርግጠኛ ከሆንበትና ከተመቻቸንበት ሁኔታ ውስጥ በመውጣት ደርሰንበት የማናውቀው ቦታ ለመድረስ አድርገን የማናውቀውን ነገር ማድረግ ማለት ነው።

ያ ዝላይ እምነት ነው። ይህ እምነት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ከመሆኑም በላይ ለራሳችንም ባለን ግምት ላይ አስደናቂ ለውጥ እንዲያመጣ እግዚአብሔርን ያስችለዋል። ከዚያ በሀዋላ ራሳችሁን "አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ"





ብላችሁ ማቆላመጥ ትጀምራላችሁ። ያኔ ነገሮች መለዋወጥ ይጀምራሉ። እምነት እግዚአብሔር የልቡን እንዲያሳየን ይማርከዋል።

## 2. እምነት ይፈታዋል

እምነት ለእግዚአብሔር የሚያደርገው ሁለተኛው ነገር እግዚአብሔር እንዲያደርግ ይፈታዋል። እምነት በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ላለው ስምምነት ወኪል ነው። ሰውን ከአቅሙ በላይ እንዲዘረጋ የሚያስችለው እምነት ነው። ችግሮች ምንም ያሀል የተመሰቃቀሉ ቢሆኑም ከእኛ ችሎታ ውጪ ያሉትን መፍትሔዎች አግኝተን ልንጠቀምባቸው እንድንችል የሚያደርገን እምነት ነው። ተዘግቶ ያለውን የመልስ በር የምንከፍትበት ቁልፍ እምነት ነው።

እግዚአብሔር በእኛ እምነት ላይ ያዋለው ካፒታል (investment) አለው። ፍጹም አፍቃሪ፤ ሙሉ ችሎታ ያለው አምላክ ስለሆነ ሊያደርግ የፈቀደውን እንዲያደርግ ይፈታዋል፤ ይህ መንፈሳዊ ምስጢር ነው። እምነት ሊያደርግ የሚወደውን መልካም ነገር እንዲያደርግ የሚያስችለውና የሚፈታው ስለሆነ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በእምነት የሚተባበሩትን ይፈልጋል።

## 3. እምነት ያረካዋል

እግዚአብሔር እምነትን በእኛ ላይ ሲያይ ስለሚያረካውና ስለሚፈነቅለው ሊያደርግ የሚወደውን እንዲያደርግ አሳቡን ያሟላዋል። ልጆቻችን ገና መራመድ ሲማሩና ሲጀምሩ ቆም ብለው እንደገና ይወድቃሉ። ስናለማምዳቸው ግን እጆቻችንን ዘርግተን ትንሽ ራቅ ብለን እንቆምና ኑ እንላቸዋለን። አንድ እርምጃ ሲራመዱ ካየን ደስ ይለንና እናቅፋቸዋለን፤ እንስቃለን በድርጊታቸው እንረካለን። መናገር ሲጀምሩ፣ ሌላ ሌላ ድርጊትም ሲማሩ ያረኩናል። የእያንዳንዱ የእድገታቸው እርምጃ በእኛ በወላጆቻቸው ውስጥ ትልቅ የመሟላት ስሜት ይፈጥራል።

እምነት ልጆቻችንን በሕጻንነታቸው "ኑ!" ብለን ስንጠራቸው የሚወስዱት ያ የመጀመሪያ ትንሽ እርምጃ ነው። አንዳንዴ እግዚአብሔር ከእኛ ሩቅ የሆነ ይመስለናል፤ ያ ከሆነ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው ከፍ ያለ የእድገት ወይም የእምነት ደረጃ አለ ማለት ነው። ያንን ስናሟላ እርሱን ያረካዋል።

ይህ ማለት ደግሞ የእግዚአብሔር እርካታ በእኛ እምነት ብቻ የተደገፈ ነው ማለት እንዳልሆነ መግለጽ እወዳለሁ። ያ ከሆነ የአምላክነት ባሕሪው የእርሱ ሳይሆን የእኛ ሆነ ማለት ነው።

ለማለት የምፈልገው ግን እግዚአብሔር የእኛን የእምነት መተባበር ለማግኘት ሲል አንዳንዴ ራሱን ከማድረግ ይቆጥባል ወይም ይገታል። ይህ የእድገት ምስጢር ነው።ጌታ የሱስ በገዛ አገሩ ሕዝቦች መካከል እምነትን በማጣቱ መደነቅ ብቻ ሳይሆን ማድረግ እንኳን አልቻለም

*"እዚያም በጥቂት ሕመምተኞች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወሱ በስተቀር ምንም ታምራት ሊሰራ አልቻለም ባለማመናቸውም ተደነቀ"*
*(ማር 6፤5-6)።*

ተአምር የማድረግ ኃይል አጣ ማለት ሳይሆን፤ ተአምር እንዲያደርግ የሚገፋፋው እምነት በሰዎቹ ውስጥ አጣ ማለት ነው። ምክንያቱም ጌታ የሱስ ሁሉን የማድረግ ኃይል አለው፤ አንዳንዴ ግን ራሱን በእምነታችን መጠን ይወስነዋል።

ጌታ የሱስ ለምኑ፤ ፈልጉ፤ አንኳኩ የሚለውን የጸሎት ሞዴል ሲያስተምር፤ (ማቴ. 7፤7) ከእርሱ ጋር ሊኖረን ስለሚገባው ሶስት አይነት ጸሎታዊ ግንኙነቶች ነው የተናገረው።

- የመለመን ትኩረት መቀበል ነው
- የመፈለግ ትኩረት ማግኘት ነው
- የማንኳኳት ትኩረት ማስከፈት ነው





እግዚአብሔር እንድለምነው የሚፈልገው እንድንበረታታና እንድንተጋ ስለሚፈልግ ነው። በልመና ውስጥ መለማመጥ ስላለ ያ ትጋትን ይጠይቃል። ስለዚህ እግዚአብሔር ትጋትን እንድንለማመድ ስለሚፈልግ አንዳንዴ ለመልሱ ዘግየት ይላል። ይህ መንፈሳዊ ምስጢር ነው።

እግዚአብሔር እንድንፈልገው የሚያደርገን፤ ፍለጋ ራሱ መንፈሳዊ ጥረት ስለሆነ ነው። እግዚአብሔርን አጥብቀን ከምንፈልግባቸው መንገዶች አንዱ ጥሞና ሊሆን ይችላል። በትዕግስት በእግዚአብሔር ዘንድ መቆየት፤ እስከምናገኘው ድረስ መጠበቅ፤ አንዳንዴ ምንም አጥብቀን ብንፈልገው የማይገኝ የሚመስልበት ደረጃ ላይ እንኳን እንደርሳለን። መልዕክቱ ፍለጋሽን ቀጥይ፤ ፍለጋህን ቀጥል ነው።

የማንኳኳት ትኩረት ከውስጥ ያለው ሰምቶ እንዲከፍት ለማድረግ ነው። ከውስጥ ያለው ሰምቶ እስኪከፍት ድረስ ማንኳኳትን መቀጠል ያስፈልጋል። አለመታከት ወይም አለመሰልቸት ነው የማንኳኳት ምስጢር። ጌታ የሱስ በሉቃስ 18 ውስጥ ያስተማረው የመበለቲቱ ታሪክ የዚህ የማንኳኳት ሞዴል ፍጹም የሆነ ገለጻ ነው።

ይህን የጸሎት ሞዴል ስንከተል የእምነት ልምምዳችን እያደገ ስለሆነ እግዚአብሔርን እናረካዋለን። ከእኛ የራቀውን ለማውረድ ተንጠራርተን በእግር ጥፍራችን ቆመን ስንፈልግ ሲያየን ደስ ይሰኛል፤ ይረካል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ የፍቅር ባሕሪ ተወዳጁን ማስደሰትና መባረክ ነው። ስለዚህ ተወዳጁ (እኔና እናንተ) ካልተባረከ ፍቅር አልተሙዋለም ማለት ነው። እምነት እግዚአብሔር ይህንን መምዋለት እንዲለማመድ ያስችለዋል።

አንድ ጊዜ እስራኤላውያን ጌታ የሱስን ጥያቄ ጠየቁት፤ *"ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?"* አሉት እርሱም በላከው ታምኑ ዘንድ *ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው"* ዮሐ 6፤28-29። ይህ ሥራ ተብሎ በዚህ ቦታ የተተረጎመው ቃል አለታዊ ተግባር (occupation) የሚለው ነው፤ በሌላ አነጋገር አለታዊ ሥራችን ወይም ተግባራችን እምነት ነው። ሁለት ሰዎች ተዋወቁና ወሬ ጀመሩ ይባላል፤ አንደኛው ሁለተኛውን

"የምትሠራው ሥራ ምንድነው?" ብሎ ጠየቀው;
ሁለተኛው "አማኝ ነኝ" አለ።
"ያንን ማለቴ ሳይሆን ሥራህ ምንድነው?"
"አማኝ ነኝ፤ አምናለሁ" አለው ሁለተኛው እንደገና፤
የመጀመሪያው ሰው ትንሽ ተረበሸና "ምን ማለቴ እንደሆን አውቀሃል?" ሲለው።

> "ሥራዬ ማመን ወይም በእምነት መኖር ነው፥ ወጪዬን ለመሸፈን ግን የቧንቧ ጥገና ሥራ እሠራለሁ።" በማለት መለሰለት።

ሁለተኛው ሰው ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክት ነበር፤ ኑሮው በገቢው ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በእምነት የሚኖር መሆኑን ለማሳየት ነው። እንዲህ ያለ አመለካከት ሲኖረን እግዚአብሔርን ያረካዋል። በእምነት የተመሠረተ ኑሮ ሲኖረን በገንዘብ ላይ ትኩረት ያንንም ተከትሎ የሚመጣው ድርቀት፤መሸማቀቅ እና ማፈር ቦታ አይኖረውም፤ በእምነት መኖር ማለት ያ ነው። እግዚአብሔር በእምነታችን ልቡ ይሞላል፤ ፈቃዱ ይፈጸማል፤ አቅዱም ይረካል። አንዳንዴ ግን የእግዚአብሔር የረጅም ጊዜ አቅድ ከኛ የአጭር ጊዜ ፍላጎት ጋር አይታረቅም። ይህ ትውልድ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ችኩል "የአሁን" ትውልድ ሆኗል።

ቡናችን ኢንስታንት
ገበያችን ኪዎስክ
ምግባችን ፋስት ፉድ
ምድጃችን ማይክሮዌቭ

ሁሉ ነገር ቶሎ ቶሎ በሆነበት ህብረተሰብ የረጂም ጊዜ ፕላን ለብዙዎቻችን አይዋጥልንም; እምነት ግን በውስጡ ቆይታ፤ ትዕግስት፤ ትጋት አለበት። እምነት ሥራችን ከሆነ ሥራችን አንዳንዱ አሁን የሚፈጸም ሲሆን አንዳንዱ ደግሞ የረጂም ጊዜ ፕላን ይጠይቃል። እምነት ሂደት ነው፤ አይቆምም፤ አይቋረጥም። ስለዚህ ነው ጌታ የሱስ ስለ ትጋት ያስተማረው፤ ትጋት ደግሞ በትርጉሙ የሚፈጸም ወይም የሚያበቃ አይደለም። ትጋት የሚለካው በጊዜ መርዘም ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብ





ጥንካሬና በግምት ስፋትም ጭምር ነው። በሉቃስ 18፤1-5 ተግታ የለመነችው የመበለት ምሳሌ፤ ምናልባት ለወር ወይም ለሁለት ወር ተመላልሳ ይሆናል። ለእርሷ ግን የብዙ ጊዜ ምናልባትም በብዙ ወራት የሚቆጠር ልመና ሆኖ ሳይሰማት አይቀርም። ወይም በእኩለ ሌሊት ወደ ጎረቤቱ ሄዶ ያንኳኳው ሰው እምቢ እየተባለ ማንኳኳቱን የቀጠለው ለአምስት ደቂቃ ይሆናል፤ ግን በግምቱ የረጂም ጊዜ ትጋት ጠይቆታል (ሉቃ. 11፤5-8)። ትጋት (persistence or importunity) ሥረ ቃሉ በግሪክ (Anadia) ሲሆን ቃሉ እንዳለ ሲተረጎም "ሐፍረተቢስ" ወይም "ያለሐፍረት" ነው። ቃሉ ሁለት አቀራረብ አለው።

አንደኛው ሰው ኃጢአቱ ሁሉ ይቅር ስለተባለለት ያለ ምንም ሀፍረት መቅረብ መቻሉ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሰውዬው ያለበት ሁኔታ ወይም ችግር የህብረተሰቡን ወግ ወይም የራሱን ይሉኝታ ያለፈ ስለሆነ አይናውጣ ሆኗል ማለት ነው። ጌታ የሱስ ሁለቱንም አይነት ሐፍረተቢስነት ይቀበላል፤ ይህ ሐፍረተቢስነት የእምነት እድገት ስለሆነ ያረካዋል። ልጆቻችን አንዳንዴ ማድረግ የማይገባንን ነገር እንኳን የሚያስደርጉን በዚህ ድፍረት መጥተው ስለሚጠይቁን እኮ ነው። እግዚአብሔር ግን ያለ ሀፍረት እንድንጠይቀው የሚያደርገን ለመስጠት ሳይፈልግ ቀርቶ ሳይሆን ሊሰጠን ስለሚወድ ነው፤ በእምነት እንድናድግ እየጠበቀን ነው።

ጌታ የሱስ እግዚአብሔርን ስለማይፈራው ዳኛና ለጎረቤቱ ግድ የሌለውን ሰው ምሳሌ ስለትጋት ለማስተማር መጠቀሙ የሚያስደንቅ አመለካከት ነው። እግዚአብሔር እንደ ዳኛውም እንደ ጎረቤቱም አይደለም፤ ግን እኛ አንዳንዴ እንደዚያ ሆኖ ስለሚሰማን እና ጌታ የሱስም ያንን ስሜታችንን ስለሚያውቅ ይመስለኛል እንዲህ አይነት ባሕርያት የተጠቀመው። ለዚህ ነው "ለምኑ፣ ፈልጉ፣ አንኳኩ" የሚሉትን ቃላት የተጠቀመው፤ የኛ ድርሻ ያለመታከት ያንን ማድረግ ነው። የእግዚአብሔር ድርሻ በሉቃስ 18፤ 7-8 ተገልጿል

> "እግዚአብሔር ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮሁ ምርጦቹ አይፈርድላቸውንምን? ከመጠን በላይስ ችላ ይላቸዋልን? እላችኋለሁ ፈጥኖ ይደርስላቸዋል"

ጥያቄው ግን አሁንም "ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?"

## 4. እምነት ሥራውን ያስፋፋዋል

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔር አንዱ ሥራ

"ያልነበረውን እንደነበረ የሚያደርግ" ሮሜ 4:17 ብሎ ነው የገለጸው።

ምንም ነገር አልነበረም፣ እግዚአብሔር ሲሠራ ግን ነገር ሆነ፤ በተለይ ሥነፍጥረትን ስናስብና ዘፍጥረትን ስናነብ ይህ አሳብ ግልጽ ይሆናል።

ላመኑበትም የሚከናወነው ሁኔታ ይህ ነው። የሁኔታዎች አለመመቻቸት እግዚአብሔርን ከማድረግ አይከለክለውም። ምክንያቱም እርሱ "ያልነበረውን እንደነበረ የሚያደርግ" ነው። እምነት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚሆን አቀባባይ ሁኔታን መፍጠር ማለት ነው። እግዚአብሔር እምነትን ይሰጠናል፤ እኛ ያንን እምነት በመጠቀም የእርሱን ኃይል እናስለቅቃለን። የእርሱ ሥራ መስጠት የእኛ ሥራ ደግሞ ያንን ስጦታ መጠቀም ሲሆን በመካከል ያለውና የሚያያይዘው መስመር እምነት ነው።

እምነት የእለት ተግባራችን የሚሆነው ለዚህ ነው። በአለም ላይ የእግዚአብሔር ኃይል በጣም ያስፈልጋል። ብዙ የፖለቲካ ሰዎች፤ የመንግሥት መሪዎች፤ የኢኮኖሚና ያሶሺያል ሳይንስ አዋቂዎች ሲተምኑ በፍጥነት እያደገ ያለው የሰው ልጅ ቁጥር ብዛትና የተፈጥሮ ሐብት ሲመጣጠን የሰውን ልጅ ፍላጎት ሁሉ ለሟሟላትና ምቾቱን ለመጠበቅ ለረጂም ጊዜ የሚበቃ አይደለም ይሉናል። የተፈጥሮ ሃብት እያለቀ ሲሄድ አስቀድሞ ያንን ሃብት የፈጠረው የእግዚአብሔር ኃይል ማስፈለጉ የእምነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የምክንያትም ስሌት ነው።

ይህንን እውነት የተረዱ ብዙዎች መልሳችን ጸሎት ነው ብለው ያምናሉ፤ ወይም እንደዚያ ለማመን ተገደዋል። መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ወይም ነውጥ (revival) ካላገኘን በስተቀር የሚደረገው ጥረት ሁሉ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ ብቻ ይሆናል። ይህ





ሁኔታ በእያንዳችን ግላዊ ሕይወትም እውነት ነው። የሚጠበቅብንን ሁሉ ለሟሟላት ማንኛችንም ብቃት የለንም። ጌታ የሱስ ይህንን እውነት በማያወላውል መንገድ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል፥

*ዮሐ. 15:5" ...ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና"።*

ያለ እርሱ ምንም ማድረግ ካልቻልን በራሳችን ብቻ ለመሆን ያለን ተስፋ ቢመዘንና ቢለካ ምን ያህል የሚሆን ይመስላችኋል? ያለ እርሱ ምንም ማድረግ አለመቻላችንን ተረድተን የእርሱን እርዳታ በእምነት ስንፈልግ ግን የእርሱን ሥራ መሥራታችንና ማስፋፋታችን ነው።

## 5. እምነት ይገልፀዋል

እንዲህ አስባችሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ለመግለፅ ባይፈልግ ኖሮ ስለ እርሱ ምንም ማወቅ አንችልም ነበር። እንዲያ ቢሆን ኖሮ በጣም የሚያሳዝን ሁኔታ አይሆንም ነበር? በሰብዓዊነትና በመለኮታዊነት መካከል ያለውን ርቀት ለማጥበብ በራሳችን ችሎታውም ፍላጎቱም የለንም። እግዚአብሔር ግን ራሱን ለእኛ ለመግለጽ መረጠ። ያንን መገለጽ ለእኛ እውን የሚያደርግልን ታዲያ እምነት ነው። ለጊዜው ይህንን አሳብ እስቲ በአእምሮአችን እያሰላሰልነው እንቆይ። በሚቀጥሉት ምዕራፎች ይህንን እንዴት ማድረግ እንደምንችል በሰፊው እናያለን።እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች ገልጾአል፤ ያንን መገለጽ ለሰዎች እውን የሚያደርግልን እምነት ነው።

እግዚአብሔር ራሱን በመግለጹና ያ መገለጽ ለእኛ እውን በመሆኑ መካከል ልዩነት አለ። እግዚአብሔር ራሱን ገልጿል፤ ያ መገለጽ (revelation) ተብሎ የሚታወቀው ነው። እምነት ደግሞ ያንን መገለጽ እንድናየው ያስችለናል፤ ያ (disclose)የሚባለው ነው።ለምሳሌ የገና ስጦታ ስንሰጣጥ ሰጪው ስጦታውን ይሰጣል፤ ተቀባዩ ግን ስጦታውን ተቀብሎ ካልከፈተው ስጦታው ሳይገለጽ ይቀራል። እግዚአብሔር ራሱን በመግለጽ ስጦታ አድርጎ ሰጥቶናል፤ ያንን ስጦታ ተቀብለን በጥቅም ላይ ማዋል የእኛ ሥራ ነው ያንን ለማድረግ የሚያስችለን ችሎታ እምነት ነው።

የገና ሥጦታችንን ለመክፈት የሚያስቸኩለንን ያሀል ይሀንን ዘለዓለማዊ ሥጦታ ለመክፈት ብንጥር እግዚአብሔርን በሙላት እናውቀዋልን። ይሀ ግን እንዲሀ እንደቀረበው ቀላል እንዳልሆነ እናውቃለን። ሕይወት ጥልቅ የሆነ ክስተት ነው። የሕይወት ሰጪ የሆነው እግዚአብሔር ታዲያ ምን ያሀል የበለጠ ጥልቅ ነው? ኢዮብ 9:10 እና ሮሜ 11:33 የእግዚአብሔር ጥልቀት የማይመረመር እንደሆነ ይመሰክራሉ። ተረድተነው ተረድተነው የምናበቃው አይደለም፣ እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት ራሱን ገልጿል፤ በተጻፈው ቃሉ አነገግሮናል፤ በሰዎች መልዕክት አነጋግሮናል፤ በውስጣችን ተገልጾልናል፤ ይሀ ሁሉ እኛ እርሱን እንድናውቅ ለማድረግ በቂ መገለጽ ሲሆን እርሱን ግን በሙላት አይገልጸውም።

## 6. እምነት ፍርዱን ይገታዋል

እግዚአብሔር በሰዎች ለመፍረድ አይቸኩልም፤ አይፈልግምም። እንዲያውም በባሕርዩ ደስ የሚሰኝበት ነገር የዚሀን ተቃራኒ ማድረግ ነው። ያም ምሀረትን መስጠት ነው። የሚከተሉትን ጥቅሶች እስቲ እንመልከት

*"...ምሀረትን ይወዳልና..."*
ሚልክያስ 7፥18

*"ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም"*
ሕዝቅኤል 33፥11

*"...ሁሉ ወደንሰሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ..."*
2ጴጥሮስ 3:9

*"ከዚሀ ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን አድኑ"*
ሐዋ. ሥራ 2:40

የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እንዲሀ ቢሆንም ደሀንነትን ግን በግድ እንድንቀበል አያደርገንም። እግዚአብሔር የሰጠንን እምነት በሥራ በምናውልበት ጊዜ በውስጣችን





የሚንቀሳቀስ ሂደት ይጀምራል፤ መዋጀት፤ መመለስ፤ ይቅርታ፤ ደሀንነት፤ ጽድቅ፤ ቅድስና።

ኃጢአት መቀጣት አለበት፤ ወይም ለኃጢአት ፍርድ አለው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል

*"የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው"* ሮሜ 6:23 ይላል።

ይሀንን በሚመለከት ለእያንዳንዳችን ሁለት ምርጫዎች ተሰጥተውናል። የኃጢአት ፍርድ ወይ በእኛ ላይ መውደቅ አለበት ወይ ክርስቶስ የከፈለውን ዕዳ ለእኔ ነው ብለን መቀበል አለብን።

ታላቁ እንግሊዛዊ የእግዚአብሔር ሰው ሲ. ኤስ ሉዊስ እንዲሀ ብለው ጻፉ፤ " በመጨረሻ ሰናየው ሁለት አይነት ሰዎች አሉ፤ ለእግዚአብሔር *"ፈቃድሀ ይፈጸም"* የሚሉ ወይም እግዚአብሔር *"ፈቃድሀ ይፈጸም"* የሚላቸው። እኛ ፈቃድሀ ይፈጸም የምንለው ከሆነ የልጁን የየሱስ ክርስቶስን መወለድ፤ ሕይወት፤ ሞትና ትንሣኤ አምነን ኢየሱስ ያድናል ማለታችን ነው። እርሱ *"ፈቃድሀ ይፈጸም"* ካለን ግን በራስሀ ጥረትና ችሎታ የተበላሸውን አስተካክል፤ አለዚያ ፍርድ ይመጣብሃል ማለቱ ነው። ውሳኔያናችን ሁለተኛው ከሆነ ጊዜያዊና ዘለአለማዊ ከሆነው የፀጋ ጥበቃ ውጪ እንሆናለን።

## እምነት ለእኛስ ምን ያደርግልናል?

እስካሁን ድረስ እምነትን ያየነው ከእግዚአብሔር አንጻር ነው። አሁን ደግሞ እስቲ ጥቂት ጊዜ ወስደን እምነትን ከእኛ አንጻር ለማየት እንሞክር። ከዚሀ በኋላ የሚበዛው የመጽሐፋ ክፍል *"ምን"* ወይም *"ለምን"* ከሚለው ጥያቄ ይወጣና *"እንዴት"* የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ላይ ያተኩራል።

እምነት ለእኛ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ እስካሁንም ቢሆን በተዘዋዋሪ መንገድ

አይተነዋል። እግዚአብሔር ደስ ሲሰኝ፣ እግዚአብሔር ሲፈታ፤ እግዚአብሔር ሲረካ፤ እግዚአብሔር ሲገለጽ፤ እግዚአብሔር ሲሰፋፋና ፍርዱን ሲገታ ጥቅሙና ትርፉ ለእኛ ነው። "ፍላጎት ለፍቅር አበዳሪ ነው"፤ ይህም ማለት አበዳሪ ሁልጊዜ እንዲከፈለው የሚጠብቀው ዕዳ አለ። ፍቅር ደግሞ በጣም አፍቃሪ ስለሆነ፤ የፈለጊውን ፍላጎት ለማሟላት ሁሌ ዝግጁ ነው። ብዙ ፍላጎቶች አሉን፤ ፍቅር ታዲያ አሟላቸዋለሁ ይለናል፤ እምነት ደግሞ እንዲያደርግ ይፈቅድለታል። ስለዚህ እምነት እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆነውን መልካም ነገር እንድንጨብጥ ያግዘናል።

ወንጌል እምነት ለእኛ የሚያደርገውን በብዙ ጥቅሶች ዘርዝሮታል።

__በማቴዎስ__

6:30 - እምነት ለልብሳችን

8:26 - እምነት ፍርሃትን ያስወግዳል

9:22,29 - እምነት ለፈውስ

13:58 - እምነት ለተአምር

15:28 እምነት ጥርጣሬን ለማስወገድ

16:8-10 - እምነት ለምግባችን

25:21 - እምነት ለትልቅ ሹመት

__በማርቆስ__

2:5 - እምነት ለይቅርታ

2:11-12 - እምነት ለፈውስ

10:52 - እምነት ለዓይን ብርሐን

16:14 - እምነት ለትንሣኤ

__በሉቃስ__

7:9 - እምነት ያስመሰግናል

8:25 - እምነት የአየር ጠባይን ይቀይራል

17:6 - እምነት እንቅፋትን ያስወግዳል





22:32 - እምነት የተለወጠውን ይለውጣል

__በዮሐንስ__

2:11፣ 7:31፣ 8:30 - እምነት ከክርስቶስ ጋር ያገናኛል

11:45፣12:11 - እምነት ለእምነት የሚያበቃ ተአምር ያደርጋል

14:1 - እምነት ያድናል

14:12 - እምነት ክርስቶስ በምድር ካደረገው ነገሮች በላይ እንድናደርግ ያስችለናል

እነኚህ ሁሉ በእምነት የሚከሰቱ ታላላቅ በረከቶች ናቸው። እነኚህ ሁኔታዎች በሕይወታችን እንዲከናወኑ ለማድረግ ብዙ የእምነት እድገት እና ጥረት ይጠይቃል። ከእግዚአብሔር የምናገኘውን እንክብካቤ ሁሉ፤ ጤንነት፤ ተአምራት፤ ሌሎችን መባረክ፤ መንፈሳዊ ኃይል፤ የተፈጥሮን ሁኔታ መለዋወጥ መቻል፤ ዘለአለማዊ ህይወት እነኚህ ሁሉ የእምነት ውጤቶች ናቸው። እምነት ለእነኚህ ነገሮች ሁሉ ወሳኝ ነው፤ እምነት ድማሚት (dynamo) ነው፤ ያስፈልገናል፤ ልንለማመደው ይገባናል፤ ሌሎችም እንዲለማመዱት ልንረዳቸው ይገባል። የዚህ መጽሕፍም ዋና አላማ ይኸው ነው።

**ምን ያህል እምነት ያስፈልገኛል?**

**ምናብን ለመኮርኮር -1**

**በሰናፍጭ ቅንጣት ሚዛን ሲለካ የሚያስፈልገኝን የእምነት መጠን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**

ምን ያህል የሚለው ጥያቄ ራሱ የእምነትን ልክ የሚጠይቅ ይመስላል። የእውነተኛ እምነት ትንሽ የለውም፤ ግን የእውነተኛውን እምነት ጉዳይ አሳስቶ መረዳት ቀላል ነው። አንድ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ጌታ የሱስን ለምን አጋንንት ማስወጣት እንዳልቻሉ ጠየቁት፤

> *"እምነታችሁ በማነሱ ምክንያት ነው፣ እላችኋለሁ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህንን ተራራ ከዚህ ተነስተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳናችሁ ነገር አይኖርም" (ማቴ. 17፤20)*

የዚህ ጥቅስ አሳብ ጥልቅ ነው፤ የእምነታችሁ ማነስ ካላቸው በኋላ ከሰናፍጭ ቅንጣት ጋር አወዳደረው። በመካከለኛው ምስራቅ በተለይ ፓልስታይን (ፍልስጤም) ተብሎ በሚጠራው አካባቢ፤ እስራኤልንም ጨምሮ ማለት ነው፤ የሰናፍጭ ፍሬ በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ በአይን ለማየት እንኳን ያስቸግራል ይባላል። ይህ ቅመም ታዲያ





በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ ትንሽ ቁንጥር ለብዙ ሰው ይበቃል። ለመገበያየት እንኳን የሚጠቀሙት በጣም ትንሽ የሆነች ልዩ መስፈሪያ ነበር ይባላል። ጌታ የሱስ ምን ለማለት እንደፈለገ ደቀ መዛሙርቱ በደንብ ተረድተውታል። በጣም ትንሽ ተብሎ ከሚገመተው ነገር እንኳን ያነሰ እምነት ቢኖራችሁ ትልቅ የሆነባችሁን እክል ልታሸንፉት ትችላላችሁ።

በዚህ ውስጥ እኛን ሊያበረታታን የሚገባው ትልቅ እውነት አለ። እምነት እውነተኛ እስከሆን ድረስ ትንሽም እንኳን ቢሆን ኃይለኛ ስለሆነ ለሁሉ ነገር በቂ ነው። ጥያቄው ታዲያ "ምን ያህል?" ሳይሆን "ምንድነው?" የሚለው ነው። ስለዚህ እስቲ ራመድ ብለን እምነት ምን መሆኑን እንመርምርና እንዴት እንደምንጠቀምበትም እንይ።

## ምን ያህል እምነት ያስፈልገኛል?

### ምናብን ለመኮርኮር -1

በሰናፍጭ ቅንጣት ሚዛን ሲለካ
የሚያስፈልገኝን የእምነት መጠን
እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

# ምዕራፍ ሁለት

## ለእምነት የሚያስፈልጉን ግንዛቤዎች

ቦታው አሜሪካን አገሩ በቴክሳስ ስቴት ኮሌጅ የተማርኩበት ትምህርት ቤት ነበር። ጊዜው የኮሌጅ ትምህርት ለመጀመር ቴክሳስ እንደደረስኩ ነበር። ቀኑ ትምህርት ለመጀመር የመመዝገቢያ መጀመሪያ ቀን ነበር፤ ለአገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ ነበርኩ።

በዕለቱ ያጋጠመኝ ጉዳይ እምነትን የሚሰልብ ስሜትን ዝቅ የሚያደርግ እንቅልፍ የሚነሳ ነበር። ለሲሚስተሩ የምወስዳቸውን ኮርሶች መርጬ አስተማሪዎቼን አስፈርሜ ሬጂስትራር ጋ ስሄድ ነው ያልጠበኩት ዱብዳ ያጋጠመኝ፤ የገንዘቡን መጠን ቆልሎ የሌለኝን መጠን አሁን ካልከፈልክ መመዝገብ አትችልም አለኝ። ወገቤ ተቆረጠ። የመጣሁት ዕርዳታ ታገኛለህ ተብዬ ነበር ብዬ ለማስረዳት ብሞክር፤ ሰውዬው ግን ወይ ፍንክች ወይ ንቅንቅ (ለዚያን ጊዜ የጊዜው አባባል ነበር) አልል አለ። እንዲያውም በመሰልቸት አመለካከት ገላመጠኝ። ወረቀቴን ሰብስቤ ወደኃላዬ ተመለስኩ። በጣም ግራ ገባኝ፣ ምን ማድረግ እችላለሁ ብዬ በእግዚአብሔር ላይ መማረር ጀመርኩ። እግዚአብሔር ጨርሶ የተወኝ መሰሎ ተሰማኝ። ስሜቴም በጣም ዝቅ አለብኝ።

ወደአንድ ወዳጄ ወደሆነ የእግዚአብሔር ሰው ደወልኩና እግዚአብሔርን ወቀስኩለት፤ "አይዞህ እግዚአብሔር አንድ ነገር ያደርጋል" አለኝ። በውስጤ "ምንም የሚደረግ ነገር ያለ አይመስለኝም" አልኩና ስልኩን ዘጋሁት። ትንሽ እምነት አጣሁ እንጂ በማግስቱ ሁኔታው ተቀያየረ። በእርግጥ እንደጠበቅሁት ዕርዳታ አገኘሁ፤ እንዳውም ከጠበቅሁት በላይ። በመጀመሪያው ቀን መዝጋቢ ሆኖ ይሠራ የነበረው ሰው ለካ ሥራው አልነበረም፤ ምትክ ሠራተኛ ሆኖ ነበር የሚሠራው። እኔ ደግሞ አላወቅሁም እንጂ የዛን ዕለት ለምዝገባ መሄድ አልነበረብኝም። እኔ መመዝገብ በነበረብኝ ቀን ስሄድ ግን ዋናው መዝጋቢ ተመልሶ መጥቶ ነበር። ገና ስደርስ ስሜን አየና "አንተ የ 50% tution ስኮላርሺፕ አለህ፤ ለተቀረው ደግሞ work study ተፈቅዶልሀል

" አለኝ። የሚታመን አምላክ ጠፍቶ ሳይሆን ስሜቴ ቀዝቅዞብኝ ነበር ለካ እንቅልፍ አጥቼ ያደርኩት።

ብዙ ጊዜ ሰዎች እምነትን ከመለማመድ አኳያ የጋራ የሆነ ስህተት እናደርጋለን። አንደኛው ስህተታችን እምነትን ከስሜት ጋር እናያይዘዋለን። እንዳውም ለአንዳንዶቻችን እምነት ማለት ስሜት ነው። አንድ ነገር ለማድረግ ስሜታችን ከገፋፋን ያንን ነገር እናደርገውና የእምነትን መንገድ የተከተልን ይመስለናል። ያ ያደረግነው ነገር የተሳካ ውጤት ካመጣ እምነታችን ሠራ ብለን ደስ ይለናል። ራሳችንንም የእምነት ሰዎች አርገን እናያለን። በእርግጥም እምነት ከስሜታችን ጋር ተስማምቶ የሚሠራበት ብዙ ጊዜ አለ። ብዙ ጊዜ ግን እምነት ትኩስ ስሜት ሳይሆን ቀዝቃዛ እውነት ብቻ ነው። ይህም ማለት እምነት ከስሜታችን ጋር ተቃራኒ የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ ታዲያ እምነታችንን ከስሜታችን ጋር ብቻ ካያያዝነው የማያቋርጥ የእምነት ሕይወት መኖር አንችልም።

እምነት ውሳኔ ነው። ጌታ የሱስ ደቀመዛሙርቱን በ "ትንሽ እምነት" ምክንያት ሲገስጻቸው እናያለን። ይህ የሚያመለክተው የእምነታቸው መጠን እነርሱ እንደወሰኑት መሆኑን ነው። የእምነታቸው መጠን ከእነርሱ ቁጥጥር ውጪ ቢሆን ኖሮ መገሰጽ አይገባቸውም ነበር። በአንጻሩ ግን የስሜታችን ጉዳይ የተለየ ነው። እስቲ ስለስሜታችን ትንሽ እናስብ። ስሜታችንን እኮ መቆጣጠር አንችልም። የስሜትን አገላለጽ መቆጣጠር ይቻል ይሆናል። ለምሳሌ የሚያሳዝን ሲኒማ አይታችሁ ማልቀስን መቆጣጠር ትችሉ ይሆናል፤ ማዘናችሁ ግን ከቁጥጥራችሁ ውጪ ስለሆነ ታዝናላችሁ። የሚያስፈራ ነገር ስናይ መደንገጥ፤ የሚያሳዝን ነገር ስንሰማ ማዘን፤ መልካም ዜና ስንቀበል ደስ መሰኘት፤ እነኚህ ሁሉ ከቁጥጥራችን በላይ የሆኑ ሰብዓዊ ስሜቶች ናቸው። እነኚህ ሁኔታዎች በውስጣችን የሚፈጥሩት ስሜታዊነትን (emotions) ሲሆን፤ እምነት ወይም አለማመን እነኚህ ሁኔታዎች በሕይወታችን ሲከሰቱ በምንወስደው እርምጃ ላይ ይመጣል። ስሜታዊነቱ ግን እምነት አይደለም። ይህንን አጥብቄ የምደጋግመው ስሜት እንደ እምነት እየተቆጠረ ብዙ ስህተት ሲሠራ ስላየሁ ነው።





በደረሰብን መጥፎ ነገር ስሜታችን በንዴት ገንፍሎ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የሆነ ነገር እንድናደርግ ከገፋፋን፤ ያ እምነት አይደለም፤ ዜናውን ተቀብለን ግን ሐዘናችንን ዋጥ አድርገን "በዚህም ውስጥ እግዚአብሔር መንገድ አለው" ካልን ያ እምነት ነው። በሌላው በኩል ደግሞ በስሜት በመገፋት ብቻ እግዚአብሔር ያላለውን አለ፤ ያላደረገውን አደረገ ማለትም እምነታዊ እርምጃ አይደለም። በሰሙትና ስሜታቸው በተነቃቃበት ነገር ተገፋፍተው የእምነት እርምጃ ነው በማለት ማድረግ የማይገባቸውን አድርገው በኋላ የሚፀፀቱ ብዙ ሰዎች አውቃለሁ። የእምነት እርምጃ በረከት እንጂ በኋላ ፀፀት እንደማያመጣ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ሁለተኛው ስህተት እምነትን በእውቀት ላይ የተመሠረተ አድርጎ መውሰድ ነው።በእርግጥ አዕምሮአችን ስለ እምነት በማሰብ የእምነትን እርምጃዎች ማጤን ይኖርበታል። ነገር ግን እምነት ራሱ በአዕምሮ እውቀት ላይ የተመሠረተ አይደለም። አዕምሯችን የተወሰነ ነው። ያልተወሰነውን የእምነት እውነት በሙሉ ለመረዳት አቅም የለውም። የምናምነው በአዕምሮአችን የምንረዳውን ብቻ ከሆነ በጣም የምናሳዝን መንፈሳዊ ስንኩላን ሆነናል ማለት ነው። እምነት አንዳንድ ጊዜ ከምክንያት (reason or logic) ውጪ ወይም ተቃራኒ ይሆናል። አንዳንዴ ደግሞ ምክንያትን እንኳን አልፈው የሚሄዱ እርምጃዎችን እንድንወስድ ያደርገናል። ይህንን አሳብ ወደፊት በሰፊው እናየዋለን። አሁን ላነሳው የፈለኩት ነጥብ ግን የዕውቀት ችሎታ ብቻ ዋናው እውነትን የመረጃ መንገድ አለመሆኑን ለማሳየት ነው፤ ወይም የእውነት መኖሪያ አዕምሮ ውስጥ አይደለም።

ይህንን ሁሉ በምልበት ጊዜ ግን እግዚአብሔር ስሜትንና እውቀትን ይጠላል ወይም ይቃረናል ማለቴ አይደለም፤ የስሜትም የአዕምሮም ፈጣሪ እኮ እርሱ ነው። በስሜታችን ደስ እንድንሰኝ በእውቀታችንም ብዙ እንድንሠራ ፈቃዱም አቅዱም ነው።

ሆኖም እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጣቸው ክፍሎች ሁሉ የተመደበ ሥራ አቅዶላቸዋል። የስሜት ሥራ እንዲሰማን ማድረግ፤ የአዕምሮ ሥራ ደግሞ እንድናስብና እውቀት እንድንቀስም ነው። የሁለቱም ሥራ ግን የእምነት አላፊነት አይደለም። ይህንን እውነት በደንብ መረዳት አለብን።

ወደፊት በዚህ መጽሐፍ እንደምናየው ሰይጣን በእነኚህ በሁለቱም ክፍሎቻችን (በስሜትም በአዕምሮም) መጠቀም ስለሚችል እምነት የስሜትም ሆነ የእውቀት ተገዢ አለመሆኑን መረዳት ከብዙ መዘበራረቅ ያድናል። እስቲ ይህንን አሳብ ፊታ አድርገን እንየው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለተለያዩ ሰብአዊ ክፍፍል ብዙ የሚናገረው አለው። ሰው የተለያየ ክፍል አለው ለማለት ነው። ይህንን ልዩነት መረዳት ስንጀምር እግዚአብሔር ለእምነት ያቀደውን ክፍላችንን ማወቅ እንጀምራልን። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን እውነት ለመረዳት መንደርደሪያ የሚሆን አሳብ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሰጥቶናል።

> *"የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤መንፈሳችሁ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለነቀፋ ይጠበቅ" 1ተሰሎንቄ 5፤ 23-24*

ሐዋርያው በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሶስት ታላላቅ የሰውን ክፍሎች ይገልጻል፤ መንፈስ ነፍስና ሥጋ። አስቀድመን መረዳት ያለብን አንድ ነገር ታዲያ እነኚህ የተለያዩ ክፍሎች የተለያየ አገልግሎት መፈጸማቸው ነው። በሌላ ቦታ ላይ ጳውሎስ በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለንን የሥራ ድርሻ በሰውነት ብልቶች ውስጥ ካለው የአሠራር ክፍፍል ጋር ያመሳስለዋል።

> *"አካል በሙሉ ዓይን ቢሆን ኖሮ መስማት ከየት ይገኝ ነበር? አካል በሙሉ ጆሮ ቢሆን ኖሮ ማሽተት ከየት ይገኝ ነበር? ነገር ግን እግዚአብሔር እንደወደደ እያንዳንዱን በቦታው መድቧል።" 1ቆሮንቶስ 12፤ 17-18*

ጆሮ አገልግሎቱ መስማት ነው፤ ዓይን ማየት፤ ሆድ ደገሞ ምግብ መፍጨት ነው። ሆድ ካላየሁ ብሎ ወደ ላይ ቢንጠራራ ብዙ መደናበር ይፈጠር ነበር።

ልክ እንደዚሁ የመንፈስ የነፍስና የሥጋ አገልግሎት የተለያየ ነው። ይህ ሶስት የአገልግሎት ልዩነት የሚጀምረውም የሚያንጸባርቀውም የሰላሴን ባሕሪ ነው። አሁንም ጳውሎስን እንደገና እንጥቀስ።





> *"ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልገሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው" 1ቆሮንቶስ 12፤4*

ጳውሎስ እንዲህ ነው የሚለው፤ መንፈስ ቅዱስ የስጦታዎች ሐላፊ ሲሆን ጌታ የሱስ የአገልግሎትን ክፍል ያያል፤ እግዚአብሔር ደግሞ በአጠቃላይ ሁሉን ይመለከታል። ይህ መወዳደርና አለመግባባት የማይኖርበት ፍጹም የሆነ በመለኮታዊ ስምምነት ያለ የሥራ ክፍፍል ነው።

የእግዚአብሔር ቃል በተለያዩ ቦታዎች የሥነ ፍጥረትን (የመፍጠርን) አላፊነት የአብ፥ የደህንነት አገልገሎት የጌታ የሱስ፤ የመቀደስና የማጽናናት አገልግሎት የመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያመለክታል። በእርግጥ ጌታ የሱስም መንፈስ ቅዱስም በመፍጠር ሥራ ውስጥ ተሳትፎ ነበራቸው።

> "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር" ዘፍጥረት 1፤27

የሚለው ጥቅስ በፍጥረት ሥራ ውስጥ ህብረት እንደነበረ ያመለክታል። ግን ዋናው ሀላፊነት የእግዚአብሔር አብ መሆኑን "በመጀመሪያ እግዚአብሔር" ከሚለው የመጽሐፉ መክፈቻ ጀምሮ ያለው ገለጻ ያመለክታል። የሰውን ልጅ ደህንነት ያቀደው አብ እንደሆነ አሁንም መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታዎች ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስም ከጌታ የሱስ ጋር ሆኖ በደህንነት አገልግሎት ተሳትፎ አለው። ነገር ግን ለአባቱ ታዛዥ ሆኖ ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ ዕዳችንን የከፈለው ጌታ የሱስ ነው። አብ አባትና ልጁ ጌታ የሱስ ዛሬ በሰማያት ዙፋን ላይ ተቀምጠው መንፈስ ቅዱስን ወደ አለም ሲልኩ፤ በአለም ውስጥ ሆኖ መለኮታዊ ተግባራትን ዛሬ የሚያከናውነው፤ እኛም ቅዱሳን ተብለን አብ አባት በሰማይ አለን፥ ኢየሱስ ጌታ ነው ለማለት የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነው።

በተመሳሳይ መንገድ በሰዎችም ውስጥ ሶስት የተለያዩ ሆኖም የተቀናጁ ሕልውናዎች አሉ። መንፈስ፤ ነፍስና ሥጋ። የሶስቱም አገልግሎታቸው የተለያየ ነው። የሚከተለውን ጥቅስ እስቲ በትኩረት እንየው፥

*"እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል። መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳን ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል። በውስጡ ካለው ከራሱ መንፈስ በስተቀር ከሰው መካከል የአንድን ሰው አሳብ የሚያውቅ ማን አለ?"* 1ቆሮንቶስ 2፤10-11።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከሰለሴዎች ክፍል አንዱ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ከግላዊ ሰው መንፈስ ጋር ነው የሚያወዳድረው፤ ይህንን የተዛመደ አሳብ እንደገና የበለጠ እያስፋፋው ይሄዳል።

*"የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያውቅ ማንም የለም ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የአለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፤ ይህም እግዚአብሔር በነፃ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው። እኛ የምንናገረው ይህን ነው፤ ከሰው ጥበብ በተማርነው ቃል ሳይሆን፤ ከመንፈስ በተማርነው ቃል እንናገራለን፤ መንፈሳዊ እውነትንም የምንገልጸው በመንፈሳዊ ቃል ነው። መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው (ነፍሳዊ ሰው) ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው። በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊረዳው አይችልም። መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉንም ይመረምራል። ራሱ ግን በማንም አይመረመርም"* 1ቆሮንቶስ 2፤12=15።

የሰውን አስተሳሰብ የሚያውቀው አዕምሮው ወይም ስሜቱ ሳይሆን መንፈሱ ነው። ይህ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ እንዴት ነው አንዲት ሴት መንፈሷን የምትለማመደው? ተገቢ ጥያቄ ነው፤ ግን ቆይ እንደርስበታለን። አሁን የደረስንበት ደረጃ በእመንበት ነገር ስለ መመለለስ ነው። እዚህ ጋ ለአደጋ የምንጋለጠው በመንፈስና በአዕምሮ መካከል ያለውን ልዩነት ሳንረዳ ቀርተን ልዩነት የላቸውም በሚል ግምት ስንሆን ነው። ስለዚህ እስቲ ወደኋላ ወደ መጀመሪያው መለስ እንበልና እያይዘነው እንምጣ።

እግዚአብሔር በኤደን ገነት ለአዳምና ለሔዋን ደንብን ሲያወጣላቸው፤

*"ነገር ግን መልካምና ክፉን ከምታሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ"* ዘፍጥረት 2፤17።





ከዛፉ ከበሉ በኋላ ግን አዳምና ሔዋን በሕይወት መኖራቸው አላቋረጠም ወይም ወዲያው አልሞቱም። ነገር ግን የሞተ ነገር ነበር፤ እነርሱም የተለዩ ሰዎች ሆኑ። እግዚአብሔር እንዳስጠነቀቀው መንፈሳቸው ነበር የሞተው። በሌላ አነጋገር ወዲያው በመንፈስ የሞቱ ሆኑ፤ አካላቸው ግን የሞተው ቆይቶ ነው።

ጌታ የሱስ ኒቆዲሞስን በተገናኘው በዚያ ሌሊት (ዮሐንስ 3) በመጀመሪያ ያስተዋለው በመንፈስ ሙት መሆኑን ነበር። ለዚህ ነው

*"ማንም ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም"* ዮሐንስ 3፤5-6 ያለው።

ጌታ የሱስ ለኒቆዲሞስ የሚለው፤ "አንተ ወላጆቹ በተፈጥሮአዊ ደረጃ የወለዱት ሰው ብቻ ነህ። በመንፈሳዊ ደረጃ ደግሞ በመንፈስ እንደገና መወለድ አለብህ" ነበር የሚለው። የአዳምና የሔዋን መውደቅ በሰው ዘር ላይ እንዲሰለጥን ያደረገውን ሞት ሊገታው የሚችለው የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው

*"ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ"* 1ቆሮንቶስ 15፤22።

ይህ አዳም ያመጣውን ክርስቶስ ግን ሕይወቱን ከፍሎ የመለሰው ሞት አካላዊ ሞት ሳይሆን መንፈሳዊ ሞት ነው። የሚከተለውን ሰዕላዊ መግለጫ ብናይ ለማለት የምፈልገውን ነገር በደንብ ይገልጸዋል። ይህ ስዕል በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በተለይም የመንፈስ ቅዱስን አገልገሎት በግል በተለማመዱ ሰዎች ተደጋግሞ በጥቅም ላይ የዋለ ሞዴል ነው።

በአራት ዳይሜንሽን የተያዘን አሳብ በሁለት ዳይሜንሽን በሙላት ለመግለጽ ስለማይቻል በስዕሉ ውስጥ የራሳችሁን ግምት ማስገባት ይኖርባችኋል። የተለያዩ ክፍሎችን ለመከፋፈል የተጠቀምንባቸው መስመሮች በሕይወትም ሁልጊዜ እንደዚህ ግልፅና ጉልህ ናቸው ማለት አይደለም።




ይህ ስዕላዊ መግለጫ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለቀረበው ትምህርት በጣም ጠቃሚ ስለሆነ በደንብ እንድታጠኑት አበረታታችኋለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥም ደጋግመን በተለያየ አቀራረብ እናየዋለን።

በስዕሉ ላይ ውጪያዊው ክፍል አካል ነው። ከሚታየው አለም ጋር የቅርብ መነካካት ያለው አካል ነው። አካል የሚለው ቃል በግሪክ ሶማ ይባላል። መካከለኛው ክፍል ነፍስ ነው። ይህ ክፍል በአካል ውስጥ የተያዘ ሲሆን የእያንዳንዱን ሰው እርሱነት የሚገልጹት ባህርያት ያሉበት ክፍል ነው፣ እነኚህም ባሕርያት አዕምሮና (mind) ስሜት (emotions) ናቸው። የሰውን ሰውነት የሚተረጉሙት እነኚህ ባሕርያት ናቸው። ነፍስ በግሪክ ሳይክ (psyche) ሲሆን ሳይኮሎጂ እና ሳይካትሪ የሚባሉት ጥናቶች በዚህ ክልል ላይ ያተኩሩ ናቸው። ይህ ቃል በ 1ቆሮንቶስ 2፤14 ላይ "ፍጥረታዊ ሰው" ተብሎ ነው የተተረጎመው። አዲሱ መደበኛ ትርጉም "መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው" ብሎ ነው የተረጎመው። ቃሉ በእንግሊዝኛ ባሉ የተለያዩ የመጽሐፍ





ቅዱስ ትርጉሞች እንዲህ ተተርጉሟል። "ተፈጥሮአዊ፤ መንፈሳዊ ያልሆነ፤ መንፈስ የለሽ" ፤ የቃሉን ስፋት ለማጉላት ብዬ ነው ትርጉም ያበዛሁት።

እነኚህ ሁለቱ ውጫዊ ክፍሎች፤ አካልና ነፍስን ትንሽ እናስፋፋቸው (አካል-ሰውነት ተብሎ መተርጎም ይችላል፤ ነገር ግን ሰውነትን personality ለሚለው ቃል መቆጠቤ ነው። አካልና ነፍስ በአንድነት በግሪኩ (Sarx) ተብለው ይጠራሉ። ይህ ቃል በአማርኛ ሥጋ ተብሎ ነው የተተረጎመው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ 3:1 ላይ "እንደ ሥጋውያን እንጂ እንደ መንፈሳውያን ልናገራችሁ አልቻልኩም" ሲል Sarx ነው ሥጋ ተብሎ የተተረጎመው። ባርክሊ የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሜንተሪ በ1ቆሮንቶስ ኮሜንተሪ ላይ ስለዚህ ጥቅስ እንዲህ ይላል። "ለሐዋርያው ጳውሎስ ሥጋ ተፈጥሮአዊ አካል ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ነው። ሥጋ ለእርሱ ያ ከእግዚአብሔር የተለየው ሰብአዊ ተፈጥሮ ማለት ነው። ያ አዕምሮአዊና (mental) ተፈጥሮአዊ (physical) የሆነው ክፍል ለኃጢአትም መግቢያ ድልድይ ነው"።

ልብ አድርጉ ጳውሎስ የሚጽፈው ለክርስቲያኖች ነበር፤ ሆኖም ሥጋውያን እያለ ይጠራቸዋል። አማኝ ከመንፈሳዊነት ውጪ በሆነ ሥጋዊ ልምምድ ብቻ መኖር ከመረጠ ያን ማድረግ ይችላል ማለት ነው።

የሥጋንና የመንፈስን ልዩነት ሐዋርያው በሁለት ታላላቅ ምዕራፎች ገልጾታል፤ (ሮሜ ምዕራፍ 7 እና ምዕራፍ 8) በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ያለውን እንይ

> *"ለኃጢያት የተገዛ አዕምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም መገዛትም አይችልም። በሥጋ የሚመሩትም እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችሉም።" ሮሜ 8፥ 7-8።*

ስለዚህ ሥጋ (አካልና ነፍስ በአንድነት) እግዚአብሔርን የማስደሰት ችሎታ የለውም። ስለሆነም በእኛ ውስጥ ያለውን ከእግዚአብሔር ጋር ሊግባባ የሚችለውን ማንነታችንን ለመፈለግ ወደ ራሳችን ውስጥ ጠልቀን ማየት ይኖርብናል። ሥጋችን ይህ ችሎታ የለውም።

ይህ ውስጠኛው ክፍላችን መንፈስ ነው። የግሪኩ ቃል ኒውማ (pneuma) ሲሆን በሕይወታ ጌታ የሱስን አዳኛችንና ጌታችን አድርገን ልንቀበለው ስንወስን በውስጣችን እንደገና የሚወለደው ክፍል ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሊግባባ የሚችለውና መንፈስ ቅዱስ የሚለውን መስማት የሚችለው ይህኛው እኛነታችን ነው። መንፈሳዊ ነገርንም መረዳት የሚችለው ክፍል ይህ ነው። ለዚህ ነው ሮተርሀም የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሜንታተር በ1ቆሮንቶስ 2:14 ላይ ሲጽፍ እንዲህ ያለው "ነገር ግን የነፍስ ሰው የመንፈስን ነገር እሺ ብሎ አይቀበልም፤ ምክንያቱም ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ ሊረዳቸውም አይችልም፤ ምክንያቱም መመርመር የሚችሉት በመንፈስ ብቻ ነው"።

ባርክሌ ደግሞ በዚያው በ1ቆሮንቶስ ኮሜንተሪው ላይ እንዲህ ብሎ ጽፏል፦

ጳውሎስ መንፈሳዊ ነገርን ለመንፈሳዊ ሰዎች ስለመተርጎም ይናገራል። ሁለት አይነት መንፈሳዊ ሰዎችም እንዳሉ ለይቶ ያሳያል። 1. መንፈሳውያን (pneumatikos) ለመንፈስ ሴንሲቲቭ የሆነ፣ ሕይወቱን በመንፈስ የሚመራ ሲሆን 2. ነፍሳዊ ሰው ሱቺኮስ (psuchikos) ሳይክ (psyche) ለሚለው ቃል ስሩ ሲሆን ነፍስ ተብሎ ይተረጎማል… ስለዚህ በቁጥር 14 ላይ ጳውሎስ ነፍሳዊ ስለሆነ ሰው ነው የሚናገረው። ይህ ሰው የሚኖረው ከዚህ ሕይወት ውጪ ሌላ ሕይወት እንደሌለ በማሰብ ነው። አስፈላጊውም ነገር ተፈጥሮአዊ ንብረት፤ ዋጋ የሚሰጠውም ነገር ለሚያየውና ለሚጨብጠው ብቻ ፤ እንዲህ ያለ ሰው መንፈሳዊ ነገር አይገባውም።

እንዲህ ያለ ሰው ሁላችንም የምናውቅ ይመስለኛል፤ ጥያቄው ግን ጠዋት ጠዋት በመስታወት የምናየው ያን ሰው ይሆን?

መንፈሳችን የእግዚአብሔርን ነገር ለመረዳት በጣም አስፈላጊ ከሆነበት ምክንያቶች አንዱ፤ እግዚአብሔርን የምንመስልበት ክፍላችን መንፈሳችን በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ጌታ የሱስ በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ላገኛት ሳምራዊት ሴት እንደነገራት (ዮሐንስ 4) በመንፈስና በእውነት ልናመልከው ይገባናል። ሐዋርያው ጳውሎስም ከክርስቶስ ጋር አንድ መንፈስ አለን ብሏል።





ምናብን ለመኮርኮር 2.

ከአዕምሮአዊ እርግጠኛነት ወደልባዊ እምነት የምንሸጋገረው እንዴት ነው?

ጌታ የሱስን አዳኛችን አድርገን ስንቀበለው መንፈስ ቅዱስ ወደ መንፈሳችን ይመጣና ከክርስቶስ ጋር ቋሚና ዘለዓለማዊ ኅብረት እንድንፈጥር ያደርጋል። እግዚአብሔር የራሱ በሆነ ምክንያት ከሰዎች ጋር ግንኙነት የፈጠረበት ክፍል አዕምሮ ወይም ስሜት ሳይሆን መንፈሳችን ነው።አንድ የእግዚአብሔር ሰው ይህንን የአሠራር ቅንጅት በምሳሌ እንዲህ ብለው አብራሩት። "አካል እንደ መርከብ ነው፤ ነፍስ ደግሞ የአዕምሮና የስሜትን ኢንፎርሜሽን የሚከታተል ሹም ሲሆን የመርከቡ ካፒቴን ግን መንፈስ ነው። ፈቃድ ደግሞ የካፒቴኑን ትዕዛዝ የሚያስተላልፍ የበላይ መኮንን ይመስላል።" ትርጉም የሚሰጥ አገላለጽ ነው። አዕምሮና ስሜት አስፈላጊ የሆነ እውቀት (information) ይሰጡናል። ነገር ግን አዕምሮም ሆነ ስሜት የአዛዥነት ሥልጣን አልተሰጣቸውም። የአዛዥነቱ ሥልጣን የመንፈስ ነው። ይህ የሥራ ክፍፍል ሲዘበራረቅ ነው ሕይወት የሚመሳቀለው። ፈቃድን የሚመለከቱ እስቲ አራት ነጥቦችን እንይ፡-

## 1. የፈቃድ አስፈላጊነት

ይህ እስካሁን ያየነው አሳብ ትክክል ከሆነ ታዲያ ሰው እንዴት አድርጎ ነው ከመንፈሱ ጋር መገናኘት የሚችለው? የሚለው ጥያቄ ቢጠየቅ ተገቢ ይመስላል። ከዚህ

ምናብን ለመኮርኮር 2 .

ከአዕምሮአዊ እርግጠኛነት
ወደልባዊ እምነት የምንሸጋገረው
እንዴት ነው?

ጋር የሚሄዱ ሌሎች ጥያቄዎችም አሉ; መንፈሳችን እንዴት አሳባችንን ሊያውቅ ይችላል? ሰው መንፈስ ቅዱስን መስማት የሚችለው እንዴት ነው? መንፈሳችን እንድናደርግ የሚፈልገው ምን እንደሆነ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

ለዚህ ሁሉ ጥያቄ መልሱ አጭር ነው፦ የፈቃድን ሚና መገንዘብ ነው።

ይህ ገለጣ (discussion) ረዘም ያለ እንደሆነ እረዳለሁ። እንዳውም ይህ ሁሉ ሐተታ ከእምነት ጋር ምን ያገናኘዋል ብላችሁ ጠይቃችሁ ይሆናል። መልሱ እምነትን ልንለማመድበት የምንችለው የእኛነት ክፍላችን ፈቃድ መሆኑ ነው።

ከፍ ብሎ ባየነው ሰዕላዊ መግለጫ ላይ ፈቃድ ያለበትን ክልል ስናይ፤ ፈቃድ ከመንፈሳችን ጋር በአንድ ፀውድ ውስጥ ሲሆን አዕምሮና ስሜት ግን ከመንፈሳችን ውጪ ናቸው። ያም ሆኖ ግን በፈቃድና በመንፈስ መካከል ልዩነት አለ፤ መንፈሳችን የእግዚአብሔር መኖሪያ ሥፍራ ነው። መንፈሳችን እኛና እግዚአብሔር እምንገናኝበት ሥፍራ ነው። ፈቃድ ግን ፍጹም ሰብዓዊ ባህሪ ነው። ስለዚህ አንድ ቦታ ላይ ፈቃዳችንንና መንፈሳችንን የሚለይ የማይታይ መስመር አለ ማለት ነው። ያ መስመር የት እንደሆነ ማወቅ አይቻልም። ቁምነገሩም ያንን ማወቅ አይደለም፤ ቁምነገሩ እምነት ነው። እምነት ሲኖር መንፈስ ራሱን በፈቃድ ውስጥ ገለጸ ማለት ነው፤ መንፈስ በፈቃዳችን ውስጥ እየጎላ ሲመጣ ያ ክስተት የእምነት እድገት ይባላል፤ በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔር ፈቃድ በፈቃዳችን ተገለጠ ማለት ያ ነው። እንደ እግዚአብሔር ሰዎችም ትጋታችንና ጥረታችን ይህ ክስተት በሕይወታችን የበለጠ እንዲጎላ መሆን አለበት።

ጆርጅ ማክዶላንድ በ19ኛው መቶ ምዕት የታወቁ ስኮትላንዳዊ ወንጌል ሰባኪና ጸሐፊ ነበሩ። "ያልተነገሩ ስብከቶች" (Unspoken Sermons) በተባለው መጽሐፋቸው ስለ ሰው ፈቃድ በሰፊው ጽፈዋል፦ (ለመተርጎም በሚያስቸግር የጥንት እንግሊዝኛ የተጻፈ ስልሆን ቃል በቃል ሳይሆን የአሳብ ለአሳብ ትርጉም ነው)

> "በሰው ውስጥ የላቀው ነገር አዕምሮው ወይም አስተሳሰቡ ወይም ምክንያታዊነቱ አይደለም። እነኚህ ሁሉ ከፈቃድ በታች ናቸው፤ በብዙ መንገድም በፈቃድ ላይ ተደጋፊዎች ናቸው....እግዚአብሔር ለሰው





> በፈቃዱ እንዲፈቅድ ኃይል ሰጥቶታል። ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፍቃዱ ለማድረግ አለመፍቀዱ እግዚአብሔርን መገመት ከምንችለው በላይ ዋጋ አስከፍሎታል። ሰው ግን እውነትን የሚቀበልበት ቦታ ደርሶ ሲቀበል ያ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው"።

ለምን እኚህ ሰው ፈቃድ በሰው ውስጥ ከፍተኛው ወይም የላቀው ክፍል ነው አሉ? መክንያቱን ሲሰጡ ለመረዳትም ሆነ ለአውቀት ፈቃድ ቁልፍ እንደሆነ ያሳያሉ። ቀጠል አድርገውም፦

"መረዳትን ዝቅ ዝቅ ማድረጌ ከመሰላችሁ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ፤ ምክንያቱም አዲስ ኪዳን እንድንረዳ በሚያበረታቱ አሳቦች የተሞላ ነው። ሕይወታችንም ትርጉም ያለው ሕይወት እንዲሆን በመረዳት ማደግ ይኖርብናል። እኔ የምናገረው ግን ሰው ያለመታዘዝ ለመረዳት ሲሞክር የሚፈጠረውን አለመረዳት (ወይም መዘበራረቅ) ለማሳየት ነው። ኃይላችን መዋል ያለበት በመታዘዝ ላይ ነው፤ መረዳት ያንን ተከትሎ ይመጣል - ሳንታዘዝ ወይም እያወቅን ሳናደርግ ቀርተን እውነተኛ ልብና ንፁህ ነፍስ ሊረዳ የሚችለውን እውነት እንዴት ልንረዳ እንችላለን?"

አዕምሮን እንዲረዳ የሚያስችለው ፈቃድ ነው። ስለዚህ መረዳት በፈቃድ ነፃ መሆንና እውነትን የመቀበል ችሎታ ላይ የተመሠረተ ነው። እግዚአብሔር ለሚለን ነገር ታዛዦች መሆናችን መረዳት እንዲሰጠን ይፈታዋል። መረዳት ከመንፈሳችን በፈቃዳችን በኩል አድርጎ ወደ አዕምሮአችን ይመጣል። ኢዮብ እንዳለው

> *"ነገር ግን በሰው ያለው መንፈስ፤ ሁሉን የሚችል አምላክ እስትንፋስ ማስተዋልን ይሰጣል" ኢዮብ 32:8።*

ማክዶላንድ እንደገና "የሚያደርግ፥ መረዳትን ያገኛል፤ ከማድረግ በፊት መረዳት አለኝ የሚል ግን ሲደናቀፍ፤ ሲሳሳትና ሞኝነትን ሲናገር ይኖራል" ብለዋል።

ብራዘር ሎሬንስ የጻፉት "የእግዚአብሔርን መገኘት መለማመድ" (Practice of the presence of God) በሚለው ክላሲክ መጽሐፋቸው ይህንን አረፍተ ነገር አስቀምጠዋል "መረዳትን በመለማመድና ፈቃድን በመለማመድ መካከል ትልቅ

ልዩነት ማድረግ አለብን። የመጀመሪያው በጣም ትንሽ ዋጋ ሲኖረው፤ ሁለተኛው ግን ሁሉን ያጠቃልላል"። መረዳትን ያን ያህል ከማሳነሳቸው አሳብ ጋር እኔ ብዙ ባልስማማም፤ ስለፈቃድ ያሉት ግን ትክክል ነው።

በፈቃድና በመረዳት መካከል ያለውን ግንኙነት እንደዚህ ማያያዝ ይቻላል። ለእውነት መጋለጥ (exposure to the truth) ወደመታዘዝ፤ መታዘዝ ወደ መረዳት፤ መረዳት ወደ ኃይል ያደርሳል። ልብ አድርጉ መታዘዝ የፈቃድ እርምጃ ነው። በመጀመሪያ ለአንድ እውነት እንጋለጣለን፤ ይህ እውነት ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሊሆን ይችላል፤ ወይም በሌላ መንገድ ያገኘነው እውነት ሊሆን ይችላል። ለዚያ ለተጋለጥንለት እውነት ስንታዘዝ፤ መረዳትን እናገኛለን። ያ መረዳት ደግሞ በተራው የእግዚአብሔርን ኃይል እንድንለማመድ በሩን ይከፍትልናል። ከዚያ ኃይል የተነሳ ከዚያ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ተባብረን በማናውቀው መንገድ መተባበር እንጀምራለን።

እግዚአብሔርን ለመተማመን ወስነን ስናደርግ እርሱ ለአዕምሮአችንና ለስሜታችን ታማኝነቱን እንዲገልጽ ይፈታዋል። ይህ የሚሆነው ግን በውሳኔ ድርጊት ስንጀምር ብቻ ነው። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ አውጎስጢኖስ (St. Augustine) ይህን አሳብ ሲገልጽ እንዲህ አለ። "እምነት ማለት ያላየነውን ነገር ማመን ሲሆን፤ የእምነት ውጤቱ ደግሞ ያመነውን ነገር ማየት ነው።" (Faith is to believe what we do not see, and the reward of faith is to see what we believe.) ይህ በሚሆንበት ጊዜ በፍርሀት ላይ ኃይል ይኖረናል። አስፈሪ ነገር ሕይወታችንን በሚገዳደርበት ጊዜ እንኳን ለእውነት ለመቆም ኃይል ይኖረናል። ለእውነት ከመጋለጥ ተነስተን በመታዘዝ በኩል ወደ መረዳት እንደርሳለን ማለት ነው። ሁል ጊዜ ግን መታዘዝ መረዳትን ይቀድማል (ይህ አሳብ ትንሽ ማብላላትን ይጠይቃል) ።

ስለዚህ የእምነት ጥያቄ በቲዮሪ እና በቲዮሎጂ ደረጃ የሚፈታ አይደለም። ምክንያቱም እምነት ድርጊት እንዲቀድም ይጠይቃል፤ ድርጊት እውቀት ያመጣል፤ እውቀት ደግሞ መረዳትን የሚያመጣ ወኪል ነው። ድርጊትን የሚቀሰቅሰው ደግሞ ፈቃድ ነው።





ይህንን በደንብ መረዳት ወሳኝ ነው። የእውቀት ሃቀኝነት (intellectual integrity) በሚል የተዛባ ቦታ ላይ ቆመው ያአጉል ቦታ ያቆማቸው ሃቀኝነታቸው እምነታቸውን እንዳይለማመዱ ማሠሪያ ሰንሰለት የሆነባቸው ብዙ ሊቃውንት አሉ። እንዲህ አይነቶቹ ሰዎች እምነት የእውቀት ውጤት ስለሚመስላቸው ያልተረዱትን ነገር መቀበል ሃቀኝነታቸውን የሚያመቻምችባቸው (compromise) ይመስላቸዋል። ይህ አጉል ቦታ ላይ ያለው ሃቀኝነታቸው የእግዚአብሔርን ነገር እንዳይታዘዙ ይከለክላቸዋል; ከዚህም የተነሳ እምነትን በሕይወታቸው ቦታ የሌለው ነገር አድርገው የሚጠይቀውን አላፊነትም ሆነ የሚሰጠውን ተስፋ እርግፍ አድርገው ይተዉታል።

## 2. ፈቃድ ደካማ ሲሆን

እምነትን የሚያንቀሳቅሰው ፈቃድ ነው ካልን ፈቃድስ ደካማ ከሆን? አስፈላጊ ጥያቄ ይመስለኛል። ምክንያቱን ሁላችንም በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ፈቃዳችን የወደድነውን ያህል ጠንካራ ያልሆነበትን ጊዜ አሳልፈናል። ስንፈተን፤ ስንጨነቅ፤ ስንናደድ፤ በራሳችን ስናፍር፤ መጥፎ ልምምድ ስንለማመድ፦ እስቲ እነኚህን አሳቦች በተራ ባጭሩ እንያቸው።

### ፈተና

1ቆሮ 10:13 ልብን የሚያሞቅ ተስፋ ይሰጠናል።

> *"በሰው ሁሉ ላይ ከደረሰው ፈተና የተለየ አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው። ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም። ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።"*

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለት የሚቃረኑ የሚመስሉ አሳቦች እናያለን። በመጀመሪያ በፈተናችን ፊት ብቻችንን አይደለንም፤ ሁሉ ሰው ይፈተናል። በዚህ መንገድ ከሌሎች የተለየን አይደለንም። አንዳንዴ የኛ ፈተና ከሁሉ የባሰ ቢመስለንም ሁኔታው ግን እንደዚያ አይደለም፡

ባለቤቴ አንድ ቦታ አንብባ የነገረችኝና እኔም ብዙ ቦታ የደጋገምኩት አንድ ታሪክ አለ። ሰዎች ሁሉ "የኔ ችግር የባሰ ነው፤ ከማንም አይወዳደርም" እያሉ ሲያጉረመርሙ እግዚአብሔር ሰማ። ከዚያ እግዚአብሔር የሚያጉረመርሙትን ሁሉ ጠራና " እንዲህ ያሰለቻችሁን ችግራችሁን አምጡና እዚህ ጣሉት። በልዋጩ ግን እዚህ ከተጣሉት ችግሮች በጣም ቀላል ነው የምትሉትን ይዛችሁ ሂዱ" አላቸው። አጉረምራሚዎቹ በጣም ቀላል የሆነውን ችግር ፈልገው ፈልገው በመጨረሻ ራሳቸው አምጥተው የጣሉትን ችግር ይዘው ይሄዳሉ።

የታሪኩ መልዕክት ግልጽ ነው። የኛ ፈተና ከሌሎቹ ሁሉ የከፋ ሆኖ አይደለም። እግዚአብሔርም ለሌሎች በፈተናቸው ጊዜ የሚሰጣቸውን እርዳታ ለእኛም ያዘጋጅልናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥቅሱ የሚለው ከፈተናችን ለመውጣት ግላዊ ሁኔታም አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር የዚህን ዩኒቨርስ ፕላን ሲያወጣ፤ እኔን የሚገጥመኝ ፈተና ሁሉ በአሳቡ ነበር። በኛ ላይ ሊሆን ያለውን ነገር ሁሉ እንዲሆን የሚፈቅድና የሚቆጣጠር እግዚአብሔር ነው። እርሱ ከአቅማችን በላይ የሆነ ፈተና እንዳይደርስብን በጥንቃቄ ይመለከታል። ያም ማለት እያንዳንዱን ፈተናችንን እግዚአብሔር በትኩረት ያየዋል፤ ስለዚህ ከልክ ማለፍ አይችልም። ፈተናችንን እንድናሸንፍ እስከሚያስችለን ድረስ ይጠባበቃል። ፈተናችንን አሸንፈን ወደ ድል በመጣን ቁጥር የእምነት ጡንቻችንን እናጠነክራለን። የፈቃዳችንን ድካምና ብርታት እግዚአብሔር ያውቀዋል፤ ስለሆነም መቋቋም የማንችለው ፈተና እንዳይደርስብን ይጠነቀቅልናል። ፈተናው ከበድ ሲል ለመቋቋም ያለን አቅም በቂ አይደለም ብለን እናስብ ይሆናል፤ ነገር ግን በቂ ነው።

## ጭንቀት

አንዳንድ ጭንቀቶች የምርጫ ውሳኔዎች ናቸው። ጌታ የሱስ እንደነዚህ ያሉትን ጭንቀቶች በመቃወም አስተምሯል። በተራራው ስብከቱ ላይ አትጨነቁ የሚለው ትምህርቱ የመልዕክቱ መካከለኛ ነበር (ማቴዎስ 6:25-34) ። የጭንቀት ስሜት እንጨነቅ ብለን የምናደርገው አይደለም። ጭንቀት የለመደ አዕምሮ ግን ጭንቀትን





ይራባል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚጨነቅን እንደኃጢአተኛ እንጂ እንደተጠቃ አድርጎ አያየውም።

ምክንያቱም ጭንቀት የእግዚአብሔርን ታላቅነት፤ ብርቱነትና ጥበበኛነት መርሳት ነው። በአጠራጣሪ ቦታ ላይ ቆመን በእምነት ወደርሱ ለመመለስ ወይም በአለማመን ወደ ጭንቀት ለመሄድ ስናመነታ ጌታ ሁል ጊዜ "በኔ ታመኑ" ይለናል። አንዳንድ ጭንቀቶች ከቁጥጥራችን ውጪ ናቸው። እንዲህ አይነት ጭንቀት በሚይዘን ጊዜ አላፊነት አለበን። የእግዚአብሔርን እንክብካቤና ፈውስ እንዴት ተቀብለን ስሜታዊ ጉዳታችንን እንዴት ልናክምበት እንደምንችል መማር ያስፈልገናል። ምክንያቱም በዚህ አይነት ጊዜ ከሁሉም በላይ ውስጣዊ ፈውስ ያስፈልገናል።

## ንዴት

ንዴት ብዙ ጊዜ ባለፈው ሁኔታ የተጎዳ ስሜት የተወው ጠባሳ ሲነካ በውስጣችን የሚፈጠረው መልስ (reaction) ነው ይላሉ የዲሲፕሊኑ ባለሙያዎች፤ ቁጣ በውስጣዊ ፈውስ ላይ ባተኮረ የጸሎት አገልግሎት መፈወስ ያለበት በሽታ ነው። ስለዚህ ንዴትን ለማሸነፍ ለሁኔታው ያለን አቀራረብ ትክክለኛ መሆን አለበት።

ሁለት መንፈሳዊ የሆኑ የአቀራረብ መንገዶች በተለይ ንዴትን ለማሸነፍ ወሳኞች ናቸው። የመጀመሪያው ይቅርታ ነው። ይቅርታን በሕይወታችን መለማመድ ስንጀምር፤ ሌሎችንም ሆነ ራሳችንን ይቅር ስንል እግዚአብሔር የንዴትን ስር በመንቀል በውስጣችን ፈውስ እንዲያመጣ እንፈቅድለታለን። ችግሩ ግን የእኛ እዚያ ቦታ ላይ መድረስ በጣም ከባድ መሆኑ ነው። ይቅር አለማለት ለንዳንዶቻችን የተወረሰ ቅርስ ያህል በሕይወታችን የተከበረ ቦታ ተሰጥቶት ቁጭ ብሏል፤ ሌሎቻችን ደግሞ ይቅር አለማለትን እንደ መንፈሳዊ ብስለት (spiritual maturity) ነው የምንቆጥረው።

በተለይ ራሳችንን ይቅር አለማለት ለእኛ ህብረተሰብ የቅድስና ምልክት የሆነልን ብዙዎች ነን። "የኔ ሥራ ስንቱ ተቆጥሮ" እያሉ ፍርድን በራስ ላይ መቆለል የጽድቅ ሥራ የሚመስለን ብዙዎች ነን።

ይቅርታ ፍርድን ከእኛ እጅ አውጥቶ በእግዚአብሔር እጅ ያደርገዋል። እግዚአብሔርም ያንን ይወዳል፤

*"በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ" ሮሜ 12፤19።*

ፍርድን ለእግዚአብሔር ከተውንለት እኛ የዕለት ሕይወታችንን በሰላም ለመኖር ነፃ እንሆናለን።

ሁለተኛው ንዴትን የመቆጣጠር እርምጃ ራስን መቀበል ነው። ሌሎች ስለእኛ የሚናገሩትን መልካም ነገር ጤነኛ በሆነ ሁኔታ መቀበል መቻል አለብን። ይህን አሳብ፤ በተለይ ራስን ዝቅ ማድረግ እንደትህትና በሚቆጠርበት በእኛ ህብረተሰብ ለመቀበል አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን ያ ከሌሎች ያገኘነው ሙገሳና ተቀባይነት የክርስቶስ ተከታዮች በመሆናችን እንደሆነ አድርገን ብንቆጥረው ለመቀበል ይቀለን ይሆናል። ሌሎች ቢቀበሉንም እንኳን ራሳችንን መቀበል የሚያቅተን ሁልጊዜ በዚያ አሁን ሌሎች በሚያዩን ሁኔታ አልገኝ ይሆናል የሚለው ፍርሐት ነው። ማስታወስ ያለብን ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኘነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። የጌታ የሱስ በአባቱ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ደግሞ የማይለወጥ፤የማይጠየቅ ነው። እኛም ክርስቶስን በተቀበልን ጊዜ የተሰጠን ስጦታ ይህ ተቀባይነት ነው። ሌሎች የሚቀበሉንም መነሻው ይህ ስለሆነ ነው። ይህንን እውነት ደሞ ለራሳችን ደግመን ደጋግመን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

## ሐፍረት

ሐፍረት በመሠረቱ ራስን ዝቅ አድርጎ ማየት ነው። ሐፍረት ራሱን በሚደጋገምና በክብ መሽከርከሪያ ላይ በሚሄድ አጉል ሂደት ውስጥ ይከተናል። በእንግሊዝኛ ይህ ሁኔታ (vicious cycle) ይባላል። ይህ መውጫ የሌለው አዙሪት ራስን ዝቅ አድርጎ (negative self image) በማየት ይጀምርና ወደ ፍርሀት (fear) ያመጣናል፤ ፍርሀት አለመሳካትን (failure) ፤ አለመሳካት መልሶ ራስን ዝቅ አድርጎ ወደ መመልከት አዙሪቱ ይቀጥላል ማለት ነው።





የሥነ ልቡና ባለሙያዎች እንደሚሉት ደግሞ ይህ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ከመጠቃት የሚመነጭ ሲሆን የተጠቃው ሰውም በተራው ሌሎችን የማጥቃት ዝንባሌ ያሳያል። በስድብም ሆነ ስም በማጥፋት ወይም በጉልበት ወይም በማኩረፍ ሌሎችን ለማጥቃት የሚሞክሩ ሁሉ ለራሳቸው ያላቸው ግምት ዝቅተኛ የሆነ ነው። እግዚአብሔር ካልፈወሳቸው በስተቀር ይህ ሁኔታ ራሱን እንደገና እያጎለመሰ ይቀጥላል። ታላላቅ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች ሕይወት ሲጠና ብዙዎቹ ታሪካቸው ይህ ነው፤ ለራሳቸው ያላቸው ግምት በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ያሳፍራቸዋል፤ ለሌሎችም ሕይወት ያላቸው ግምት ዝቅ ያለ ስለሚሆን ነው ሲገድሉ እንኳን የማይገዳቸው።

## ክፉ ልማድ

የደካማ ፈቃድ ሌላው ፈተና በቀላሉ በመጥፎ ወይም በክፉ ልማድ መጠመድ ነው። መጥፎ ልማድ ሰይጣናዊ ተግባር ነው። መጥፎ ልማድ ዛሬ አጊጦና ዘመናዊ ልብሶችን ለብሶ በታላላቅ ስፍራዎች፤ በፖለቲካ መድረኮች፤ በዜናና ኢንፎርሜሽን ማሠራጫ ቦታዎች ተንሰራፍቷል። በቴሌቪዥን፤ በሲኒማ፤ በኢንተርኔት አሁን ደግሞ በፌስ ቡክ፤ በትዊተር ሳሎኖችን ብቻ ሳይሆን መኝታ ቤታችን ድረስ፤ መቅደሳችን ብቻ ሳይሆን ቅድስተ ቅዱሳናችን ድረስ ሰተት ብሎ ይገባል።

ክፉ ልማድ ቅጥ የለሽ ዝሙትና ወሲባዊ ፊንጠዝያ (pornography and orgie) ያጠቃልላል። ክፉ ልማድ ባዕድ አምልኮ፣ መተት አስማት፣ ጥንቆላ፣ እና ተመሳሳይ ልምምድ ነው፣ ክፉ ልማድ ራስን ሱስ ለሚያሲዙ እጾች ማጋለጥ ነው። ክፉ ልማድ የሌሎችን ደግ አለማየት፤ ስም ማጥፋትንና መሠረተ ቢስ ነቀፋን ሁሉ ይጨምራል

ዛሬ ይህ ሁኔታ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ተስፋፍቶ ሠለጠኑ በሚባሉት ሕብረተሰቦች እንኳን ቆንጆ ቆንጆ ስም ተሰጥቶት እምሮና አጊጦ ተቀባይነት አግኝቷል። ይህ ልማድ ሰይጣንን በመቃወምና በሥራዎቹ ላይ ዘመቻ በማድረግ ብቻ ነው ልናሸንፈው የምንችለው።

## 3 . ፈቃድን ማጠናከር

ፈቃድህን ለማጠናከር ወይም ፈቃድሽን ለማጠናከር ምን ማድረግ አለብሽ ብዬ ብጠይቅ ጥሩ መልስ እንደምትምልሱልኝ እርግጠኛ ነኝ። ለእኛ ለክርስቲያኖች የደከመ ፈቃዳችንን ለማጠናከር እንዲያገለግሉን ዝግጁ የሆኑ ነገሮች በአካባቢያችን አሉ።

ቤተ ክርስቲያን መሔድን ማዘተር፣ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ከሚያውቁ ሰዎች የምንገናኘው እዚያ ነው። ከድካማቸውና ከእንከናቸው ጋርም ቢሆን እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎች ፈቃድን የሚያጠናክር ብዙ ሌላ ቦታ የማይገኝ ጥበብ አላቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚጠብቅብንን ነገር የምናገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ቀላል መንገዶች ይመስላሉ። ግን አዘትረው ወደቤተ ክርስቲያን የሚሄዱና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነቡ በቀላሉ አይደፈሩም፤ ፈቃዳቸውም ጠንካራ ነው።

እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ነገሮች ማድረግና መለማመድ ስንጀምር ደግሞ፣ መንፈሳዊ ጉልበታችን መጠንከር ይጀምራል። ሌሎችን መውደድ፣ ከፈተና መጠበቅ እና እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ ማመን፣ እግዚአብሔር ከሚጠብቅብን ነገሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

## 4 . ምናብ (Imagination)

ይህንን ምዕራፍ ከመዝጋቴ በፊት አንድ አሳብ ለመግለጽ እወዳለሁ። ምናብ (በአምስቱ የስሜት አውታሮች ማለትም በማየት፣ በመስማት፤ በማሽተት፤ በመቅመስ እና በመዳሰስ የማይደረስባቸውን ነገሮች በዓይነ ሕሊና እንዲደረስባቸው የሚያደርግ ተፈጥሮአዊ ችሎታ) በሕይወታችን በጣም አስፈላጊ ኃይል ነው። ምናብ መንፈስንና አዕምሮን ከሚያገናኙት የግንኙነት መስመሮች አንዱ ነው። በሌላ አነጋገር ምናብ መንፈሳችን የሚፈልገውን ነገር ከምናውቅባቸው መንገዶች አንዱ ነው። እግዚአብሔርንም ለማዳመጥና በምን ላይ እምነት እንዲኖረን ለማወቅ ምናብን ማጎልመስ ያስፈልጋል፤





በመካከለኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ላይ (ከ16ኛው እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት) ምናብ የተነቀፈ ብቻ ሳይሆን የተወገዘም ነበር። ከዚህም የተነሳ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ገለል እየተደረገ አዕምሮአዊና ጥበባዊ ነገር በቻ እየጎላ መጣ። ዊሊያም ዴርቴጋ መንፈስን ማጥፋት (Quenching the Spirit) በሚለው መጽሐፋቸው የሚከተለውን ጽፈዋል።

የአዕምሮንና የነፍስን ግንኙነት ለመረዳት በተደረገው ጥረት አዕምሮ (intellect) ከፍተኛውን ቦታ ብቻ ሳይሆን በነፍስ ላይ የመሪነት ቦታ ተሰጥቶት ነበር። ይህ አሠራር ታዲያ አውቆም ይሁን ባለማወቅ ምናብን ዋጋ የሌለው በጣም ርካሽ ነገር አድርጎ አቀረበው ፤ ምናብ አሳብን ለማጎልመስና ፍልስፍናን ለማጥራት ሊሰጠው የሚገባውንም ቦታ አጣ።

ምናብ በውስጡ በደመ ነፍስ የማወቅ ስጦታ (intuition) አለው። ይህ ደግሞ የአዕምሮ ውጤት ሳይሆን ብዙ ጊዜ የመንፈስ ግፊት ነው። ወደ መጽሐፉ መጨረሻ አካባቢ በምዕራባውያን ሥልጣኔ ውስጥ አዕምሮ መሪነቱን እንዴት ሊይዝ እንደቻለ እናያለን።

### በአጭሩ

እግዚአብሔር በውስጣችን የተለያዩ ክፍሎች (Faculties) አስቀምጧል። ሁሉም መልካም ናቸው፣ ሆኖም ለመጥፎም ድርጊት ሊውሉ ይችላሉ። እያንዳንዱ ክፍል በውስጣችን የሚጫወተው የተለያየና የተወሰነ ሚና አለው። ሁሉም ክፍሎቻችን የተወሰነላቸውን ሚና ሲጫወቱ፣ እምነትን ለመለማመድ ቀላል ይሆናል።

በምናብ ተገፋፍተን ለማድረግ ስንነቃቃ የምናደርገውን ከማድረጋችን በፊት አዕምሮአችን ሙሉ ለሙሉ ሊረዳው ያስፈልጋል ማለት አይደለም። ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ አዕምሮ ይተባበራል።

አሳብ የአዕምሮ ይዘት ነው። በአንድ አሳብ ላይ ድርጊትን ከመፈጸም በፊት የግድ ስሜት መስማማት የለበትም።

ስሜት (Feeling) የስሜታዊነታችን (emotions) ይዘት ነው። ከስሜታችን ጋር ሁልጊዜ አዕምሮችን መስማማት ወይም መተባበር አለበት ማለት አይደለም።

ፈቃድ ከአዕምሮም ከስሜትም የበላይ ነው። እምነት ደግሞ የፈቃድ ልምምድ ነው። እምነት ከአዕምሮም ከስሜትም ቀዳሚነት ሊኖረው ይገባል። እምነት በድርጊት የተመሠረተ፣ በውጤት ላይ ያተኮረ፣ በግንኙነት የተደገፈ በፀጋ የተነቃቃ ነው። አዕምሮም ስሜትም ምናብም ፈቃድ እምነትን እንዳይለማመድ መከላከል የለባቸውም።





## ክፍል ሁለት
## የእምነት መንገዶች

በዚህ በሁለተኛው ክፍል ሐተታና ቲዮሪ የሆነውን የክፍል አንድን አቀራረብ ተወት አናደርግና ልምምዳዊና ተግባራዊ ወደ ሆነ አቀራረብ እንገባለን። እምነትን እንተረጉማለን፣ ተግባራዊ የሆኑና እምነትን ለማሳደግ የሚረዱ ሞዴሎችንና ዘዴዎችን እንጠቁማለን።

# ምዕራፍ ሶስት

## የእምነት አሠራር

የእምነት አሠራርን ለመግለጽ አስቀድመን ለእምነት ተግባራዊ ትርጉም መስጠት ይኖርብናል። እንዳንዴ ደግሞ እምነት ምን መሆኑን መተርጎም ብቻ ሳይሆን እምነት ምን እንዳልሆነ ማሳየቱ ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል። ስለዚህ እስቲ እምነት የሚመስሉ ነገር ግን እምነት ያልሆኑ ነገሮችን በመዘርዘር እንጀምር።

1. እምነት ያልሆኑ ነገሮች

*ሀ.* እምነት እርግጠኛነት አይደለም። ሰዎች በተለይ ተማሩ በሚባሉት አገሮች የነገርን ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ በሪሰርች ወይም በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ብዙ ትኩረት ያደርጋሉ። ከእነኚህ ሥራዎች የሚመጡትም ውጤቶች ለብዙ ሳይንሳዊ ግኝቶች፣ የሕክምና እውቀቶችና የቴክኔዎሎጂ እድገቶች መሠረት ሆነዋል። እኛም በየእለቱ ኑሮአችን ምንም ከማድረጋችን በፊት እርግጠኛ መሆን ይጠበቅብናል፤ ተሳሳትክ ወይም ተሳሳትሽ መባል አንፈልግም። በዚህ ሁኔታ ተመቻችተን ሳለን እግዚአብሔር ጎነጥ ያደርገንና።

> *"ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም። "*
> *(ዕብራውያን 11:6)* ይለናል።

በሌላ አነጋገር አንድ እርምጃ ለመውሰድ ሁልጊዜ እርግጠኛ መሆን አለብኝ የምንል ከሆነ እግዚአብሔር ደስ አይሰኝም። ምክንያቱም እምነት ማለት እርግጠኛ ሳይሆኑ ማድረግ ወይም እርግጠኛ ባልሆኑበት ነገር ላይ እርምጃ መውሰድ ነው። እርግጠኛ ከሆንን እምነት አያስፈልገንም፤ እምነት ካስፈለገ ደግሞ እርግጠኝነት የለም።

ለ. እምነት ስሜት አይደለም፤ የእውቀት ውጤትም አይደለም። ይህንን ሀሳብ በሰፊው ስላየነው በዚሁ እንለፈው።

ሐ. እምነት እግዚአብሔርን ማግባባትና እኛ የወደድነውን እንዲያደርግ መሞከር አይደለም። እግዚአብሔር የማይወደውን ነገር ለማድረግም እምነትን መጠቀም አንችልም።

እኔ በነበርኩበት ቤተ ክርስቲያን የሆነ ታሪክ ነው። ልጅቷ የቤተክርስቲያን ውስጠኛ አይደለችም። አንድ እግሯን እየሸመቀቀ ሲያማት ብዙ ቆይታለች። እንዳውም እየባሰባት እግሯም እየደነዘዘ ብዙ አስፈርቷት እንደነበር ነው ያጫወተችን።

አንድ የምታውቀው የቤተክርስቲያን ሰው ነው "ቤተክርስቲያን መጥተሽ ቢፀልይልሽ" ብሎ የጋበዛት። ለጸሎት የመጣች እለት መጋቢው ካነጋገራት በኋላ "እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ ወይ?" ብሎ ጠየቃት፤ በደንብ እንደምታምን አረጋግጣ መለሰች። መጋቢው ቀጠለና አሁን እግዚአብሔር ቢፈውስሽ ምን ታደርጊያለሽ ብሎ ጠየቃት፤ እርግጠኛ ነኝ የጠበቀው መልስ "እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ወይም የእግዚአብሔርን ታምር ለሌሎች አወራለሁ… በዚህ መስመር ያለ አሳብ ይመስለኛል። እርሷ ግን "እዚህ አውራ መንገድ 67 (Hwy. 67) ላይ የተከፈተ አዲስ ናይት ክለብ አለ። እዚያ ሄጄ ያን ያማረኝን ዳንስ እስቲነጋ ድረስ እስነካዋለሁ" ብላ ነበር የመለሰችው። እግዚአብሔር በቸርነቱ ልጅቱን ፈወሳት። ፈውሱ ግን የእምነት ውጤት አልነበረም።

መ. እምነት ከእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማግኘት የምንከፍለውም ዋጋ አይደለም። እግዚአብሔር እንዲያደርግ እምነት ያስፈልጋል። ነገር ግን እምነት ለተደረገልን ነገር ውለታ ሆኖ መታየት የለበትም። በእምነትም ሆነ አለ እምነት እግዚአብሔር የሚሰጠው ከቸርነቱ የተነሳ ብቻ ነው።





ሠ. እምነት የሰው ድርጊት ብቻ አይደለም፣ እግዚአብሔርም ሙሉ በሙሉ የሚሳተፍበት ነው። እንዲያውም እምነትን የሚጀምረው እግዚአብሔር ነው፤ የሚያስኬደው እርሱ ነው፤ ለኛም የሚያሳውቀን እርሱ ነው፤ የሚያስችለው እርሱ ነው፤ ከዚያም ለእምነታችን ምላሽ የሚሰጠው እርሱ ነው።

*"የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ እርሱ ነው. ." ዕብራውያን 12፤2*

ረ. እምነት አላፊነትን መተው አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እኛ ልናደርጋቸው በሚገባን ትዕዛዞችና አላፊነቶች የተሞላ ነው።እንዳውም እምነት ራሱ እንደ እግዚአብሔር ሰዎች ከሚጠበቁብን አላፊነቶች አንዱ ነው። ወይም እምነት ድርጊት ነው ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ ከሆነ እስካላደረግነው ድረስ አላመነውም ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ

*"ሊሠራ የማይወድ አይብላ" 2ተሰሎንቄ 3፤10*

ብሎ አስተምሯል። አልሠራም እግዚአብሔር እንደሚመግበኝ አምናለሁ ብለን ቁጭ ካልን እምነት መለማመዳችን ሳይሆን አላፊነታችንን መተዋችን ስለሆነ፣ ረሀብ ቢቆነድደን እንደነቅ።

ሰ. እምነት እንደ ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ ሌሎችን ዝቅ ዝቅ የምናደርግበት፣ ራሳችንንም ከፍ ከፍ ለማድረግ የምንጠቀምበት አይደለም።

## 2. እምነት ምንድነው?

1ዜና 5፤20 ላይ *"ስለታመኑበት ጸሎታቸውን ሰማ"* የሚል ቃል አለ። እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲመልስ የሚያስፈልገን እምነት ከሆነ፣ ይህ እምነት የተባለ ነገር ምን እንደሆነ ጠጋ ብለን መመርመር ይገባናል ማለት ነው። በሰፊው የሚጠቀሰው

የእምነት ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዕብራውያን 11:1 ላይ ያለው ነው።

> *እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር <u>የሚያስረግጥ፤</u> የማናየውንም ነገር <u>የሚያስረዳ</u> ነው።*

አዲሱ መደበኛ ትርጉም ይህንኑ ጥቅስ ሰፋ አድርጎ ተርጉሞታል፣

> *እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም <u>እርግጠኛ የምንሆንበት፣</u> የማናየውም ነገር <u>እውን መሆኑን</u> የምንረዳበት ነው።*

በእንግሊዝኛ ኪንግ ጀምስ የተባለውን ቅጂ ያስቀመጠውን የዚህ ጥቅስ ትርጉም ደግሞ እንዲህ ይላል፣

> *እምነት ተስፋ ያደረግነውን ነገር <u>የምንጨብጥበት</u> ላላየነው ነገር <u>እርግጠኛ የምንሆንበት</u> ነው።*

አስፈላጊ የሆኑትን ሐረጎች ወይም ቃላት አስምሬባቸዋለሁ። እነኚህ ቃላት በግሪኩ ቋንቋ የነበራቸውን ትርጉም ማየት ይጠቅማል። "እርግጠኛ የምንሆንበት" "የሚያስረግጥ" በተለያዩየእንግሊዝኛትርጉሞች "sure","confidence", "substance", "trust", "assurance" በሚሉት ቃላት የተተረጎመ ነው። በግሪኩ ቃሉ ሃይፖስታስስ (hypostasis) ሲሆን የአሳብ ወይም የግምት ወይም የጥላ እውነተኛ አካል ማለት ነው። ቃሉ በገጹ ሲተረጎም፣ ከስር የሚቆም ነገር፣ እርግጠኛ በሆነ ነገር ላር የተመሠረተ ገለጣ ነው። ጥላ ከጥላው በስተኋላ እርግጠኛ ነገር አለ፤ ነፀብራቅ ካየን በሩቅ ወይም በቅርብ አንፀባራቂው አካል አለ ማለት ነው። ስለዚህ በዚህ ትርጉም መሠረት ስናየው፣ እምነት ተስፋ ከምናደርገው ነገር ስር የቆመ ነገር ወይም ተስፋ የምናደርገውን ነገር ማረጋገጫ ነው። የዚህ ሐተታ ዋናው ፍሬ አሳብ እምነት ከእርግጠኝነት አለማነሱን ለማሳየት ነው። እምነት ምኞት አይደለም፣ እምነት ያልሆነውን በጭፍን መቀበልም አይደለም፣ እምነት ትልቅ ነው።





እምነት የመተካት ባሕሪም አለው፤ ተስፋ ያደረግነውን ነገር ተክቶ ይቆማል።የተስፋ እርግጠኝነት እምነት ነው፤ እምነት ተስፋ ያደረግነውን ነገር ቦታ ይዞ ያ እውነተኛው ነገር እስኪገለጥ ድረስ በዚያ የሚቆም ነው፤ ያ ተስፋ ያደረግነው ነገር ሲመጣ አሁን ለዚያ ነገር እምነት አያስፈልገንም።

ሌላው በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተሠመረበት ሐረግ "እውን መሆኑን የሚያስረዳ" የሚለው ነው። ይህ ሐረግ በተለያዩ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች በእነኚህ ቃላት ተተርጉሟል። "certain, handle, conviction, evidence" ይህ ቃል በግሪኩ ኤልግሞስ (elegmos) ሲሆን proof ወይም evidence የሚል የሕግ (legal) ቃል ነው።

እነኚህ ቃላት በተለይ በምዕራባውያን የሕግ ተቋም ውስጥ በጣም ቁልፍ ናቸው። ብዙዎቻችን የኦጄ ሲምሰንን የፍርድቤት ጉዳይ እናስታውሰዋለን። በአሜሪካ የምዕተ አለሙ የፍርድቤት ጉዳይ (The case of the century) የተባለ ነው። ብዙዎች ሲምሰን ከፍርድ ነጻ የሆነው የ evidence መበላሸትና የproof ማነስ ነው ብለው ያምናሉ። እነኚህ ቃላት በሕጉ ሥርዓት ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ ቦታ ለማሳየት ነው። "የማናየው ነገር እውነት መሆኑን የምንረዳበት" የሚለው ገለጻ ጥሩ ትርጉም ነው። ይህ ገለጻ የሚያስታውሰኝ አንድ ታሪክ አለ።

ወንድሜ መስፍን ለማ ዱሮ የነገረኝ ነው። ከጊዜው መርዘም የተነሳ እርሱ ራሱ ሳይረሳው አይቀርም። የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የነበሩ ጊዜ እግር ኳስ ለመጫወት ከነበሩባት ትንሽ ከተማ ሌላ ትንሽ ከተማ ይሄዳሉ።

ከጨዋታው ሲመለሱ በሎንቺና (ህዝብ ማመላለሻ) ነበር ወደ ቤታቸው የሚሄዱት።ሾፌሩ የሰዉ ቁጥር ስለበዛ፥ ከከተማው እስኪወጡ በእግሩ የሚሄድና እዚያ የሚጭነው አንድ ፈቃደኛ ሰው ካለ ይጠይቃል። ከእነርሱ የቡድን አባሎች አንዱ የሆነው ጌታቸው እሺ ብሎ ይወርድና ከከተማው ለመውጣት ሩጫ ይጀምራል። ሾፌሩ ግን ታማኝ ሆኖ አልተገኘም። እንዲ መንገዱን ስለጀመረ እንደገና ወደ ኋላ መመለስ ወይም መዘግየት አልፈለገም። ብዙ ከሄደ በኋላ ነው በቡድኑ ውትወታና ማስፈራራት ሊመለስ የተገደደው። ሲመለሱ ያስደነቃቸው ነገር ጌታቸው

ከከተማው ወጥቶ ብዙ ቢርቅም ባለማቋረጥ ይሮጥ ነበር። በኋላ “ምነው?” ሲባል፥ “ቮፌሩ እምቢ ቢልም እናንተ ጥላችሁኝ እንደማትሄዱ አውቃለሁ” ነበር ጌታቸው ያላቸው።

በዚህ ገለጻ ያለው ዋና አሳብ እንግዲህ እምነት አሁን የማናየው ነገር እስክናየው ድረስ እውነት መሆኑን ያረጋግጥልናል። እምነት ባሁኑ ጊዜ ያለ እርግጠኝነት፤ ወደፊት የሚሆነውን ነገር ተክቶ ያ የሚሆነው ነገር እስኪሆን ድረስ የሚቆይ፣ የማይታየውን ነገር አየዋለሁ ብሎ ተደላድሎ መቆም ነው።

## 3. እምነት የሚሠራው እንዴት ነው?

የዚህን እምነት የተባለ ድንቅ ስጦታ አሠራሩን እስቲ እንየው፥

አንደኛ፥ እግዚአብሔር ለኛ ሊያደርግልን ይፈልጋል።

ሁለተኛ፥ ይህ የሚያደርግልን ነገር ምን መሆኑንም ያስታውቀናል። በፍላጎት፣ በቃሉ፡ በአሳባችን፣ በሌሎች በኩል፣ ሊያደርግልን የፈለገውን ነገር ያሳውቀናል።

ሶስተኛ፥ ያን የሚያደርግልንን ነገር የምንጠይቅበትን እምነት ይሰጠናል።

አራተኛ፥ እኛ በፈቃዳችን ያንን እምነት መለማመድ እንጀምራለን።

አምስተኛ፤ እምነታችን እርሱ ሊያደርግልን በወደደው ነገር ላይ እንዲሠራ ያነሳሳዋል። እኛ በእምነታችን እያደረግን ስንሄድ፣ እግዚአብሔር ደግሞ መልስ ማዘጋጀቱን ይቀጥላል።

ስድስተኛ፥ በዚህ ጊዜ እምነታችን የመልሱን ቦታ ይይዛል። እግዚአብሔር የወደደውን ያህል ጊዜ ወስዶ እንዲሠራበት እምነታችን እግዚአብሔርን ያነሳሳዋል፤ ለእኛ ደግሞ እምነታችን የመልሱን ቦታ ይዞ ይቆምልናል፤ ለመልሱም እርግጠኛነትን በውስጣችን ይሠራል።





ሰባተኛ ፥ ጊዜው ትክክል በሚሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር መልሱን ይልክልናል።

የሁላችንም ጥድፊያ ቁጥር ሰባት ላይ ለመድረስ ነው። ጊዜው ሲደርስ ለማየት ... መቼ ነው ያ ጊዜ? መልሳችንን የምናገኘው መቼ ነው? ወይም እምነታችን እስከመቼ ነው የሚቆምልን?

ዕብራውያን ምዕራፍ 11 በእምነት አርበኞች ምስል ያጌጠ ባለ ግርማ የክብር ሰሌዳ ይመስላል። በዚህ ሰሌዳ ላይ የተደረደሩ ቆራጥና ታላላቅ የእምነት አርበኞች ናቸው። የሚገርመው ነገር ግን ብዙዎቹ በእምነት የጠበቁትን ነገር በዚህ ሕይወታቸው እያሉ አላዩትም።

> *“እነኚህ ሁሉ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ሳያገኙ፣ እምነታቸውን እንደጠበቁ ሞቱ፤ ሆኖም ከሩቅ አይተው ሰላም አሉት” ዕብራውያን 11:13።*

የእምነት ኃይል የሚሰጠው እርግጠኝነት በእነኚህ አርበኞች ሕይወት ተመስክሯል። የዕብራውያን ጸሐፊ “የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል” ብሎ የሚጠቅሰው ገና ያልተከሰተውን የክርስቶስን በሥጋ መምጣት ነበር። ሌሎች በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱ ለእምነታቸው ፈጣን ውጤት አግኝተዋል። አብርሃም፣ ይስሃቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ሙሴ፣ ረአብና ሌሎችም የተመሰገኑ የእምነት ሰዎች ውጤታቸውን ተቀብለዋል። ጸሐፊው የእምነት ፍሬዎችን እንዲህ ሲል በማዥጎድጎድ አሳቡን ይደመድማል።

> *“እነዚህ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሱ፣ በቅን ፈረዱ፣ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ተቀበሉ፣ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፣ የእሳትን ኃይል አጠፉ፣ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፣ ከድካማቸው በረቱ፣ በጦርነት ኃያል ሆኑ፣ ባዕዳን ወታደሮችን አባረሩ፣ ሴቶች ሙታናቸውን በትንሳኤ ተቀበሉ”*
> *ቁጥር 33-35*

አንዳንድ ነገሮች እስከ ሩቅ ጊዜ መልስ አያገኙም፤ አንዳንዶቹ የመልሳቸው ጊዜ ከዚያም ያለፈ ይሆናል። ብዙዎች ግን መልሳቸው በቅርብ ጊዜ የሚሆን ነው። በሁሉም ጊዜ ግን እምነትን መለማመድ ያስመሰግናል፤ ያፀናል።

የእምነትን ትርጉም ከማጠቃለላችን በፊት እስቲ አንድ የግሪክ ቃል እንመልከት።

እምነት በግሪክ ቋንቋ ፒስቲስ (pistis) ነው። የቃሉ ትርጉም ለመስማማት ራስን መክፈት (allowing to be persuaded) ። የአንድ ነገር እርግጥኛነቱ ሳይረጋገጥ ወይም መረጋገጡ ሳይጠበቅ መቀበል ማለት ነው። ምክንያቱም እምነት እርግጠኝነት አይደለም። ሰው ነገር እርግጠኛ ነው ብሎ ለመቀበል ከአምስቱ የስሜት ህዋሶቹ (ማየት፣ መስማት፣ መቅመስ፣ ማሽተት፣ መንካት) ቢያንስ በአንዱ ማረጋገጥ አለበት። በዚህ ሁኔታ ነገር ከተረጋገጠ ጥሩ ነው። ያ ግን እምነት አይደለም። እግዚአብሔርን ለመታዘዝ፣ እርግጠኛ መሆን የለብኝም፣ ግን እድርግ ያለኝን አደርጋለሁ ብሎ መወሰን ያ እምነት ነው።

Vines Expository Dictionary እምነትን ሲተረጉመው እንዲህ ይላል "እግዚአብሔር በሰጠው መገለጥና እውነት ላይ የሆነ ሙሉ ማሳወቅን የሚያመጣ ጽኑ ስምምነት፣ በግል ራስን ለርሱ መስጠት፣ ወይም ራስን መስጠት የሚያንፀባርቅ ባሕሪ፣ ታማኝነትን ማሳወቅ" (A firm conviction, producing a full aknowledgement of God's revelation or truth , it is a personal surrender to Him, conduct inspired by such surrender. It is a pledge of fidelity.) እምነት በግዴለሽነት የሚሆን አይደለም። አማኙ የእምነቱን ውጤት በጉጉት መጠበቅ አለበት። ልብን በዚያ በእምነት በሚጠብቁት ነገር ላይ አውሎ በነገሩ መጸለይን ይጠይቃል። "ከሆነ ይሁን" የሚል ግዴለሽነትና ስንፍና በእምነት ወጥ ቦታ የለውም።

## 4. <u>የሚያድግ እምነት</u>

እምነት በፈለግነው ጊዜ የፈለግነውን ያህል የምናገኘው አይነት የገበያ ሸቀጥ አይደለም።

> *ሮሜ 3፤13 "እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ በሰጣችሁ እምነት መሠረት"፣* ይላል።





ለሚኖረን የእምነት መጠን ኃላፊው እግዚአብሔር ነው፤ ያ ብቻ ሳይሆን ያለን እምነት እንዲጎለምስ እግዚአብሔር ኃላፊነት ይሰማዋል። የ20ኛው መቶ ምዕተ አመት ታላቁ ክርስቲያን አሳቢ (The Great Christian thinker) የተባሉት እንግሊዛዊው C.S. Lewis, "The Efficacy of Prayer" በሚለው መጽሐፋቸው፣ የሚከተለውን አሳብ አስቀምጠዋል።

> "ብዙ አስደናቂ የሆኑ የጸሎት መልሶችን አይቻለሁ።አንዳንዶቹ እንዳውም ተአምር ናቸው ለማለት ይቃጣኛል። ብዙ ጊዜ እነዚህ የጸሎት መልሶች የሚመጡት ግን ምናልባት ደህንነትን ከማግኘታችን በፊት፣ ወይም ወዲያው ደህንነት እንዳገኘን ነው። በክርስትና ሕይወታችን እየቆየን ስንሄድ የዚህ ዓይነት የጸሎት መልሶች የተቆጠቡና የተራራቁ እየሆኑ ይመጣሉ። የጸሎታችን አለመመለስ ደግሞ ቶሎ ቶሎ የሚሆን ክስተት ብቻ ሳይሆን የበለጠ ግልጽና የበለጠ ጠንካራ እየሆነ ይመጣል።"

ይህ ትንተና ትክክል ይመስላችኋል? ከብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ጋር ባደረግኋቸው ውይይቶችና በራሴም ሕይወት ባሳለፍኩት ልምምድ እኔ የ C.S. Lewis ግምገማ ትክክል ነው እላለሁ። ታዲያ እዚህ ላይ ጉዳዩ ምንድነው? እግዚአብሔር የራሱ ባደረጋቸው ላይ ይጨክናል? በዚህ አሳብ ላይ አተኩሬ ሳስብ ነው እምነት እንደ ጡንቻ መሆኑን መገመት የቻልኩት። ጡንቻ የሚጠነክረውና ጠንካራ ሆኖ የሚቆየው ተጽእኖ ስናደርግበት ብቻ ነው። ሰው ታምሞ ባልጋ ላይ ለረጂም ጊዜ ቢቆይና ሕመሙ ሲሻለው ቢነሳ፣ ዱሮ ያደርግ የነበረውን ነገር ሁሉ ማድረግ አይችልም። ማገገም አለበት፣ እንዳውም አንዳንዶች ወደ ቴራፒ ይላካሉ። ጡንቻቸው ተመልሶ ዱሮ የሚሠራውን ለመሥራት ረጂም ጊዜ ይጠይቃል።

ላስተላልፈው የምፈልገው ነጥብ ይህ ነው። እግዚአብሔር ሁኔታችንን የሚከታተለው በቅርብ ነው። እምነታችን እያደገ እንዲሄድ በመጠናችን የሆነ ተጽእኖ (እኛ ፈተና ብለን የምንጠራውን) ይፈቅዳል። የጡንቻው ምሳሌ ሊላው የሚያስተላልፈው ትምሕርት ማንኛችንም ወዲያው ተነስተን ታላቅ የእምነት ሰው መሆን እንችልም። የእምነታችን እድገት በጥንቃቄ የተቀየሰ ሂደት ነው። ከምንቋቋመው ወይም ከአቅማችን በላይ የሆነ ፈተና እንዲደርስብን እግዚአብሔር አይፈቅድም፣ በሌላ

በኩል ደግሞ ሁሉ በቀላሉ እየተሳካልን ሞልቃቃ ሕይወት እንድንኖር አይተወንም። የእምነት ሰው ታታሪ፤ ትጉህ፤ ኅበዝ፤ ጠንካራ ነው። የእምነት ሰው ጽናትንና ብርታትን የሚለማመድ ነው። ሞልቃቃ ክርስቲያን ልብስ ሲቆሸሽም ልጅ ሲታመምም ማጉረምረሙ እኩል ነው። ለእግዚአብሔር ሥራም አይመችም።

## 5. <u>ፈታኝ እምነት</u>

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እየተፈተነ የተጠናከረና የነጠረ የእምነት ታሪክ አለ። ከጥቂት አመታት በፊት በቤተ ክርስቲያናችን የጸሎት ፕሮግራም ላይ አካፍዬው ብዙዎች ተምረውበት ነበር። ታሪኩ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 15፣ 22-28 ያለው የከነአናዊቷ ሴት ታሪክ ነው። ፈተናው ደግሞ ወግድ በመባል ወይም ፊት በመነሳት ስለ ሆነ የዚህ አይነት ፈተና በተለይ ለሴት ልጅ በጣም ከባድ ነው። ጥቅሱን እየተነተንን እንየው።

*የመጀመሪያው ወግዷ*
*አንዲት ከነዓናዊት ሴት ከዚያ አካባቢ በመውጣት ወደ ኢየሱስ መጥታ "ጌታ ሆይ የዳዊት ልጅ ራራልኝ፤ ልጄ በርኩስ መንፈስ ተይዛ በጣም ትሰቃያለች" ብላ ጮኸች። እርሱ ግን አንድም ቃል አልመለሰላትም*

ሁለተኛው ወግዷ
*ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው "እየተከተለች ትጮኻለችና ብታሰናብታትስ?" ብለው ጠየቁት*

ሶስተኛው ወግዷ
*እርሱም "የተላክሁት ከእስራኤል ቤት ሆነው ወደጠፉት በጎች ብቻ ነው" አለ፤ ሴትዮዋም እግሩ ላይ ወድቃ ጌታ ሆይ እርዳኝ" አለችው።*

እራተኛው ወግዷ
*እርሱም መልሶ "የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መወርወር አይገባም" አላት።*





ሴትዮዋ ግን ወስና የመጣች ስለነበረች  የተወረወረባትን ፍላጻ ሁሉ ችላ ተገፍትራ ከወደቀችበት እንደገና ብድግ ትላለች። ደቀ መዛሙርቱም ሆኑ ጌታ የሱስ ተሰፋ ያስቆረጧት በሚመስልበት ጊዜ በሌላ በኩል እንደገና ትመጣለች። እያችሁ በእያንዳንዱ ወግዷ እምነቷ እየተጠናከረና እያደገ ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔርን እናውጦ እንዲያደርግላት የሚያስችላት የእምነት ደረጃ ላይ ደረሰች።

*"እምን ጌታ ሆይ! ውሾችም እኮ ከጌታቸው ማዕድ ፍርፋሪ ይበላሉ" አለችው። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ "አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው፣ እንደፈለግሺው ይሁንልሽ" አላት። ልጇም ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰች።*

በመጀመሪያ የደረሰባት የዝምታ መስተንግዶ ነው። ጌታ የሱስ የሰማት እንኳን ሳይመስል ዝም አላት። የዚህ አይነት አቀባበል በሕይወታችሁ ተለማምዳችሁ እታውቁም? የመናቅ ዝቅ ዝቅ የመደረግ ስሜት ነው የሚያመጣባችሁ። እንዲህ ያለ የልብን ስብራት የያዘ ጥያቄ ጠይቆ ዝም መባል፣ ገበናን ከፍቶ አሳይቶ መልስ አለማግኘት በጣም ፈታኝ ሁኔታ ነው።

ይህቺ ሴት ራሷን ያገኘችው በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው። ከዚያ በላይ አስፈሪ የሆነው ነገር ደግሞ እግዚአብሔር ዝም ያለ ሲመስል፣ ድምጽ ሳይገኝ ሲቀር፣ መጽናናት ሳይመጣ፣ ሰማይ ሲዘጋ፣ እንዴት የሚያስፈራ ሁኔታ ነው?

ምናልባት ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዞር ብላ "እባካችሁ እርዱኝ፣ እስቲ እናንተ ጠይቁልኝ ብላ ይሆን?" ምክንያቱም ሁለተኛው መገፋት የመጣው ከእነርሱ ነበር። "እየጮኸች አስቸገረችን፣ ሂጂ በላት፣ አሰናብታት" ነው ያሉት።

ይህንንም ሁኔታ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የተለማመድን ብዙዎች አለን። ሰዎች ከችግራችን ጋር ስንሆን ከእነርሱ እንድንርቅ ሲገፉን፣ባያዩን፣ ችግራችንን ባይሰሙ የሚፈልጉ ሲሆኑ፣ "መጣ ደግሞ፣ መጣች ደግሞ" ሲባባሉብን፣ አይተውን

እንዳለዩን ሲሆኑ፣ መንገድ አቋርጠው ሲሸሹ፤ ይህ ሁሉ ሲደርስብን የሚሰማን የስሜት ጉዳት ነው ይህቺ ሴት የተሰማት። "አዘንኩ፣ ተሰበርኩ" ብላ ግን አላማዋን አልለወጠችም።

ሶስተኛው መገፋት ደግሞ ግራ የሚያጋባ ነው። ከሁለተኛው ጠንከር ያለ፣ ግላዊና ቀጥተኛ ነበር።

"ከተመረጠው ወገን አይደለሽም፣ ካልተመረጠ ወገን ነሽ" ነው የተባለችው። በታሪካችን ብዙ የዚህ አይነት ሁኔታዎች እናውቃለን፤ ሰው ከአንድ ወገን ሳይሆን ከሌላ ወገን ብቻ ስለሆነ የሚገለልበት። ይህ በጣም ከባድ ፈተና ነው። መርጠን ያደረግነው ሳይሆን ሳንመርጥ የሆነው ነገር እንቅፋት ሆኖ ሲያደናቅፈን ከባድ ፈተና ነው። ይህቺ ሴት ግን አሁንም ወድቃ አልቀረችም።

አራተኛው መገፋት ከሶስተኛው እንዳውም የባሰ ነው። ሶስተኛው ወገንን ሲከፋፍል አራተኛው ግን በጊዜው በአይሁዶችና በአሕዛብ መካከል የነበረውን የዘር ልዩነት የሚያጎላ ስለነበር ዘረኝነት ይመስላል። ዘረኝነት በትርጉሙ አንዱን ወገን ከሌላው መለየት ብቻ ሳይሆን አንዱን ወገን ከሌላው የበለጠ፣ የተሻለ ነው የሚል የሚያድግ ነቀርሳ ነው።

ይህ ሁኔታ ቅን የሆነ ነገር የለበትም። ሆኖም ግን የዚችን ሴት ውስጧን ባወቀው በጌታ የሱስ የተደረገ ነገር ነው። እርሷን ሊገናኛት ወደሚችልበት የእምነት ደረጃ ሊያደርሳት በጥንቃቄ የተቀየሰ ሂደት ነው። በመጀመሪያ ለአይሁዶች ብቻ በተፈቀደው መንገድ ስለጠየቀች ነው ግፊት የገጠማት፤ እንደ አሕዛብ መጠየቅ ወደምትችልበት ደረጃ መድረስ ነበረባት። ይህ አይነት መገፋት ቢደርስብን የእምነት ባልሆነ መንገድ እንዴት መመለስ እንደምንችል እናውቃለን። ብዙዎቻችንም በየጊዜው የምንለማመደው መንገድ ነው።

በዝምታው ጊዜ፥ "ይኸው ዘጋኝ፣ ሊሰማኝ እንኳን አልወደደም" ብለን ነበር ብዙዎቻችን የምንመልሰው።





"ትጮሀለች፣ ሂጂ በላት አሰናብታት"፥ በተባለች ጊዜ 'ጓደኞቼ ተከብሬ በኖርኩበት አገር አዋረዱኝ' ብለን ነበር ምናልባት ብዙዎቻችን የምንመልሰው።

"አንቺ እኔ ከተላክሁላቸው ወገን አይደለሽም"፥ በተባለች ጊዜ የነበረው ሁኔታ ላይ ራሳችንን ብናገኘው፣ 'እኔም ባለ ወገን ነኝ፣ ባባቴም በናቴም የትልቅ ሰው ዘር ነኝ' ብለን መመለስ ይቀለን ነበር።

ዘራችን እንደ ውሻ ዝቅ ዝቅ ቢደረግ ግን ዱላ መማዘዝ ባንደርስ እንኳን እኛም ሌላውን ዘር የበለጠ ማናናቃችን ተገቢ መልስ የሚመስለን ጥቂቶች ብቻ አይደለንም።

የትምህርቱ ዋና ክፍል ግን በሴትዮዋ ላይ የደረሰው አይደለም፤ እኛም በሰዎች ላይ እንዲህ ያለ ግፊት ማድረስ ተፈቅዶልናል ማለትም አይደለም። ምክንያቱም እኛ እንደ ጌታ የሱስ የማንንም የውስጥ አስተሳሰብ ማወቅ አልተሰጠንም። የትምህርቱ ትኩረት ግን በሴትዮዋ ያልተናወጠ አመለካከት ላይ ነው። ለእኛም የተተውልን "እየለመንኩት ብቆይ ይመልስልኛል" የሚለው የሴትዮዋ የእምነት ሚና እንጂ የጌታ የሱስን ሚና መጫወት አይደለም። በእኛም የሚደርስብንን ግፊት ሁሉ መነሻው ጌታ ሊሆን ይችላል። ግን ታግሰን ብንጠብቅ፣ እያንዳንዱም እንቅፋት በውሳኔ ብንቋቋመው መልስ ይመጣልናል። የትምህርቱ ጣዕም እሲህ ላይ ነው።

ያዕቆብ በመልዕክቱ ውስጥ ከሰላምታው ቀጥሎ የሚናገረው በዚህ አሳብ ላይ ነው።

> *"ወንድሞቼ ሆይ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደሙሉ ደስታ ቁጠሩት፣ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግስትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ" ያዕቆብ 1፤ 2-3።*

በምትፈተኑበት ጊዜ ደስ ይበላችሁ ነው ሐዋርያው የሚለው። ምክንያቱም እምነታችሁ እየነጠረ ነው።

## 6. <u>ሽክም እምነት አሳራፊ እምነት</u>

ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ውስጥ አንድ ታሪክ አለ። ስለ ሁለት የእምነት ደረጃዎች የሚተርክ ነው። በቅፍርናሆም የሚኖር አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ልጁ በጠና ታሞ በሞት አልጋ ላይ ነበር።

ጌታ የሱስ በቅርብ ቦታ ቃና በተባለችው መንደር መሆኑን በሰማ ጊዜ፣ ወደዚያ ሄዶ መጥቶ ልጁን እንዲፈውስለት ጌታን ለመነው።

*"ይህም ሰው ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መምጣቱን በሰማ ጊዜ፤ ወደ እርሱ ሄደና በሞት አፋፍ ላይ የነበረውን ልጁን መጥቶ እንዲፈውስለት ለመነው (ቁጥር 47)።*

ጌታ የሱስ ይህንን ሰው የተቀበለው የከነአናዊቷን ሴት ከተቀበለበት ሁኔታ ብዙ የተሻለ አልነበረም።

*"መቼውንም እናንተ ምልክቶችንና ድንቆችን ካላያችሁ አታምኑም" አለው (ቁ. 48)።*

የሚያግባባ ወይም አይዞህ የሚል አቀባበል አይመስልም። እንዲያውም ከሰውዬው ጋር ለመተባበር የፈቀደ አይመስልም። አነጋገሩም ግሳጼ ያለበትም ይመስላል። ሹሙ ግን አልተበገረም።

*"ጌታዬ ልጄ ከመሞቱ በፊት እባክህ ድረስልኝ አለው ኢየሱስም ልጅህ በሀይወት ይኖራልና ሂድ አለው" ቁ 49-50።*

ለምንድነው አንድ ግፊት ብቻ ያጋጠመው? መልሱን በእርግጥ አናውቅም። ምናልባት ከዚያ የበለጠ መቀበል አይችል ይሆናል። ምናልባት የእምነቱ መጠን ጌታ የሱስ ሊገናኘው የሚችልበት ደረጃ ደርሶ ነበር። ምክንያቱ ምንም ቢሆን ለእርሱ ጊዜው ነበር።





ጌታ የሱስ ግን ሹሙ እንደጠየቀው አልነበረም ያደረገው። ሹሙ ጌታ የሱስ አብሮት ወደቤቱ እንዲመጣ ነበር የጠየቀው፣ ጌታ የሱስ ግን

*"ልጅህ በሕይወት ይኖራልና ሂድ" ነው ያለው።*

ራሳችሁን በሹሙ ቦታ አስቲ አስቀምጡት፣ ቃሉን ብቻ ተቀብላችሁ ትሄዳላችሁ ወይስ ጌታ አብሯችሁ እንዲሄድ ትነተንቱታላችሁ?

ቁጥር 50 ላይ *"ሰውዬውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አምኖ ሄደ" ይላል።*

የዚያን ጊዜ ቀኑ ከመሸ ጉዞ ስለማይደረግ ሹሙ በመንገድ አድሮ በማግስቱ ጉዞውን ቀጠለ። በመንገድ እንዳለ አገልጋዮቹን አገኛቸውና ልጁ በሕይወት መኖሩን ነገሩት። ልጁ መዳን የጀመረበትን ሰዓት ሲነጋገሩ ጌታ የሱስ ልጅህ በሕይወት ይኖራል ብሎ በተናገረበት ሰዓት እንደሆነ ተረዳ።

*ቁጥር 53 "እርሱና ቤተሰቡ ሁሉ አመኑ" ይላል።*

ቆይ እስቲ ሹሙ በቁጥር 50 ላይ ጌታ ሲናገር እኮ አምኖ ነበር። ከባድ እምነትና የሚያሳርፍ እምነት ልዩነቱ ይህ ነው።

እግዚአብሔር ቃል ሲናገራችሁ ያንን ቃል ትይዛላችሁ፣ የጉዳዩ ውጤት ምን እንደሆነ አታውቁም፣ ታምናላችሁ ነገር ግን ከባድ እምነት ነው። የሚጎረብጥ ነገር አለው፣ የሚያስፈራ ነገርም ይኖራል፣ ጥርጣሬ ቀስ እያለ ይገዳደራችኋል፣ የፈለጋችሁት መልካም ነገር ሊሆን የማይችልበት ሁኔታ እየታያችሁ ይመጣል። ነገር ግን ያን ያገኛችሁትን ቃል ይዛችሁ ድርጊት ብትጀምሩ፣ ጌታን በቃሉ ይዛችሁት መንገዳችሁን ብትሄዱ ጌታ በሰጣችሁ ቃል ላይ እንዲሠራ ታደርጉታላችሁ።

ይህ ወደሚያሳርፍ እምነት ያደርሳል። ይህ ደስ የሚል የእምነት ደረጃ ነው፣ የሚያስደንቅ፣ ሰላም ያለበት፣ እንዲህ ያለው እምነት የሚተላለፍ እምነት ነው።፣ሹሙ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡ ሁሉ አመኑ፤ ወንጌልን የሚያስፋፊ እምነት፤ የመንፈስ ኃይል በሥራ ሲገለጥ ሲታይ ፈንድቶ ብዙዎችን የሚነካ እምነት። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሁለት ሀብረተሰቦች በአንድ ጊዜ ወደ ደህንነት እምነት የመጡበት ታሪክ አለ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ በሚፀልይበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ነክቶት ሽባው ሲፈወስ፣

*"በልዳና በሰሮና የሚኖሩትም ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ተመለሱ" 9:35*

ሁላችንም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ መተረክ እንችላለን።

## 7. በቃል የሚቀሰቀስ እምነት

እምነት የሚያድግበት ሌላው መንገድ በእግዚአብሔር ቃል ሲቀሰቀስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ስለቃል ሲመሰክር፤ ሕያውና የሚወጋ፣ እለትን የሚያደቅ፣ መደሻ፣ አዝርዕትን እንደሚያበቅል ዝናብ ይለዋል። "ቃል" ስለሚለው ቃል በግሪኩ አስደናቂና ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ አለ። ሁለት ልዩ ልዩ የሆኑ ቃላት ናቸው "ቃል" ወይም በእንግሊዝኛው "Word" ተብሎ የተተረጎመው።

የመጀመሪያው ሎጎስ (logos) ሲሆን አጠቃላይ ስለሆነው የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው ነው። ሁለተኛው ሬማ (rhema) ሲሆን ይኸኛው ጠባብና ትኩረት ያለው ትርጉም አለው። እግዚአብሔር ሎጎስን በተለየ ሁኔታና በተለየ ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ ሲቀሰቅሰውና ሲያጎላው ያ ቃል ሬማ ይሆናል። የተለየ ቃል ለተለየ ምክንያት፣ ለተለየ ውጤት ሲሠራ ያኔ ቃሉ ሬማ ሆነልን ማለት ነው።








ብዙ ክርስቲያኖች ይህንን ልምምድ ይለማመዳሉ። የእግዚአብሔርን ቃል በሚያነቡበት ጊዜ አንድ ቃል ወይም ሐረግ ከምንባቡ ውስጥ ዘሎ ቀልባቸውን ይይዘዋል፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ በአንድ ጉድይ ላይ ስናስብ ድንገት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ትዝ ይለናል። በእንዲህ ያለ ጊዜ እግዚአብሔር ሬማ እየሰጠን ይሆናል። እንድናደርገው የሚገባን ወይም ልንበረታታበት የሚሆን ቃል በዚያ ውስጥ ይኖራል። ሬማ ቃሉ በተያዘበት ምንባብ ውስጥ ባለው ትርጉም ብቻ የተወሰነ ላይሆን ይችላል። አንድ የእግዚአብሔር ሰው ስለ ራሳቸው ልምምድ እንዲህ ብለው ጻፉ።

የአንድ ሳምንት የጸሎት ቆይታ ለመውሰድ ብቻዬን በበረሀማ ሥፍራ ወዳለ ካምፕ ሄድኩ። ከአራት ቀናት በኋላ በጣም ብቸኝነት ስለተሰማኝ ሳምንቱን መጨረስ የምችል አልመሰለኝም ነበር። ስለዚህ "ጌታ ሆይ ወደ ቤቴ ልመለስ ወይ?" ብዬ አፀልይ ጀመር። መዝሙር 34፤7 በአዕምሮዬ ይመላለስ ጀመር፤

*"እግዚአብሔርን በሚፈሩት ዙሪያ የእግዚአብሔር መልአክ ይሰፍራል ያድናቸውማል"።*

አሳቤን የያዘው ቃል ይሰፍራል (encampas) የሚለው ነበር። ቃሉን በቦታው በተሰጠው ትርጉም እንዳልወሰድኩት አውቃለሁ፤ ግን ጌታ በካምፕ እንድቆይ እንደፈለገ ተረዳሁ። ውጤቱ በሚቀጥሉት ሶስት ቀናት እግዚአብሔር ግልጽ የሆነ ራዕይ ሰጠኝ። ያ ራዕይ አገልግሎቴን በአዲስ መንገድ ቀይሶ በአዲስ መንገድ ላይ መራኝ። ቃሉ ግን በተቀመጠበት ጥቅስ ውስጥ በካምፕ ቆይ የሚል ትርጉም አልነበረውም።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 10:17 ላይ

*"እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው"*

ሲል የተጠቀመው ቃል ሬማ ነው። በሌላ አነጋገር ያ የእግዚአብሔር ቃል ሰሚውን ወደ እምነት ለማምጣት በሰውዬው ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። ጳውሎስ እንደገና በኤፌሶን 6:17 ላይ

## ምናብን ለመኮርኮር 3 .

የእግዚአብሔርን ቃል መስማት
እምነቱን የሚያሳድገው እንዴት ነው?

*“የመንፈስን ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።”*

ሲል የተጠቀመው አሁንም ሬማ ነው። ግላዊና ልዩ በሆነ ሁኔታ ቃሉ በጠላት ላይ ሲሰነዘር ያጠቃል ለማለት ነው።

“ለምሳሌ የእግዚአብሔርን ሥራ የምታሰናክሉ የሰይጣን ሠራዊት የታሰራችሁ ሁኑ” ብሎ መገሰፅ ሎጎስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ማፅናት ነው። በአንፃሩ ግን “እዚህ ሰው ውስጥ ሆነህ የምታሰቃየው ሰይጣን ውጣ” ማለት ያንን ቃል በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ ሬማ ያደርግዋል። ጥያቄው እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ወስደን ለተለየ ሁኔታችን በተለየ ጊዜ ለማዋል ስንጠቀም ከመንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንዴት እናውቃለን? አንደኛ፣ ቃሉን የምናደርግበት ሁኔታ ከአጠቃላዩ የእግዚአብሔር ቃል የተቃረነ አይሆንም። የክርስቶስን ወንጌል ለማሠራጨት ስለሚያስፈልግ ገንዘብ ስርቀህም ቢሆን አምጣ የሚል ትርጉም ከሰጠን ትክክል አይደለም። ምክንያቱም አትስረቅ የሚለውን ግልጽና ቋሚ ትዕዛዝ ይሽራል።

ወጣት ክርስቲያን በነበርን ጊዜ አንድ ወንድም የመሰከረልኝ ታሪክ ትዝ ይለኛል። ጊዜው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በአገራችን የጀመረበት ጊዜ ነበር። ያን ወንድም ታዲያ ወላጆቹ “እነኚያ ጴንጤዎች ጋ ትሄዳለህ ወይ?” እያሉ ሲያጣድፉት “ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሀሴትን አድርጉ የሚለው ቃል ትዝ አለኝ” አለ። ችግሩ ግን ሀሴት የሚለውን ቃል ከሀሰት ጋር አሳስቶት ነው የተረዳው። “እግዚአብሔር ለካ ሀሰትን አድርጉ ያለው ለዚህ ጊዜ ነው ብዬ በዛ አምልጥኩ ” አለ። ያ ንሰሀ ልንገባበት የሚገባን ኃጢአት እንጂ ሬማ አይደለም። ስለዚህ ሬማ እነኚህ ባህርያት አሉት፣

ከአጠቃላዩ የእግዚአብሔር ቃል ጋር የተስማማ መሆን አለበት። ራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል እየሞላን ስንሄድ ደግሞ፣ ከእግዚአብሔር የሆነውንና ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ለመለየት ይቀለናል።

የመጣላችሁ ቃል በውስጣችሁ እንዲታወቃችሁና እንዲቀሰቅሳችሁ የሚያደርግ ነገር ይፈጥራል፤ የሚያጓጓ፣ ደስ የሚል የእርግጠኛነት ስሜት በውስጣችሁ ያደርጋል። ለማድረግም በምትጀምሩበት ጊዜ የአክብሮት፣ የመፍራት ትልቅ ነገር የማድረግ ስሜት ይፈጠርባችኋል።





ምንም እንኳን እነኚህ የተመሰቃቀሉ ስሜቶች ቢመጡባችሁም፣ በዚያ ነገር ላይ ሰላም ይኖራችኋል።

ከነበረችበት ከተማ ተነስታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ የወሰነች አንዲት ልጅ ትዝ ትለኛለች። ከወሰነች በኋላ ሌላ ወሬ አልነበራትም። እርሷ ብቻ ሳትሆን ሰዉ ሁሉ ስለርሷ ውሳኔ ብቻ ሌት ተቀን የሚያስብ ይመስላታል።በፈለገችው ሰዓት ደውላ የጉዞዋን ሁኔታ ለማውራት፣ የሚጠብቃትን መልካም እድል ለማካፈል ይቅርታ አትጠይቅም።

በቅርብ የምናውቃት ሁሉ በሆዳችን ምነው ሄዳ አፎይ ባልን ያልን ይመስለኛል። የሷ በነገሩ መያዝ ሁላችንንም ፋታ ነሳን። እቃዋን ሸጠች፣ አንዳንዶቻችን ለመቆየትዋ ምክንያት እንዳይሆን ብለን ይመስለኛል ባያስፈልጋትም የገዛናት።

ሁለት ቀን ቀራትና፣ እሁድ ከቤት ክርስቲያን በኃላ ለመሄድ ቲኬት ገዛች። እርብ ማታ ጸሎት ላይ ግን አንድ ነገር ሆነ። ሳባን ቀየረች፣ አልሄድም አለች። በመጀመሪያ አቀማ ያናገረችኝ እኔን ነበር። “እግዚአብሔር አትሂጂ አለኝ” አለች። “እንዴት ተናገረሽ?” ብዬ ጠየቅኋት “ዛሬ አንድ ሰው አንድ ቃል ተናገረ፣ ብነግራችሁ ትስቁብኛላችሁ፤ ለኔ ግን ትርጉም ያለው ቃል ነው” አለችኝ። ቃሉ ምንድነው ብዬ ለመጠየቅ እንኳን አላስፈለገኝም፤ የመሄዷን ውሳኔ ካሳወቀች ጀምሮ ያላየሁባት ፀጥታና ሰላም በላይዋ ይነበብ ነበር። “እግዚአብሔር እንደተናገረሽ እንደዚያ አድርጊ” አልኳትና ተለያየን። የሚያስደንቀው ነገር ደግሞ ይህን እኔ በርሷ ላይ ያየሁትን ሁኔታ ሌሎች ሁሉ አይተዉት ስለነበር መጥተው “ምን አለችህ?” ብለው ይጠይቁኝ ጀመር። “ሳባን ቀየረች፣ አትሄድም” ስላቸው ምነው ሄዳ አፎይ ባልን ብለው ያላጉረመረሙትን ያህል ትክክለኛ ውሳኔ እንዳደረገች መሰከሩላት። ያ ውሳኔ ደግሞ ከእርሱ መሆኑን እግዚአብሔር በብዙ ባርኮት አፀናላት። ያ በዚያ ጸሎት ጊዜ የሰማችው ቃል ሬማ ሆነላት።

## 8 . ትጋትና እምነት

ስለ ትጋት ገና ብዙ እናያለን። ላሁን ግን ትጋት ከእምነት ጋር ያለውን ግንኙነት በትንሹም ቢሆን አይተነው እንለፍ። ባለቤቴ የጸሎት ጥያቄ ትፅፍ ነበር። መልሱን

ሰናገኝ አመስግነን ሌላ ደግሞ ይፃፋል። አንዳንዴ ግን ጸሎቱ በቀረበበት መልኩ መልስ የማይኖረው ይሆናል። ስለዚህ ጥያቄው መሻሻል ይኖርበታል። አንዳንዴ ሁለት ሶስቴ ይሻሻላል፣ ትርጉም ያለው ጸሎት እንዲሆን። ይህ ታዲያ ትጋትን ይጠይቃል።

ጌታ የሱስ ደጋግመን እንድንጠይቅ ከሚያደርገን ምክንያቶች አንዱ ይህ ይመስለኛል። መለመናችንን፣ መፈለጋችንን፣ ማንኳኳታችንን እንድንቀጥል ይፈልጋል። በጸሎታችን ላይ ትጋት እንዲኖረን፣ ደግመን ደጋግመን እንድናሰበውና እንድናሰላሰለው ያደርገናል።

ጸሎታችን እግዚአብሔር ሊመልሰው የማይፈልገው ቢሆንም እንኳን በጸሎት የምንቆይበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት ወሳኝ ነው። መልካም ነገር በሕይወታችን ያከናውናል። ያ ግንኙት ደግሞ በኛ ላይ እየሠራ አመለካከታችን እንዲለወጥና የጸሎት ጥያቄአችንንም እንድናስተካከል፣ ከእርሱም ፈቃድ ጋር የሚስማማ ጸሎት እንድንጸልይ ያደርገናል።

## 9. እምነት ሲሠራ

እምነት የሚያድግበትን ሌላውን መንገድ በዮሐንስ 11 ላይ ካለው የአልአዛር ታሪክ መማር እንችላለን። ጌታ የሱስ በየሩሳሌም ነገሮች አስጊ እየሆኑ ሲሄዱ እርሱና ተከታዮቹ ዮርዳኖስን ተሻግረው እንዲሄዱ አደረገ።

ከዚያ መልዕክት ለጌታ መጣለት። *"አልአዛር ታሟል"* የሚል መልዕክት ነበር የደረሰው።ጌታ የሱስ መልዕክቱን ሲሰማ በመጀመሪያ ያለው፥

*"ይህ ሕመም … ለሞት አይደለም" (ቁ.4)።*

ይህንን ማን እንዳለው አስተውሉ፤ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ጌታ የሱስ ክርስቶስ በሙሉ አፉ "ለሞት የሚያደርስ አይደለም ብሎ በግልጽ አወጀ። ቁጥር 11 ላይ ደግሞ

*"ወዳጃችን አልአዛር ተኝቷል እኔም ላስነሳው እሄዳለሁ"* አለ።





ለምን ጌታ ይህን አለ? ምክንያቱም እምነት ወደፊት ተሻግሮ ውጤቱን ማየት ስለሚችል ነው።

በጌታ አመለካከት ወደ ቢታኒያ ሄዶ ከአልአዛር ጋር የሚኖረው ጉዳይ ልክ ተኝቶ ከአንቅልፉ ከተነሳ ሰው ጋር የሚኖረው አይነት ሆኖ ነው የሚታየው። ደቀ መዛሙርቱ ግን ይህ ምስጢር ስላልገባቸው ግልጽ አደረገና

*"አልዓዛር ሞቷል"* አላቸው።

ቀጥሎም *"ታምኑ ዘንድ በዚያ አለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል" ቁ. 15* አላቸው።

የዚህ ታሪክ ዋናው ቁም ነገር በእነኚህ ቃላት ይጠቃለላል፣ *"ታምኑ ዘንድ"*። ቀጥሎም እምነት ላስቸገራት ማርታ እንዲህ አላት፤

*"ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ። በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳን በሕይወት ይኖራል፣ በእኔ የሚኖር የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም ይህን ታምኛለሽ?" ቁ. 25-26።*

*"አዎን ጌታ ሆይ…. . አምናለሁ"* እንዳለችው፣ ጌታ በአጀንዳው ላይ ወደ ሚቀጥለው ነጥብ ሄደ።

የእርሱ አጀንዳ እምነት ነበር። በኋላም ከመቃብሩ አጠገብ ቆሞ ማርታን

*"ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርኩሽም" ቁ. 40.* አላት።

አሁንም አጀንዳው እምነት ነው። አልአዛር ሞቷል፣ ሰውነቱ ቀዝቅዟል፣ ተቀብሯል፥ ይህ እውነተኛው ነገር ነው። እርሱ ግን ማርታን "አልነገርኩሽምን?" ይላታል።

እምነት የሆነውንና የሚታየውን አልፎ በተነገረው ቃል ላይ መጽናትን ይጠይቃል። ከዚያም ጌታ ሁሉም ሊሰሙት አስፈላጊ የሆነ የእምነት ጸሎት ጮክ ብሎ ጸለየ።

*"አባት ሆይ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ አውቃለሁ፣ ይህ ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደላከኝ ያምኑ ዘንድ ነው።" ቁ. 41-42።*

የአልአዛር ከሞት መነሳቱ ውጤት ይህ ነበር።

ቁጥር 45 *"ከአይሁድ ወደ ማርያም ከመጡት ኢየሱስ ያደረገውን ካዩት አይሁዶች ብዙዎች በእርሱ አመኑ።"*

አጠቃላይ ትዕይንቱ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ሲሆን *"ታምኑ ዘንድ"* በሚለው ሐረግ ላይ ያተኮረ ነው። እንዳቀደውም በሚገባ ሠራ፤ ደቀመዛሙርቱ አመኑ፣ ማርታ አመነች፣ አይሁዶች አመኑ። እምነት እግዚአብሔርን ያስደስተዋል፣ እኛ ማመን ከምንፈልገው የበለጠ እግዚአብሔር እንድናምን ይፈልጋል፤ እምነታችንንም ለማሳደግ አጥብቆ ይፈልጋል። የእግዚአብሔር የሥራው ድርሻ እምነታችንን መገንባት ነው እዚህ የምናየው ያንን ነው።

በእምነታችን ውስጥ የኛ የሥራ ድርሻስ ምን ይመስላል? የእኛ ድርሻ እግዚአብሔር የሚለንን ነገር ማድመጥ (ቃሉ ሬማ ሲሆንልን ቶሎ መቀበል ማለት ነው።)፤ የሰማነውን ነገር ጥብቅ አድርገን መያዝ፣ ሌሎች ሁኔታዎችና በአካባቢያችን ያሉ ክንዋኔዎች ወደ ሌላ አቅጣጫ ቢገፋፉንም፣ "አምቢ" ብለን የያዝነውን በማጥብቀ እስከፍጻሜው መጠበቅ ነው። ለዚህ ነው እምነት የፈቃድ ጉዳይ ነው የሚለውን ነጥብ የማጠብቀው። ሁኔታዎችና ሰዎች ለአዕምሮአችንና ለስሜታችን በሚያደርጉት ግብ ግብ የያዝነውን እውነት ወይም የተቀበልነውን ቃል ላለመተው ጠንካራ ፈቃድ ይጠይቃል። ይህንን ነጥብ ብደግመው ደስ ይልኛል። እኛ ማመን ከምንፈልገው የበለጠ እግዚአብሔር እንድናምን ይፈልጋል። እምነታችንንም ለማሳደግ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ያሳልፈናል።

## 10. እምነትና ሥልጣን

ጌታ የሱስ ትልቅ እምነት አላቸው ብሎ የመሰከረላቸው ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው።፣ የመጀመሪያዋ ባለፈው ምዕራፍ ያየናት ከነዓናዊቷ ሴት ነች። ሁለተኛው ደግሞ





አገልጋዩን እንዲፈውስለት ጌታን የጠየቀው ሮማዊው መቶ አለቃ ነው። ጌታም ወደቤቱ ለመሄድ ሲስማማ መቶ አለቃው ይህንን የእምነት ንግግር ተናገረ።

*"ጌታ ሆይ ወደቤቴ እንድትገባ የሚገባኝ አይደለሁም፤ ነገር ግን ከዚሁ ሆነህ አንዲት ቃል ብቻ ብትናገር አገልጋዬም ይፈወሳል። እኔ ራሴ የምታዘዛቸው አለቆች፣ ለእኔም የሚታዘዙኝ የበታቾች አሉኝ፤ ከእነርሱም አንዱን ሂድ ብለው ይሄዳል ሌላውን ና ብለው ይመጣል። አገልጋዬንም ይህን አድርግ ስለው ያደርጋል" ማቴዎስ 8፤ 8-9።*

መቶ አለቃው ጌታን ሲያደርግ አይቶ ከእግዚአብሔር የሆነ ሥልጣን እንዳለው ተገንዝቦ ነበር። በዚህ ንግግሩ ጌታ ተደንቆ እንዲህ አለ፣

*"እውነት እላችኋለሁ፣ ከእስራኤል መካከል እንኳን እንዲህ ያለ እምነት ያለው አንድ ሰው እንኳን አላገኘሁም" ቁ. 10።*

በኃይልና በሥልጣን መካከል ያለውን ልዩነት እናውቃልን? ኃይል ብርታት ሲሆን ሥልጣን ብልሃት ነው። ጠመንጃ ወይም ሽጉጥ የደገነባችሁ ሰው አድርጉ ያላችሁን ታደርጋላችሁ፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በእናንት ላይ ኃይል አለው። ዩኒፎርም የለበሰ ፖሊስም አድርጉ ያላችሁን ታደርጋላችሁ፤ ምክንያቱም በእናንተ ላይ ሥልጣን አለው።

ብዙዎቻችን እግዚአብሔር ኃይል እንዳለው እናውቅ ይሆናል። ግን እግዚአብሔር ያንን ኃይሉን እኛ እንድንጠቀምበት ለእኛ የሰጠንን ሥልጣን የምንገነዘብ ጥቂቶች ነን። ጌታ የሱስ በኃይልም በሥልጣንም ነበር ያገለገለው።

ሥልጣን ሁለት መነሻዎች አሉት። የመጀመሪያው እኛ ስለ ክርስቶስ ባለን እውቀት ላይ የተመሠረተ ነው። ስለ ክርስቶስ ማንነት ያለን እውቀት እያደገ ሲሄድ፤ ክርስቶስ በሠራውና በሚሰራው ሥራ ላይ ስናተኩር፣ የሥልጣናችን ልክ ከፍ እያለ ይሄዳል። የሥልጣን ሌላው መነሻ ደግሞ እኛ በክርስቶስ ማን መሆናችንን እየተረዳን ስንሄድ

የሚመጣ ነው። እርሱ የሰጠን ተልዕኮ ምን እንደሆነ ስንገነዘብ፣ የእርሱንም ትዕዛዛት ለመፈጸም በምናወጣቸው እቅዶች ውስጥ ሥልጣናችን እያደገ ይሄዳል።

## በአጭሩ

እምነት መንፈሳዊ ክስተት ነው። እምነት ከእኛነታችን፣ ከሰብዓዊነታችን የበለጠ ክስተት ነው። እግዚአብሔር ቃሉን በሕይወታችንም ሆነ በሁኔታችን እውነት አድርጎ ሲያመጣው (ሬማ ሲያደርገው) የሚቀሰቀሰው መንፈሳችን የሚረዳው ክስተት ነው። ጌታ የሱስ የማይታየውን አባቱን በምድር ላይ በሥጋ እንደገለጠው፣ የማናየውን ነገር እውነት የሚያደርግልን ክስተት ነው። ፍቅሩንና ኃይሉን እንዲሠራ የሚያደርገው ክስተት ነው።

በሚቀጥለው ምዕራፍ እምነታችንን በሥራ የምንገልጥበትን ተግባራዊ ዘዴዎችንና ሞዴሎችን እናያለን።





# ምዕራፍ አራት

## ተግባራዊ ዘዴዎችና ሞዴሎች

"እምነታችንን የሚያቅደው እግዚአብሔር ነው" የሚለውን አሳብ በመድገም ይህንን ምዕራፍ መክፈት እወዳለሁ። የሚሠራ እምነት እንዲኖረን እኛ ከምንፈልገው የበለጠ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ምክንያቱም የኛ እምነት እየጨመረ በሄድ ቁጥር እርሱ ለሕይወታችንና ለሁኔታቸን የበለጠ ለማድረግ ቀላል ይሆንለታል። እምነታችንን የሚጀምረው እግዚአብሔር ሲሆን፣ እምነታችንን በሚያሳድጉ ድርጊቶች መሠማራት ግን የኛ ፋንታ ነው። ይህንን ማድረግ የምንችልባቸውን በርካታ ዘዴዎች በዚህ ምዕራፍ እናያለን። አስቀድመን ግን ሰንካላ (negative) እምነቶችን እናጋልጣቸው።

### 1. ሰንካላ እምነቶች

ሰው ሁሉ እምነት አለው፤ እምነት የሌለው ሰው የለም። ጥያቄው እንግዲህ እምነትን እንለማመዳለን ወይ የሚል ሳይሆን የምንለማመደው እምነት ምን አይነት ነው የሚለው ነው። ጠንካራ እምነት አለ፣ ደካማ እምነት አለ፤ የሚሠራ እምነት አለ፣ የማይሠራ እምነት አለ፤ ቅን (positive) እምነት አለ፣ ሰንካላ (negative) እምነት አለ። ሰንካላ እምነት ማለት አይሳካም፣ ይበላሻል፣ የሚል እምነት ነው። መጥፎ ነገር ይሆንብኛል ብዬ ካመንኩ፣ የዚያ መጥፎ ነገር የመሆን እድሉ ይጨምራል። ለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል "አይዟችሁ" "አትፍሩ" እያለ የሚመክረን። ፍርሀት ሰንካላ እምነትን ያመጣል። ጌታ የሱስ በማርቆስ 4 የዘሪውን ምሳሌ ከተናገረ በኋላ

*"ስለምትሰሙት ነገር ጥንቃቄ አድርጉ" ቁ.24 አላቸው።*

ልባችን መልካሙን አፈር አይነት ከሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይተከላል፣ ይበቅላል፤ ብዙ ፍሬ አፍርቶ ለአዝመራ ይደርሳል። ግን ይህ ልባችን የሰይጣንንም ቃል ተቀብሎ፣ አብቅሎ እንዲያፈራ የማድረግ ችሎታም አለው። በሚቀጥሉት ምዕራፎች ይህንን

አሳብ በሰፊው እናየዋልን፤ ለአሁኑ ግን እንድንይዘው የምፈልገው አሳብ ሰይጣን ቃሉን በሚዘራበት ጊዜ አላማው ቃሉ በውስጣችን ተተክሎ ብዙ ፍሬ እንዲያፈራ ለማድረግ መሆኑን ማወቅ ነው። ልብ አድርጉ መልካም አፈር የተዘራበትን ሁሉ ነው የሚያበቅለው።

ስለ በሽታ አንዳንድ አስደናቂ እውነቶች አሉ። አንዳንዴ ጠዋት ስነቃ አንዳንድ ለውጦች በራሴ ላይ ካየሁ፣ ለምሳሌ የጉሮሮ መድረቅ፣ ትንሽ የራስ ምታት፣ ደጋግሞ ማስነጠስ ካጋጠመኝ "ሊያመኝ ነው መሰለኝ" የሚለው አሳብ ይመጣብኛል። ያንን አሳብ ተቀብዬ ካስተናገድኩት እታመማለሁ። ምክንያቱም ያልሰለጠንኩበትን ሙያ ወስጄ በምልክት ብቻ ተመርኩዤ፣ ሰይጣን የወረወረልኝን ሰንካላ እምነት ተቀብዬ ያ ሰንካላ እምነት በውስጤ አድጎ እንዲያፈራ እድል እሰጠዋለሁ። ነገር ግን ምልክቶቹን በዚህ ሳልተረጉም ብድግ ብዬ ወደ ዕለት ተግባሬ ከሄድኩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሕመሙ ነገር ትዝም አይለኝ። እንዳውም ያ ስሜት ሲሰማኝ ሰይጣንን በግልጽ ጮክ ብዬ እገስጻለሁ፤ "የበሽታ ስሜትና ምልክት ሁሉ፣ በሀሳቤም ልትታመም ነው እያላችሁ የምትመሰክሩ መናፍስት ሁሉ በየሱስ ስም ከኔ ራቁ" እላቸዋለሁ። እንዴት ያለ አስደናቂ ውጤት እንደምታገኙ አሳባችሁ ይቅመሰው። ሰንካላ እምነት ተቃዋሚ ነው፣ ይዋጋናል፤ አንድ የእግዚአብሔር ሰው በመጽሐፋቸው ያስቀመጡት ታሪክ ትዝ ይለኛል። ኖርማ ስለተባልች ሴት እንዲህ ብለው ጻፉ።

*ስሟ ኖርማ ነው። ኖርማ በወጣትነት እድሜዋ በሞት ስለተለየችን እርሷን ቀብረን መመለሳችን ነው። ኖርማ ሞትን በጣም ትፈራ ነበር። ከፍርሃቷ የተነሳ "ሞት" የሚለው ቃል እርሷ ባለችበት አካባቢ እንዲነሳ እንኳን አትፈልግም። ቃሉ ያስጨንቃታል፣ ያቁነጠንጣታል "ያንን ቃል አትጥሩ" ብላ ትቆጣለች። "ያንን ቃል" ትላለች እንጂ "ሞት" ብላ እንኳን ለመናገር አትደፍርም። እኔ እንደሚመስለኝ ፍርሃቷ ራሱ ለሞት ባያደርሳት እንኳን ጊዜውን ያጣደፈው ይመስለኛል። ስለ ሞት ያላት ሰንካላ እምነት አመለካከቷን ሁሉ ስለቀየረባት "ቶሎ እሞታለሁ" የሚለውን አሳብ በውስጧ አሳድጋዋለች። እድሜዋ ገና ወደ ሰላሳዎቹ መግባቷ ነበር። የሳይኮሎጂ ባለሙያዎች ይህን አይነቱን ክስተት "ራሱን ወደ ፍጻሜ የሚያመጣ ትንቢት" (self fulfilling prophecy) ይሉታል። ሲተነትኑትም ሰዎች በአንድ አሳብ በጣም ከመያዛቸው የተነሳ ነገሩ እንዲፈጸም ራሳቸው ሳያውቁት እንኳን ይገፋፉታል።*

ይህ መተት ወይም ምትሃት አይደለም፣ እምነት ነው እንጂ። እምነት የበላይ የሆነው በኛ ላይ እንዲሰለጥን ሥልጣን ይሰጠዋል። በሕይወታችን የበላይ የሆነው እግዚአብሔር ከሆነ ለኛ ለመልካም ይሠራልናል። በሕይወታችን የበላይ የሆነው ሰይጣን ከሆነ ሊያበላሽብንና ሊያሳዝነን ይሠራል። ሰይጣን ግን የእግዚአብሔርን ያህል ኃይል የለውም። እግዚአብሔር ደግሞ የነፃ ፈቃድ ስለ ሰጠን በእርሱና በሰይጣን መካከል ያለውን ምርጫ ለኛ ትቶታል። ሀሳባችንን ወይም ቀልባችንን (attention) እንዲይዝ የፈቀድንለት ያ በኛ ላይ ይሰለጥናል። ይህንን አሳብ ከሚገባው ትርጉም በላይ ትርጉም ልንሰጠው አይገባም። ስለዚህ እያንዳንዱን የደረሰብንን መጥፎ ነገር ሁሉ ወስደን ትክክለኛ ያልሆነ እምነት ውጤት ማድረግ አይገባንም። ለመጥፎ ነገር መድረስ ሌሎች ብዙ ምክንያቶች አሉ። ለምሳሌ መንፈሳዊ ውጊያ የብዙ መጥፎ ነገሮች መነሻ ምክንያት ሊሆን ይችላል። መንፈሳዊ ውጊያ ለርግማን፣ ለፈተና፣ ለተቃውሞ፣ ለክስ፣ ለጉስቁልና፣ በጠላት ለመታለል መነሻ ምክንያት ይሆናል። ሰንካላ (negative) ነገሮች ያለንን ቅን እምነት ለመቃወምና እንዳንለማመዳቸውም ለማድረግ ነው የሚጥሩት። በሌላው በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ሰይጣንን ለሁል ጊዜ አሸናፊ እንዲሆን ይፈቅድለታል ብላችሁ አታስቡ። የኖርማን ታሪክ መጨረሻውን እንዲህ ብለው ነው የጻፉት።

*ኖርማ የሞተች ዕለት ሆስፒታል ውስጥ አጠገቧ ነበርኩ ። ሐኪሞቹ እንዲህ ብለው አጫወቱኝ "ኖርማ ከቀናት በፊት ትሞት ነበር። ነገር ግን ለመሞት በተቃረበች ጊዜ ሁሉ ከፍርሃቷ የተነሳ ተሸማቃ ወደውስጧ ስለምትገባና ስለምትደበቅ መሞቷ ይቀርና መሰቃየት ብቻ ይሆናል የሚደርስባት።" በመጨረሻ ጊዜው ከሌሊቱ ስምንት ሰአት (2 AM) ነበር። ቀስ ብዬ ጠጋ አልኩና "ኖርማ በሚቀጥለው ጊዜ ሞት ጫፍ ላይ ስትደርሺ እርሱን አሻግረሽ ተመልከቺና ከዚያ ወዲያ ያለው ማን መሆኑን እዪ" አልኳት። ከግማሽ ሰዓት በኃላ እንደገና ሰውነቷ መሸማቀቅ ጀመረ፣ ፍርሃቷም በፊቷ ላይ ይነበብ ነበር። የዚያን ጊዜ "ኖርማ! ቀና ብለሽ ተመልከቺ" ብዬ በኃይል ተናገርኳት። ልክ ያንን ማድረግ ስትጀምር የፊቷ ገጽታ መለወጥ ጀመረ። ከሞት*

*ባሻገር ጌታ የሱስ ስላለ ሞት የሚያስፈራ አልሆነባትም። ከጥቂት ጊዜ በኃላ ሕይወቷ አለፈ። በፊቷ ላይ ግን ውብ የሆነ ፈገግታ ነበር። በሕይወትዋ መጨረሻ ሞት ለካ ወደ ሕይወት የመሻገሪያ በር መሆኑን የተረዳች ይመስላል።*

ስንካላ እምነት እንድንለማመድ ሰይጣን እየሞከረ ለመሆኑ ዋናው ምልክታችን ፍርሃት ነው። በበሽታ ፍርሃት ሲያስፈራራን እኛም መፍራት ስንጀምር በፈቃዳችን በሽታን እየመረጥን ነው ማለት ነው።የድህነት ፍርሃት እንዲይዘን ከፈቀድንለት፣ ለሰይጣን ኃይላት የገንዘቤንና የንብረቴን ነገሮች እንዲቆጣጠሩ ፈቃድ መስጠቴ ነው። አይሳካልኝም የሚል ጭንቀት እንዲወጥረኝ ካደረግሁ የሰይጣን ኃይላት ለውድቀቴ እንዲሠሩ በር እየከፈትኩላቸው ነው። ለዚህ ነው ጭንቀት ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ኃጢያት ሆኖ የቀረበው። ጭንቀት እግዚአብሔር በቃሉ የገባልንን ተስፋ ማፍረስ ነው፤ ጭንቀት እግዚአብሔር አይችልም ወይም ታማኝ አይደለም ብሎ ጮክ ብሎ የሚናገር ሁኔታ ነው። ጭንቀት የእግዚአብሔርን እምላክነት በመጠራጠር ሌላ ከርሱ የበለጠ ክፉ ኃይል በላያችን ሰልጥኗል ብሎ መቀበል ነው።

የብዙዎቻችን ምክንያት "ከቁጥጥሬ በላይ ነው፣ ስሜቱ እንደዚያ ሲሆን ምንም ላደርገው አልችልም" የሚል ይሆናል። ይህ አነጋገር እውነትነት አለው። በምዕራፍ 2 እንዳየነው ሁል ጊዜ ስሜታችንን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር አንችልም። ነገር ግን ፈቃዳችንን መቆጣጠር እንችላለን። ድርጊታችን ደግሞ ፈቃዳችንን ነው የሚከተለው።

ስለዚህ ስሜታችንን ፍርሃት አንቅ አድርጎ ቢይዘውም ድርጊታችንን ግን መቆጣጠር ያስፈልገናል። ፍርሀት ይሰማናል፤ በፍርሃት ግፊት ግን ምንም ማድረግ የለብንም። ስንካላ እምነት የምንለማመደው በፍርሃት የተያዘው ስሜታችን የፍርሃት ድርጊቶችን ማድረግ ሲጀምር ነው። እግዚአብሔርን ከሰማነው ለመንፈሳችን ይናገራል። "አታድርገው፣ ከዚህ ውስጥ አወጣሀለሁ፣ ለፍርሃት እምቢ በለው፣ እኔን ለመተማመን ወስን" ይለናል። በዚህ እውነተኛ መንፈስ ድርጊት ስንጀምር የፍርሃት ስሜት እየለቀቀን ይመጣል፤ አንዳንዴ አንዳውም በውሳኔው ደረጃ ብቻ ፍርሃት ይሸሻል።





የሚያስፈራችሁ ምንድነው? በሽታ፣ እጦት፣ የትዳር መፍረስ፣ ውድቀት፣ አለመሳካት፣ አደጋ፣ እምቢ መባል፣ ሱስ፣ ግድያ፣ ወንጀል፣ ሥራ ማጣት፣ ከምንወዳቸው መለየት፣ ወይስ በምንወዳቸው ላይ መጥፎ ነገር ይደርሳል ብሎ መፍራት? በእነኚህ ነገሮች መፍራት የለባችሁም የሚል ብያኔ ለማስተላለፍ አይደለም ይህንን ጥያቄ ያነሳሁት። እግዚአብሔር ያውቃል በአንድ ጊዜ ወይም በሌላ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ካሉት ጭንቀቶች አንዳንዶቹ ብቻ ሳይሆኑ ብዙዎቹ ነካክተውኛል። እግዚአብሔር ግን መልካም ነው። በቀስታ በጊዜ ውስጥ እርሱ እኔን ሊያስፈራሩኝና ሊያስጨንቁኝ ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ በላይ እንደሆነ አሳይቶኛል። ከእነኚህ ነገሮች ነፃ ወጥቻለሁ ማለቴ አይደለም፤ ወይም ከመረዳቴ መጠን የተነሳ ጥያቄዬ ሁሉ ተመልሶልኛል ማለቴም አይደለም። ግን ከጭንቀቴና ከፍርሃቴ የተነሳ የጠላት ኃይላት በሁኔታዬ ላይ እንዲሠለጥኑ በማድረጌ ይቅርታ መጠየቅን ተምሬአለሁ። በእርሱም መተማመን እንዳለብኝ አውቃለሁ።

2 . ምስጋና

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ጥቅሶችን በትክክል ማንበባችንን ብቻ ሳይሆን መረዳታችንን እርግጠኛ መሆን አለበን። ለምሳሌ

> *ኤፌሶን 5፥20 "እግዚአብሔር አብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሁሉ ነገር ሁል ጊዜ አመስግኑ"*

ጥቅሱ የሚለው ስለ ሁሉ ነገር ሲሆን ብዙዎቻችን በአሳባችን የምንረዳው ግን ስለ ሁሉ መልካም ነገር መሆን አለበት ብለን ነው። እንዳለማ ብንተረጉመው ስለ መጥፎውም ነገር እግዚአብሔርን አመስግኑ ማለት ይሆናል። የኤፌሶንን መልዕክት የጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ የክፉ ነገር መነሻ እግዚአብሔር ነው ብሏል ማለቴ አይደለም። እግዚአብሔር ግን በሁሉ ነገር ላይ (በደጉም በክፉም) የበላይነት አለው። በሌላው መልዕክቱ ላይ ደግሞ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፣

> *"እግዚአብሔርን ለሚወዱትና እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚደረግላቸው እናውቃለን" ሮሜ 8፣28።*

እግዚአብሔርን መተማመን ይገባናል፣ በሁሉ ነገርም እግዚአብሔርን መተማመንም እንችላለን። እግዚአብሔርን ለመተማመናችን ትልቁ መግለጫ ደግሞ ማመስገን ነው። በዚህ ሁኔታ ስንሆን "ጌታ ሆይ አመሰግንሀለሁ" የሚለው ትንሽ ሐረግ ምን እንዳጠቃለለ ታውቃላችሁ?

ሀ. እግዚአብሔር የሁሉ የበላይና ተቆጣጣሪ መሆኑን

ለ. እግዚአብሔር ሰይጣንንም እንኳን እንዲሠራ ይፈቅድለታል፤ ምክንያቱም ሰይጣን የሚሠራውን ክፉ ነገር እርሱ በበለጠ መልካም ነገር እንደሚለውጠው ስለሚያውቅ

ሐ. እምነት እግዚአብሔርን እንዲሠራ የሚፈታው መሆኑን መገንዘብ

መ. እግዚአብሔርን ለሚወዱትና እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚሠራ ማወቅና ፣ እንደ አሳቡም መጠራት ማለት እርሱን መተማመን እንደሚጨምር ማወቅ

ሠ. "አመሰግንሀለሁ" ማለት የእምነት ድርጊት መሆኑን መገንዘብ

ረ. ስለመጥፎ ነገር የማመስገን ስሜት የሚኖረው የለም። ነገር ግን ማመስገንን መፍቀድ ይቻላል። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን እንዲቀይር እናደርገዋለን፤ ዘማሪው "በምስጋና ድል ይገኛልና" ያለው ይህንን ተረድቶ ይመስላል።

ይህንንነገርእኔበራሴሕይወትተለማምጄዋለሁ።በተለይስሜቱመጥፎነገርሲነግረኝ ፈቃዴ ግን ድርጊቱን ወደ መልካም እንዲለውጠው ማድረግን ተለማምጃለሁ።

ዘመኑ በፈረንጆች አቆጣጠር 2004 ነበር። አገሩ ኢራክ ቦታው ደግሞ ደቡባዊዋ ከተማ ባስራ (መጽሐፍ ቅዱስ ባሶራ ብሎ ነው የሚጠቅሳት)። ጊዜው የአሜሪካና የሌሎች ተባባሪ አገሮች ኃይላት አገሪቷን ከሳዳም ሁሴን አገዛዝ ነፃ እንወጣለን ብለው የወረሩበት ክፉ ጊዜ ነበር።እኔ በሥራ ምክንያት በዚያን ጊዜ ባስራ ነበርኩ። ተቃዋሚ ኃይሎች ደግሞ የወራሪ ኃይሎች ያሉበትን ቦታ በሮኬት በተወረወረ በቦምብ





(Rocket Proppelled Grende (RPG)) ያጠቁ ነበር። የነበርኩበትና በወራሪ ኃይሎች የተያዘው የባስራ ቤተ መንግስትም አልፎ አልፎም ቢሆን ይመታ ነበር። ሆኖም ያን ያህል አሳስቦኝ አያውቅም ነበር።

አንድ ቀን ግን ድንገት በፍርሃት ተሞላሁ። ለሥራ ግቢው ወስጥ በመኪና እያተዘዋወርኩ ነበር። ከዚያ በአሳቤ "አንድ ነገር ብሆን ባለቤቴና ልጆቼ ምን ሊሆኑ ነው" የሚል ፍርሃት ያዘኝ።

"ለምን ራሴን እዚህ ነገር ወስጥ አስገባሁ፣ በየጊዜው ቦምብ ነው፣ በየጊዜው ቦምብ መጠለያ (Banker) ግቡ ነው፣ የሳይረኑ ድምጽ ራሱ ያስፈራራል" እያልኩ ፍርኃቴን አሳድገው ጀመር። ሰይጣን ደግሞ ያንን ፍርሃቴን ወስዶ የበለጠ አጎለበተው። " ከዚያ ከግንቡ ውጪ ሆነው የሮኬት ቦምብ ቢተኩሱ ቢሮህን ወይም መኝታ ቤትህን መምታት ይችላሉ" እያለ ፍርሃቴን ያራግበው ጀመር። እንዲያውም እያባባሰው መጣ፣ "አሁን እኮ የተተኮሰ ቦምብ ወደ እዚህ እየመጣ ሊሆን ይችላል፣ ምናልባትም እዚህ መኪና ወስጥ ቁጭ እንዳልክ . . . " የሚል ስሜት ሲነዛብኝ መኪናዬን ካቆምኩበት ቦታ ማንቀሳቀስ ጀመርኩ። ፍርሃቱ እያስጨነቀኝ ሲሄድ በአሳቤ

*"በኃይልህ ጩኽ አትቆጠብ ድምፅህን እንደመለከት አንሣ" ኢሳይያስ 58፣1* የሚለው ጥቅስ መጣልኝ።

በዚያን ጊዜ ነው ራሴን እስከሚያስደነግጠኝ ድረስ "ጌታ ሆይ" ብዬ ጮሀኩ። እዚያም ለኔ ግልፅ በሆነ ሁኔታ፣ በድምፅ አይደለም፣ በሚታይም ነገር አይደለም ግን በውስጤ "ሰይጣን እየፈተነህ እኮ ነው" የሚል እውነት ተገለጸልኝ። የቀድሞ ፓስተሬ መጋቢ ሰይፉ ከበደ ካስተማረኝ ብዙ ነገሮች አንዱ ሰይጣንን መገሰፅ ነው። ጥሩ አድርጌ ሰይጣንን በሥልጣን ከገሰፅኩ በኋላ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመርኩ፤ ስለ ባለቤቴና ስለ ልጆቼ፣ ስለ ጥበቃውና ስለ እንክብካቤው እያመሰገንኩ ስሄድ በውስጤ ትልቅ ደስታና ሰላም ሞላኝ።

ከጥቂት ጊዜ በፊት የነበረኝን ሁኔታ ሳስበው በጣም አሳቀኝ።

ስሜታችን ያን ዕለት የኔ ስሜት ወዲያው እንደተለወጠ ቶሎ አይለወጥ ይሆናል። የአንዳንዶቻችን ስሜት እምቢ ሊለን ወይም ሊታገለን ይችላል። ቁም ነገሩ ግን ፈቃዳችን ለስንኩለው እምነት ሳይበገር ትክክለኛውን እምነት መምረጡ ላይ ነው። ባይሰማንም እንኳን ሰይጣንን መገሰጽና እግዚአብሔርን ማመስገን መቻል አለብን። ይህም ማለት፣

ያልተሰማችሁን መልካም ነገር ተሰምቶኛል በማለት እግዚአብሔርን ለማግባባት መሞከር ማለት አይደለም።

ለእግዚአብሔር ስሜታችሁን በግልጽ ንገሩት፤ "እኔ የሚሰማኝ እንዲህ እንዲህ ነው፣ ግን አንተ ወደ መልካም እንደምትለውጠው አምናለሁ" በሉት።

እግዚአብሔርን አመስግኑት።
ደጋግማችሁ አመስግኑት።

ስሜታችሁ ሌላ ቢልም በፈቃዳችሁ ደጋግማችሁ አመስግኑት፣ ሊዘገይ ይችላል፣ ጌታ ግን በሰዓቱ ያስተካክለዋል። ለተወሰነ ጊዜ (ምናልባት ለአንድ ሳምንት) በምትጸልዩበት ነገር ውጤት ላይ ማተኮር ትታችሁ ምስጋና ላይ ብቻ አተኩሩ። ያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነገሩን የምትጸልዩበትን ነገር እንደገና ገምግሙት፤ እርግጠኛ ነኝ ለውጥ ይኖራል፤ ለውጡ ወይ በምትጸልዩበት ነገር ላይ ወይ በእናንተ አመለካከት ላይ ሊሆን ይችላል።

## 3. ድርጊት

እምነት ድርጊት ነው ብለናል። በሰዋሰው የንግግር ክፍል ስም (noun) ሳይሆን ግሥ (verb) ነው ለማለት ነው። እምነትን እንዲህ ከተረዳነው ታዲያ ያ የአመንበት ነገር እንደሆነ ቆጥረን ድርጊታችንን በዚያ አንጻር ማከናወን እንጀምራለን። ባለቤቴ ኤልሳቤጥ የመጀመሪያ ልጃችንን እርጉዝ በነበረችበት ጊዜ ክፍሉን ስታመቻች፣ አልጋውን ስትሠራ፣ ቤቱ ሲዘገጃጅ የምትወስደው የእምነት እርምጃ ነበር። ያ ብቻ ሳይሆን "ልጁ ይህን ቀለም አይወድም፣ መለወጥ አለበት" ብላ ሌሊት ከእንቅልፌ ትቀሰቅሰኝ ነበር። "እሺ" ብላትም እርግጠኛ ለመሆን እንደገና ትቀሰቅሰኝ ነበር።





ይህ የእናቶች ሁሉ ታሪክ ነው። ቁም ነገሩ ግን በሌላውም ነገር ላይ የእምነታችን እርግጠኝነት በተመሳሳይ ድርጊት መገለጥ አለበት። እምነት የእግዚአብሔር ፈቃድና የእግዚአብሔር መሪነት ባለበት ነገር ላይ ነው የሚሠራው። የመቶ ሺ ብር ደሞዘተኛ የሚሊዮን ብር ሞርጌጅ ቢገባና እምነቴን በሥራ መግለጼ ነው ቢል የራሱን ፈቃድና ፍላጎት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እንዳያደባልቅ ወይም እንዳያምታታ መጠንቀቅ አለበት።

እግዚአብሔር አብረሃምን በካራን ባናገረው ጊዜ አብረሃም ያገኘው መመሪያ ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አምኖ ነው ማድረግ የጀመረው፤ እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለውን ሁሉ እንደተደረገ ተቀብሎ ነው የራሱን ድርጊት የቀጠለው። ያደረገው ድርጊት ደግሞ ትንንሽ ውሳኔዎች ብቻ ሳይሆኑ የሕይወቱን አቅጣጫ በሙሉ የቀያየረው ድርጊት ነው። እግዚአብሔር እኛንም የሕይወታችንን ሂደት ወደሚለውጥ አቅጣጫ ይመራን ይሆናል። ግን እንዲህ አይነቱ ሰርነቀል መመሪያ እግዚአብሔርን በሚገባ ማዳመጥ ከተለማመድን በኋላ የሚመጣ ነው።

እምነትን መለማመድ ስንጀምር በአንዳንድ ነገሮች ላይ ቶሎ የማድረግ እርምጃ መውሰድ ያስፈልገናል።

*1ኛ ዮሐንስ 1፡9 "ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው" ይላል።*

ስለዚህ አንዱ ቶሎ ማድረግ የሚገባን የእምነት ነገር፣ ኃጢአታችን ሙሉ ለሙሉ ይቅር እንድተባለልን እርግጠኞች ሆነን፤ እንደዚያ መኖር መጀመር ያስፈልገናል።

ሁሌ አትኮራመት ደስታ እንዲህ አይደለም
ባንተ (በንቺ) ውስጥ ካለው የሚበልጥ የለም

ይህ የድሮ መዝሙር ብዙ ትርጉም አለው። መመጻደቅ አይደለም፤ ለእኛ ሕዝብ በተለይ ራስን ዝቅ አድርጎ እንደ ኃጢአተኛ መመልከት ትሁት እንደ መሆን ከሚቆጠርበት ዳራ (Background) ለመጣን ራስን እንደ ጻድቅ ማየት ያስቸግረናል። ይህንን ልምምድ ስንለማመድ ግን የተለየ አመለካከት ስለራሳችን ይሰጠናል፣ ባለፈው

በሆነው ሁሉ ራሳችንን ይቅር ለማለት በር ይከፍትልናል። የብዙዎች የረጂም ጊዜ ትግል ራስን ይቅር አለማለት ነው። ስሜት እምነትን ይከተላል። ስለዚህ ስሜታችን እንዲከተል እምነታችንን መለማመድ አለብን። በታዛዥነት የምናደርገው የእምነት ድርጊት ለስሜት መከተያ አውራ ጎዳና ይከፍትለታል፤ ከድርጊት ወደ ስሜት ማለፍ ቀላል እርምጃ ቢመስልም ነገር ግን አስቸጋሪ ሞዴል ነው። ምክንያቱም አንዳንዴ ስሜት የራሱ የሆነ አሳብ አለው።

ሌሎችንስ ይቅር ማለት እንዴት ይቻላል? ይህንኑ ሞዴል መከተል ነው ዘዴው። ሙሉ ለሙሉ ይቅር እንዳልናቸው በድርጊትና በቃል ስንገልጽላችው፣ ስሜትም ይከተላል። እርግጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ስሜት ያንገራግር ይሆናል። ግን ያ መጠቃታችን ወይም መጎዳታችን ትዝ ባለን ቁጥር "ይቅር ብዬ አልፌዋለሁ፣ ተመልሼ እዚያ ውስጥ አልገባም" ብለን ለስሜታችን በመንገር የበደሉንን መልስን ለመበደል በውሳኔ "እምቢ" ማለት ነው። ምስክርነታችው ይህንን ነጥብ የሚያጎላ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። በተደጋጋሚ ይቅርታ ማድረግን ሲለማመደዱ ስሜታቸው ወደ ይቅርታ የመምጣቱ ፍጥነት እየጨመረ ይመጣል።

በመንፈሳዊ ትርጉሙ እግዚአብሔርን መጠበቅ እያደረጉ የሚሆን እንጂ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ አይደለም። መጠበቅ የተሻለ የሥራ በር እስኪከፈት ድረስ አነስተኛ ሥራ መሥራት ሊሆን ይችላል። ያንን የምንሠራውንም ሥራ በሙሉ ልብና በተከፈተ አዕምሮ ማድረግን ያጠቃልላል፣ ማድመጥና መመልከትንም ይጨምራል፤ ምናልባት መልሳችን በዚያ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ከእግዚአብሔር የምንጠብቃችውን ብዙዎቹን ነገሮች መልሳቸውን የምናገኘው በደረጃ ነው። ጥያቄያችንን አንዴ ካቀረብን ጉዳያችን በእግዚአብሔር ዙፋን ሥር እንደተቀመጠ መቁጠር እንችላለን። በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ፣ እርሱ ደግሞ ልናደርገው የሚያስታውሰን ነገር እንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል። አንዳንዴ ከምንጠብቀው ነገር የተለየ ሌላ ነገር እንድናደርግ ይፈልግ ይሆናል። ለምሳሌ የጠየቅነው ስለምናውቀው አንድ ሰው ደህንነት ከሆነ፣ እልፎ እልፎ ለዚያ ሰው ልናደርገው የሚያስፈልገንን ይጠቁመን ይሆናል። ቸርነት ማሳየት፣ ትንሽ ኖት ለሰውዬው መተው፣ በጸሎት ላይ ጊዜ ወስደን ስለዚያ ሰው መማለድ፣ የማበረታቻ ቃል ለዚያ ሰው መስጠት፥ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ





ጥናት መጋበዝ እና የመሳሰሉ ድርጊቶችን ያስደርገን ይሆናል። እነኚህ ነገሮች ሁሉ በመጠበቅ ጊዜ ያሉ ቢሆኑም ለዋናው ጸሎታችን መልስ ደግሞ ቁልፍ ሊሆኑ ይችላሉ። መጠበቅ ማለት እግዚአብሔር ሰምቶኛል ብሎ መወሰንና ለጥያቄዬም ተገቢውን መልስ ይሰጠኛል ብሎ ማመን ነው። መጠበቅ እግዚአብሔርም ከሚያስፈልገው ጊዜ በላይ እንደማያስጠብቅ ማመን ነው። እርሱም ፈቃዱን እንዲፈጽም ጊዜና ቦታ መስጠት ማለት ነው። መጠበቅ መልሳችን ምን እንድሆነና መቼ እንደሚሆን ከእኛ የበለጠ እርሱ ያውቃል ብሎ ማመን ነው። ዘሩን የዘራ ገበሬ በየሳምንቱ የዘሩን ሁኔታ ለማወቅ እየቆፈረ ለማየት ቢሞክር ጥሩ ምርት አይኖረውም። ነገር ግን ዘሩ ተደብቆ በማይታይበት፣ ሞቶ በሚበሰብሰበት ጊዜ እንኳን ይሆናል ብሎ አምኖ በትዕግስት ይጠባበቃል።

## 4. መስማት

ጌታ የሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረ ጊዜ የአሠራር ሞዴሉን እንዲህ ብሎ ነው የገለጸው፣

*"እውነት እላችኋለሁ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም" ዮሐንስ 5፥19።* ኃጢያት የሌለበት፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሙሉ ጤነኛ፣ እጅግ ብልህ የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ይህንን ካለ በኋላ ደግሞ ስለ እኛ ሲናገር

*"ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" አለ። ዮሐንስ 15፥5*

እግዚአብሔርን መስማት እለታዊ ትኩረታችን መሆን አለበት። ይህ ደግሞ የችሎታ ጉዳይ ሳይሆን የአመለካከት ጉዳይ ነው። እግዚአብሔርን መስማት እንድሚያስፈልገን እናውቃለን? በራሳችን ዕውቀትና ጥበብ ብቻ በመተማመን በልምምዳችንና በፈጠራ ችሎታችን ብቻ ተደግፈን እንቆማለን የምንል ከሆነ እግዚአብሔርን መስማት እንደሚያስፈልገን ገና አላወቅንም ማለት ነው። የራሳችሁ ዕውቀትና ብልህነት አልበቃ ካላችሁ ወይም የትም ካላደረሳችሁ እግዚአብሔርን መስማት እንድትለማመዱ አበረታታችኋለሁ።

እግዚአብሔርን መስማት እኮ የምንገምተውን ያህል ከባድ አይደለም። በመጀመሪያ የጥሞና ጊዜ በራሳችን መውሰድ መለማመድ ያስፈልገናል። እነኚህን ደረጃዎች እንከተል፣

ሀ. በፀጥታ ልትሆኑ የምትችሉበትን ቦታ ምረጡና ተቀመጡ፣ ጋደም በሉ ወይም ተንበርከኩ፣

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳችሁ በእጃችሁ ወይም በአጠግባችሁ ይሁን፣

ሐ. ያጋጠማችሁን ችግር ወይም የጸሎት ጥያቄ አሰላስሉ፣

መ. አጠገባችሁ ላለ ሰው እንደምትነግሩ ለእግዚአብሔር ንገሩት፣

ሠ. ፀጥ በሉ፣ በእግዚአብሔር ፊት የተፈታችሁ ሁኑ፣ እዚህ ደረጃ ላይ ረዘም ያለ ጊዜ ውሰዱ፣

ረ. ወደ አዕምሯችሁ የሚመጡትን አሳቦች አዳምጧቸው፣ ራሳችሁን ለማሰብ በማስገደድ ሳይሆን በተፈታ ሁኔታ ተዝናኑ፣

ሰ. መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አንብቡ፣

ሸ. የሚመጡላችሁን አሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ መዝኗቸው፣

ቀ. እግዚአብሔር የሚላችሁን አድርጉ።

ብዙ ጊዜ ችግራችን እግዚአብሔር ሳይናገረን ቀርቶ ሳይሆን እኛ መስማት የማንፈልገው ነገር ይሆንና አዕምሮአችን አልቀበል እያለን ነው። እግዚአብሔር በአንድ መንገድ ወይም በሌላ ይናገራል፤ እኛ ግን አናስተውልም። ለመልሳችን ሳናውቀው በውስጣችን ዳር ድንበር አበጅተንለታል፤ መልሳችን ከዚያ ወጣ ካለ ከእግዚአብሔር ነው ብሎ ለመቀበል ይከብደናል። አንድ ምስጢር ልንገራችሁ። በራሳችን የመስማት ችሎታ ሳይሆን በእርሱ የመናገር ችሎታ እንተማመን። በራሳችን የመስማት ችሎታ ብቻ ከተማመንን ትኩረታችን በራሳችን ላይ ብቻ ይሆናል ያ ደግሞ ትክክለኛ ትኩረት





አይደለም። ነገር ግን በእርሱ የመናገር ችሎታ ከተማመንን፣ ማተኮር በሚገባን ነገር ላይ አተኩረናል ማለት ነው`። እርሱ ስለ እኛ ሁሉን ያውቃል፤ ሙሉ ታሪካችንን፣ የአፈጣጠራችንን መዋቅር፣ የተፈተልንበትን ድርና ማግ፣ የተለማመድናቸውን ነገሮች፣ ያነበብናቸውን መጽሐፎች፤ ተሰፋችንን፣ አቅዳችንን፣ ፍላጎታችንን፣ ግባችንን ሁሉ ያውቃል። ስለዚህ አንተን እንዴት ማናገር እንደሚችል፣ ካንቺ ጋር እንዴት መግባባት እንዳለበት ያውቃል። በዚህ እንተማመን። አንድ ሌላ ምክር ልጨምር፣ እግዚአብሔር ለመናገሩ ሙሉ በሙሉ የሆነ እርግጠኝነት ለማግኘት አንሞክር። ልብ አድርጉ ቀደም ብለን እንዳየነው እርግጠኛነትን መፈለግ እምነትን ይተካዋል። እግዚአብሔር ደግሞ በእምነት እንድንራመድ ነው የሚፈልገው። ለራሳችን ሐቀኛ ከሆንን፣ እግዚአብሔርም በቀስታ ለውስጣችን እንደሚናገር ከተገነዘብን፣ እግዚአብሔር ሲናገር እናውቀዋለን። የሚለንን ሰምተን ለመከተል ብንወስን ከፈቃዱ ብዙ ርቀን አንሄድም። በእውነት ልንታዘዘው መጣራችንን ካወቀ፣ የሰማነው የመሰለን የተሳሳተ እንኳን ቢሆን በመታዘዛችን ውስጥ ገብቶ ሁሉን ወደ መልካም ይለውጠዋል። እርሱ ውስጣችንን የሚያውቅ አምላክ ነው። ጌታ እንድታደርጉት የሚነግራችሁ ነገር ምንድነው?

- በእምነት እርሱ እንደነገራችሁ እንደዚያ ማድረግ
- ሁሉን ለመልካም እንዲሠራ ያደርገዋል ብሎ ማመን

## 5. መናገር

በቃላት ችሎታ ወይም ኃይል የተሰሩ አንዳንድ ስህተቶች አሉ። እነርሱን በምዕራፍ 7 ውስጥ እናያቸዋለን። ለጊዜው ግን ሁለት ጥቅሶችን እንመልከት።

ሮሜ 4፥17 "ያልነበረውንም እንደነበረ የሚያደርግ" ይላል።

አንድ የእንግሊዝኛ ትርጉም ይህንን ጥቅስ እንዲህ ብሎ ነው የተረጎመው፣ "የሌለውን ነገር እንደ አለ አድርጎ የሚጠራ" (calls things that are not as though they were) "እንደ አለ..." የሚለው ገለፃ እግዚአብሔር ቃል ብቻ በመናገር ለውጥ ስለሚያመጣ የመፍጠር ኃይሉን አስቀድሞ በቃል ያጸናዋል።

እግዚአብሔር ይህንን ማድረግ ይችላል፣ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ነው። እኛም ደግሞ  ቃል የመናገር ኃይል ተሰጥቶናል፣ ጌታ የሱስ ሲያስተምር እንዲህ ብሏል፤

*"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። በእግዚአብሔር እመኑ፣ እውነት እላችኋለሁ ማንም ይህን ተራራ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢለውና ይህንንም በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን ይሆንለታል። ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደተቀበላችሁ አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል" ማርቆስ 11፥ 22-24።*

ይህ ማለት እግዚአብሔር ብሎታል ብለን አምነን ያንን ቃል ስንናገር መፍጠር የሚችል ኃይል አብሮት ይወጣል ማለት ነው። ያንን ኃይል ነው የምንፈታው።

**ምናብን ለመኮርኮር 4፡**

**እንዴት ነው ማንም እስባሁን ድረስ ተራራ ማንቀሳቀስ ያልቻለው? ይህንን ተስፋ ደግሞ እንዳለ ካልተቀበልኩ ቃሉን መሻር አይሆንም? በዚህ እንጻር ሲታይ ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋዎችስ ለመሆናቸው ምን ዋስትና አለ?**

ጊዜው በጣም ቆይቷል። አገሩ አሜሪካ ሲሆን በሒውስተን ቴክሳስ ገና የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን ማቋቋማችን ነበር። ሰዎችን ለመድረስ ከምናደርጋቸው ነገሮች አንዱ መንገድ ፒክኒክ አዘጋጅተን ምግብ በተለይ ሥጋ ጥብስ (Barbeque) ሰርተን ሰዎችን መጋበዝ ነበር። አንድ ጊዜ ሒውስተን ሐይቅ አካባቢ ይህን አይነት ዝግጅት አዘጋጅተን እሳቱን ለማቀጣጠል ደፋ ቀና ስንል ትልቅ ዝናብ መጣ። ከፓስተርችን





ዶክተር ተስፋ ወርቅነህ ጋር ምን ማድረግ ይሻል ይሆን እያልን ስንነጋገር ተስፋዬ የሚባል አንድ በዚያን ጊዜ ለእኛ አዲስ የነበረ ወጣት መጣና ተገዳደረን። "በሉ እስቲ እንግዲህ እምነታችን በሥራ ሲገለጽ ይታይ፣ ይህንን የመጣ ዝናብ ቁም ብለን እንገስጸው" አለን። ከዚያም ጮክ ብሎ እየጸለየ ዝናቡን ቁም ማለት ጀመረ። ዝናቡ አካባቢያችንን በኀርፍ ሲያጥለቀልቀው እኛ የነበርንበት ቦታ ግን ምንም አልዘነበም። ብዙዎች በአካባቢያችን ፕሮግራማችውን እየዘጉ ሲሄዱ እኛ ግን ፕሮግራማችንን ጨርሰን እዚያው ውለን ተመለስን። እርግጠኛ ነኝ ብዙዎች ይህን ታሪክ ይጠራጠሩታል። ነገር ግን እውነትነቱን የሚመሰክሩ አንዳንድ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በሒውስተን ቴክሳስ ከተማ አሉ።

የምንናገረው ቃል ሁሉ እንዲህ ቶሎ የሆነ መልስ ሁል ጊዜ ያመጣል ለማለት አይደለም። ተናግረን ተናግረን ያልሆኑ ብዙ ነገሮችም አሉ። ማወቅ ያለብን ግን በእምነት ከተናገረን እንደተናገረን ባይፈጸምም እንኳን እግዚአብሔር ያንን ሸፍኖ መልካም ወይም የተሻለ ውጤት እንደሚያመጣ ማወቅ ነው። ያ ራሱ የእምነት ክፍል ነው። ትክክለኛ ነገር ለመስራት እየሞከሩ መሳሳት እኮ ሰብዓዊነት ነው። ከተሳሳቱ በኋላ አልተሳሳትኩም ብሎ ድርቅ ማለቱ ነው ጥፋቱ። የዛን ዕለት ዝናቡ ባይቆም ኖሮ ጥፋቱ ብዙ አይሆንም ነበር። ነገር ግን ዝናቡ ባለመቆሙ የሰዎችን እምነት ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ብንጀምር ጥፋቱ የከፋ ይሆን ነበር። ያ ተራ የሆነውን ስህተት ወደ አደገኛ ደረጃ ማድረስ ነው። በውጤቱ ምክንያት ወደተሳሳተ ትምህርት፣ እንዳንገባ ወይም በህብረቱ መካከል መለያየትን እንዳይመጣ መጠንቀቅ አለብን። ጸሎቱ ካልተመለሰ ለሁኔታው የሚስማማው መልስ እንዲህ ሊሆን ይችላል፣ "እግዚአብሔር ዝናቡን እንዲቆም ተናገረው ያለኝ መስሎኝ ነበር፣ ዝናቡ ግን ቀጥሏል፣ እንግዲህ በትክክል አልሰማሁም ማለት ነው። በሉ ወደ መጠለያ እንሂድ"።

የእግዚአብሐር ቃል በማቴዎስ ወንጌል 17:20 ላይ እንዲህ ይላል

*"የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህንን ተራራ ከዚህ ተነስተህ ወደዚያ ሂድ ብትሉት ይሄዳል፤ የሚሳናችሁ ነገር አይኖርም"*

ምናብን ለመኮርኮር 4 .

እንዴት ነው ማንም እስካሁን ድረስ ተራራ
ማንቀሳቀስ ያልቻለው? ይህንን ተስፋ ደግሞ
እንዳለ ካልተቀበልኩ ቃሉን መሻር አይሆንም?
በዚህ አንጻር ሲታይ ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ
ተስፋዎችስ ለመሆናቸው ምን ዋስትና አለ?

የእነዚህ ተራሮች ጉዳይ እንዴት ነው? መቸም እስካሁን ክርስቲያን ሲያዘው ተነስቶ ስለሄደ ተራራ ሰምቼ አላውቅም። ግን እርግጠኛ ነኝ የሞከረ ሰው ሳይኖር አይቀርም። እኔ እንደሚመስለኝ ጌታ የሱስ መግለጫ አድርጎ ነው የተጠቀመበት። በዚህ ትርጉሙ ካየነው ብዙ ተራራ የሆኑ ነገሮች ሲወድቁ አይቻለሁ። ተራራ በሕይወታችንና በሁኔታችን ያስቸገሩን ትላልቅ ነገሮች ናቸው፤ ተቃውሞ፣ ግራ መጋባት፣ ዕዳ፣ የመሳሰሉት ናቸው። እነኚህ ተራሮች ሲነጉዱ፣ ለእምነት እሺ ሲሉ አውቃለሁ። ታዲያ ለምድር ውበትን የሚሰጥ የተፈጥሮ ተራራ ተነስቶ ከሚወድቅ እንዲህ ያሉት ነገሮች ቢወድቁ አይሻልም? ለእኛ ብዙ ጥቅምና ትርጉም የሚኖረው የራስ ዳሽን መውደቅ ወይም የኪሊማንጃሮ መንኮታኮት ሳይሆን አላጸልይ ብሎ የሚያጣብበንሽክም ወይም ቃሉን እንዳናነብ የዞረብን እዚም ቢለቀን ነው።

## 6. አሥራት መስጠት

አሥራትን መስጠት ከእምነት ጋር በጣም ብዙ ግንኙነት አለው። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የጌታ የሱስ ምሳሌዎች ገንዘብን ይጠቅሳሉ።

*“ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያው ይሆናልና” ማቴዎስ 6፡21።*

ለእግዚአብሔር አላማ ገንዘባችሁን የማትሰጡ ከሆነ እርሱ በረከቱን ከሚለቅበት ትልቅ ክፍል ራሳችሁን እርቃችኋል ማለት ነው። እምነት ድርጊት ነው ብለናል። አሥራትን መስጠት ደግሞ ጉልህ የሆነ የእምነት ድርጊት ነው። የመስጠትና የመተማመን ምልክት ነው። አሥራታችሁን መስጠት ለምትለማመዱ የምናገረው የማታውቁትን ነገር እንዳልሆነ ይገበኛል። አሥራታቸውን በመስጠት ስለተባረኩ ብዙ ሰዎች ታሪክ ልነግራችሁ እችል ነበር። ግን አላማውም ቦታውም ስላልሆነ በዚሁ እናልፈዋለን። አስቀድመን እንዳነሳነው መረዳት መታዘዝን ይከተላል። በታማኝነት ለእግዚአብሔር ቤት የምትሰጡት በተለይ ገንዛባችሁን በተመለከተ እንዴት ሊባርካችሁ እንደሚችል ካልተለማመዳችሁት (መታዘዝ) ሊገባችሁ (መረዳት) አይችልም። አሥራት የእግዚአብሔርን ታማኝነት የምንገልጽበትና እርሱም እንዲያደርግ የምንፈታበት ትልቅ የእምነት ልምምድ ነው።





በየቦታው ስሄድ ከቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች የምሰማው አንድ የጋራ ችግር አለ። ብዙዎቹ ስለ አሥራት መናገር ከባድ ይሆንባቹዋል። እንዳውም አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያናቸው ገንዘብ ስለ መስጠት ከተሰበከ ከአስር አመት በላይ እንደሆነ በመንፈሳዊ ኩራት ይናገራሉ። “እኔ ወንጌልን ለመስበክ እንጂ ስለ ገንዘብ ለመናገር አልተጠራሁም” ብለው የነገሩኝም አሉ። የሚያሳዝነው ታዲያ እነኚህ ሰዎች በእምነታቸው የቆዩ፣ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ፣ ጥሩ ምስክርነት ያላቸውና የቆዩ መንፈሳዊ አባቶች ናቸው። እስካሁን ያልተረዱት ነገር ግን ስለ መስጠት በትክክል ማስተማር የወንጌል ክፍል መሆኑን ነው። በሌላ አነጋገር ስለ አሥራት አለማስተማር ወንጌልን በሙላት አለመስበክ ነው። ከዚያም በላይ ማወቅ የሚገባውን ምዕመን ባለማሳወቃቸው ትልቁን የበረከት በር እየዘጉባቸው ነው። ስለ ገንዘብም ብዙ የተዛባ ትምህርት ሊበዛ የቻለው፤ ታማኝ የሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች ትክክለኛውን የአሥራት ትምህርት በሰፊው አለማስተማራቸው ከምክንያቶቹ አንዱ እንደሆነ እገምታለሁ።

## 7. በዓይነ ሕሊና ማየት

እግዚአብሔርን ስለመስማት ባልፉት ምዕራፎች አንብበናል። አንድ ሰው እግዚአብሔርን የሚሰማ ከሆነ በውስጡ የሚመጣው ምናብ (imagination) የእግዚአብሔርን ኃይል የሚፈታበት መንገድ ሊሆንለት ይችላል። ይህ ምናብ በሚለው ቃል የገለጽኩት ሁኔታ በውስጣዊ ዓይናችን ነገሮች ሲለወጡ የማየት ችሎታ ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር የእጅ ቁርጥማት (አርትራይተስ) የያዘውን ሰው እንደሚፈውስ ታምኑ ይሆናል። በምናባችሁ ታዲያ በአርትርይተስ የተሸማቀቀ እጅ ታዩ ይሆናል። ከዚያም እነኚያ ጣቶች ተፈተው መሥራት ሲጀምሩ ይታያችኋል። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር እነኚያን እጆች እንደፈወሰ በማመን ማመስገን ትጀምራላችሁ። ይህ አይነቱ ልምምድ በእውነተኛ እምነት ያልተደገፈ ከሆነ ከሌሎች ባዕድ ልምምዶች ጋር ሊዘበራረቅ ይችላል።

እንደምናውቀው ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ብዙ አይነት የባእድ መንፈስ ልምምዶች አሉ። ኒው ኤጅ (New Age) በሚል ዘመናዊ ስም በተለይ በሂንዱኢዝምና በቡዲሂዝም ላይ የተመሠረቱ ልምምዶች ዛሬ ሠለጠኑ በተባሉት አገሮች

ተሰፋፍተዋል። እነኚህ ልምምዶች በቀላሉ ሲታዩ ክፋት የሌላቸው ቢመስሉም፣ በጣም አደገኛ መሆንም ይችላሉ። አደገኛ በሚሆኑበት ደረጃ ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ጋር ተሳትፎ ይኖራቸዋል። እነኚህ ኃይላት ደግሞ ምንም አምረው ቢቀርቡም፣ ምንም ዘመናዊ ቋንቋ ቢናገሩም፣ ምንም በሆሊዉድና በታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች ተቀባይነት ቢኖራቸውም ለሰው ልጅ ያላቸው አላማ ጥፋት ብቻ ነው። ከኒው ኤጅ ኮከብ ቆጣሪዎች(Star Gagers) መዳፍ አንባቢዎች(Palm Readers) ሞራ ገላጮች (Chart Readers) እድል ነጋሪዎች (Fortune Tellers) ሌላው ቀርቶ ከቴሌቪዥን ወሬ አድቃቂዎችና ሰላቂዎች (Talk Show) የሰማነውን በማየት (visualize) የአጋንንት ኃይል በራሳችንና በሌሎች ላይ እንዲሰለጥን እንፈቅድለታለን። የእግዚአብሔር ሰዎች በጣም ልንጠነቀቅበት የሚገባን ዘመን ላይ ነን ያለነው። ሰይጣናዊ መንፈሳዊነት የበዛበት ከእግዚአብሔር አሠራር ጋራ በጣም የተቀራረበበት፤ ቋንቋው እንኳን ሳይቀር የተደበላለቀበት ነው ያለንበት ዘመን። በሙያቸው በጣም የምናደንቃቸውና የምንከተላቸው በቴሌቪዥን ሁሌ የምናያቸው፤ በሲኒማ የምናውቃቸው ብዙዎቹ ባለሙያዎች የኒው ኤጅ ተከታዮች መሆናችውን በግልፅ ከመናግራቸውም በላይ ክርስትናን የዘረኞች፣ የአክራሪዎች፣እና የኋላ ቀሮች እምነት ብቻ አድርገው ነው የሚያቀርቡት (በዚህ አሳብ ላይ በሰፊው አምላክን ፍለጋ በተባለው በቅርቡ በሚወጣው መጽሐፌ ውስጥ ጽፌአለሁ)

ነገር ግን አንድ ችሎታ በተሳሳተ መንገድ ስለሚሠራበት ያንን ችሎታ ሙሉ ለሙሉ መጣልም ትክክል አይደለም። ይህ የትምህርትና የዲሲፕሊን ጥያቄ ነው። ክርስቲያናዊ ካልሆኑ መነሻዎች የሚመነጩትን መንፈሳዊ ልምምዶች ለይቶ የማወቅ፣ የማስወገድና የመቃወም ዲሲፕሊን ሊኖረን ይገባል። ክርስቲያኖች ሁሉ በቅርባችን በሚገኝ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አካል መሆን የሚጠበቅብን ለዚህ ነው።

ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይስማማ ምንም ነገር ከእግዚአብሔር አይደለም። ቃሉን ስናውቅ ያርመናል፤ ከመሠረታዊ የክርስትና ዲሲፕሊኖች አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል የማንበብ ልምምድ ነው። ቃሉን ስናውቅና በቃሉ ስንመራ ማንም መጥቶ "ምንም አይደለም ካምፒንግ ሄደን አብረን በድግምት ብንቃትት (meditation and chanting) ቢለን" በቀላሉ አንወሰድም። አንድ ጓደኛዬ ልምምዱን እንዲህ





*ብሎ ነው ያጫወተኝ። "አንድ የኮሌጅ ጓደኛዬ ወደ እንደዚህ አይነት ቦታ ሲጋብዘኝ ያለኝ ትዝ ይለኛል "it will be a cross cultural experience" ነበር ያለኝ።እኔ ኮሌጅ በነበርኩበት ጊዜ ይህ ልምምድ የተስፋፋ ነበር። እንዳውም እንደ ትልቅ የዕውቀት ማዳበሪያ መንገድ ይቆጠር ስለነበር ያንን መቃወምም ሆነ አለመሳተፍ ኋላ ቀር መሆን ነበር። ታዲያ እኔ የዛን እለት "እምቢ ብዬ መኝታ ቤት ለመቅረት ትልቅ ብርታት ነበር የጠየቀኝ" አለኝ።*

መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ አሳብ ላይ ያለውን አቋም ለማወቅ በአማርኛ ከቻላችሁም በሌላ ቋንቋ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ዘዳግም 18፡9-13 ያለውን ክፍል አንብቡት። በሩቁ ማስወገድ የሚገባችሁ የባዕድ መንፈስ ልምምዶች ምን ምን እንደሆኑ ይነግራችኋል።

እግዚአብሔርን ለመስማትና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በፈቃዳችን የተሰጠን ከሆንን በመንፈሳዊ አይናችን የማየት ችሎታችን ሌላው የእምነት መንገድ ይሆንልናል። ጌታ የሱስ የሚሠራው አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ ነው (ዮሐንስ 5፡19)፣ የሚያስተምረው አብ የላከውን ብቻ ነው (ዮሐንስ 7፡16)፣ የሚናገረው አብ የነገረውን ብቻ ነው (ዮሐንስ 8፡28)፣ ምን እንደሚል፣እንዴት እንደሚል እንኳን (ዮሐንስ 12፡49) ሳይቀር ከአባቱ ነው የሚቀበለው። በራሱ አጀንዳ ሳይሆን የአባቱን አጀንዳ ነበር የሚያደርገው (ዮሐንስ 7፡28)።

ምናብን ለመኮርኮር 5.

የአብረሃም እምነት ስለኝ አያሉ የሌለን ነገር እንዳለ በመቁጠርና ራስን በማታለል መካከል ምን ልዩነት አለ? እምነትስ መንፈሳዊ የሆነ ራስን ማታለል አይደለም እንዴ?

**ምናብን ለመኮርኮር 5.**

**የአብረሃም እምነት አለኝ እያሉ የሌለን ነገር እንዳለ በመቁጠርና ራስን በማታለል መካከል ምን ልዩነት አለ? እምነትስ መንፈሳዊ የሆነ ራስን ማታለል አይደለም እንዴ?**

ጌታ የሱስ አልዓዛርን ለማስነሳት ሲሄድ እኔ እንደሚመስለኝ በመንፈሳዊ አይኑ አልዓዛርን ከመቃብሩ ውጪ ቆሞ ያየው ይመስለኛል። ፍላጎታችሁን ለእግዚአብሔር ገልጻችሁ እርሱ ደግሞ ወደ አንድ አቅጣጫ የጠቆማችሁ ከመሰላችሁ፣ ያንን ነገር በመንፈሳዊ አይናችሁ ማየት ትችላላችሁ። የልጆቻቸሁ በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት ማምጣት ሊሆን ይችላል የሚታያችሁ፣ ችግራችሁ ገንዘብ ከሆነ ገንዘብ የሚመጣበትን መንገድ ማየት ትጀምራላችሁ፤ ጸሎቱ ለበሽታ ከሆነ የእግዚአብሔር የፈውስ ኃይል የበሽታውን ሥር ሲነቅለው ማየት ትችላላችሁ፤ ጓደኛችሁ ወይም ወዳጃችሁ ጌታ የሱስን እንዲያገኝ ከሆነ ጸሎታችሁ፣ ያ ሰው አጠገባችሁ ተንበርክኮ ሲጸልይ ማየት፤ ወይም ቅር የተሰኛችሁበት ሰው ካለ ይቅርታ ስትለዋወጡ ማየት ትችላላችሁ። ማየት፣ መስማትና በአዕምሮ ውጤቱን መገንዘብ ተፈጥሮአዊ ምናብ (imagination) የሚሠራባቸው መንገዶች ናቸው። ይህንን አሳብ በምዕራፍ ሰባት "የስህተት ትምህርቶች (ኑፋቄ) በሚለው አርዕስት ስር በሰፊው አቅርቤዋለሁ።

## 8. እምነት ለጥበቃ

*መዝሙረኛው ዳዊት ለችግራችን መልስ የሚሆን እምነት እንዴት ሊኖረን እንደሚችል ልንከተለውና ልንለማመደው የሚገባን ሞዴል አሳይቶናል። መዝሙር* 143 በተከታታይ ያሉ ርምጃዎች ናቸው።

- ሀ. ችግርን እንዳለ አምኖ መቀበል *"ጠላት አሳደኛል...መንፈሴ በውስጤ ዝለለች.... .ልቤም በውስጤ ደንግጧል" ቁ. 3-4።*
- ለ. እግዚአብሔር ባለፈው ያደረገልንን መልካም ነገር ማስታወስ *"የቀደመውን አስታውሳለሁ፣ ሥራህንም ሁሉ አሰላስላለሁ፣ የእጆችህን ሥራ አውጠንጥናለሁ" ቁ. 5።*
- ሐ. የእግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ "እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ" ቁ. 6።
- መ. *መልስ መጠየቅ "ፈጥነህ መልስልኝ...ምህረት አሰማኝ.... መንገድ አሳየኝ.... አድነኝ.... ፈቃድህን እንድፈጽም አስተምረኝ" ቁ. 7-10*





ለ እምነትን ለመገንባት ቁልፍ ነው። "ትናንት ያደረገው ለዛሬ እምነት ሆኖልናል" የሚል የዱሮ መዝሙር አለ፣ ይህንን አሳብ ያጎላዋል። እግዚአብሔር ባለፈው ያደረገውን ማስታወስ በአሁኑ ሁኔታችን ላይ ሊያደርግ ይችላል የሚለውን እምነታችንን ያጠብቀዋል፣ ያቀጣጥለዋል። ስለዚህ ጊዜ ወስደን እግዚአብሔር ባለፈው ጊዜ ያደረጋቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክ፣ ከራሳችንም ሕይወት እያወጣን መከለስ ይኖርብናል።

ነቢዩ ዕንባቆም እንዲህ አለ

> *"እግዚአብሔር ሆይ ዝናህን ሰምቻለሁ፣ እግዚአብሔር ሆይ ሥራህም አስፈራኝ፣ በእኛ ዘመን አድሳቸው፣ በእኛ ዘመን እንዲታወቁ አድርግ" ዕንባቆም 3፥2።*

ነቢዩ ኢሳይያስም ተመሳሳይ ነገር ነው የተናገረው፣

> *የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነስ፣ ተነስ፣ ኃይልን ልበስ እንዳለፉት ዘመናት፣ በጥንት ትውልዶች እንደሆነው ሁሉ ተነስ ... የታላቁን ጥልቅ ውሆች ያደረቅህ ... አንተ አይደለህምን? " ኢሳ. 51፥9-10*

እግዚአብሔር ባለፈው የሠራውን ማስታወስ ስንጀምር አሁን ሊሠራ ላለው ነገር እምነታችን ማደግ ይጀምራል።

አሁንም ኢራቅ የነበርኩ ጊዜ የሆነ አንድ ታሪክ ልንገራችሁ። አንድ ሌሊት ከተኛን በኋላ ኃይለኛ ተኩስ ተጀመረ። ተኩሱ እየበዛ እኛ ወዳለንበት ካምፕ እየቀረበ ከየአቅጣጫው መጣ። ከነበርንበት ድንኳን ወጥተን በግቢው ባለ አንድ ሕንጻ ውስጥ ታመቅን። ምንም እንኳን የዛን ዕለት ማታ ካምፓችን የሚሰበርና የምንያዝ መስሎ ቢታይም በውስጤ ግን ልረዳው የማልችለው ሰላም ነበረኝ። እንዳውም አጠገቤ የተቀመጠች እንዲት እንግሊዛዊት ሴት ደንግጣ በጣም ስታለቀስ ዞር በዬ አየኋትና "አይዞሽ ምንም አንሆንም" አልኳት። በውስጤ የነበረኝ እርግጠኝነት በብዙ ሁኔታ ወስጥ ጠብቆ ያሳለፈኝ በዚያን ጊዜ እንደማይተወኝ ማወቁ ነበር። እርሷም ሁኔታዬን አይታ ተረጋጋች። በኃላ ስንሰማ ግን ተኩሱ በኛ ላይ ሳይሆን የሚያከብሩት በአል

ስለነበረ እንደሆነ ሰማን። ከዚያ በኋላ ሴትዮዋ ባየችኝ ቁጥር Mr. Teflon ብላ ነበር የምትጠራኝ (ሙቀት በቀላሉ የማይሰማው ለማለት ነው)። ለምን እንደዚያ ሊሰማኝ እንደቻለ ራሴን ደጋግሜ የጠየቅሁት ጥያቄ ነው።

ስለ መንፈሳዊ ውጊያ በሰፊው በምዕራፍ 6 አቀርባለሁ። እዚህ ቦታ ግን ስለ ጥበቃ አንድ አሳብ አቅርቤ ልለፍ። ሁኔታውች አስቸጋሪና አስጨናቂ በሚሆኑበት በዚህ አለም በቀላሉ ራስን መቆጣጠር ወደማይቻልበት መርበትበት (Paranoia) መግባት ቀላል ነው። በኤፌሶን 6 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ በግልፅ የሚናገረው ነገር አለ። የምንዋጋው ጠላታችን አቅሙ እኛ በተፈጥሮ ኃይላችን ልናሸንፈው የማንችለው ነው። ስለዚህ ጳውሎስ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ጥበቃ መቀበል እንዳለብን ነው የሚያስተምረን። በሌላ አነጋገር ያለ እግዚአብሔር ጥብቃ የጠላት መጫወቻ ኳሶች ነው የምንሆነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ስንሆን ግን በጠላት ላይ ከአሸናፊዎች በላይ እንሆናለን።

ከቤተሰቤ ሩቅ በነበርኩበት ጊዜ በየጠዋቱ እግዚአብሔር ቤተሰቤን እንደሚንከባከብ በምናብ እመለከት ነበር። የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦችን በመጠቀም እግዚአብሔር በዙሪያቸው ቅጥር ሆኖ ከክፉ ሲጠብቃቸው በመንፈሴ እመለከታለሁ። ስጸልይላቸው በመንፈሴ በክርስቶስ ደም እሸፍናቸዋለሁ፣ ወይም በጽድቁ ጽዳል አሸብርቀው አያቸዋለሁ፤ ከዚያም "ጌታ ሆይ! በአሁኑ ጊዜ ጥበቃህ በቤተሰቤ ላይ ነው" ብዬ አመሰግናለሁ።ይህ መንገድ የእምነት መንገድ ስለሆነልኝ በየቀኑ የቤተሰቤን ጥበቃ በዚህ እምነት እጸናው ነበር።ከዚያም ስልክ ስደውል አስግቶን የነበረው ነገር ለመልካም ተለውጦ፣ ውጤቱ አያምርም ይሆናል ብለን የፈራነው ነገር በታወቀ ወይም ባልታወቀ ምክንያት መልካም ሆኖ እሰማለሁ። ፍርሀትና ሥጋት ከቤታችን እየጠፉ፣ መነፋፈቃችን እንኳን ጣፋጭነት ያለው ናፍቆት እንጂ የተጎዳንበት አልነበረም። ጭንቀትን ዘር በል አልነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር እንክብካቤና ጠበቃ በቤታችን ላይ ተሰፋፋ።

## 9. የእግዚአብሔር መገኘት

እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ ለወንድማችን ለሄናክ ሰይፉ ከበደ ብዙዎቻችን እንጸልይ





ነበር። ሄኖክ የመጋቢ ሰይፉ ከበደ ልጅ ሲሆን የዳላስ ቴክሳስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረና በዳላስና በአካባቢዎቿ ባሉ አብያተ ክርስቲያናትና ክርስቲያኖች ውስጥ የፍቅርና የትህትና ማህተሙን ትቶ ያለፈ ወጣት ነው።

የሄኖክን መታመም ስሰማ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ቀረብኩ። ከአባቱ ጋር ካለኝ የቅርብና የረጂም ጊዜ ወዳጅነት በላይ ሄኖክን ገና በጨቅላነቱ ስለማውቀው የእርሱ መታመም በጣም ካስደነገጡኝ ክስተቶች አንዱ ነበር። ስለዚህም ብዙ እጸልይለት ነበር። አንድ ጊዜ እንዳውም በምጸልይበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል መዝሙር 68፥20 ወደ አሳቤ መጣልኝ፣ "አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው፤ ከሞት ማምለጥ የሚቻለውም በጌታ በእግዚአብሔር ነው"። "ከሞት ማምለጥ" የሚለው ቃል በአሳቤ ስለጎላ ቃሉ ሬማ ሆነልኝ። ስለዚህ ሄኖክ አይሞትም ብዬ ተበረታታሁ። ወዲያው ደግሞ ተሻለው የሚል ወሬ ስሰማ እጅግ ተጽናናሁ። ግን ብዙ ሳይቆይ በተለይ ሄኖክን በቅርቡ ሆነው ከሚያስታምሙት አንዱ በሽታው እየባሰ እንደ ሆነ ሰማሁ። "እንዴት ነው ጌታ ሆይ ፈወስኸው የለም እንዴ" ብዬ ጌታን ጠየኩት። ሕዝቅኤል 33፥16 በአሳቤ መጣ፤ ስመለከተው የጥቅሱ መጨረሻ "...በእርግጥ በሕይወት ይኖራል"። ይላል።

እግዚአብሔር በእነኚህ ጥቅሶች ስለተናገረኝ ስለፈውስ እንድፀልይለት ይፈልጋል ማለት ነው ብዬ ወሰንኩ። ሄኖክ ከመሞቱ በፊት በሌሎች ብዙ ምልክቶችም እግዚአብሔር በበሽታው ጣልቃ ሲገባ፣ ከስቃዩ ሁሉ ነጻ እንደሆነ የሚመሰክሩልኝ፣ የገንዘብ ጥያቄው ተአምራዊ በሆነ መንገድ ሲፈታ፣ ሄኖክ ራሱ ያለው ጥያቄ ሁሉ ሲመለስለት ይታወቀኝ ነበር። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ግን በሽታው እየፀናበት እንደሆነ ነበር የምሰማው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሄኖክ ወደ ጌታ ሄደ የሚል ስልክ ተደወለልኝ። ሞቱን ስሰማ ዜናው በጣም መታኝ፤ ብዙ ጥያቄዎችም ወደ አሳቤ መምጣት ጀመሩ። ለብዙዎቹ እስካሁን ድረስ አጥጋቢ መልስ አላገኘሁላቸውም። ለምን እግዚአብሔር ይፈውሰዋል የሚል ስሜት እንዲኖረኝ ሆነ? እነዚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ለምን ወደ አሳቤ መጡ? ለምን? ለምን? ብዙ ጥያቄዎች ይዤ ለቀብሩ ሥነ ሥርዓት ወደ ዳላስ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ።

በዳላስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጠን ግን አንድ ነገር ሆነ። የረጂም ጊዜ ፓስተሬና የሄኖክ አባት መጋቢ ሰይፉ ከበደ መድረኩ ላይ ቆሞ መናገር ሲጀምር እግዚአብሔር በዚያ ቦታ ነበር። እግዚአብሔር በዚያ ስለተገኘ አባቱ ተጽናንቶ ቆሞ ወንጌልን መስበክ ቻለ፤ እናቱ፣ ባልቤቱ፣ ወዳጆቹ ሁሉ ተጽናኑ። እዚያው ቁጭ እንዳልኩ ለጥያቄዬ ሁሉ መልሱ እኮ ይሄ ነው ብዬ ለራሴ ተናገርኩ። መልሱ የእግዚአብሔር በመካከላችን መገኘት ነበር። መልሱ አጽናኝ የሆነው እርሱ ለባለቤቱ፣ ለወላጆቹ፣ ለወዳጆቹ የሰጠው መጽናናት ነበር። ከዚያ በኋላ ጥያቄ አልነበረኝም። ምክንያቱም ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን ነው የሄደው፣ ለጥያቄአችንም ሆነ ለፀሎታችን ፍፁም የሆነው መልስ የእግዚአብሔር መገኘት መሆኑን ተረዳሁ።

## 10. ለታላቅነቱ እሰግዳለሁ

አንድ ቀን በጸሎት ጊዜ ከመዝሙር 119 አነብ ነበር (መዝሙር 119፣ 176 ቁጥሮች ያሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ረጂሙ ምዕራፍ ነው)።

ቁጥር 18 ላይ *"ከህግህ ድንቅ ነገርን እንዳይ አይኔን ክፈት"* ይላል።

ለምንድነው ጌታ አይኔን እንዲከፍት የምለምነው? ለምን ራሴ ከፍቼ አላይም? በውስጤ ነበር የምጠይቀው፤ ግን ማንበቤን ቀጠልኩ ከቁጥር 33 እስከ 37 ውስጥ ደግሞ እንዲህ የሚሉ ቃላት አሉ፣

> *እግዚአብሔር ሆይ የሥርዓትህን መንገድ አስተምረኝ....ማስተዋልን ስጠኝ....በትዕዛዝህ መንገድ ምራኝ...ከንቱ ነገር ከማየት አይኖቼን መልስ"*

ዳዊት እግዚአብሔር እንዲያደርግለት የሚጠይቀው በተፈጥሮ የራሳችን አላፊነት የሆነውን ነገር እንደሆነ አስተዋልሁ። ከዚያም ራሴን ለማሻሻል እየፈለግሁ የወሰድኳቸውን አንዳንድ እርምጃዎች ማሰላሰል ጀመርኩ። ማን እንዳለው ትዝ አይለኝም ግን የዱሮ የሰብከት ማስታወሻ ደብተሬ ላይ የተጻፈ አንድ ጽሁፍ ነበር "ማንም የራሱን ልብ መለወጥ አይችልም፣ የሚችለው ግን እግዚአብሔር እንዲለውጥለት መጸለይ ነው"። እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነው። በእግዚአብሔር ታላቅነትና የበላይነት ላይ እተኩረን ታላላቅ ነገሮች ያደረገበትን ጊዜ እያስታወስን ችሎታውን ስናደንቅ እግዚአብሔር አሁንም ያደርጋል። ለእኛ አስቸጋሪና የማይቻል የሆኑት ነገሮች ሁሉ ለእርሱ ቀላል ናቸው። ለታላቅነቱ በመንበርከክ፣ ለበላይነቱ በመጸለይ " ልቤን ለውጥው፣ ፍላጎቴ የአንተ ፈቃድ እንዲሆን አድርግ፣ እግሮቼን ወደ ክፋት እንዳይሄዱ ከልክል፣ ወደ ጽድቅ መልሰኝ" እንበለው።

እምነት የሚጠቁመው ወደ ጌታ የሱስ እንጂ ወደ ጸሎት መልስ መሆን የለበትም። ደህንነታችንን የሰጠን ጌታ የሱስ ብቻ ስለሆነ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ እርሱ ብቻ ነው። መቼም በድርጊት ለምንመራ በተለይም የምዕራባውያን አመለካከት አመለካከታችንን ለቀረጸው ለብዙዎቻችን ይህ አሳብ ከበድ ይላል።

የተባልነው፣ የተነገረን፣ የተማርነው "ድርጊትህ ይተረጉምሃል" (you are what you do) የሚል ነው። በእርግጥ አምላካችን የድርጊት አምላክ ነው። ነገር ግን ማተኮር ያለብን በእርሱ ላይ ነው እንጂ በድርጊቱ ላይ ብቻ መሆን የለበትም። የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ክርስቶስ ሲናገር

*"የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ" ዕብ. 12፥2* ይለዋል።

እርሱ የእምነት መጀመሪያና መጨረሻ፣ መነሻና መድረሻ፣ ሥርና ጫፍ፣ ፍጹም አድራጊ ነው። ስለዚህ አይናችን በእርሱ ላይ መተከል አለበት እንጂ እንዲያደርግልን በምንፈልገው ነገር ላይ መሆን የለበትም። ሙሉ ትኩረቴ እርሱ እንዲያደርግልኝ በምፈልገው ነገር ላይ ብቻ ከሆነ በቀላሉ መሳሳት እችላለሁ፣ ውጤቱም ሊያሳዝነኝም ላያረካኝም ይችላል። እውቀቴና ጥበቤ የተወሰነ ስለሆነ፣ የችግሬንም አይነት አሳስቼ ማየት እችላለሁ፣ መልስ ያልሆነውም መልስ መስሎ ሊታየኝ ይችላል። ጌታ ሊያደርግልኝ ይገባል ብዬ የጠበቅሁት ነገር ልቤን ከሰረቀው ትኩረቴ መሆን የማይገባው ቦታ ላይ ነው ያለው ማለት ነው። እምነቴን ግን በእርሱ ላይ ካደረግሁ፤ ኃይሉን፣ ቸርነቱን፣ ምህረቱን፣ ቅድስናውን፣ ዕውቀቱን ጥበቡን፣ ብልጽግናውን ካሰላሰልኩ፣ አሁን ትኩረቴ መሆን የሚገባው ቦታ ላይ አደረግሁ ማለት ነው። ዳዊት ይህንን የተረዳ ይመስላል እንዲህ ሲል፣

> *"አለቴና መድኃኒቴ እርሱ ነው፣ መጠጊያዬም እርሱ ነው፣ ከቶም አልናወጥም" መዝሙር 62፥2።*

ዳዊት ሰባ አምስት በመቶ በሚያክለው የመዝሙሩ ክፍል እግዚአብሔርን ስለጠላቶቹ ያስታወሰበት ነው ይላሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች። ጌታ በጠላቶቹ ላይ እንዲያግዘው የጠየቀበት ነው። ነገር ግን የዳዊት ዋና ተስፋ ራሱ እግዚአብሔር እንደነበረ ግልጽ ነው፤ እየደጋገመ እግዚአብሔርን "አንተ ብርታቴ ነህ' ይለው ነበር።

በጌታ ላይ ካተኮራችሁ ጨርሶ አትሰቱም፣ አትሳሳቱም። በእርሱ ላይ የሚያተኩር እምነት እርሱን እንዲያደርግ የሚያነሳሳ ብቻ ሳይሆን፣ ባያደርግም እንኳን እለማድረጉ ራሱ መንፈሳችሁን የሚያረካ ይሆናል። ጌታ ራሱ ከመልሶች ሁሉ በላይ ነው። ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ከሚደረግልን ነገር ሁሉ በላይ ውድና የከበረ ነው።

## 11. የቆራጥ ዘዴ

ይህን የቆራጥ ዘዴ በሕይወቱ ምሳሌነት ያስተማረን ኢዮብ ነው። ተስፋ ላለመቁረጥ መወሰን፣ ወይ ፍንክች ወይ ንቅንቅ የሚል ቆራጥ ውሳኔ ያስፈልጋል እንደ ኢዮብ፣

*"ቢገድለኝም እንኳን በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ" ኢዮብ 13፥15።* ማለት መቻል አለብን።

የታወቁት አየርላንዳዊው ወንጌል አገልጋይ ጆርጅ ማክዶላንድ እንዲህ ጻፉ፦

እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ጻድቅ ሰው፣ እምነቱ ፍጹም ነው። ሁኔታዎች ምንም አይነት አስቸጋሪ መልክ ቢኖራቸውም፣ እግዚአብሔር በፍቅርና በጽድቅ እንድፈጠረው ያምናል። እግዚአብሔር ለኢዮብ የደረሰበት ሁሉ ለምን እንደ ደረሰበት አልነገረውም፣ እምነቱ እንዳይዛባ ግን ልቡን ጠብቆለታል።

በጣም የቃተትንባቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ሳያገኙ የሚቀሩባቸው ጊዜያት አሉ። የምናደርገው ነገር ሁሉ መንፈሳዊውም ሆነ ሌላው በሁኔታችን ላይ ምንም ለውጥ ሳያመጣ የሚቀርበት ጊዜ፣ ሁኔታዎች ከቁጥጥራችን በላይ ብቻ ስይሆን ከአቅማችን በላይ ሲሆኑ፤ ሆኖም የሚቀጥለውን እርምጃ እንወስዳለን፤ የማይቻል





ቢመስልም፣ ተስፋ የሌለው ቢሆንም

*ምንም ነገር ሳይሠራ ቢቀር - እግዚአብሔር ዝም ሲል*
*የሌሎች እርዳታ ሳይኖር - ተስፋ ሞኝነት ሲመስል*
*በጣም ደክመህ - ዕረፍት ማግኘት ግን ሲያቅትህ*
*ነገር ሲዘበራረቅ - ስትንገዳገድ ለመውደቅ*
*አይዞህ ቁም!*
*በርታ!*
*ብድግ ብለህ ቁም!*
*ከፍ ብለህ ቁም ...*
*... አምን ቁም!*

ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሰዎች፥

*"ሁሉን ከፈጸማችሁ በኋላ ጸንታችሁ መቆም..." ኤፌ 6፥13 ይላቸዋል።*

መቆም በራሱ ስኬት ነው። ሲገፉ እምቢ ማለት ቦታን አለመልቀቅ የአሸናፊ ጸባይ ነው። ለጊዜው ወደፊት መራመድ አንችል ይሆናል፣ ምናልባትም በቆምንበት እንንገዳገድ ይሆናል። ነገር ግን እምቢ አልወድቅም፣ ወደ ኋላ አልመለስም ማለት የደፋር አቋም ነው። የቆራጥ ዘዴ ይህ ነው፣ ይሠራል ምክንያቱም እግዚአብሔር ከበስተኋላው ነው።

## በአጭሩ

እምነታችንን ለመሳደግ የሚረዱ በርካታ ዘዴዎችን በዚህ ምዕራፍ አየን። የሚሠራው ግን ዘዴው ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን እንደገና ባሳስባችሁ ደስ ይለኛል። የምናምነው እምነታችንን ሳይሆን፣ እምነታችን እንዲሠራ የሚያደርገውን እግዚአብሔርን ነው። ሆኖም እነዚህ ዘዴዎች ከእግዚአብሔር ቃል የወጡ ናቸው። በታላቁ እግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ለማጎልመስ በጣም ጠቃሚ ዘዴዎች ሆነው ታገኟቸዋላችሁ። ቀጥሎ ወደ ሶስተኛው የመጽሐፉ ክፍል እንገባለን። ለእምነታችን ጠንቅ የሆኑትን ዘመናዊ እንቅፋቶችን በዚህ ክፍል እናያለን።





# ክፍል ሶስት
# የእምነት እንቅፋቶች

አሁን ደግሞ እምነትን ለየት ካለ አቅጣጫ ወይም ለወጥ ባለ ርዕዮት (perspective) እንየው፤ እምነት ጠላት አለው። ስለዚህ ውጊያ አለበት። እንግዲህ ጊዜው መሣሪያችንን የምናነሳበት፣ አካኪ ዘራፍ ብለን የምንታጠቅበት፣ ጊዜ ነው። ምክንያቱም እምነታችንን እንደ አደገኛ ነገር የሚመለከቱ ኃይላት በአለም ወስጥ እየሠሩ ናቸው። ከእነኚህ አንዳንዶቹ ባሕላዊና ማኅበራዊ ናቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ግላዊ ናቸው፤ የአንዳንዶቹ መነሻ ከነፍሳችን ጠላት ከሆነው ከሰይጣን ነው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ከተሳሳተ ትምህርት የሚመነጩ ናቸው። ያንን ትምህርት ከቤተ ክርስቲያንም አግኝተነው ሊሆን ይችላል። እነኚህ ተዋጊዎች ሁሉ እምነታችንን ለማሳነስ፣ ወይም በእምነታችን የተሳካ ውጤት እንዳናገኝበት ለማደናቀፍ ይሠራሉ። ስለዚህ እነኚህን ሁኔታዎች ለመመርመር የታጠቅን መሆን አለብን። በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት አሳቦች አንዳንዶቹ ከበድ ያሉ የአዕምሮ ነገር ወይም በትምህርት ብቻ የተገኙ ሊመስሏችሁ ይችላሉ። ግን ተስፋ ቆርጣችሁ አታቁሙ። ሥጋ ሥጋውን እየበላችሁ አጥንቱን ወደ ዳር አስቀምጡትና እለፉ። ምን ይታወቃል ክፍሉን ከመጨረሳችሁ በፊት አጥንቱ ራሱ ሥጋ ይሆን ይሆናል፤ ያውም ሙክክ ብሎ የበሰለ። የእምነት ጉዳይ እኮ ፈርጁ ብዙ ነው።

# ምዕራፍ አምስት

## ባሕልና ርዕዮት

የአማርኛ ቃላት ሲያጥረኝ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ረዳት መጋቢ ፓስተር አለማየሁ ደምሴ ዘንድ ሄጄ ትርጉም እጠይቀዋለሁ። እርሱ አዳዲስ ቃላት ሲያገኝ ከነ ትርጉማቸው የሚይዝበት ማስታወሻ ደብተር አለው። ርዕዮት ከእርሱ ካገኘኋቸው ብዙ ቃላት አንዱ ነው። perspective የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ትርጉም ነው። ርዕዮት አመለካከት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊሆን የምንፈልገውንና የምናቅደውን የምናይበት የአስተሳሰባችን አቀራረጽ ነው።፣

እውነት የሚቀርብበት ማህደር ወይም ዐውድ (context) አለው። በሌላ አነጋገር እውነት መፈክር ብቻ ከሆነ ኃይሉን የሚገልጽበት ዐውድ አላገኘም ። "ኢየሱስ ጌታ ነው" ማለት እውነት ነው። ግን እየሱስ ጌታ የመሆኑን እውነት በግል ሕይወታችን ካልገለጽነው፣ በቤተሰብና በመኅበረሰብ ተቋሞች ካልኖርነው፤ ከዚያም አንኳን አልፎ በኢኮኖሚው በፖለቲካው፣ በሶሺያልና በሳይኮሎጂካል ዐውድ ካላቀረብነው ትርጉም የለውም፤ "ተፈጥሮን እናሸንፋለን" ይባል ከነበረው ባዶ መፈክር የተሻለ አይሆንም። ግን እውነትነቱ አይለወጥም።

ዐውድ (context) ሊለዋወጥ ይችላል። ምክንያቱም ተጨባጭ ነው ያልነው ነገር (reality) ነውጥ (dynamic) አለው። ስለዚህ እውነት ራሱ ባይለወጥም፣ ተግባራዊነቱ ይለዋወጣል። ለዚህ ነው ከትምህርት ቤት ጨርሰን ከወጣን በኋላ እንኳን ወደኋላ እንዳንቀር ማንበብ ያለብን፣ ለዚህ ነው ለዘመኑ የሚሆኑ አዳዲስ መጻሕፍት መጻፍ ያለባቸው። ባሕል ደግሞ እውነት ከተያዘባቸው ማሕደሮች አንዱ ነው። ለዚህ ነው አባት ለልጁ "በእንተ እድሜ በነበርኩባት ጊዜ..." ማለቱ የማያበቃው፤ ምክንያቱም በመካከሉ ታላላቅ የሆኑ ባሕላዊ ለውጦች ተከስተዋል።

ልጁ መልሶ አባቱን "የእኔን እድሜ ሆነህ አታውቅም" ቢለው ብዙ የተሳሳተ አይሆንም፤ ምክንያቱም አሁን ልጁ በቆመበት ጫማ ውስጥ አባቱ ቆሞ አያውቅም። ይህ ደግሞ ከማንም የበለጠ በዲያስፖራ ትውልድ ጉልህ ሆኖ ይታያል።

በእያንዳንዱ ትውልድ የሰውን አዕምሮ ለመያዝ የሚሻሙ የኃይሎች ውጊያ አለ። ሰዎች ስለሚያስቡት ወይም ስለማያስቡት፣ ስለሚያምኑት ወይም ስለማያምኑት ለመወሰን ብዙ ሽሚያ አላቸው፣ በተለይ ከእምነት አንጻር በዘመናችን አስፈላጊ የሆኑትን አንዳንድ ባሕላዊ ሁኔታዎችን በዚህ ምዕራፍ እናያለን። በዚህ ቦታ የምናቀርባቸውን አንዳንዶቹን አሳቦች ለመያዝ ትንሽ ማሰላሰልን ይጠይቃሉ። የሚከተሉትን ሰባት አሳቦች አጥርቶ ማጤን ለብዙ መረዳቶች በር ከፋች ይሆናል።

## 1. ሉአላዊ አመለካከት (Worldview)

ባሕላዊ ሁኔታዎችን በምንገመግምበት ጊዜ ሉአላዊ አመለካከት ትልቅ ሚና ይጫወታል። ሉአላዊ አመለካከትን ብዙ ምሁራን ሲተረጉሙት ሰዎች አለምን እንዴት እንደሚያዩትና አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሚያዩትን የሚተረጉሙበት መላ ወይም ግምት ነው። ሰዎች ይህንን አመለካከታቸውን ለማጥራት የሚጠቀሙበት ወንፊት የተለያየ ነው። ባህላዊ የሆነ ነውጥ ሲንቀሳቀስ በተለይ በኢንተርናሽናል ዲፕሎማሲ በፖለቲካ፣ ንግድ፣ ሃይማኖት፣ የጦር ትብብርና የትምህርት ልውውጥን በሚመለከት፣ በዘር ልዩነት፣ ሌላው ቀርቶ በወንድና በሴት አለመግባባት ሉአላዊ አመለካከት ትልቅ ቦታ አለው። ብዙ ጠበብቶች ግኑኝነት እየተስፋፋ ሲሄድ፣ ሰዎች ከተወለዱበትና ከአደጉበት አካባቢ ወደ ሌላ እየሄዱ መኖር ሲቀጥሉ ሉአላዊ አመለካከት እየተቀራረበ ይመጣል የሚል ተስፋ አላቸው። እንደ አሜሪካ ያሉ ብዙ የውጪ ዜጎችን የሚቀበሉ አገሮችም ሉአላዊ አመለካከታቸው ቶሎ ቶሎ ይለወጣል ይላሉ።

ዛሬ ተቀባይነት ያለው ሉአላዊ አመለካከት ከአውሮፓውያን ያስተሳሰብ ሂደት የተወረሰ ምላ ምትን (assumption) ወደ ምክንያታዊነት (rationalisem) በመለወጥ ላይ የተመሠረተ ነው። ታዋቂው ፈላስፋ ሬኔ ዴስካርቴስ "አስባለሁ ስለዚህ እኔም ነኝ" (I think therefore I am) የሚል ብዙ ተቀባይነት ያለው አባባል አወጡ። የአባባሉ ይዘት በቀላሉ ሲተረጎም ርዕዮቱ እኔ ራሴ በማስበው አሳብ የተመሠረተ ነው እንደ ማለት ነው። ይህ አመለካከት ታዲያ እውቀትን (intellect) በምእራባውያን አስተሳሰብ ሚዛናዊ ያልሆነ ከፍተኛ ቦታ ሰጠው። ከአስራ ስምንተኛው ምዕተ አመት ጀምሮ





ይህ አመለካከት ሳይገታና ሳይታረም እስከዛሬ ድረስ እንዳለ ነው። ይህ አመለካከት የሰውን መንፈስ ዝቅ ያለና ባይተዋር አደረገው። ስለዚህ በደመ ነፍስ የማወቅ ችሎታ (intuition) ምናብ(imagination) እና የመንፈስ ንቃት (conscience) በአስተሳሰብ ሂደት ውስጥ ከግምት የማይገቡ ሆኑ። ይህ አስተሳሰብ እያደገ መጥቶ አብርሆት (Enlightenment) ተብሎ ተሰየመ። አብርሆት በዚህ መልኩ ሲታይ አራት ክፍሎች ብቻ ነው ያሉት፦ ምክንያታዊነት (rationalism) መማር(learning) መጠራጠር (Skepticism) የሳይንስ ህግ (Empiricism)። በእነኚህ ያልተደገፈ አስተሳሰብ ተቀባይነት የለውም። እነዚህን ሀነች ዘርዝር አድርገን እንተርጉማቸው።

ሀ. ምክንያታዊነት፦ አንድን አሳብ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ዋናው ወሳኙ ምክንያት ብቻ እንደሆነ አድርገን የምንከተለው መንገድ፣ ወይም የምናደርገው ልምምድ።

ለ. መማር፦ እውቀትንና ብልሃትን መቅሰም፣ መሰብሰብ።

ሐ. መጠራጠር፦ እውነት ነው ተብሎ የሚቀርብ ነገር ሁሉ መጠየቅ አለበት። እንዳውም ያንን እውነት በመጠራጠር የምናመጣቸው ጥያቄዎች ለአመለካከታችን ወሳኝነት አላቸው።

መ. የሳይንስ ህግ፦ እውቀትን ለመፈለግ የምንከተላቸው መንገዶች፣ ለምሳሌ መመልከት (observation), ሙከራ (experimentation)፣ በእንኚህ መንገዶች የተገኘ ግኝት ብቻ ነው ተቀባይት ያለው ብሎ ማመን ነው።

የአብርሆት መልካምነቱ ይህንን ዘዴ በመከተል አለማችንን ለማሻሻል በጣም ብዙ ነገሮች ተፈልስፈዋል። ዘመናዊ ህክምና፣ የግንኙነት ግኝቶች ከቴሌፎን እስከ ቴሌቪዥን እስከ ኢንተርኔት፤ ሜካኒካል የሆኑ ቁሳቁሶች፤ የአመራርና የአስተዳደር ዘዴዎችን እንኳን ሳይቀሩ ያሻሻሉ ብዙ ግኝቶች የዚህ መንገድ ውጤቶች ናቸው። አብርሆት ባይኖር ኖሮ አለም ከዚህ የባሰ የችግርና የረሀብ ቦታ ትሆን ነበር። ሆኖም ይህ መንገድ መልካም ያልሆኑ ውጤቶችንም በአለማችን ትቷል።

እስቲ በአሳባችሁ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መስመር እንዳለ ተመልከቱ።

## እግዚአብሔር

## የሰው ዘር

አብርሆት የሚለው እንዲህ ነው። እግዚአብሔር ካለ ሳይንሳዊና ምክንያታዊ መንገዶችን በመጠቀም፣ የመጠራጠርን ጥያቄዎች አልፎ በትምህርት ብዛት መገኘት አለበት። በሌላ አነጋገር ሰው በራሱ ችሎታና ጥበብ፣ በራሱ ምርምርና ፍለጋ ያንን መካከል ላይ ያለውን ግድግዳ ተሻግሮ እግዚአብሔርን ማግኘት አለበት። ይህ መንገድ ሌሎች አማልክትን ለመገናኘት መጠቀሚያ መንገድ ሊሆን ይችላል። ከእውነተኛው አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ግን ያንን በመካከል ያለውን ግድግዳ ማለፍ ካልቻለ አብርሆት (Enlightenment) የሚለው "ግድግዳውም የለም፣ ስለዚህ እግዚአብሔርም የለም" ነው።
አብርሆት ሊደርስበት የሚችለው የመጨረሻው የበሰለና ከፍተኛ መልስ ይሄ ነው። ለምሳሌ አንድን ቁስ (matter) በሁለት አቅጣጫ (Two Dimension) ማየት እንችላለን። ያንኑ ቁስ በሶስት አቅጣጫ (3-D) አሁን ደግሞ በተሻሻለው በአራት አቅጣጫ (4-D) ማየት እንችላለን።

በአራተኛው አቅጣጫ የምናየውን እንዳንዱን የቁሱን ክፍል በሁለት ወይም በሶስት አቅጣጫ እንኳን ለማየት፣ መኖሩን እንኳን ማወቅ አንችልም። መንፈሳዊ አቅጣጫ Spritual Dimension) ደግሞ ከዚህ የተለየና የመጠቀ ነው። በሁለት ወይም በሶስት ወይም በአራት አቅጣጫ በምናገኘው እውቀት ብቻ ልንረዳው አንችልም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ግን (ከሉአላዊ አመለካከት ጋር ሲነጻጸር) ያንን ግደግዳ አልፎ መሔድ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው ይላል። ያንን ግድግዳ አልፎ የመምጣቱ ክስተት መገለጥ (Revelation) ይባላል። ስለ እግዚአብሔር የምናውቀው ነገር ሁሉ እርሱ ራሱን ለእኛ ስለገለጠልን ብቻ ነው። ስለ እርሱ ያለን እውቀት በሙሉ፣ ከተፈጥሮ ቢሆን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት፣





ከእርሱ ጋር ባለን የጥሞና ጊዜ፣ በምንም መንገድ ስለ እርሱ ላለን እውቀት መነሻው እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ዘር በአጠቃላይ መንገድ ራሱን ገልጿል። ይህን ራሱን የገለጸውን እግዚአብሔርን የማወቅ ችሎታ ደግሞ በግል ለእያንዳንዳችን የተሰጠን ስጦታ ነው። ከብዙ ዘመን በፊት ለኢሳይያስ የተገለጠ እውነት አለ፣ እኔ ደግሞ የዚያ እውነት ተጠቃሚ እንድሆን ዛሬም ለእኔ መገለጥ አለበት። በተጨማሪም በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት እንዳየነው፣ እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጸው ለአዕምሯችን (የንቃተ ህሊና መቀመጫ) ሳይሆን ለመንፈሳችን ነው ከእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ሁሉ መቀበል የሚችለው የእኛነታችን ክፍል መንፈሳችን መሆኑን አይተናል። የሰው ምርምርና ጥናት ምንም የመጠቀና የጠለቀ ቢሆን፤ በራሱ እግዚአብሔርን ማግኘት አይችልም።

ምክንያታዊ ብቻ ለሆነ ሰው (Rationalist) መንፈስ ቅዱስም ሆነ የሰው መንፈስ የሚባል ነገር የለም። ምክንያቱም በሳይንስ መንገድም ሆነ በምክንያታዊ መንገድ ሊረጋገጡ አይችሉም። ይህ ግን ብዙ የሚናገረው ስለእውነተኛ ነገር (reality) ሳይሆን ስል ምክንያታዊነት (rationalism) ነው። የምክንያታዊ ሰው አስተሳሰብ እርሱ ራሱ ሳያስበው ነው የሚሠራው፤ ምክንያታዊ ሰው በሕይወቱ ላይ ተፅእኖ ስላላቸው ኃይሎች የሚያውቀው በጣም ትንሽ ነው፤ እርሱ ሊረዳው ያልቻለ ለየት ያለ አመለካከት ካጋጠመው፣ የሚገባውን ትኩረት እንኳን ሳይሰጠው እንደ ተረት ያየዋል ወይም ያረጀ ያፈጀ ፈሊጥ ብሎ ይጥለዋል። ስለዚህ መንፈሳዊው ክፍል ምናብንና (Imagimation) በደመ ነፍስ የማወቅ ችሎታን ጨምሮ (Intuition) በምክንያታዊው ሰው ዘንድ ጥቅም የሌለው ይሆናል። ለዚህ ነው የምዕራባውያን አመለካከት ለምሥራቁ (ለቡዲስትና ሂንዱ) እንዲሁም ለእስላሞችና ለሶስተኛው አለም ክርስቲያኖች እንኳን ባዶ የሚሆንባቸው። የእነኚህ ባሕሎችና ሕዝቦች አመለካከት ለመንፈስ ቦታ ይሰጣል። በእነኚህ ባህሎች መንፈስ፣ እርግማን፣ መለዕክት፣ አጋንንት፣ ምትሃት፣ እና የመሳሰሉት ገለጣዎች ቦታ አላቸው። አተረጓጎሙ የየግሉ ቢሆንም፣ አንዳንዶቹ ከክፉ መናፍስት ጋር መጎዳኘትና አብሮ መስራት የሚያዋጣ ቢመስላቸውም፣ ከክፋታቸው ደግነትን የሚያገኙ መስሎ

ቢታያቸውም፣ ህልውናቸውን ግን ያምናሉ። ለእነኚህ ባሕሎች የምዕራቡ ባሕል ባዶና ርካሽ ሲሆንባቸው፣ ለምዕራቡ ደግሞ የእነኚህ ባሕል ኋላ ቀርነትና የድንቁርና ምልክት ይሆንባቸዋል። ልዩነቱን ለማጥበብ እንኳን አይቻልም፤ የዕውቀትን ባለ ሀቅነትን ማመቻመች (compromising intellectual integrity) ይሆንባቸዋል።

## 2. ርዕዮትና እምነት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተደረጉ ድርጊቶች ለመቀበል የሚያስቸግራችሁ አለ? ለምሳሌአንዳንድተአምራትወይምክስተቶችበእርግጥመሆናቸውያጠራጥራችኋል? ያ ከሆነ ምናልባት ከምታስቡት በላይ በአብርሆት (Enlightenment) ርዕዮታችሁን እየተጫነው ነው። በተለይ በምዕራቡ ባሕል ብዙ ለቆየን ሳይታወቀን ነው እየተለወጥን ያለነው። ብዙዎቹ ለመቀበል የሚያስቸግሩን በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጹ ድርጊቶች ከተፈጥሮ መንገድ ውጪ የተከሰቱትና እኛ ተአምራዊ ብለን የምንጠራቸውም ናቸው። ያ ማለትም የአብርሆት ሰዎች አጥብቀውና ተደራጅተው የሚያጸኑትን ብቻ መቀበል ማለት ነው። ለምሳሌ ጸሎት በብዙ ምዕራባውያን ዘንድ ክርስቲያኖች እንኳን ሳይቀሩ ለበሽታ መፍትሔ ያመጣል ብለው መቀበል ያልተለመደ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ ባለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ለበሽተኛ መጸለይ የሚታይ ልምምድ እየሆነ መጣ እንጂ ከአርባአና ከአምሳ አመት በፊት በወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያኖች እንኳን ለበሽተኛ መጸለይ የተለመደ ነገር አልነበረም። የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ወደ አገራችን በገባበት ጊዜ ሲጸለይና አጋንንት ሲጮሁ ከምዕራብ የመጡ ሚሲዮናውያን ግራ ይገባቸው ነበር። ምክንያቱም የብዙዎቹ አስተሳሰብ ሕክምና ካላዳነው ተስፋ የለውም የሚል ነበር። የእምነት ጸሎት አንዳንዴ ቢሞከርም እንኳን፣ ዋናውና የመጀመሪያው ልምምዳቸው ሳይሆን በሌላው ነገር ሁሉ ተስፋ ከቆረጡ በኋላ የሚደረግ ሙከራ ብቻ ነበር።

እውነተኛ ፈውስና ተአምር በሶስተኛው አለም ክርስቲያኖች ዘንድ የሚሰጠው ትልቅ ግምት በምዕራቡ አይሰጠውም። በእርግጥ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ከ 1980ዎቹ ጀምሮ ለቴሌቪዥን ተመልካች የሚሆኑ የፈውስ ፕሮግራሞች በዝተዋል። እዚህ ላይ የምጠቅሰው ይህንን አዲሱን ልምምድ ሳይሆን ባሕላዊ ቅርስን ነው። መሠረታዊ





ነጥባችንን እንደገና ለስታውሳችሁ፤ መታዘዝ መረዳትን ይቀድማል። በፈቃድ የሆነ መታዘዝ፣ በእውቀት የተገኘ መረዳትን ይቀድማል። እግዚአብሔር በእውቀት የተገኘ መረዳትን አይወድም ማለቴ አይደለም፤ ግን መረዳት የእምነት ውጤት ነው እንጂ የእምነት ምክንያት ሊሆን አይችልም።

ርዕዮታችን በመንፈስ አለም የሚሆነውን ነገር ተቀባይ ካልሆነ የእምነታችን ጠላት ነው። እንደገና ገለጽ ባለ መንገድ ላስቀምጠው፤ በሁሉ ነገር ላይ እርግጠኛ ካልሆንን ብለን ከጠበቅን፣ ወይም የተጨበጠ መረጃ የሌለው ነገር እግዚአብሔርን የመታዘዝ እርምጃ ከመውሰድ የሚከለክለን ከሆነ፣ አመለካከታችን የእምነታችን ጠላት ነው። እውቃለሁ ይህ አባባል በጣም አጠቃላይ የሆነና አላፊነት የጎደለው አባባል ይመስላል። ታዲያ ይህ ከሆነማ ሰው ሁሉ በስሜቱ የተሰማውን ብቻ ያድርግ ማለት ይመስላል፣ አይደለም! ያም የእምነት መንገድ አይሆንም። እርግጠኛ ለመሆን እምነት የሚጠይቃቸውን ነጥቦች ማስታወስ ይጠይቃል።

> *"ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት" ዕብራውያን 11፥6።*

ጥቅሱ "ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩን … ማረጋገጥ" አይደለም የሚለው፣ ወይም "መኖሩን … በማያጠያይቅ ጥናት መደገፍ" አይልም። "መኖሩን . . . ማመን" ነው የሚለው። እንዲያውም የጥቅሱ መንፈስ እርግጠኛነትን መፈለግ እግዚአብሔርን እንደማያስደስተው ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔርን የሚያስደስተው እምነት ነው ይላል። ታዲያ ታያላችሁ በጣም የበሰለ፣ በአላፊነት የተሞላና ምጥቅና ጥልቅ የሆነ የሚመስለው የምዕራባውያን አመለካከት ሳይታወቅ የእምነት ጠላት እንዳሆነ?

ለአንዳንድ አንባቢዎች ይህ የማይዋጥ መዘላበድ እንደሚሆንባቸው እርግጠኛ ነኝ። አንዳንዶቻችሁም ደህና ጀምሮ ነበር አሁን ግን መዘባርረቅ ውስጥ ገባ ትሉኝ ይሆናል። ግን ግዴላችሁም ለጥቂት ጊዜ እንቻቻል። በዮሐንስ ምዕራፍ 6 ውስጥ ሰዎች ጌታ የሱስ የነበራቸውን አመለካከት ሲያዘበራርቅባቸው እንደዚያ ገምተውት

ነበር። እንዲያውም ሰው በላነትን (Cannibalism) ተለማመዱ ያላቸው ነበር የመሰላቸው። እርሱ ግን ለየት ባለ መንገድ ይላቸው የነበረው እርግጠኛ መሆንን ከመፈለግ ይልቅ እመኑ፤

*"መንፈስ ሕይወትን ይሰጣል፤ ሥጋ ግን ምንም አይጠቅምም" ዮሐንስ 6፥61-63።*

ጌታ የሱስ ሥርዓትና ወጋቸውን በመጣስ እንደሚያስቆጣቸው በደንብ ያውቅ ነበር። በሌላ መንገድ ደግሞ መልስ የሚያገኙት በእምነት ብቻ እንጂ በገለጻ አለመሆኑንም ያውቃል። ከላይ ያየነው ጥቅስ ዝቅ ብሎ

*"ብዙዎቹ ወደ ኋላ ተመለሱ፤ አልተከተሉትም" ቁጥር 66 ይላል።*

እርሱን መከተል ትተው ሲሄዱ ዝም አላቸው ማለት ነው። የተቆጡበትን የአመለካከት ነገር አስተካክሎ ተከታዮቹ ሊያደርጋቸው አልፈለገም፤ በዚያ አይነት መንገድ ተከታዮቹ ከሚሆኑ በእምነት ቢከተሉት ይወዳል። በጌታ አመለካከት መታዘዝ ከመረዳት ይቀድማል። ታዲያ ከማመናችን በፊት መረዳት ብንፈልግ ጌታ ለዕውቀታችን ይተወናል። ይህንኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እስቲ አሁንም ዝቅ ብለን እንየው። እንኚያ ትምህርቱ ያስቆጣቸው ትተውት ከሄዱ በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፣

*"እናንተም ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ? አላቸው" ቁጥር 67 ይላል።*

ደቀ መዛሙርቱን እንዲሄዱ ከተዋቸው ለእኛ የተለየ የሚያደርግ ይመስላችኋል? ጴጥሮስ የመለሰው መልስ ብዙ ቁም ነገር አለው። ተመልሰው መሄድ እንኳን ቢፈልጉ የተሻለ ምርጫ እንደማይሆንላቸው ነው የገለጸው፤

*"ጌታ ሆይ ወደማን እንሄዳለን? አንተ የዘለአለም ሕይወት ቃል አለህ፤ አንተ አንድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆንህ አምነናል አውቀንማል" ቁጥር 68-69።*

የሁለቱን የመጨረሻ ቃላት የአቀማመጣቸውን ቅደም ተከተል አስተውሉ፤





*"አምነናል አውቀንማል"* ። ጌታ ግን አሁንም በእነርሱ መተማመን እንደጎደለው ነው የሚነግራቸው፤

*ቁጥር 70 "አስራ ሁለታችሁን የመረጥኋችሁ እኔ አይደለሁምን? ነገር ግን ከእናንተ አንዱ ዲያቢሎስ ነው"*

ይህ ተግሳጽ እንጂ መተማመንን የሚያሳይ ንግግር አይደለም። በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ ማስታወስ ያለብን የመጀመሪያውን "የሰው በላሽነትን" ጥያቄ አልመለሰውም። "ሥጋውን መብላት አለባችሁ" የሚለው አባባል ያስነሳውን ጥያቄ አንጠንጥሎ ነው የተወው። ይህ አባባል ዛሬ እኛ በትርጉም ስለምንረዳው እንግዳ አባባል አይደለም። ለእነርሱ ግን

*"ይህ የሚያስጨንቅ ነው" ቁጥር 60 ነው ያሉት።*

ጌታ ትርጉሙን ያሳወቃቸው ቆይቶ በሌላ ጊዜ፣ በሌላ ቦታ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ግን የእምነትን ፈተና አለፉ። የሚለውን ባይረዱም፣ የሚለው ነገር ቢያስጨንቃቸውም፣ ሳይረዱ አመኑበት። ትምህርቱ እያስጨነቃቸውም ተከታይነታቸውን ቀጠሉ።

*"መንፈስ ሕይወትን ይሰጣል" ቁ. 63*

ስላላቸው፣ ያንን ተከትለው ባስጨነቃቸው ነገር ላይ እንኳን ሰላሙን እንደሚያበዛላቸው ተማምነው ራሳቸውን ሰጡት።

አመለካከታችን ከእግዚአብሔር ሊያርቀን ወይም ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን ይችላል። እምነታችን ግን እንድንከተለው ያስችለናል። እነኚህ ሁለቱ በሚጋጩበት ጊዜ ከእምነታችን ጋር እንተባበር።

## 3. የፍልስፍና ተጽእኖ

የሚቀጥለው ንጥብ አብርሆት (enlightment) ሉአላዊ አመለካከት (worldview) በባህላዊ ፍልስፍና ላይ ያስቀመጠውን አሳዛኝ ተጽእኖ የሚመለከት ነው። በምክንያታዊነት፣ በመማር በመጠራጠርና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ

ላይ የተመሠረተ አመለካከት ከአይሁዳዊ ክርስትና (Judial-Christian) አመለካከት ጋር ብዙ አብረው መጓዝ አይችሉም፣ ግጭት ይፈጠራል። የአብርሆት አመለካከት ነው ዛሬ ያለውን የህብረተሰብ ፍልስፍና ለመፍተል ድርና ማግ የሆነው። በምዕራብ (አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ) በ 18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክርስትና ሥነ መለኮት (theology) ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት በምክንያታዊነት መወገዝና መነቀፍ ጀመረ። አንድ ቦታ ላይ እነኚህ ሁለት ፍልስፍናዎች መንገድ ለዩ፣ ያልታወጀ ውጊያም ጀመሩ። ልዩነታቸው ከክርስትና አንጻር ሲታይ በጣም መሠረታዊ በሆነ ነገር ላይ ነው። የልዩነታቸው ስር እንዲህ የሚል ነው። የእውነተኛ ነገር (reality) መካከለኛ እግዚአብሔር ነው ወይም ሰው ነው፤ ሁለቱም ሊሆኑ አይችሉም ። የአይሁዳዊ-ክርስትና አመለካከት መካከለኛው እግዚአብሔር ነው ይላል፤ የሰብዓዊ ፍልስፍና (humanstic) ደግሞ መካከለኛው ሰው ነው ይላል።

የሰውነት ወይም የአካል ባለቤትነት ወይም ሰውነትን ማን መቆጣጠር አለበት የሚለው የፍልስፍና ግጭት ብዙ ግላዊና ባህላዊ የሆኑ ድርጊቶች ላይ ተጽእኖ አለው። ለምሳሌ ያህል እስቲ ራስን ስለመግደል እንይ።

በ1990ዎቹ አመታት ውስጥ በአሜሪካ አገር በየጊዜው በዜና ማሠራጫ ላይ የሚወጡ አንድ የሕክምና ደክተር ነበሩ። ስማቸው ዶክተር ጃክ ኬቮርኪያን ይባላል። በዚያን ጊዜ አሜሪካ ውስጥ የነበራችሁ ብዙዎቻችሁ የኒህ ሰው ስም ትዝ የሚላችሁ ይመስለኛል። ኮቮርኪያን የታወቁት ሕመምተኛ በበሽታ ከመሰቃየት ራሳችንን መግደል እንፈልጋለን ካሉ ራሳቸውን እንዲገድሉ በመርዳት ነው። በዚህም የሚሰነዘርባችውን ነቀፋ ሁሉ እየተሟገቱ ይከላከላሉ፤ እስር ቤት እስከመውረድም ደርሰዋል። “ሰዎች መሰቃየት ካልፈለጉ ያለመሰቃየት መብት አላቸው” ይላል የሰብዓዊ ፍልስፍና፣ “የራሴ ሰውነት የራሴ ነው፣ በዚያ ላይ ማንም ሥልጣን የለውም፣ ራሴን መግደል ብፈልግ ማንም ሊከለክለኝ አይገባም” የሚል ነው የፍልስፍናው መካከለኛ ክርክር፤ በእርግጥ ደግሞ በሰው ላይ ላተኮረ ፍልስፍና ይህ ክርክር ትርጉም ይሰጣል። በእግዚአብሔር ላይ ላተኮረ ፍልስፍና ግን የሕይወት ባለቤት እግዚአብሔር ነው።

*“ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣ አለምና በውስጧ የሚኖረው ሁሉ*





*የእግዚአብሔር ነው” መዝሙር 24፥1።*

በሌላ ቦታ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች እንዲህ ብሎ ጽፏል፣

*“እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም፣ በዋጋ ተገዝታችኋልና” 1 ቆሮንቶስ 6፥ 19-20።*

መቼ እንደምንሞት የእግዚአብሔር ውሳኔ ነው።ስቃይም እንኳን ቢኖርበት፣ የራሳችንን ሕይወት ለመፈጸም ውሳኔው የእኛ አይደለም። ይህ የክርስቲያናዊው ፍልስፍና አመለካከት ነው። ከዚያም በላይ ክርስትና የሚለው የሕይወታችን ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑ ለእኛ የተሻለ ነው፣ ትርፍ አለው። ያ ትርፍ አሁን የሚታይ ይሁን ወይም ዘለአለማዊ ይዘት ይኑረው እናውቅ ይሆናል። ነገር ግን ሞታችንና የአሟሟታችን ሁኔታ ለእግዚአብሔር የተተወ መሆን ይገባዋል። ይህ አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፤ ለግልም ለህብረተሰቡም ጥሩ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ደግሞ ሕብረተሰቡን ያጎላል።

ሰብዓዊነት (humanism) በሰው ላይ ማተኮሩ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ጠበብ ብሎ በግለኝነት ላይ ያተኮረ ነው። ይህም ማለት የግል መብት ከህብረተሰቡ መብት የቀደመ ነው። በምዕራብ አስተሳሰብ ላደገ ይህ አመለካከት ትርጉም መስጠት ብቻ ሳይሆን ህጋዊ መብትም ነው። ለዚህ ነው በምዕራብ ኅብረተሰቦች ብቸኝነት ( privacy) በመመለክ ደረጃ የሚከበረው። በእስያ፣ በአፍሪካና በደቡብ አሜሪካ እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ ኅብረተሰቦች የቤተሰብ፣ የቤተዘመድ፣ የኅብረተሰብ ጉዳይ ቀዳሚ ነው። ሚስስ ክሌንተን (የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዜዳንት ቢል ክሌንተን ባለቤት) ቀዳሚ እመቤት (First Lady) በነበሩበት ጊዜ የልጆች ጉዳይ ከሚያራምዱት አጀንዳ አንዱ ነበር። በዚህ ነገር ላይ ንግግር ሲያደርጉ “ልጅን ማሳደግ የመንደሩ ሰው ሥራ ነው” ( It takes a village to raise a child) ብለው ተናገሩ። (በኋላም በሽያጭ ስኬታማ የሆነ መጽሐፍ Best seller Book) ወጣው) ። ይህ አባባል በሌሎች ኅብረተሰቦች ለምሳሌ በአፍሪካ ቢሆን የታዋቀ ከመሆኑ የተነሳ እንደ አባባል እንኳን አይቆጠርም ነበር። በአሜሪካ አገር ግን እንደ አዲስ ስር ነቀል አሳብ ተቆጥሮ ብዙ የሚዲያው መነጋገሪያ አሳብ

ሆኖ ከረመ። ወንጀልን በሚመለከት የምንሰማው አንዳንድ የፍርድ ቤት ጉዳይ በተለይ ለእኛ በሌላ ባህል እድገን ለመጣን አልገባ የሚለን ለዚህ ነው። ስክሮ ራሱን የጎዳ ሰው የጠጣበትን መጠጥ ቤትና መጠጡን የሰራውን ፋብሪካ መክሰስ ይችላል፤ መክሰስ ብቻ ሳይሆን ለጉዳታቸው ብዙ የካሳ ገንዘብ ያገኙም አሉ። ከአመታት በፊት ማክዶላንድ ከተባለው ታዋቂ ምግብ ቤት ትኩስ ቡና ገዝታ እቃውን በጭኗ መካከል ይዛ መኪና ስትነዳ ‘የሸጡልኝ ቡና ለበለበኝ’ ብላ ካሳ የተፈረደላት ሴት ትዝ ትላችኋለች? ከዚያም የተነሳ የማክዶላንድ ሰዎች ቡናቸውን ለብ ያለ ብቻ እንዲሆን አርገው ነበር በኋላ የገበያው ማነስ እንዲያስተካክሉ አደረጋቸው አንጂ። ታዲያ ይህ ሁሉ ሀተታ ከእምነት ጋር ምን ያገናኘዋል? አራት ነጥቦችን እስቲ እንመልከት።

<u>አንደኛ፤</u> እግዚአብሔር የእርሱን ፈቃድ የሚጻረርን ውሳኔ አይባርከውም። ምንም ውሳኔው የተደረገው በደግነት፣ በጥንቃቄና መልካም በሆነ ግምት ቢመስለንም፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚጻረር ከሆነ የሰው ደግነት ብቻ ትክክል ሊያደርገው አይችልም። ለምሳሌ በሽተኛ መሆኑን (pre-birth congenital deformity) ከመወለዱ በፊት ወላጆቹ አውቀው ሳያስወርዱ ወልደውት በሽተኛ ሆኖ እንዲኖር በማድረጋቸው ልጁ ከሶ ሁለት መቶ ሺዶላር የተፈረደለት ሰው አለ)። ይህ ፍርድ በደግነት፤ በጥንቃቄና መልካም ከሆነ ግምት የመነጨ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ግን አይባርከውም።

<u>ሁለተኛ፤</u> ሰብዓዊነት (humanism) በሞራል ከፍተኛውን ደረጃ እንደያዘ አድርጎ ነው ራሱን የሚያቀርበው። የተማሩ ቀልጣፋ ንግግር አዋቂዎች የሰብዓዊነትን ፍልስፍና ሲያስተላልፉ የክርስትናን ፍልስፍና የሚያዳላ፣ ጥበብ የጎደለው፣ ያረጀ፣ ኋላ ቀር፣ ቀዝቃዛ አድርገው ነው የሚያቀርቡት። በብዙ መንገድ ወደው አይደለም፤ ክርስቲያኖች የምንለካበት ልክ፣ የምንቀርብበት ደረጃ፣ የምናስተምርበት ሥልጣን የተለየ ነው። በእርግጥ እንዲረዱን እንፈልጋለን፣ ግን ያ የሚሆን ነገር አይደለም። ምክንያቱም እነርሱ የሚረዱት ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ እንዳየነው ከ 2-D እስከ 4-D ባለው መንገድ ነው። መንፈሳዊ አቅጣጫ (Spritual D) መኖሩን እንኳን አያውቁም። በሌላ አነጋገር ለመረዳት እውቀት ሳይሆን እምነት ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ እኛ ማድረግ የምንችለው የሰብዓዊነትን ግፊት በመቋቋም የእግዚአብሔርን





ሥራ ለማራመድ በእምነት መጠንከር ነው። ይህ ማለት ግን በክርስቲያኖችና ክርስቲያን ባልሆኑ መካከል ለመነጋገር ቦታ የለም ማለት አይደለም። ሰብዓዊነትና ክርስትናም በሁሉ ነገር አይስማሙም ማለትም አይደለም። እምነት ተሻግሮ ምክንያትን መድረስ ይችላል። እምነት ነውጣዊ (dynamic) ነው። ከልልንና ድንበርን መጣስ ይችላል። እምነትና ሎጂክ ብዙ ጊዜ አብረው ጉዞ ይጀምራሉ፣ ሎጂክ አልቆ ሲወድቅ እምነት ግን ይቀጥላል።

<u>ሶስተኛ፤</u> አማኞች አስቸጋሪ የሆኑትን የዘመኑን ችግሮች የሚፈቱበትን መላ ለማግኘት፣ እምነትንም በሥራ የሚገልጹበትን ዘዴ ለማወቅ ወደ እግዚአብሔር ቃልና ወደ መንፈስ ቅዱስ ምሪት መሄድ አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስም፣ መንፈስ ቅዱስም አስፈላጊዎች ናቸው። መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲም ተርጓሚም ነው።

ያለ መንፈስ ምሪት ሰው መጽሐፍ ቅዱስን የፍርድና የቁጣ ቃል ብቻ አድርጎ ነው የሚቀበለው። ያለ መንፈስ ቅዱስ እንኳን የብሉይ የአዲስ ኪዳን ቃል ገዳይ ነው።

*“እርሱም በፊደል ሳይሆን በመንፈስ ላይ የተመሠረተውን የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንድንሆን ብቁዎች አደረገን፤ ምክንያቱም ፊደል ይገድላል፣ መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል” 2 ቆሮንቶስ 3፥ 6።*

ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የፍርድ ወይም የሞት መጽሐፍ አድርገው ሲያቀርቡት ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ያ የሚመነጨው ቃሉን ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ አንብቦ ለመረዳት ከመሞከር የተነሳ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ካልተደገፈ መልእክትም ንግግርም ከእግዚአብሔር ነው ብሎ መቀበል ወደ ስህተት ሊመራ ይችላል፤

*“ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር መሆናቸውን መርምሩ” 1 ዮሐንስ 4፥ 1።*

በካሪዝማቲክ ክርስቲያኖች አካባቢ ይህ ስህተት ብዙ ይታያል፤ በመንፈስ ቅዱስ ያልተመረመረ ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ የመጣ የሚመስልን መልዕክት ለመቀበል ቶሎ እርምጃ ይወስዳሉ። መገለጥም ሆነ ትንቢት በእግዚአብሔር ቃል የተደገፈ መሆኑን ጊዜ ወስዶ መመርመር አለማመን አይደለም፣ ትጋትን ግን ይጠይቃል፣

ከብዙ ጥያቄና ችግርም ያወጣል።

<u>አራተኛ፣</u> "ሰብዓዊ ፍልስፍና ከእምነት ጋር አይስማማም በማለት ፍልስፍናን ሙሉ በሙሉ ለሰብዓውያን መተው የለብንም። ቤተ ክርስቲያንም የፍልስፍና ሰዎች ያስፈልጓታል። እምነታቸውን አጥርተው መናገር ብቻ ሳይሆን በተቀላጠፈ ሁኔታ ማስረዳት፣ ማሳመን የሚችሉ ሰዎች መነቃቃት አለባቸው ጳውሎስ ከአቴና ፈላስፋዎች ጋር የነበረው ልውውጥ ሙሉ በሙሉ በአዕምሮ ደረጃ ነበር። ግን በአዕምሮ ደረጃ ብቻ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርባቸው እንደማይችል ስለወቀ ነው ጳውሎስ የአዕምሮን ነገር ወስዶ ወደ መንፈሳዊነት ያዞረው (የሐዋርያት ሥራ 17)።

## 4. ሰኔና ሰኞ (Timing)

ሰኔና ሰኞ ገጠመ የሚል አባባል አለ በአገራችን። ፈረንጆቹ (Friday the 13th) የሚሉትን አይነት ነው። የጊዜንና የሁኔታን መገጣጠምን ለመግለጽ ይመስለኛል። በዚህ ክፍል ትንሽ ስለ ጊዜ እንመለከታለን። እምነትንና ባህልን ለመግለጽ ጊዜ ደግሞ ምን ቦታ አለው? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል፤ ጥሩ ጥያቄ ነው። ለጊዜ ያለን አመለካከት በጣም እየተለወጠ ነው።

ቤታችን ቁጭ ብለን ቴሌቪዥን ስናይ፣ በመንገድ ላይ መኪና እየነዳን ስንሄድ፣ ወይም ሱቅ ወይም ሬስቱራንት ሄደን ተራ ስንጠብቅ መጠበቅ የሚለው የጊዜ ተመናችን በጣም ተለውጧል። ከሃያ ወይም ከሰላሳ አመት በፊት የነበረን አመለካከትና አሁን ያለን እንኳን በጣም የተለያየ ነው። መቸኮል፣ ቶሎ ቶሎ ማለት ዘገየ ብሎ መበሳጨት በጣም የተለመደ ሆኗል። የቴክኖሎጂ ግኝቶች ነገሮቸን ለማድረግ የጊዜውን መጠን ባሳጠሩልን ቁጥር የኛ የመጠበቅ ችሎታ ግን በበለጠ ፍጥነት እያነሰ ነው።

በእርግጥ እግዚአብሔር ስለ ጊዜ ያለንን ችኩልነት ያውቃል። ግን እርሱ በዚያ የሚገፋ አይደለም። እርሱ እግዚአብሔር ነው። እኛ ራሳችንን ከምናውቀው የበለጠ ያውቀናል፤ የፀጉራችንን ቁጥር ሳይቀር ለይቶ ለሚያውቀው ለእርሱ (ሉቃስ 21፥18) ለጸሎታችን አስፈላጊውን መልስ መቼና እንዴት መስጠት እንደሚችል ማመንና ማወቅ አለብን። እርሱ ስለ እኛ ሙሉ እውቀት አለው።





ሁኔታችንን፣ ታሪካችንን፣ ፍላጎታችንን፣ ችኩልነታችንንም ጭምር በደንብ ያውቀዋል። የእምነታችንን መጠን፣ መቼ የእምነታችንን ውጤት እንደሚያስጨብጠን እርሱ ጊዜውን በእርግጥ ያውቀዋል። እኛ በሁኔታችን የተያዝን ነን፣ እርሱ ግን ሁኔታችንን የያዘ ነው። እርሱ ለጊዜ ያለው ግምት ፍጹምና ትክክል ነው። ታዲያ ዘመኑ በተለዋወጠ ቁጥር የእኛ ቶሎ ቶሎ ቢጣደፍ፣ እስከ 11፥59 (እኩለ ሌሊት ሊሆን አንድ ደቂቃ እስቲቀረው ድረስ ለማለት ነው) ሊያስጠብቀን ይችላል፣ ግን አይዘገይም።

> *"የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፣ በእርግጥም ይመጣል፣ ከቶም አይዘገይም" ዕንባቆም 2፡ 3።*

ስእቱ ደርሶ እንዳውም ያለፈ ይመስለናል። ችኩል ሰዓታችንን ማስተካከል ያለብን ግን እኛ ነን። መጠበቅን የሚወድ ማንም የለም፣ ነገር ግን መጠበቅ በራሱ የሚያስተምረን ብዙ ነገር አለ፣ "ካላገኘሁት ብሞት ይሻለኛል በሚል ጉጉት እጠብቅ የነበረውን ነገር ባንድ ሌሊት ውስጥ ከሚሆንብኝ ብሞት ይሻለኛል ያልኩበት ውሳኔ ደርሻለሁ" ያለኝ ሰው ንጥፈኛ (extremist) ሊመስለን ይችላል፣ ግን ሁላችንም በዚያ አቅጣጫ የሚሄድ ታሪክ አናጣም። ጆየስ ማየርስ "How to Hear From God" ውስጥ በዚህ አሳብ ላይ እንዲህ ብለው ጽፈዋል። *"አንድን ነገር ለማድረግ ካስቸኮለኝ ቢያንስ ለ24 ሰዓት መጠበቅ እንደሚገባኝ ተምሬአለሁ። ነገርን ለጥቂት ሰዓቶች እንኳን እንዲቆዩ ማድረግ ምን ያህል የአስተሳሰብ ለውጥ እንደሚያመጣ ያስደንቀኛል። እግዚአብሔርን መጠእቅ ብንማር ራሳችንን ከብዙ ችግር እንሰውራለን"* ስለዚህ የኛ የእምነት ጸሎት እንዲህ መሆን አለበት፣ "ጌታ ሆይ ስለመቆየት ያለኝን አመለካከት ታውቃለህ፣ ግን መልሴንም መቼ መመለስ እንዳለብህ የምታውቀው አንተ ነህ፣ አንተ ሩህሩህ ነህ፣ ለእኔ ያለህም አሳብ በጎና ያማረ እንደሆነ አውቃለሁ፣ እስክታደርግልኝም ድረስ እጠብቅሃለሁ"።

## 5. ቀላልና ከባድ

ቀጥሎ ልጠቅሰው የምፈልገው እምነትን የሚነካ ባህላዊ ነጥብ ከእኛነታችን ጋራ የታተመ ከመሆኑ የተነሳ ሳናስተውል የምንወስነው ውሳኔ ነው። ይህም አንድ ነገር እንዴት ቀላል እንደሆነ ወይም እንዴት ከባድ እንደሆነ አስቀድመን በውስጣችን ወስነን እምነትን ግን መለማመድ ሳናስታውስ መቅረታችን ነው።

ባህላችን ነገርን ቀላል ለማድረግ ከፍ ያለ ዋጋ ይከፍላል። ድካምን የሚቀንሱ፣ ሥራን የሚያቀላጥፉ ቁሳ ቁስ ገበያውን ሞልተውታል አንዳንዴ የሚሰጡት አገልግሎት ከዋጋቸው ጋር ሲወዳደር ተመጣጣኝ ባይሆንም ከፍለን እንገዛቸዋልን፣ ከዚያም ሕይወታችንን በእነርሱ የተደገፈ አድርገን አልሠራ ባሉ ቁጥር ጸጉራችንን እንነጫለን። የብዙዎቻችን ወላጆች እንኳን የቤት የሀዝብ ስልክ በሌለበት ሁኔታ እኛን አሳድገው እዚህ ሊያደርሱን በቅተዋል።

ዛሬ ከምንይዛቸው አይ-ፎን፣ አይ-ፖድ፣ ስማርት ፎን አንዱ መሥራት ቢያቆም የአርማጌዶን ጦርነት የሚያክል ሽብር ይሆናል። ማይክሮዌቩ ከተበላሸ ቤቱ ጦም አደረ ማለት ነው። አንድ የመሥሪያ ቤት አለቃ ነበረኝ፣ ሴል ፎን እንዲህ ባልበዛበት ዘመን የመስሪያቤት ስልክ እንዲሰጠን የምንሆነውን ሁኔታ ሲያይ "ይህ የሶስት ሺ አመት ስልጣኔ ያለ ሴል ፎን እንዴት እዚህ ሊደርስ እንደቻለ ይገርመኛል" ይለን ነበር። የሚያስቁ ታሪኮች እያሉ በኢንተር ኔት ላይ የሚያቀርቧቸው አንዳንድ እውነተኛ ታሪኮች አሉ። ሰውዬው ቢሮ ቁጭ ብሎ ሲሠራ ኮምፒውተሩ ያስቸግረዋል፤ ከዚያ ተናዶ ኮምፒውተሩን መምታት ይጀምራል። በአካባቢው ኪዩቢክልስ (ትንንሽ ቢሮዎች) ያሉት ሰዎች ተደንቀው ያዩታል፤ የሰውዬው ንዴት እየጨመረ ይሄድና ኮምፒውተሩን ከቢሮው ወርውሮ ይጥለውና አወደቀበት ቦታ ሄዶ በርግጫና በቦክስ ያናፍጠዋል። ያ ሰው እኮ ከጥቂት አመታት በፊት እርሱ ምናልባት ሁለት ቀን ፈጅቶ የሚሰራውን ሥራ ኮምፒውተሩ ለምን በሁለት ሰዓት አልጨረሰም ብሎ ይሆናል ያ ሁሉ ጠብ።

"ሕይወት ቀላል ነው አትበሉኝ፣ ይሄ ጌታ የሱስ መጥቶ ካልገላገለኝ እኔ በጣም ሰልችቶኛል" አለች ይባላል እንዷት ሚሊዮናዊት አዲስ አበባ ሸራተን ወይ ሂልተን





መዋኛው አጠገብ ቁጭ ብላ "የሜኒፐ ሙዳይሽ ከሌላው እቃሽ ጋር አልደረሰም" ባላት የአየር መንገድ ሠራተኛ ምርር ብላ። የምግብ ትሪዋን ሊያስቀምጥላት ጎንበስ ቀና ይል የነበረው አሳላፊ ሰምቶ ነው አሉ ወሬው የወጣው፣ እውነት ባይሆን ኖሮ ያስቅ ነበር።

ራሳችንን በሐቀኝነት ለማየት ድፍረቱ ቢኖረን በጣም ተሞላቀናል። በተለይ የምዕራቡ ባህል ሰዎች መሞላቀቅን ህጋዊ መብታቸው አድርገውታል። ሪሞት ኮንትሮል ስለ ጠፋባት 911 (ለአጣዳፊ አደጋ የሚደወለውን ቁጥር) የደወለችዋ ሴትዮ፣ የፈጣን ምግብ ቤት የመስኮት አገልግሎት ስለቆመ የከሰሰው ደንበኛ፤ ያዘዘው ፒዛ ስለ ዘገየበት እንደገና ደውሎ ፒዛ አምጪውን እንደሚገድለው ስላስፈራራ ፒዛው በፖሊስ ተልኮለት ታስሮ የተወሰደው፤ እነኚህና ተመሳሳይ ብዙ የኢንተርኔት ታሪኮች የምዕራብን አመለካከት ያንፀባርቃሉ። አንዳንድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያኖች ኑዛዜ (Confession) በቴክስት ለመቀበል አሳቡን እያብላሉት እንደሆነ አንዳንድ ዜና ማሰራጫዎች የአንድ ሰሞን ሰበር ዜና አርገውት ነበር።

በመጀመሪያ ኢራክ የሄድኩ ጊዜ ያየሁትና ያስገረመኝ ነገር ነበር። አንዳንዶቹ ኢራካውያን የኮሌጅ ምሩቆች ሆነው ሳሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ኮምፒውተር ያዩት እኛ ይዘን የሄድነውን ነበር። ግን አንዳንዶቹ የሰራቸው ጥራት በኮምፒውተር የተሰራውን ያስንቅ ነበር። ሆኖም እኛ የደረስንበትና መሻሻል ብለን የያዝነው ቁሳዊነት ላይ ስላልደረሱ ቁልቁል ነበር የምንመለከታቸው፣ የሥራቸውንም ውጤት ሊሰጠው የሚገባውን ዋጋ አልሰጠነውም። እነርሱ በድካም የሰሩትን እኛ በቀላሉ ልንሰራው ስለቻልን እንበልጣለን የበላይ ነን የሚል ስሜት አሳደርንባቸው።

ምዕራባውያን ከምሥራቃውያን በተለይም ከአረቦችና ከአንዳንድ የእስያ ክፍሎች እንዲሁም ከአፍሪካ ባህል መግባባት የማይችሉበት አንዱ ችግር ይህ ነው። የመሻሻልን ልክ ራሳቸው (ምዕራባውያን) ባበጁት መለኪያ ተምነው በዚያ መለኪያ መተመን የማይፈልጉትን ዝቅ አድርገው ያያሉ። ትልቅ ዋጋ አለው ብለው የሚገምቱትን ነገር ሌሎች ያን ያህል ዋጋ ካልሰጡት የኋላ ቀርነት ምልክት ያደርጉታል፣ ከዚህ ጋር የሚሄደውን ቸርነታቸውን ካልተቀበሉም እንደ ምስጋና ቢሶች አድርገው ይገምቷቸዋል። የሀያ አምስት ሚሊዮን ዶላር ክፍያ በእናቱ የተደረገበት ቢን ላዲን

ያን ያህል ዘመን ከምዕራብ ተደብቆ ሊኖር የቻለው ያን የሚያውቅ ሰው ጠፍቶ የመሰላችኋል? አይደለም! ምስጢር መጠበቁን ከገንዘብ የበለጠ ዋጋ (value) ስለ ሰጡት ነው።

ታዲያ እግዚአብሔር የሚመርጠው የትኛውን ባህል ነው? በምዕራብ ትምህርትን ለማቅለል ብዙ ጥረት ይደረጋል። ትምህርት ስርዓትን የተከተለ ነው፤ በትምህርት ቤት ውስጥ የሆነ፣ በተማሪው ላይ ሳይሆን በአስተማሪው ብቃት ላይ ያተኮረ፣ ካሪኩለም የተከተለ ነው። የሌሎች ባህላዊ ትምህርት ደግሞ ብዙ ስርዓትን ያልተከተለ ብዙ ከመናገር ይልቅ በሥራ የሚገለጽ ፤ በተማሪው ላይ ያተኮረ በምሳሌና በፈሊጥ የተደገፈ ነው። የትኛው ነው ከባድ የትኛውስ ነው ቀላል? ከሰው ኃይልና ከንብረትስ (ሪሶኡርቸስ) አኳያ ሲታይ የትኛው የተሻለ ምርጫ ነው?

ቅደም ተከተላችንን ለማስተካከል ምርጫ ማድረግ አለብን። ጊዜያችንን፣ ጉልበታችንን፣ ንብረታችንን በምን ላይ ማዋል እንደሚገባን ቀላልና ከባዱ ምን እንደሆነ ለመለየት ዳራ (baskground) ወሳኝ ነው። አንዳንዴ ነገሮች እየከበዱ ሲመጡ አጥብቀን የያዝነውን ለመለወጥ ትግል ስለሚሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ መተማመን ያስቸግራል። በዚያን ጊዜ የቀላልና የከባድ አመለካከታችንን እንኳን ለጌታ መስጠት ይኖርብናል። ሙሉ እውቀት ያለው እርሱ ብቻ ነው፣ እርሱ ያውቃል።

እርሱ ምን እንደምንፈልግ ያውቃል፤ ለኛ ደግሞ በጎና መልካም የሆነውን ብቻ ያቅድልናል፤ ለፈቃዱም ያለንን መልስ በግልፅና በዝርዝር ያውቃል። ካንድ ቦታ ተነስተን የተጠበቀበት ቦታ እንዴት እንደምንደርስ ያውቃል። እግዚአብሔር በመምህሩ ላይ እንዳተኮረ አስተማሪ ሳይሆን ትኩረቱ በተማሪው ላይ ነው። ይህም ማለት ትኩረቱ በአንቺ ላይ ነው፣ በአንተ ላይ ነው።

የማህበራዊ ሕይወትሽን ብቻ ሳይሆን የግል ሕይወትሽን በዝርዝር ያውቀዋል፤ በቤትሽ ውስጥ ሊያስተምርሽ ነው የሚፈልገው፤ ብዙ ስርዓት ያልበዛበት፤ ካሪኩለምም ያልተከተለ፤ እንደ ቅርብ ጓደኛ ሆኖ ሊያስተምርሽ ይወዳል። ክፍል ውስጥ ቆሞ በሀተታ ሊያስተምረን ሳይሆን አጠገባችን ቁጭ ብሎ እጃችንን ይዞ





ሊመራን፤ የሕይወትንና የማንኙነትን ምስጢር ሊገልጽልን ይፈልጋል። የሚገባንና የሚጣፍጥ ታሪክ በመናገር ያስረዳናል። እውቀትን ከመስጠት የበለጠ አላማው ባህሪን መገንባት ነው። ጌታ የሱስ ራሱን እንደሰጠ፣ እኛም በመጨርሻ በፊቱ ስንቆም ከጌታ ጋር አብረን

> *"የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር አከበርኩህ" ዮሐንስ 17፡ 4 ማለት እንድንችል ያሠለጥነናል።*

ጌታ የሱስ አባቱ ያለውን ሁሉ አድርጓል። ነገር ግን በእኛ መደረግ ያለበት ብዙ ሥራ አለ። መደረግ ያለበትን በእኛ እንደሚያደርግ እናምናለን? ወይስ ቀላል ነው ብለን ንቀነዋል፣ ከባድ ነው ብለን አልፈነዋል? ወይስ ቀላል የሆነው ላይ ብቻ በማተኮር ከባድ የሆነው የእኛ እንዳልሆነ እያለፍነው ነው? ባህላችንና የጀርባ ታሪካችን ልናደርገው የሚገባንን ነገር እንዳይመርጥልን ማስተዋል ይገባናል። እግዚአብሔር እኛንም ባህላችንንም ከኛ የበለጠ ያውቀዋል፣ ማድረግ የሚገባንን እንድናደርግ ይረዳናል ብለን እንመነው።

## 6. ስኬትና ውድቀት

ስኬትና ውድቀት ብዙ አይነት ልክ ወይም ሚዛን አለው። በአንድ በኩል ሲለካ ስኬት ተብሎ የተተረጎመው በሌላው በኩል ውድቀት ይባላል። አሜሪካ በአልካይዳ ቴረሪስቶች የተመታች እለት (ዛሬ 9-11 በመባል ብቻ በታወቀው ክስተት) ለብዙዎች የውድቀት ቀን ሆኖ ሰው ሲለቀስ በምሥራቅ አፍጋኒስታን ቶራ ቦራ ተራራዎች ግን እንደ ትልቅ ስኬት ስለተቆጠረ ይጨፈር ነበር። (በቶራ ቦራ ተራራዎች ውስጥ ያሉ ዋሻዎች የረጂም ጊዜ የአልካይዳ ምሽጎች ነበሩ)። ስኬትና ውድቀት ከምንገምተው በላይ የተቀራረቡ ናቸው። አሁን ስኬት የመሰለን ወዲያው ተገልብጦ ራሱ ያ ነገር ውድቀት ይሆናል። ታዋቂው የኔ ዘመን ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ የሚተርኩት አንድ ታሪክ ነበር። ታሪኩ

በመንግሥቱ ነዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ የሆነ ነው። "ጄኔራል መንግሥቱና አባሮቹ ንጉሡ ውጪ አገር ሆነው ሥልጣን በያዙበት ትንሽ ጊዜ ውስጥ ዜናው በሬዲዮ ሲሰማ ብዙ ህዝብ አራዳ ጊዮርጊስ ተሰበሰበ። አዲሱ መንግሥት

የተሳካለት ስለመሰለን "አዲሱን መንግሥት እንደግፋልን" ብለን መዝፈን ጀመርን፤ ጭፈራው እየደመቀ መጣና ወደ ስልፍ ተለውጦ ያንኑ ዘፈን እየዘፈንን ወደ ቤተ መንግሥት አመራን። አሁን የሰልፉ የፊት ጫፍ ትምህርት ሚኒስቴርን አልፎ ቁልቁል ወደቤተ መንግሥት ሲተም "ንጉሡ ገቡ" የሚል ወሬ መጣ። ወሬው የደረሳቸው ፊት ጫፍ አካባቢ ያሉት ዘፈናቸውን ለውጠው "ለንጉሳችን እንሞታለን" ማለት ጀመሩ። ወሬው ያልደረሳቸው ከኃላ ያሉት ግን አሁንም "አዲሱን መንግሥት እንደግፋለን፣" ሲሉ ለንጉሳችን እንሞታለን" እየተባለ ሲጨፈር የተነሳውን ለማንሳት፣ የወደቀውን ለመጣል መሐሉ ላይ ድብልቅቅ ሆነ"።

ስኬትና ውድቀትን ለመተርጎም የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ምክንያቱም እርሱ ብቻ ነው ወደፊት አይቶ የቅርብም ሆነ የሩቅ ውጤቱን ማወቅ የሚችል። በሆነልን ብለን የተመኘነው ባለመሆኑ በኋላ ደስ የተሰኘንበት ነገር አጋጥሞን አያውቅም? በሪሰርቻችን ተመክተን፣ በእውቀታችን ተገፋፍተን በስሜታችን ተቀስቅሰን ራሳችንን የምናታልልበት ጊዜ በዙ ነው። እንኳን እኛ በነገሩ ሊቃውንት የተባሉት ስንቴ ይሳሳታሉ?

ሱካር ለሕጻናት ጥሩ ነው እንጂ አይጎዳቸውም እንዳውም በቂ ስኳር ካላገኙ አስፈላጊ የሆነ ንጥረ ነገር ያጣሉ የሚል ጥናት በቅርቡ ጋዜጣ ላይ አነበብኩ። ያ ከሆነ ልጆቼን ይቅርታ መጠየቅ አለብኝ ማለት ነው ብዬ አሰብኩ። ምክንያቱም ስኳር እንዳያበዙ እየተቆጣሁ የሚያስፈልጋቸውንና የሚወዱትን ስኳር እየነፈግሁ ነው ያሳደግኋቸው ብዬ አሰብኩ። ግን የሚወጡት ጥናቶች እስኪሰማሙ ከመጠበቅ እግዚአብሔር እንዲረዳኝና ትክክለኛውን ውሳኔ እንዳደርግ ስለ አገዘኝ አመስግኜ ማረፍ እችላለሁ።

የውሳኔዬን መሠረት ከጥናትና ከሪሰርች ወደ እግዚአብሔር ለመለወጥ እችላለሁ። እግዚአብሔር ጥናትን ይጠላል ማለቴ እንዳልሆነ በዚህ ጊዜ መቸም ታውቃላችሁ፣ ጥናት ግን የእርሱን ቦታ እንዲወስድ አይፈልግም። ስብ (fat) የሌለው ምግብ አለመብላት ጥሩ ነው በተለይ ጣዕም የለሽነቱን መቋቋም ከቻልን፤ ለኮሌስትሮል ቁጥጥር በጣም ይጠቅማል። ነገር ግን በአንዳንድ ሰዎች እንደሚታየው ስብ የለሽ ምግብ በአምልኮት ደረጃ ተይዞ ትንሽ ስብ የገባበት ምግብ መርዝ የገባበትን ያህል





ነው የሚፈራው። እንደዚያ ግን መሆን የለበትም። ባለቤቴ ኤልሲ ስለምንበላው ነገር ትጠነቀቃለች። ብዙ ጊዜ በዚህ አደንቃታለሁ፣ "ጥሩ ነው፣ ነገር ግን ሃይማኖት እንዳናደርገው እላታልሁ"። ጥናቱ ሁሉ ይለዋወጣል፣ አስተማማኝም አይደለም፤ ስኬትና ውድቀታችንም በእነኝህ ጥናቶች ላይ ብቻ የተመረኮዘ መሆን የለበትም። በእግዚአብሔር መደገፍ ግን ሁሌ አስተማማኝ ነው። ምክንያቱም እርሱ አይለወጥም። ከእርሱ ጋር ከቆምን ደግሞ ውጤታችን ውድቀት የለበትም። ሁል ጊዜ ስኬት ነው።

## 7. አቤት ውሸት!

ትልቁ ውሸት እንግዲህ "ምክንያታዊ ካልሆነ ትክክል አይደለም" (If it is not logical, it is not so) የሚለው ነው። የሰብዓዊነት እንቅስቃሴ ከ 1970ዎቹ ጀምሮ ይህንን ውሸት በማሻሻል አዲስ ፈርጅ ጨምሮለታል፣ "ካልተሰማህ ትክክል አይደለም"። በሰው ላይ ላተኮረ ፍልስፍና አዕምሯችን መርምሮ ወይም ስሜታችን ተስምቶት ካላረጋገጥነው እውነት አይደለም የሚለውን ይህን አሳብ መቀበል ይቀለዋል። የዚህ የሰባአዊነት አስተሳሰብ ውጤት ታዲያ የአንተ ስሜትና ከዚያም ተነስተህ የምትደርስበት ግብ ከሌላው የተለየ ስለሚሆን፣ እውነት አንድ ብቻ ሊሆን አይችልም፣ አይችልም ይላል። ስለዚህ እውነት ተለዋዋጭ (relative) እንጂ ፍጹም (absolute) አይደለም። በእግዚአብሔር ላይ ባተኮረ አመለካከት ግን እውነት እግዚአብሔር እንዳለ ነው። ስለዚህ እውነት እኔ ከምረዳው በላይ ነው፣ ወይም ስሜቴ እንደሚነግርኝ ብቻ አይደለም ብል ለእውቀት ወይም ለእምነት ያለኝን ታማኝነት (integrity) ማጓደሌ አይደለም ወይም አይቀንሰውም።

እንዲት በቅርብ የማውቃት ሴት ከባሏ ተፋታ ባሏ የበደላት ሁሉ በውስጧ እንደ ቁስል ሆኖባት ነበር። አንድ ጊዜ ስታጫውተኝ ታዲያ ይቅር እንድትለው ነገርኳት። 'ይቅር ብትዪው ለራስሽም ፈውስ ታገኚያለሽ" አልኳት

"ይቅር እለዋለሁ ብል ውሸት መናገሬ ይሆናል" አለችን

"ለምን እንደዚያ ትያለሽ?"

"ይቅር እንድለው የሚገፋፋ ስሜት የለኝም" አለችኝ

"ባይሰማሽ ምንም አይደለም፣ አንቺ ይቅርታ ልታደርጊለት ከወሰንሽ ስሜትሽም ቀስ ብሎ ይከተላል" አልኳትና "እሞክራለሁ" ብላኝ ተለያየን።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ስንገናኝ "ስሜትሽ እንዴት ነው?" ስላት "እየተከተለ ነው" አለችኝ። ካመንን ይሰማናል፣ እንዲሰማን ከጠበቅን ግን ማመን አንችልም። ትልቁ ውሸት ታዲያ ሰዎችን አሳባችሁን ወይም ስሜታችሁን ብቻ ተከተሉ የሚለው ነው።

### በአጭሩ

በሚቀጥሉት ቀናት ጋዜጣ ስታነቡ ከሰብዓዊነት አመለካከት የመነጩ አስተያየቶችን ለማየት ሞክሩ። ከዚያ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከትን የሚያንጸባርቁ አሳቦችን ፈልጉ፣ ባህላዊ አመለካከትም ከበስተ ጀርባ ሆኖ በእምነት ላይ ተጽእኖ ያደርግ እንደሆን እስቲ መርምሩ።

በሚቀጥለው ምዕራፍ እምነታችንን ስለሚዋጉ መንፈሳዊ ኃይላት እናያለን።

## ምዕራፍ ስድስት





### *መንፈሳዊ ውጊያ*

ባለፉት ሀያ አምስትና ሰላሳ አመታት እንዳየሁት በዕውቀት ንቃትና በቁስ ማካበት ላይ በተመሠረተው በምዕራቡ ባህል ሳይቀር ዋናው የእምነት ውጊያ መንፈሳዊ ውጊያ መሆኑን ነው። ታላቁ እንግሊዛዊ ደራሲ ሲ. ኤስ ሉዊስ Christian Reflections በተባለው ጽሁፋቸው ካቀረቡት አሳብ ጋር ይህ ሁኔታ ይመሳሰላል። "በሉአላዊ (Universal) አለም ውስጥ ተፅእኖ የሌለበት (Neutral) ቦታ የለም። እያንዳንዷ ስንዝር ቦታ፣ እያንዳንዷ ኢምንት ጊዜ በሙሉ የተያዙ ናቸው። ወይ በእግዚአብሔር ተይዟል ወይ ሰይጣን ይዞታል"። ጳውሎስ ስለዚህ ውጊያ ሲያስተምር

> *"የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን ..."*
> *ኤፌሶን 6፥ 16።*

ይህ ቦታ የሚናገረው ስለ እምነት ነው። ጠላት ከሚያጠቃቸው የእኛነታችን ክፍሎች ዋናው እምነታችን ነው። እምነታችንን ሊያስጥለን ወይም፣ የተሳሳተ እምነት እንዲኖረን ለማድረግ፣ ጠላት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። እምነትን እንዳንለማመድ ያስፈራራናል፣ ይፈትነናል፣ ይነቅፈናል።

ጳውሎስ ይህንን መልዕክት ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የጻፈው  እስር ቤት በነበረበት ጊዜ ነበር። ከሚጠብቀው ወታደር ጋር አብሮ ታስሮ ስለነበር፣ የጦርነት ነገር በቅርብ ነው የሚያውቀው።

ሮማዊ ወታደር ሁለት የተለያዩ ጋሻዎች ይጠቀም ነበር። የመጀመሪያው "አስፒስ" የሚባል ነው። ይህ ክብ የሆነ አነስተኛ፣ ጋሻ ዙሪያው ከሁለት ጫማ የማይበልጥ ነው። ይህንን ጋሻ ሮማዊ ወታደር የሚጠቀምበት በጨበጣ ውጊያ ጊዜ ነው። ከጠላቱ የሚሰነዘርበትን መክቶ የራሱን ማጥቂያ መሳሪያ ለመጠቀም ያስችለዋል። ሐዋርያው በዚህ ቦታ የሚጠቅሰው ግን ቱሪዮን የተባለውን ከባድ የብረት ጋሻ ነው። በቁመቱ አራት ጫማ፣ በስፋቱ ሁለት ጫማ የሆነ ባለአጄታ ጋሻ ሲሆን፣ ወታደሩ ከጋሻው

በስተኋላ አሽምቆ መደበቅና ከጠላት የሚወረወርበትን ፍላጻ ሁሉ ማምለጥ ይችላል። የሚፈናጠሩት ቀስቶች ሁለት ስንዝር (20 ኢንች) ያህል የሚሆኑና ጫፋቸው እንደ ሰም አይነት የሆነ መንደድ በሚችል (Burning Tar) ፈሳሽ የተነከረ ነው። እነኚህ ቀስቶች በጋሻው መከታ ካልቆሙ ወታደሩን ከመቱት ቆዳውን በስተው ይገባሉ። ቀስቱ እንኳን ከሰውነቱ ውስጥ ተመንጭቆ ቢወጣ፣ ያ ጫፉ የተነከረበት ነገር በሰውነት ውስጥ ይቀርና መቅለጡንና ማቃጠሉን ይቀጥላል። ወታደሩንም ውስጣዊ ብልቶቹን፣ ጡንቻውንና ነርቮቹን እየነካ፣ እያፈዘዘውና እያደነዘዘው ይሄዳል። ታሲተስ የተባለው በጊዜው የነበረ ታሪክ ጸሐፊ በአንድ ወታደር ጋሻ ላይ 300 የዚህ አይነት ቀስቶች እንዳየ መስክሮ ጽፏል። ቀስቱ አጥፊና አሰቃይቶ ገዳይ መሳሪያ ነው። ጋሻው ግን ለተከለሉበት መከታ ነው።

እምነትን በተመለከተ እነኚህ አጥፊና ገዳይ ቀስቶች በሕይወታችን ብዙ ጊዜ ይሰነዘሩብናል እልፎ እልፎም ይመቱናል። ቀስቱ ከሕይወታችን ቢነቀልም ያ የቀስቱ ጫፍ በተወው ነገር እየተቃጠልን የፈዘዝንና የደነዘዝን ግን ብዙዎች ነን። ኃጢአት በሕይወታችን በሚተወው ሐፍረትና መሸማቀቅ በመከሰስ ወይም ራስን በመውቀስ የተጨበጥን ብዙዎች ነን። አንዳንዴ የቀስቱ ራስ በቀጥታ ባያገኘንም ባጠገባችን ሲወነጨፍ የተነከረውን መርዝ መርጨት ይችላል። እያችሁ ጠላት ወደ እኛ የሚተኩሰው የተለያዩ አይነቶች የሚንበለበሉ ፍላጻዎች አሉት። ፍርሃት፣ ንዴት፣ ብስጭት፣ መጎዳት፣ ሀፍረት፣ ክፉ ምኞት፣ መደበር (depression)፣ በሽታ፤ አደጋ፣ ችግር፣ ውጊያ፣ የነገር ከቁጥጥራችን ውጪ መሆን፣ (እነሰ ካላችሁ የራሳችሁንም ጨምሩበት)። እንደ እግዚአብሔር ቃል ግን ለዚህ ሁሉ መልሱ ቀላል ነው (ልብ አድርጉ ችግሩ ቀላል ነው አላልኩም)። እነኚህን ሁሉ የሚንበለበሉ ፍላጻዎች ወይም ቀስቶች በእምነት (በትልቁ ጋሻ) ብቻ ነው መቋቋም የምንችለው።

እምስት ተንበልባይ ፍላጻዎችን ወይም ቀስቶችን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቀረብ ብለን እንድናይ እፈልጋለሁ። በእነኚህ ፍላጻዎችም ላይ የእምነታችንን ጋሻ እንዴት እንደምናነሳ ጨምረን እንመለከታለን።

## 1. ፈተና (Temptation)





ፈተና እምነትን የሚጎዳው እንዴት ነው? ኃጢአያት የሚያደርገው የመጀመሪያው ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ማቋረጥ ነው። ያ ግንኙነት ከተቋረጠ ደግሞ እምነት የለም ማለት ነው። በፈተና መውደቅ እንግዲህ በሁለት ወገን የሚቆርጥ ሰይፍ ነው።

ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ያበላሽዋል፣
ለ. ከእግዚአብሔር የምናገኘውን እምነት ያጠፋዋል

## በፈተና እንዳንወድቅ

ሰይጣን ክርስቲያኖችን በመፈተን ያሳለፈው ዘመን ክርስቲያኖች ፈተናን ለመቋቋም ካሳለፍነው ዘመን በጣም የበለጠ ነው።

ከልምምድ እንጻር ካየነው እንግዲህ እርሱ ከእኛ የተሻለ አጀማመር አለው። ሰይጣን በእርግጥ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ነው (1 ጴጥሮስ 5፥ 8)። ትግሉን የማያላላ፣ ፋታ የማይሰጥ፣ ‘ከወደቀ አልመታውም’ ብሎ ችላ የማይል፣ መጥፎ፤ ርኩስ፣ ጨካኝ ጠላት ነው። ለትግሉ ደግሞ ስልት አለው፣ ከሚያገሳ አንበሳ እስከ ብርሀን መልአክ ድረስ ያለውን ርቀት የሚያጠቃልል ነው። ሰይጣን ለፈተና ከሚጠቀምባቸው ስልቶቹ አንዱና ምናልባትም የመጀመሪያው፣ ፈተናችንን በራሳችን የምቋቋመው እንደምንችል አድርገን እንድናስብ ማድረግ ነው።

የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ የሚያስተምረው የዘጠኝ አመት ወጣቶችን ነበር ይባላል። “ሰይጣን ቤታችሁ መጥቶ በሩን ቢያንኳኳ ምን ታደርጋላችሁ?” ብሎ ጥያቄ ጠየቃቸው። አንዲት ወጣት እጇን አውጥታ “ጌታ የሱስ በሩን እንዲከፍት እጠይቀዋለሁ” ብላ መለሰች።

ለልጅ የሚስማማ ታሪክ ይመስላል፣ ብዙ አዋቂዎች ግን ያልተረዱት ምስጢር ነው። በራሳችን በሩን ለመክፈት እንሽቀዳደማለን። ጥበበኛነት ግን ብቻውን ሊቋቋመውና ሊያሸንፈው የሚችለውን ጌታን መላክ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እኮ ጳውሎሳዊ በሆነ አጻጻፉ ሊነግረን የፈለገው ይህንን ነው።

*"እግዚአብሔር ታማኝ ነው፣ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገስ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል" 1ቆሮንቶስ 10፥13።*

## በፈተና ከወደቅንስ?

ህሊና በመንፈሳችን የሚገዛ የእኛነታችን ክፍል ነው። ኃጢአት ከማድረጋችን በፊት ህሊናችን "ተው አታድርግ" ይለናል። ይህንን በተለያየ መንገድ ልንለማመደው እንችላለን። እረፍት ሲነሳን ወይም ባዶነት ሲሰማን፣ ትክክል ያለመሆናችን ግንዛቤ ሲኖረን፤ በደንብ ካዳመጥነው ይህ ሁሉ የህሊና ድምጽ ነው።

አንዳንዴ ተፈጥሮአዊ በሆነ ክስተትም ይገለጻል፤ አውቀን ኃጢአትን ለመለማመድ ስንወስን የልባችን አመታት ሲጨምር፣ ላብ ላብ ሲለን ትንፋሻችን መቆራረጥ ሲጀምር ህሊናችን እያስጠነቀቀን ነው። በዚህ ጊዜ በህሊናችን ላይ አቅመኞች ሆነን ነው በኃጢአት የምንወድቀው።

በፈተና ከወደቅንም በኋላ ህሊና "ማድረግ አልነበረብህም" እያለ ይወቅሰናል። አሸንፈነው የነበረው ህሊና እንደገና ይበረታብናል። ስለዚህ ፀፀት ይሰማናል፣ ሐፍረት ያሸማቅቀናል፣ ራሳችንን ኢይጭ አስከምንለው ድረስ እኛነታችን ያስጠላናል፣ መንፈሳዊነታችን ይከብድብናል።

ይህ ግን የእግዚአብሔር ቅጣት አይደለም። ይህን በደንብ ማስተዋል ይገባናል። እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ልጅ ኃጢአት የገዛ ልጁን ቀጥቶታል፤ አሁን እያንዳንዳችንን የመቅጣት ፍላጎት የለውም። ለመለኮታዊ ቅጣት ደግሞ ማንኛችንም ብቁ አይደለንም፣ ለኃጢአት መስዋዕት ሆኖ ዋጋውን ሊከፍል የበቃው ኃጢአት ያልተገኘበት የእግዚአብሔር ልጅ ብቻ ነው። ፀፀት የሞላው ህሊና ታዲያ የኃጢአት ቅጣት ሳይሆን ለንስሀ የሚያበቃ ማነቃቂያ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያበላሸነውን ግንኙነት እንደገና መመስረት እንድንጀምር የሚያደርግ ጥቆማ ነው።

በፈተና ስንወድቅ ሰይጣን ማድረግ የጀመረውን መጨረሱ ሳይሆን ገና መጀመሩ ነው። አሁን ግን ስልቱን ይለውጥና ፈራጅ ሆኖ ይመጣብናል፣ ይረግመናል። ፍርድ





ቁልቁል የሚጨቁን ሲሆን ወቀሳ ግን የሚያነሳ ነው። ከኃጢአት በኋላ ሰይጣንና እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚኖራቸው ሚና ይሄ ነው።

*"ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ቢቀላ እንደ በረዶ ይነጣል፤ እንደ ደም ቢቀላም እንደ ባዘቶ ነጭ ይሆናል" ኢሳይያስ 1፥18።*

ሰይጣን ይፈርድብናል፣ እግዚአብሔር ግን ይወቅሰናል፤ ሰይጣን የሚፈልገው በፍርድ ራሳችንን እንድንቀብር ነው "በድያልሁና ልሙት እኔ ለእግዚአብሔር የማልገባ ነኝ" እንድንል ነው የሚያደርግን። ይቅርታን ጠይቀን ይቅርታ ከመቀበል ይልቅ "ወንድ ይውጣህና ወይም ሴት ይውጣሽና ቀጥልበት ወይም ቀጥይበት አለዚያም ራስህ አስተካክለው አስተካክዪው" ይለናል፣ ለስህተታችን አላፊነትን የወሰድን ያስመስለዋል። ግን አይደደም፣ በራሳችን ለማስተካከል መሞከሩ የኃጢአት ውጤት እንዲበዛ ነው የሚያደርገው፤ ያ ሁኔታ ደግሞ ከእግዚአብሔር የበለጠ ያርቀናል።

በራሳችን ልናስተካክለው አንችልም፣ የክርስቶስ ደም ብቻ ነው ኃጢአትን ሊያጥብ የሚችለው። እኛ ማድረግ የምንችለው ኃጢአታችንን በመናዘዝ ይቅርታን መቀበል ነው። ይህ እውነት ነው ለብዙዎች የማይዋጥላቸው።

ምንም ያህል ደረት መድቃት፣ ፊት መቧጠጥ፣ ራስን ማንቋሸሽ ኃጢአታችሁን ሊያስወግደው አይችልም። ይህ ምስጢር ነው፤ በሁሉ ነገር ላይ የእርሱነቱ አሻራ እንዲታይ ለሚጣጣር የሰው ልጅ የማይገባው። ይህን በሚያክል ትልቅ መዳን ውስጥ የራሱ የሆነ የሥራ ድርሻ የለበትም ሲባል ስእው መቀበል ያቅተዋል፤ ስለዚህም ምስጢር ይሆንበታል። ስለዚህ አሁንም ደግሜ እለዋለሁ በኃጢአት ስንወድቅ ልናደረግ የምንችለው በኃጢአታችን መናዘዝና ይቅርታን መቀበል ብቻ ነው።

አዎን እንደዚህ ቀላል ነው! እንዲያውም ቶሎ ብናደርገው የበለጠ መልካም ነው። ከዚያ በኃላ "እርሱ በፈቃዱ ይቅር ብሎኛልና ይቅር ተብያለሁ" ብላችሁ ለራሳችሁ ንገሩት፤ ቢያስፈልግም ድገሙለት፣ አሁንም አልሰማ ካለ ጮክ ብላችሁ ንገሩት። አንዳንዴ እኮ ጆሮ ከባለቤቱ የራቀ ስለሆነ ጮክ ብሎ መነገር ያስፈልገዋል። ይቅር እንደተባላችሁ አይሰማችሁ ይሆናል፣ ያ ቀስ እያለ ይመጣል። ለማመን ግን

ስሜታችሁን አትጠብቁት።

## 2. ክስ

"ከሳሻችን" የሚለው ቃል የሰይጣን የተፀዋኦ ስሙ ነው፤ ወይም ከቁልምጫ ስሞቹ አንዱ ነው። የከሳሽ ዋና ተግባሩ ደግሞ መክሰስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን

*"የወንድሞቻችን ከሳሽ" ራዕይ 12፥ 10 ይለዋል።*

ሰይጣን ሁልጊዜ የሚከሰው የእግዚአብሔርን ሰዎች ብቻ ነው እንጂ አለማውያንን አይደለም። አለማውያን ባለፈው ክፍል እንዳየነው በሰይጣን ፍርድ ሥር ናቸው። በንስሃ እስካላመለጡ ድረስ እነርሱን መክሰስ አያስፈልገውም። የማያቋርጥ ክስ የሚመሰርተው፣ ፋይል የሚከፍተው፣ ዶሴ የሚያከማቸው በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ነው። የሚንበለበሉትን የክስ ፍላጻዎቹን ወደ እኛ የሚልከው፣ በተለይ በሶስት ሁኔታዎች በምናልፍበት ጊዜ ነው።

### ፈተናን ተቋቁመን እምቢ ስንል

ሰይጣን ባቀረበልን ፈተና ካልወደቅን፣ ኃጢአትን ካልሰራን፤ ዘዴውን ይቀይርና ክስ ይጀምራል። በምን ይከሰናል ለሚለው ጥያቄ መልሱ ራሱ ባቀረበልን ፈተና መልሶ ራሱ ከሳሽ ይሆናል። ራሱ በአሳባችን ያስቀመጠውን አሳብ እምቢ ብንልም በክስ ይመጣና "እቤት እንዴት ከእግዚአብሔር ብትርቅ ነው እንዲህ ያለ ርኩስ አሳብ የምታስተናግደው፣ ደግሞ ፀፀት እንኳን አይሰማህም?" ይለናል። ክሱን የሚያቀርበው ደግሞ የራሳችንን የአስተሳሰብ ዘዴ፣ የራሳችንን ቃላት፣ የራሳችንን ስሜት እየተጠቀመ ስለሚሆን በሰይጣን እየተከሰስን እንደሆን እንኳን አናውቀውም፤ የራሳችን ሀሊና እየወቀሰን ነው የሚመስለን። አስፈላጊ ከመሰለው ደግሞ ለክሱ መደገፊያ የሚሆን የእግዚአብሔርን ቃል ይጠቅስልናል። ጌታ የሱስን ሲፈታተን እንዱ የሞከረው ዘዴ ቃሉን መጥቀስ እንደነበረ አስታውሱ (ማቴዎስ ምዕራፍ 4)። አንዳንዴ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የማያውቁና ስለ እግዚአብሔር ምንም የማይገዳቸው ሰዎች በጥቅስ ይመቷችሁ የለም እንዴ? ክሱ እንዲህ ሊቀርብ ይችላል፣ ቀላል ምሳሌ





ሀ. ሰይጣን፣ "ተመልከት ያቺን ሽጋ ወጣት፣ ሽንጥና ዳሌዋ አያጓጓም?"

ለ. ክርስቲያን፣ "ጌታ ሆይ ወደዚች ልጅ ያለኝን የተሳሳተ አሳብ እቃወማለሁ፣ የጠላትን አሰብ ከኔ አስወግድ"

ሐ. ሰይጣን፣ "አታፍርም እንደ እንዲህ ያለ ርኩስ አሳብ የምታስተናግደው?"

መ. ክርስቲያን፣ "የሰይጣንን ክስ በጌታ ስም እቃወማለሁ"

ሠ. ሰይጣን፣ "መቃወም በፊት ነበር እንጂ፣ ጌታ የሱስ ወደ ሴት አይቶ የተመኛት አመንዝሯል ብሎ የለም"

ረ. ክርስቲያን፣ "በመፈተኔ ብቻ ኃጢአተኛ ነህ ብሎ የሚከስ የሰይጣን አሳብ በጌታ ስም ይጥፋ"

ሰ. በዚህ ጊዜ ጌታ ጣልቃ ይገባና ከሳሹን ያባርርልናል።

ብዙዎቻችን በሰይጣን ወጥመድ ጥልቅ የምንለው ደረጃ ሠ ላይ ነው። ማስተዋል ያለብን ግን መፈተን ኃጢአት አይደለም። መፈተን ኃጢአት ቢሆን ኖሮ ጌታ የሱስ ከሁላችንም የባሰ ኃጢአተኛ ነበር ማለት ነው። የዕብራውያን ጸሀፊ

*"በማንኛውም ነገር የተፈተነ ... ይሁን እንጂ ምንም ኃጢአት አልሰራም" ዕብራውያን 4፥ 15።*

ከሳሻችን እንደ ብርሃን መልአክ እየተመላለሰ በመፈተናችን ሲከሰን ለእውቀት ባሀሪያችን ተቀባይነት ያለው ጉዳይ ያቀርባል። ነገር ግን ውሸት ነው። ጌታ የሱስ ስለ ሰይጣን ያለውን አስታውሱ።

*"እርሱ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት..... " ዮሐንስ 8፥ 44።*

የእርሱን ውሸት ለማድመጥ ጊዜ ከሰጠነው፣ ላላደረግነው ኃጢያት እንኳን የክስ መጥሪያ ከተቀበልን፣ ውጤቱ ኃጢአቱን ከማድረግ ጋር አንድ ነው። ከእግዚአብሔር

የመለየት ስሜት ይሰማናል፣ ኃጢአተኛ ነኝ በማለት ራሳችንን ከእግዚአብሔር እናርቃለን። ሰይጣን በሚከሳችሁ ጊዜ ገስጹት፣ ተቃወሙት። "ብንቃወመው ግን ከእኛ ይሸሻል" ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ኪዳን ነው።

## መንፈሳዊ ዝግጅት ሲቃረብ

ይህ ዘዴ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በማዘጋጀትና በመምራት ልምምድ ላለን ለብዙዎቻችን ግልጽ ነው። ይህ ዝግጅት እየተቃረበ ሲመጣ፣ በተለይ በዝግጅቱ ላይ ሙሉ ተሳትፎ ለሚኖራቸው ሰዎች የማይቀር ውጊያ አለ። ከውጊያዎቹ አንዱ ክስ ነው። ራሳችንን ለዚያ አገልግሎት ብቁ አይደለህም ብሎ ይከሰናል፣ ሊያሳምነንም ይጥራል። እኛን በደንብ አድርጎ ስለሚያውቀን ብዙ ጊዜ ክሱን የሚመሰርትበት ትንሽ እውነት ወጥሮና ዘርግቶ ለእውቀት ባህሪያችን አስማምቶ ያቀርባታል፣ ራሳችንንም እንድንጠራጠር ያበረታታናል። ለምሳሌ፣

ብዙ ልምምድ የሌለን ከሆነ "አንተ ደሞ ማነኝ ብለህ ነው እንዲህ ያለ ቦታ ጥልቅ ያልከው፣ ራህን አታውቀውም እንዴ? ትዝብት ለማትረፍ ነው። ለራስህ እንኳን የምታደርገውን በደንብ የማታውቅ ሰው ፊት ስትቆም እኮ ያንን ሁሉ ሰው ማታለልህ እኮ ነው" ;

ወይም ይቅርታ ጠይቀን ይቅርታ የተቀበልንበትን ኃጢአት ያነሳና "ይህን ይህን ኃጢአት ስትለማመድበት የነበረው ጊዜ እኮ ሩቅ አልነበረም፣ አሁን ከዚያ ተነስተህ እዚህ ደርሻለሁ ለማለት ነው?"

ወይም በዝግጅታችን ይከሰናል፣ "እንዲህ ያለ ፕሮግራም ሲሰጥህ በጾም በጸሎት የቆየህበት ስንት ቀን ነው? ታዲያ በቂ ይመስልሀል?" ወይም "ቃሉን እኮ ለመስበክ ብቻ አጠናኸው/አጠናሺው እንጂ በሕይወትህ/ብሕይወትሽ መች ተለማመድሺው?" ወይም "ዘማሪት መባልን ፈልገሽ እንጂ መች የዘማሪ ሕይወት አለሽ?"

ወይም እኛ ልንቆጣጠረው በማንችለው ሁኔታ ላይ ይከሰናል፣ "አንተ ገና ወጣት ነህ፣ ይህ የብዙ ጊዜ ልምምድ ላላቸው እንኳን አስቸጋሪ አገልግሎት ነው"





ወይም "ሚስትህ ታማ ቤት ተኝታ እንዴት ብለህ ነው እዚህ ለበሽተኛ እጸልያለሁ የምትለው?"

ሰይጣን በአሳባችን ወስጥ ጥርጣሬ ለማስቀመጥ የሚያስችለውን መንገድ ሁሉ ይጠቀማል። ሰይጣን ትንሽ እውነት ተጠቅሞ ሙሉ ውሸት በማውጣት የረቀቀ ባለሙያ ነው። ታዲያ ለእንዲህ አይነት ክሶች መልሳችን ምንድነው? ጌታ የሱስ ያስተማረው ነዋ!

*"ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ" ማቴዎስ 5፣ 25።*

ምንድነው የምትለው፣ ከሰይጣን ጋር ተስማማ? ኧረ ቲዮሎጂህን አስተካክል፤ ይህ የብዙዎቻችሁ ጥያቄና ትችት ሊሆን ይችላል። እንደዚያ ማለቴ አይደለም። ግን ክስን ራሱን ወስደን ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን ልንጠቀምበት እንችላለን። እግዚአብሔር ደግሞ ለክስ ሁሉ መልስ አለው።

እስቲ እላይ የቀረቡትን ክሶች ወስደን በዚህ መንገድ መልስ እንስጣቸው። ሰይጣንን ግራ ለማጋባት ጥሩ መንገድ እርሱ እኛን ሲከስ እኛ ንግግራችንን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ማድረግ ነው። ይህ ሰይጣንን ግራ ያጋባዋል፣ እንዲበሳጭ (frustrate) ያደርገዋል። አንጋፋው የቤተ ክርስቲያን መሪ ዶክተር ከበደ ወልደማርያም ዱሮ እንድ አባባል ነበረው። "ከሰይጣን ጋር ምን መመካከር ያስፈልጋል?"

"አንተ ደሞ ማነኝ ብለህ ነው እንዲህ ያለ ቦታ ጥልቅ ያልከው፣ ራስህን አታውቀውም እንዴ? ሰው ፊት ስትቆም እኮ ያንን ሁሉ ሰው ማታለልህ እኮ ነው" ; ሲልህ "ጌታ ሆይ! ልክ ነው እኔ ልምምዱም ቅድስናውም የለኝም፣ ነገር ግን ይህ ትድለቴ ነው በበለጠ ባንተ ላይ እንድደገፍ የሚያደርገኝ"

"ይህን ይህን ኃጢአት ስትለማመድበት የነበረው ጊዜ እኮ ሩቅ አልነበረም፣ አሁን ከዚያ ተነስተህ እዚህ ደርሻለሁ ለማለት ነው?" ሲለን "ጌታ ሆይ ይህ ክስ የበለጠ ራሴን እንድመለከት ስላደረገኝ፤ ገና ያልተናዘዝኩበት ኃጢአት እንኳን ቢኖር ይቅር እንድትለኝ ለመጠየቅ በፊትህ እቀርባለሁ፤ እንደ ቃልህ ደግሞ ኃጢአቴን ይቅር ከልከኝ እንደማታስታውሰው አውቃለሁ"

"በደንብ አልተዘጋጀህም " ለሚለን "ጌታ ሆይ እኔ እስከምችለው ድረስ ተዘጋጅቻለሁ፤ የእኔን ዝግጅት እንድትባርከውና አንተ ደግሞ እንድትጨምርበት እጠይቅሀለሁ።

"የሚገባውን ያህል አልጸለይክም" ሲለን "ይሄም እውነት ነው ጌታ ሆይ፣ ግን መተማመኛዬ የኔ የጸሎት ችሎታ ሳይሆን የአንተ ቸርነት ነው።

ሰይጣን ክሱን አያቆምም፣ ተስፋ እንድንቆርጥ በረቀቀና በተሻለ መንገድ ተመልሶ ይመጣል። ስኬት የምናገኘው እንዴ የሰራልንን መንገድ በመጠቀም ወይም ሌሎች ያሳዩንን ዘዴ በመለማመድ ብቻ አይደለም። በእርግጥ ይህ ሁኔታ አንዳንዴ ሊሠራ ይችላል። የማይሳሳተውና ሁሌ የሚሰራው መንገድ ግን ያለማቋረጥ በጌታ የሱስ ላይ መደገፍ ነው። ሥራውን እርሱ በእኛ ውስጥ እንዲሰራ መፍቀድ ነው።

## እግዚአብሔር ዝም ሲል

በዘመናት ሁሉ ያለፉ የበሰሉ ክርስቲያኖች የሚመሰክሩት አንድ እውነት አለ። ይኸውም በክርስትና ሕይወት ዘመን እግዚአብሔር ዝም ያለ የሚመስልባቸው ጊዜያቶች እልፎ እልፎ መኖራቸው ነው። በሕይወታችን እግዚአብሔር ዝም ያለ ከመሰለን እንግዲህ ብቻችንን አይደለንም፤ ብዙ ታላላቅ የተባሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ የሚያልፉበት ወይም ያለፉበት ልምምድ ነው።

እግዚአብሔር ዝም ስላለን ብቻ እኛም እነኚያ መንፈሳዊ ሰዎች የደረሱበት ደርሰናል ማለት ባይሆንም ዝምታው ግን በእነርሱ ዘንድ ያመጣውን ስሜት ነው ወደ እኛም የሚያመጣው። የዝምታው አላማ ወይም ግብ ለኛ ለእድገት ለብስለትና ለክብር ይሆን ይሆናል፤ የዝምታው ጊዜ ግን የከባድ ፈተና ጊዜ ነው።

ፍሎይድ ማክሊንግ "Finding Friendship with God" በሚለው መጽሐፋቸው ይህንን እሳብ በሚመለከት እንዲህ ብለው ጽፈዋል። "አንድ ቀን ጠዋት ከእንቅልፋችን ስንነሳ መንፈሳዊነታችን ሁሉ ይጠፋብናል። እንፀልያለን የሚሆን ነገር ግን የለም፤ ሰይጣንን እነገስጻለን የሚለወጥ ነገር አይኖርም፤ መንፈሳዊ ልምምዳችንን ሁሉ እናከናውናለን...የምናውቃቸውን እንዲፀልዩልን





እንጠይቃለን...በሕይወታችን ያለ የመሰለንን ኃጢአት ሁሉ እንናዘዛለን፤ ያስቀየምናቸው የመሰሉንን ሁሉ ይቅርታ እንጠይቃለን፤ እንጾማለን ግን ምንም ለውጥ አይኖርም። ይህ መንፈሳዊ ጨለማ እስከመቼ ነው የሚቆየው? ለቀናት፤ ለሳምንታት፤ ለወራት፤ ጭራሹኑ ማብቂያ አይኖረው ይሆን እንዴ? ኧረ ምን ሆንኩ? እያልን የጭንቀት ጩኸት እናሰማለን" ምንም የሆናችሁት ነገር የለም። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ጓደኝነት የማደግና የመብሰል ደረጃ ነው። እያንዳንዱ ታዳጊ ክርስቲያን እሕይወት ዘመኑ ቢያንስ አንዴ ብዙ ጊዜ ግን ከአንዴ በላይ የሚያልፍበት የእድገት ደረጃ ነው። ኢዮብ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ባለፈበት ጊዜ ነው እንዲህ ያለው

> *"ዳሩ ግን ወደ ምሥራቅ ብሄድ በዚያ የለም፤ ወደ ምዕራብ ብሄድ አላገኘውም፤ በስሜን እየሠራ ሳለ አላየውም፤ ወደ ደቡብ በሚዞርበት ጊዜ ደብዛው አይገኝም። ግን እኔ የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ።"* ኢዮብ 23፥ 8-10።

አንዳንዶች ከምንም በላይ የከበዳቸው ፈተና እንደነበር ይናገራሉ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ዝም ባለበት ጊዜ ጠላት ብዙ ያወራል፣ ጮክ ብሎ ይናገራል፣ ቀልባችንንም ይይዛል። የእውቀት ባህሪያችን መረዳት በሚችለው እግባቢ መንገድ ሰይጣን ይናገራል። እግዚአብሔርም ዝም ያለበትን ምክንያቶች ይሰጠናል። በጣም ስላሳዘነው ለመጨረሻ ጊዜ ከኛ እንደተለየ ይነግረናል፣ መድረስ የማይገባን ቦታ ስለ ደረስን፣ ማድረግ የማይገባንን ስላደረግን፣ መሆን የማይገባንን ስለሆንን እግዚአብሔር ሊደርስልን የማይችል ቦታ እንደሆንን ሊያሳምነን ይጥራል። 'እግዚአብሔር ለአንተ ግድ የለውም፣ ግድ ቢለውማኖሮ ጸሎትህን ይመልስ ነበር፥ ከታላቁ የእግዚአብሔር ፕሮግራም አንጻር ሲታይ የአንተ ሕይወት ኢምንት ነው እኮ፤ … እንዲያው ተሞኝተህ ነው እንጂ እግዚአብሔር የሚባል የለም፣ … እግዚአብሔር ቢኖርም ይህ ፈቃር፣ ሩህሩህ አንተን በግል የሚከታተል የሚሉህ ሐተታ ሁሉ ሰው ሰራሽ ነው' ይለናል። ጥርጥር ይፈጠርብናል፥ስለራሳችን ጥርጥር፣ ስለ እግዚአብሔር ጥርጥር'…ጥፋቱ የኔ ነው፣ ችግሩ የእግዚአብሔር ቸልተኝነት ነው' እያለ ጠላት ያንሾካሹካል። ይህ ጊዜ በጣም አስቸጋሪ የሚሆነው፣ ሌሎችም ሰዎች በክስ እና በወቀሳ አይን

ሊያዩን ይጀምራሉ። የቅርብ ጓደኞቻችን እንኳን ሳይቀሩ በኛ ላይ የሚደርሰው ነገር አልገባ ሲላቸው የጥያቄ አመለካከት ነው የሚኖራቸው "ጢስ ባለበት በዚያ እሳት አለ" እንደሚባለው አይነት ማለት ነው። ሁላችንም ኃጢአት ስላለብን ደግሞ ለሰዎች የሚቀላችው በኃጢአታችን እየተቀጣን እንደሆነ አድርጎ መገመት ነው። እግዚአብሔር ዝም ያለ ሲመስለን ግን ከራሳችን አንጻር ማድረግ የሚገቡንን አንዳንድ ነጥቦች እንይ፣

ሀ. መንፈስ ቅዱስን ያሳዘንበት ነገር እንዳለ ለማወቅ ራስን መመርመር፤ ይህ ብዙ ጊዜ የሚወስድ አይደለም። በትህትናና በእውነተኛ መንፈስ ከቀረብን እግዚአብሔር ወዲያው ያሳየናል። ጥፋተኛ ሆነን ራሳችንን ባገኘነው ነገር ላይ ወዲያው ንስሐ መግባት፣ ሐጢአታችንን በክርስቶስ ደም እንዲሸፈንልን ለጌታ መንገር፤ የኃጢአታችን ዋጋ ደግሞ የተከፈለ ስለሆነ ለጌታ ይቅርታ መስጠት ደስ ይለዋል።

ለ. እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚሰራው ማንኛውም ነገር ለመልካም እንደሆነ ማመንና፣ ይህ ዝምታም በራሱ ይዞት የሚመጣውን መልካም ነገር ለማግኘትና ለመቀበል መዘጋጀት።

ሐ. የዝምታው ጊዜ ቢረዝምም፣ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር መሆኑን፣ በራሱም ጊዜ ወደ መጨረሻ እንደሚያመጣው ማመን።

መ. መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖቻችንን ከመለማመድ አለመቆጠብ፤ እነኚህም ጸሎት፣ ቃሉን ማንበብ፣ እግዚአብሔርን መታዘዝ፣ ህብረት፣ ምስክርነት፣ አለታዊ ዲሲፕሊኖች ናቸው።

ሠ. ሕይወትን መኖር (ቆሞ መጠበቅ ሳይሆን)

ልብ አድርጉ እነኚህ ስድስት ደረጃዎች በሙሉ የእምነት ደረጃዎች ስለሆኑ ይህንን በምናደርግበት ጊዜ በስሜት የሚሰማን ወይም በአዕምሮ የምንረዳው ነገር ላይኖር ይችላል።





እንድሩ መሬይ (Andrew Murray) "ምስጢሩን አገኙት" (They Found the Secret) በተባለው ጽሁፋቸው ይህንን አሳብ በጥሩ ምሳሌ ገልጸውታል

በመጀመሪያ "እዚህ ያመጣኝ እርሱ ነው፣ እዚህ ምድረ በዳ የደረስኩት የእርሱ ፈቃድ ስለሆነ ነው፤ በዚህ እውነት እርፋለሁ።

ቀጥሎ "እዚህ እስካለሁ ድረስ በፍቅሩ ይጠብቀኛል፤ እንደ እግዚአብሔር ልጅ እንድመላለስም ጸጋውን ያበዛልኛል።

ከዚያም "ፈተናውን በረከት ያደርግልኛል፣ ልማር የሚገባኝን ትምህርት እንድማርበት ይረዳኛል፣ በውስጤ ሊያበዛ ያሰበውንም ፀጋ እያበዛ ይሰራኛል።

በመጨረሻም "በራሱ ጊዜ ከዚህ ያወጣኛል፣ እንዴትና መቼ እንደ ሆነ እርሱ ብቻ ያውቃል። ስለዚህ እዚህ ቦታ ያለሁት

1. በእግዚአብሔር ቀጠሮ ነው
2. በእርሱ ጥበቃ ነው
3. በእርሱ ሥልጠና ስር ነው
4. ጊዜው የራሱ ነው

ይህ ወገኖቼ ሆይ እምነት ነው። ከፈተናና ከክስ ቀጥሎ ሶስተኛው መንፈሳዊ ውጊያ ትንኮሳ ነው።

## 3. ትንኮሳ (Harrassment)

ይህ ቃል በዚህ አግባቡ ብዙ ነገሮችን ያጠቃልላል። በተለይ ላንድ አገልግሎት ወይም መንፈሳዊ በረከት በምንዘጋጅበት ጊዜ ይህ የመተንኮስ ውጊያ ይፋፋማል። ብዙ ጊዜ ሁኔታው ቀላል ይመስላል። ሰውዬው ሰባኪ ከሆነ ልክ ከቤት ሊወጣ ሲል ማስታወሻ ደብተሩን ያጣዋል ወይ መብራቱ ይጠፋና ሌላ ኖት ይዞ ይወጣል።

ከብዙ አመታት በፊት የሆነ እውነተኛ ታሪክ ልንገራችሁ። ለአጭር ጊዜ ጎንደር

ያኔ ጤና ጥበቃ ኮሌጅ የሚባለው ትምህርት ቤት ገብቼ ነበር። በከተማው የሚኖሩ ዶክተር ሉዊስ የሚባሉ አንድ እንግሊዛዊ ሚሲዮናዊ የአይን ሃኪም ነበሩ። እሁድ እሁድ ማታ በቤታቸው ውስጥ በተለይ ለውጪ ዜጋዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የወንጌል ስብሰባ ያካሂዱ ስለነበር አንዳንዴ እኔና አንድ ጓደኛዬ (ተፈራ ድንቁ) እንሄድ ነበር። ዶክተር ሉዊስ የስብከቱን ፕሮግራም አንዳንዴ ጎንደር ሁለተኛ ደረጃ ለሚያስተምሩ የህንድ ዜጋ አስተማሪዎች ይሰጡ ነበር። አንድ እሁድ ፕሮግራም የተሰጠው ወጣት የኬሚስትሪ አስተማሪ ነበር። የስብከት ልምምድ ስላልነበረው ስብከቱን በወረቀት ጽፎ ለማንበብ ተዘጋጅቶ ነበር የመጣው። ግን የዛን እለት ማታ በከተማው ውስጥ መብራት ጠፍቶ ነበር። ሁላችንም እንደምንም ተደነባብረን ደረስን። የስብከቱ ሰአት ደርሶ አዲሱ ሰባኪ በፍርሃትና በድንጋጤ ተነስቶ ወረቀቱን ማንበብ ጀመረ። ይዞ የመጣው ግን የኬሚስትሪ ኖቱን ነበር።

To prepare oxygen in the laboratory Potassium Chlorate and Manganise dioxide......" ሰባኪው ከመደናገጡ የተነሳ ምን እንደሚል እንኳን አላስተዋለም። ኦክስጂን የተባለውን ንጥረ ነገር እንዴት በላቦራቶሪ ማዘጋጀት እንደሚቻል አነበበልን። ዶክተር ሉዊስ "I think you are reading the wrong side of the paper" (ወረቀቱን ያዞርከው የመሰለኛል) ከዚያ ሰባኪው ወረቀቱን ገልብጦ ማንበብ ቀጠለ (Oxygen is collected by the downward displacement of water). ሰባኪው ሊቀጥል ነበር። ዶክተር ሉዊስ አቋረጡትና "ዛሬ እግዚአብሔር ስለ ኦክስጂን እንድንማር የፈለገ ይመስለኛል" ብለው አሳቁን። ሰባኪው ግን ለረጂም ጊዜ አፍሮ ከስብሰባ ቀረ። በዶክተር ሉዊስ ጥረት ነው ወደኅብረቱ የተመለሰው። የመብራት መጥፋት ነው አስተማሪውን የተተናኮሰው።

ትንኮሳ ከባድ ላይሆን ይችላል፤ እንዲያው እንዳይመቸን የሚያደርጉ ትንንሽ ነገሮች ይሆናሉ። በድምራቸው ግን እምነታችንን እንድንጠይቅ፣ መንፈሳዊ ዲሲፕሊናችንን ችላ እንድንል የሚያደርጉ ይሆናሉ። ትልቅ መንፈሳዊ ስብሰባ በተዘጋጀ ቀን ጉንፋን የሚይዛቸው መሪዎች አታውቁም? ወይ ስብሰባው ሊጀመር አስር ደቂቃ ሲቀረው ጎማ ፈነዳብኝ ብሎ የሚደውል ፕሮግራም መሪ አላጋጠማችሁም? ትንኮሳ በትንሽ





ይጀምርና ደረጃ በደረጃ የሚያድግ ይሆናል።

## የህመም ምልክቶች

በትንሽ ጀምረው ደረጃ በደረጃ ለሚያድጉ ምሳሌ ብሰጥ፣ ጠዋት ስንነሳ ከነሰረን እኛ ደግሞ ሳናውቅ እናሳድገዋለን። "ሊያመኝ ነው መሰለኝ" ብለን እንናገራለን። ጠላት ደግሞ ያንን ይሰማል፣ (ልብ አድርጉ ሰይጣን የምናስበውን ሳይሆን የምንናገረውን ብቻ ነው ሊያውቅ የሚችለው)። ሰይጣን ይህንን ሲሰማ ዘር ለመዝራት ይበቃዋል። እሺ ብለን ካስተናገድነው ደግሞ ዘሩ ይበቅላል። በእርግጥም መታመም እንጀምራለን። ዘሩን ገስጸን ካስወገድነው ግን በሽታው ይጠፋል። ይህንን ነገር ብዙ አገልጋዮች በሕይወታቸው የለመዱት ስለሆነ ሊመሰክሩላችሁ ይችላሉ። በተለይ አንድ ትልቅ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመስራት ሲዘጋጁ ይህ ስሜት ይመታቸዋል።

## ድብርት (Depression)

አንዳንዴ ደግሞ በራስ ደስ ያለመሰኘት ስሜት ይይዘናል። ራሳችንን ዝቅ አድርጎ መመልከት፣ ነገር አልጥም የማለት፣ የመሰልቸት ስሜት ይመጣብናል። ጠላት ደግሞ ያንን ወስዶ ያፋፍመዋል፣ ምክንያቱን ሳናውቅ ብስጭት ብስጭት፣ ቁጣ ቁጣ ይለናል። ድብርት ፈርጁ ብዙ ነው። የዚህ አይነት አሳቦች ሲመጡ መገሰጽ አለባቸው፣ ልንረዳቸው መሞከር፣ ምክንያታቸውን መፈለግ በሁኔታው እንድንቆይ ከማድረጉ ሌላ የሚያደርገው የለም። የሚደበር መንፈስ ሁሉ መድኃኒቱ የጌታ የየሱስ ስም ብቻ ነው፣ ስሙ ሲጠራ የጠላት ኃይል ሁሉ ይፈርሳል። ስትገስጹም ታዲያ ድምጻችሁን አውጥታችሁ መሆን አለበት፣ ጠላት እንዲሰማ።

## ድካም

አንዳንዴ ድክም ይለንና የእግዚአብሔር ሥራ የሚከብደን ጊዜ የለም? አንዴት ምዕራፍ የእግዚአብሔር ቃል ማንበብ ያቅተንና ወደ ጋዜጣ ወይ መጽሔት ዞር ስንል ግን አንብበን ጨራርሰን የምናነበው ያልቅብን የለም? ይህም የሰይጣን ትንኩሻ ነው። ለማታው ስብሰባ ለመሄድ ድክምክም ይለናል፤ ቦታውም ይርቅብናል፤ የማታው ግብዣ ግን ቦታው ከዚያም ቢርቅ ቶሎ አልደርስ ይለናል። ይህ መንፈሳዊ ውጊያ

ነው። ገስጹት፣ ደጋግማችሁ ገስጹት።

## የቁሳቁስ ውጊያ

“ምግቤን ሰርቼ እንዳልበላ ይኸው ሰይጣን ቢላዎውን ደበቀብኝ” ብሎ ተበሳጨ አንድ ወንድም፣ ቤቱ ለጸሎት ተሰብስበን ሥጋ ጠብሶ ሊያበላን እየከታተፈ ነበር። ወጣ ብሎ ሲመለስ ግን ሲከትፍበት የነበረውን ቢላዎውን ማግኘት ስላልቻለ ተበሳጭቶ ነው እንዲህ ያለው፤  ከተሰበሰብነው አንዱ ታዲያ “ወንድሜ ሰይጣን ቢላዎ በማቀበል እንጂ ቢላዎ በመደበቅ ብዙ ስለማይታማ እስቲ ቀስ ብለን እንፈልገው” አለው። ግን የአስተናጋጃችንም ብስጭት እውነትነት አለው።

ሰይጣን በቁሳቁስ ውጊያም ሰዎችን ይተናኮሳል። የእቃዎች መጥፋት፣ ወይ መሰበር በተለይ የእግዚአብሔርን ጊዜ ጠብቆ አዲስ ነገር አይደለም። ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ስንነሳ ደህና እቤት ድረስ መጥቶ የቆመው መኪና አልነሳ ይላል። ቀኑን ሙሉ ሲሞከር በደንብ ይሠራ የነበረው ድምጽ ማጉያ መሪው ወጥቶ እምልኮ ሲጀመር ወይ ጩርሶ ይጠፋል፣ ወይ እሪ ብሎ መጮህ ይጀምራል። ቤተ ክርስቲያን ምነው ቀራችሁ ስትሏቸው ቁልፌ ጠፍቶብኝ ነው የሚሉ ብዙዎች አላጋጠማችሁም? አንዳቸውም ግን በቁልፍ መጥፋት ምክንያት ከሥራ የቀሩ አይመስለኝም። እነርሱም ምክንያት ማብዛታቸው ብቻ እኮ አይመስለኝም፣ ስለደረሰብኝ አውቀዋለሁ። መኪናው እምቢ አልነሳም ብሎ የሚገስጸውን ሞኝ መስሎኝ ፈዝዤ ሳየው ሳለ መኪናው ተነስቶለት ሲፈተለክ ሞኙ እኔ መሆኔን አወቅሁ። ይሄ የጌታ ስም ለካ መካኒክነትም ያውቅበታል። ጠላት በቁሳቁስም ላይ መምጣት ይችላል፣ ተቃውሞ ማባረር ደግሞ ሥልጣናችን ነው።

## የመግባባት ችግር

ሌላው የሰይጣን ትንኩሻ አለመግባባትን በመፍጠር ነው። “ለትልቅ መንፈሳዊ ዝግጅት ወደ አርጀንቲና ለመሄድ ሁለት ሳምንት ሲቀረን እኔና ባለቤቴ መነጋገር አቃተን” አሉ ማይክ ፍሊን ሲጽፉ፣ “አንድ ቋንቋ መነጋገራችን እንኳን አጠራጣሪ ሆነ። እርሷ በቀጥታ የተናገረችውን እኔ የምሰማው በሌላ ትርጉም ነው፣ እኔ የተናክርኩት ተቃራኒው ነው ለእርሷ የሚገባት። በዚህ ልውውጥ ውስጥ ጥቂት ቀናት





አሳለፍን። አንድ ቀን ግን ሁለታችንም የሚሆነው ገባንና ተሳሳቅን። የሰይጣን ትንኮሳ እንደሆነ ገባን፣ ስለዚህ ወዲያው ይቅርታ ተጠያይቅን ሰይጣንን መገሰጽ ጀመርን።

## ሥጋ አቅሙን ሲያሳይ

በትንሹ ትበሳጫላችሁ? እስቲ የሚያበሳጫችሁን ነገር ቆም ብላችሁ አስላስሉት፤ እንዲህ ስታደርጉ አንዳንዴ ከጠላት መሆኑን በግልጽ ታውቃላችሁ። በአንዳንድ ሁኔታ ላይ የሚታያችሁ ሁል ጊዜ አለመሳካቱ ብቻ ነው? ምንም እንኳን የበለጠው ክፍል በስኬት ቢሰራም? ትልቁን ትልቅ ትንሹን ደግሞ ትንሽ (majoring in majors and minoring in minors) አድርገን ማየት እንችልበታለን? “ተጎዳሁ፣ ተሰበርኩ” ማለት እናባዛለን? ሌሎች በተማሩበት ትምህርት እኛ እንሰደብበታለን፣ በተጠጉበት እንሰበርበታልን? ለእንዲህ አይነቶቹ የስጋ ትንኩሳዎች መፍትሄዎቹ የመንፈስ ፍሬዎች ናቸው። የመንፈስ ፍሬዎችን በሕይወታችን ስንለማመድ የሥጋ ሥራዎች እየከሰሙ ይሄዳሉ። ምክንያቱም አንዱ በገነነበት ሌላው መቆየት አይችልም።

## 4. የእውቀት ውጊያ

አራተኛው የሰይጣን የሚንበለበል ፍላጻ ማታለል ነው። ማታለል በእውቀት ላይ ያተኮረ ውጊያ ሲሆን አላማው እማኙን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱ ላይ ለማናጋት ነው። ማታለል ለእውቀትና ለምክንያት ባህሪ እንዲስማማ ተደርጎ፣ በጥናት ተደግፎ፣ ዝነኛ በሆኑ ሰዎች ተናጋሪነት በቅልጥፍና ሲቀርብ ብዙ ጊዜ አይተናል። “አምላክን ፍለጋ” በተባለው በቅርቡ በሚወጣው ሌላው መጽሐፌ የምሥራቅ እምነቶች ይህንን ዘዴ በመጠቀም እንዴት የምዕራብን የሲኒማና የፋሺን መዲና ሆሊ ዉድን እንደወረሱት ጠቅሻለሁ። ዛሬ በአክተርነታቸው ልባችንን በሰረቁና በምናደንቃቸው የስፖርት ሰዎች ደጋፊነትና አስተዋዋቂነት ተደግፎ የወጣ ዘመቻ (campaign) አለ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋም ምክንያታዊ አይደለም፤ ያልሰለጠኑ ሰዎችአመለካከት፣ የኋላ ቀሮች ወይም የአክራሪ ሰዎች አቋም ነው ይሉናል፤ እቤት ሳሎናችን ድረስ መጥተው ይህን ይነግሩናል።

የዚህ ውጊያ ዋና ትኩረቱ እኛ ላይ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ላይ

ነው። በገነት ውስጥ ሰይጣን በእባብ ተመስሎ ለሔዋን ያለት ያንን ነው ዛሬም የሚደግምልን።

*"በእርግጥ እግዚአብሔር ... ብሏልን?" ዘፍጥረት 3፥ 1።*

የሔዋን መልስ መሆን የነበረበት "አዎን፣ ልክ እንደዚያ ነው እግዚአብሔር ያለው፣ ስለዚህ እኔ ከአንተ ጋር መነጋገር አያስፈልገኝምና ከጠግቤ ሂድ" ነበር።

እግዚአብሔር ያለውን መጠየቅና አጠራጣሪ ማድረግ የጠላት የመጀመሪያ እርምጃዎቹ ናቸው። ምክንያቱም የእምነት መሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል ነው

*"እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው፣ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው" ሮሜ 10፥ 17።*

በእርግጥ እኛ ለቃሉ ያለን ትርጉም አንዳንዴ ስህተት ውስጥ ይከተን ይሆናል። ማስታወስ ያለብን ግን የእግዚአብሔርን ቃል የጻፈው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመግለጽ መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገናል። የኛ ውሳኔ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በመረዳት ለማደግና ጌታን ለመከተል ከሆነ፣መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ይመራናል፣ ያስተካክለናል፣ ያበረታታናል፣ይፈውስናል፣ ይባርከናል።

ጠላት ግን በቃሉ ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረን ማድረግ ከቻለ ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበትን ዋና መንገድ አያበላሸው ነው። እግዚአብሔር ለቃሉ የሚሰጠው ቦታና ጥንቃቄ በጣም ከፍ ያለ ነው። ቃሉ ከእርሱ ጋር ያለውን አንድነት ለመግለጽ ነው ጌታ የሱስ ሥጋ የለበሰው ቃል ተብሎ የተጠቀሰው

*"ቃልም ሥጋ ሆነ፣ በመካከላችንም አደረ፣ ፀጋንና እውነትንም ተመልቶ ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጁን ክብር አየን" ዮሐንስ 1፥ 14።*

ለእግዚአብሔር ያለን ክብር የሚለካው ለቃሉ በምንሰጠው ክብደት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር እምነትን ማናጋት ነው። ለምሳሌ

ጠያቂ፥ "ጌታ የሱስ ከሞት ተነስቷል ብለህ ታምናለህ?"





መላሽ፥ "አዎን"

"እንዴት ሊነሳ ቻለ? እስቲ አስረዳኝ"

"እንዴት ሊነሳ እንደቻለ እኔ አላውቅም፣ መነሳቱን ለማመን ግን እንዴት እንደተነሳ ማወቅ የለብኝም። ቃሉን ማጥናት፣ ማሰላሰልና ማንበቤን እቀጥላለሁ፤ እግዚአብሔር እንድረዳው የሚገልጥልኝን እውነት በመረዳት አድጋለሁ፣ ወደ አለማመን የሚገፋኝን መረዳትም ሆነ አለመረዳት ግን እቃወማለሁ"።

## 5. የፈቃድ ውጊያ

ፈቃድ የእምነት መሰማሪያ ቦታ ነው። ቀደም ብለን ያየነውን ስዕል እስቲ ትንሽ አሻሽለን እንየው። በስዕሉ ውስጥ መንፈስና ፈቃድ የተዘጉት ሰይጣን ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ከእነርሱ ጋር እንደሌለው ለማሳየት ነው። መንፈስ የሰው ልጅ ውስጠኛው ክፍል ነው። መንፈስ በሰይጣን ሊታለል የሚችለው በፈቃድ በኩል ነው። ኃጢአት ለማድረግ የሚወስነው ፈቃድ ነው። ኃጢአት ሳደርግ መንፈሴ ይቃወማል፣ የሕሊና ወቀሳ የምንለው ያንን ነው። የሕሊና ወቀሳ መንፈስ የሚጫወተው ሚና ነው። እግዚአብሔርን ባለመታዘዜ ከእርሱ ጋር ያለኝ ህብረት ሲቋረጥ መታረቅ ያስፈልገኛል። ህሊናዬን እምቢ ብዬ ከሄድኩ የመንፈሴ መታወክ ወደሌላው ክፍሌ እየተሰራጨ ይሄዳል፤ ያ ሲሆን በአካሌ እታመማለሁ፣ በመንፈሴ እረበሻለሁ፣ በአዕምሮዬ እመሰቃቀላለሁ።

ስለዚህ የሰይጣን ዋናው ትኩረት መንፈሳችን ላይ ነው። ኃጢአት እንድንሰራ ማድረግ ከቻለ ከሰማያዊው አባታችን ጋር ያለንን ኅብረት ማናጋት ችሏል ማለት ነው። ራሳችንን በማታለልና በማመጽ በዚያው እንድንቀጥል ካደረገ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ላይ ከባድ ጥፋት ሊያደርስ ይችላል፤ ያ ከሆነ ደግሞ ለእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይነት ያለን ጥቅም በጣም ያነሰ ይሆናል።

እግዚአብሔር ግን ሲሰራን እንደብልህ ግንበኛ ነው የገነባን። የመንፈስ ቅዱስ መኖሪያ የሆነው መንፈሳችን ከሰይጣን እርቆ ስለ ሰራው፣ ሰይጣን መንፈሳችን ጋ ሊደርስ የሚችለው በፈቃዳችን በኩል ብቻ ነው። ፈቃዳችን ደግሞ ሊደረስበት የሚችለው

በአዕምሯችንና በስሜታችን በኩል ነው። ይህ ከሆነ ለሰይጣን ውጊያ የአሰራር አላማው ፈቃዳችን ነው። አምስተኛው የሚንበለበል ፍላጻ ታዲያ የሚቀሰተው ፈቃዳችንን ለመምታት ነው።




ፈቃድ በቀጥታ ከሚመጣው ቀስት የተከለለ ነው። ከመንፈሳችን ጋር በመገናኘቱ ሊደረስበት ቀላል አይደለም። አሠራሩ እንዲህ ነው። የውሳኔ ችሎታ ያለው በፈቃድ ውስጥ ነው። ፈቃድ ውሳኔ ለማድረግ የሚያስችሉትን አሳቦች ከተለያዩ ቦታዎች ያገኛል። መንፈስ የሚለውን፣ አዕምሮ የሚለውን፣ ስሜት የሚለውን፣ ሥጋና አለም የሚሉትን ሁሉ ያዳምጣል። የፈቃድ ውሳኔ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ከሆነ መነሻው ከመንፈስ ነው። ውሳኔውም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ውሳኔው እግዚአብሔር ያለውን የሚቃወም ከሆነ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የሆነ ውሳኔ ይሆናል አላማውም ጥፋት ነው።





ለዚህ ሚና የምንጠቀመው ቃል እምነት ይባላል። እግዚአብሔር ሲሠራን ያደረገው እምነት ሊሠራ የሚችለው በፈቃድ ውስጥ ብቻ እንዲሆን አድርጎ ነው። እምነት ስሜት አይደለም፣ እምነት እውቀትም አይደለም። እምነት በፈቃድ የሚደረግ የውሳኔ ጉዳይ ነው። ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ቢሊ ግርሃም እንዲህ ያሉት ለዚህ ነው "ውሳኔ በእንግሊዝኛ ቋንቋ (ለኛ ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ) አስፈላጊው ቃል ነው"። ጌታ የሱስ ክርስቶስን ወደ ልብ ለማስገባት የሚደረገው ውሳኔ በጊዜያዊነቱም ሆነ በዘለአለማዊነቱ አጠያያቂ የሌለው ዋነኛው ቁም ነገር ነው።

ፈቃድ አንድ ጊዜ ዘለአለማዊ የሆነ ውሳኔ ወስኖ ቁጭ ማለት አይችልም። ፈቃድ ሁልጊዜ ከጠላት ግፊያ ይደርስባታል ወይም አለበት። ውሳኔውንም እንዲቀይር ብዙ ማግባቢያዎችና መገፋፊያዎች ይቀርብለታል። ውሳኔውን ከቀየረ እምነትን ለወጠ ማለት ነው። ለዚህ ነው ያለማቋረጥ ውሳኔን ማጥበቅ፣ ማረጋገጥ፣ ማደስ፣ ማሳደግ ያለብን።

ሰይጣን ደግሞ ይህንን አሳምሮ ያውቃል። እምነት የሚሠራው በፈቃድ እንደሆነ ይረዳል። ከፈቃድ ጋርም ቀጥተኛ ግንኙነት እንደሌለውም ያውቃል፤ ስለዚህ በቀጥታ ሊደርስባቸው የሚችለውን ክፍሎቻችንን በመጠቀም ፈቃዳችን ጋ ለመድረስ ይሞክራል። ከእነኚህ እርሱ ሊደርስባቸው ከሚችለው ክፍሎቻችን (አካል ወይም ሥጋ፣ አዕምሮና ስሜት) ስዕሉን ስትመለከቱ ቀስቶቹ ወደ ፈቃድ ተቀስተው ታያላችሁ። የሚንበለበሉት የሰይጣን ፍላጻዎች (ቀስቶች) በየት በኩል አድርገው እንደሚመጡ ለማሳየት ነው። ሰይጣን ሊያደርግ የሚፈልገው ይህንን ነው። አካልን አዕምሮንና ስሜትን ተጠቅሞ ፈቃድን በማግባባት የራሱ የሆነ ውሳኔ ለማስወሰን ነው። ልብ አድርጉ ውሳኔውን እንድንወስን ሊያደርገን አይችለም፤ ይህንን ነጥብ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

አካላችንን፣ አዕምሯችንና፣ ስሜታችንን እንዴት መጠበቅ እንዳለብን እስቲ እንይ። አካላችን በመንፈሳዊም ሆነ በተፈጥሯዊ አቋሙ ዲስፕሊን ሊኖረው ይገባል። በመንፈሳዊው ረገድ ቁጭ ብሎ የእግዚአብሔርን ቃል የማንበብና የማድመጥ ዲሲፕሊን፣ ጉልበትን በእግዚአብሔር ፊት የማንበርከክ ዲስፕሊን፣ በቃልም ሆነ በሕይወት ክርስቶስን የማንጸባረቅ (ምስክርነት) ዲስፕሊን፣ እግዚአብሔር እንዳለ

እንዳዚያ ለመኖር የመጣር ዲስፕሊን፣ ይህም "እምቢ" ማለት ለሚገባን ነገር እምቢ የማለት ዲስፕሊን፣ ማድረግ የሚገባንን የማድረግ ዲሲፕሊን፣ መስጠት የሚገባንን የመስጠት ዲስፕሊን፤ ይህ መንፈሳዊ ዲስፕሊን ነው።

ተፈጥሮአዊ ዲስፕሊን ከመንፈሳዊ ጋር የተያያዘ ነው። ለምንበላውም ሆነ ለምንጠጣው ለምንለብሰውም ሆነ ለምናጌጥበት ነገር ተገዢ አለመሆን ማለት ነው። መቼም ምግብን ባለመቆጣጠር የሚመጣው ጦስ ባሁኑ ጊዜ ምግብ በማጣት ከሚመጣው ጦስ እኩል እየሆነ ነው።

የጤንነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለራሳችን ያለን ክብርም እየቀነሰ ስለሚሄድ፣ ዲፕሬሽን ወስጥ ገብተን መጉላላት እንጀምራለን። ወደ ሰውነታችን ውስጥ በምናስገባው ሱስ በሚያሲዙ መጠጦችና እፆች አካላችን ከተገዛ ብዙ ሳይቆይ ነገሮች ከቁጥጥራችን ውጪ ይሆናሉ።

በዚህ ሁሉ የድራግ (እፅ) ጦርነት በሚደረገው ደም መፋሰስ የሰይጣን እጅ የሌለበት ከመሰለን መንፋሳዊ አመለካከታችን ሊስተካከል ይገባዋል። መልበሳችንና ማጌጣችን በአንድ በኩል ራሳችንን ማክበራችን ስለሆነ በዲስፕሊን እስከተደረገ ድረስ ውበት ይጨምርልናል። በተቃራኒው ደግሞ እንዲያው ሆሊዉዶች አድርገውታል፣ ወይም በቲቪ ቀርቧል ብለን ራስን የወሲብ ሸቀጥ (sexual commodity) የሚያስመስል ልብስና ጌጥ አድርጎ አደባባይ መውጣት ከዲስፕሊን ውጪ መሆን ማለት ነው። የዚህ አይነት አለባበስ ደግሞ በተለይ አሁን አሁን በእግዚአብሔርም ቤት እየተስፋፋ ነው። ሰይጣንም ያንን ሁኔታ ለራሱ የሚጠቀምበት መንገድ አለው።

አዕምሯችን የጠላት ማግባባት ከሚደርስባቸው ክፍሎች ሌላው ነው። አዕምሮ የእውቀት (Information) መከማቻና መገናዘቢያ ቦታ ነው። እውቀት ደግሞ በአምስቱ የእውቀት መቅሰሚያ መንገዶች፤ በማየት፣ በመስማት፣ በማሽተት፣ በመቅመስና በመዳሰስ ነው ሊዳብር የሚችለው። በየትኛውም የእውቀት ደረጃ ላይ ያለ ሰው፣ ከፊደል ቆጠራ እስከ ፒ ኤች ዲ እውቀት የሚቀስመው በእነኚህ መንገዶች ነው። አመለካከታችንንም የሚቀርጸው በእነኒህ መንገዶች ባካበትነው እውቀት





ነው። ሰዎች ስለ ኮምፒውተር ሲያወሩ (garbage in garbage out) ይላሉ። የኮምፒውተሩ ችሎታ ባስገባነው ዳታ ጥራት ላይ የተመሰረተ ነው ለማለት ነው።

የእውቀታችንም ጥራት ባካበትነው ኢንፎርሜሽን ጥራት ላይ የተመሠረተ ነው። በሴኩላር ትምህርት በተለይ በምዕራቡ ከፍተኛ የእውቀት ተቋማት ውስጥ እምነትን የመቃወም አድልኦ (bais) ስላለ እውቀታችን እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚገፋፋን ሳይሆን ወደተቃራኒው የሚያደላ ነው። ሰይጣንም ያንን አድል በደንብ ይጠቀምበታል። ስለዚህ ነው እምነትን በሚመለከት ሙሉ በሙሉ በሴኩላር እውቀታችን ላይ መመርኮዝ የማንችለው፤ ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ ላይ የደረሱ እንኳን እምነትን በሚመለከት አልተማሩም ከሚባሉ ሰዎች መማር የሚችሉትም ለዚህ ነው።

ስሜት ጠላት ከሚያግባባቸው የእኛነት ክፍላችን ሌላው ነው። የስሜታችንን ውጤት ልንቆጣጠረው እንችላለን፣ ወይም ስሜታችን ሊቆጣጠረን ይችላል። ካልተቆጣጠርነው ንዴት፣ ብስጭት፣ ቁጣ፣ መደበር ይፈራረቁብናል። ሰይጣን ደግሞ እንኚህን ሁኔታዎች እያፈራረቀ ካንዱ ወደ ሌላው እየገፋፋ ያታክተናል። በስሜታችን ተገፋፍተን የምንወስዳቸው እርምጃዎች በጣም ወሳኞች ናቸው። ስሜታችንን ሊገራውና ሊያስተካክለው የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ ውስጥ የአካልን፣ የአዕምሮንና የስሜትን አሰራር ነው የተገለጸው የሥጋ ሥራ ብሎ የዘረዘረው።

> *"የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው፤ ይኸውም ዝሙት ርኩሰት መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኝነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እንዲሁም ይኸን የሚመስለው ነው።" ገላትያ 5፥ 19-20*

በአንጻሩ ደግሞ የመንፈስ ፍሬዎችን አከታትሎ በዚያው ስፍራ አስፍሯቸዋል።

> *የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው።" ገላትያ 5፥ 21-22።*

እዚህ ቦታ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ያደረገውን የቃላት ምርጫ ተመልከቱ። "የሥጋ ሥራ"፣ "የመንፈስ ፍሬ"። ሥራ ወዲያው ተወስኖ (impulsively) የሚደረግ ነው። ፍሬ ግን ጊዜ የሚፈጅ፣ ብዙ ዲስፕሊን የሚጠይቅ የመጨረሻ ውጤት ነው።

የበሽታን ምልክቶች በመጠቀም የበሽታን ዘር እንድንቀበል ጠላት እንዴት እንደሚገፋፋን ቀደም ብለን አይተናል። ጥሩ ምሳሌ ነው። ትኩረቱ ፈቃዳችን ላይ ነው። ፈቃዳችን እነኚያን ምልክቶችና አሳቦች ተቀብሎ እንዲስማማ ካደረገ ሥጋ ለመታመም ዝግጁ ነው። ውጋቱ ይወጥረናል፣ ቁርጠቱ ያጣድፈናል፣ ራስ ምታቱ ይዠቀዥቀናል። ፈቃዳችን ግን ምልክቶቹንና አሳቦቹን አልቀበልም ካለ ላለመታመም ያለን እድል የበለጠ ይሆናል።

ይህ ማለት ግን አካል፣ አዕምሮና ስሜት ጠላቶች ናቸው ማለት አይደለም። ግሩምና ድንቅ የእግዚአብሔር የእጅ ሥራ የሆነው ሥን ፍጥረት ክፍል ናቸው። ከሌላው ሥን ፍጥረታችን ጋር በሥን ፍጥረት ቀን "እጅግ መልካም" ያላቸው ናቸው ዘፍጥረት 1፥ 31። ነገር ግን የእምነት ባለ አደራዎች አድርጎ አልፈጠራቸውም። ያ የፈቃድ ሙያ ነው። ጠላት አካሌን አዕምሮዬንና ስሜቴን ተጠቅሞ ወደ ፈቃዴ ለመድረስ ሲሞክር፣ ፈቃዴን ተጠቅሜ እነኚህን ክፍሎቼን እምቢ እንዲሉ ማድረግ ሐላፊነቱ የእኔ ነው።

ምሳሌውን ከዚህ ተማሩ፣ ሁላችንም ልጆቻችንን በጣም እንወዳለን። ልጆቻችን ደግሞ የሚፈልጉትን ነገር እንድናደርግላቸው ሊያግባቡን፣ ሊያታልሉን ይሞክራሉ። አንዳንዴ በመሞላቀቅና በማልቀስ ይሞክሩናል። እንደዚያም ሲሆኑ እንወዳቸዋለን። ነገር ግን ያ ሁኔታቸው ውሳኔያችንን የሚያስለውጠን ከሆንን ልክ አይደለንም። ውሳኔያችን መሆን የሚገባው በእኛ ግምት ለእነርሱ መልካም የሆነ ከሌላው አላፊነታችን ጋር የሚስማማ በመሆኑ ነው።

አካላቴን እወደዋለሁ፣ አዕምሮዬን መጠቀም ደስ ይለኛል፣ ስሜቴን በመጠቀም ራሴን





እገልጻለሁ። እነኚህ ሁሉ ነገሮች ግን በራሳቸው የሕይወቴን አቋም የሚመለከት ውሳኔ እንዳደርግ ገፋፊዎቼ መሆን የለባቸውም። እነኚህ ክፍሎቻችን ወሳኞች አይደሉም፤ ውሳኔ የፈቃድ ተግባር ነው። ስለዚህ ጠላት አካሌን አዕምሮዬንና ስሜቴን በመጠቀም ፈቃዴን ሲታገል መቃወም አለብኝ፤ ውሳኔ የፈቃድ ብቻ ነው፣ ስለዚህ እምነት የፈቃድ ተግባር ነው። እምነት ውሳኔ ነው።

### በአጭሩ

ሰይጣን በጣም ተንኮለኛ ነው። የሰይጣንን ተንኮል አሳንሰን ካየን ስህተት እናደርጋለን። በሌላ በኩል ደግሞ የሰይጣንን ኃይል በማግነን ሌላ ስህተት መሥራት ይቻላል። ሰይጣን ኃይለኛ ቢሆንም ኃይሉ ከእግዚአብሔር ጋር ተመጣጣኝ አይደለም። ምናልባት የመላዕክት አለቃ ያህል ቢሆን ነው ኃይሉ ማወዳደር ካስፈለገ። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥና በእግዚአብሔር ኃይል ስር ሆነን ከሆነ የምንሠራው የሰይጣን በሮች ናቸው የእኛን ውጊያ መቋቋም የማይችሉት እንጂ የእኛ አይደሉም። የሚሸሸው እርሱ ነው፤ የእርሱን ውሸት "እህ" እያልን እስካላዳመጥን ድረስ፣ ከሰይጣን ጋር ያለን ግንኙነት ውጊያ ብቻ ነው። ሰላም ወይም የዕርቅ ድርድር፤ ብትለማመጠኝ፣ ብትሰዋልኝ፣ ብታመልከኝ ሁሉ የማታለያ መንገዶቹ ናችው።

# ምዕራፍ ሰባት

## የስህተት ትምህርቶች

(ኑፋቄ)

ትምህርት ሰዎችን በእምነት ለመገንባት፣ ለማሳወቅና ለማለማመድ እግዚአብሔር ከሚጠቀምባቸው ዋነኛ መንገዶች አንዱ ነው። አንድ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለአስተማሪዎች ስልጠና ሳካሂድ እንዲህ ብዬ የነገርኳቸውን ጽሁፍ ማስተማሪያ ደብተሬ ውስጥ አገኘሁት፣

ትምህርት የታቀደው እንዲረዳን እንጂ እንዲያደናቅፈን አይደለም። ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ስለሆነ ትምህርት ቅባት አለው። ለእኔ ደግሞ የማገለግልበት ስጦታዬ ስለሆነ ለልቤ በጣም ቅርብ ነው። እኛ የማስተማር ስጦታ ያለን አገልጋዮች ለምናስተምራቸው ሰዎች ያለን አሳብ ሁልጊዜ በጎ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። ነገር ግን የምናስተምረው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ሚዛኑን የጠበቀ፣ በልምምድ የተደገፈ፣ ለመጠየቅና ለመረጋገጥ ክፍት የሆነ ፣ ከመሪዎችም ሆነ ከምናገለግለው ምዕመን ሒሰም ሆነ እርማት ለማስተናገድ የተዘጋጀ፣ መሆኑን እርግጠኞች መሆን አለብን። ያ ካልሆነ ሰዎችንም ሆነ ራሳችንን ይዘን ከመጥፋት የሚጠብቁንን ማሰሪያ ቀበቶዎች አበላሸን ማለት ነው። የአገልግሎቱን አላፊነት ለማጥበቅ ያዕቆብ በግልጽ እንዲህ ብሎ ነው የጻፈው፣

> *"ወንድሞቼ ሆይ ከናንተ ብዙዎች አስተማሪ አይሁኑ፤ ምክንያቱም እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ እንደምንቀበል ታውቃላችሁ" ያዕቆብ 3፥1።*

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬ ያሉት ብዙ ችግሮች የተነሱት በተሳሳተ ትምህርት ምክንያት ነው። አስተማሪዎች የሚሰሙ ናቸው፣ የሚቀርጹ ናቸው፣ አመለካከትን የሚያስተካክሉ ናቸው። ስለዚህ ለእውነት ያላቸው መሰጠት ሊሰዉለት የሚገባ መሆን አለበት። እናንተ አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በልታችሁ፣ አላምጣችሁ፣ አድቅቃችሁ ራሳችሁን ከገነባችሁ በኋላ ነው ሌሎችን ለመመገብ መሞከር ያለባችሁ። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚሰራ ማረጋገጥ አለባችሁ፣

ስለዚህ ቃሉን በሕይወታችሁ ማኖር አለባችሁ። በቃላችሁ ከማስተማራችሁ በፊት አዕምሯችሁ በቃሉ መረስረስ አለበት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተሳሰብ መለማመድ አለባችሁ"

የተሳሳተ ትምህርት ለኑፋቄ እምነት የመጀመሪያው ዘር ነው። ይህ አባባል በጣም ጠንካራ ክስ ይመስላል። ኑፋቄ (Heresy) ማለት ቃሉ ሲተረጎም አንድን እውነት ከሚያስፈልገው በላይ በመወጠር ሌሎችን እውነቶች እንዲደመሰስ ማድረግ ነው። ኑፋቄ በቀጥታ የሚነገር ውሸት ሳይሆን እውነትን አበላሽቶ ማቅረብ ነው።

አስቀድሞ የተነሱ ኑፋቄዎች በስላሴ ትምህርት ላይ ያተኮሩና በተለይም በጌታ የሱስ ፍጹም አምላክነት እና ፍጹም ሰውነት ላይ ጥያቄ የፈጠሩ ነበሩ። ክርስትና ጌታ የሱስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ እንደሆነ ነው የሚያስተምረው። ይህንን ትምህርት የሚያበላሹ ኑፋቄዎች ተነሱ፤ አንድንዶቹ "ሰው መስሎ መጣ እንጂ ፍጹም አምላክ ብቻ ነው" የሚሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ "በምድር ላይ ከኖሩ ሰዎች ሁሉ የበለጠ ጥሩ ሰው ነው እንጂ አምላክ አርደለም" የሚሉ ነበሩ። የመጀመሪያው ፍጹም አምላክነቱን አጉልቶ ለማሳየት በመጣር ፍጹም ሰው የመሆኑን እውነት አሽቀንጥሮ ጣለው። ሁለተኛው ደግሞ ሰው የመሆኑን እውነት በጣም ዘርግቶና ወጥሮ አምላክ መሆኑን ቦታ አሳጣው።

ዘመናዊ ኑፋቄዎች ደግሞ ትኩረታቸው በሰዎች ላይ ይመስላል። በ1970ዎቹ በተለይ በምዕራቡ ካሪዝማቲክ ንቅናቄ አካባቢ የተነሳ ኑፋቄ ነበር። ይህ ትምህርት የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችን ሥልጣን የሚያጎላ ከመሆኑ የተነሳ መጋቢዎችን ከሥልጣን እኪያ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሆነ ቦታ መስጠት ጀመረ። ከእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ሚዛን ውጪ በሆነ መንገድ መጋቢዎች ተከታዮቻቸው ማን ማንን ማግባት እንዳለበት፣ የት ቦታ መኖር እንደሚገባቸው፣ ምን አይነት ሥራ መቀበል እንደሚችሉ መወሰን ሥልጣናቸው ሆነ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ለመጋቢዎቹም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ነውጥ አመጣ። ተዋደው ተጫጭተው ለመጋባት የወሰኑ ወጣቶች እንዲለያዩ ይደረግ ጀመር፤ ሴቷም የማትወደውን ወንዱም ያልመረጠውን እንዲያገባ የተገደዱበት ጊዜ ነበር። የኑፋቄ





ትምህርት ጠባዩ ደግሞ በትምህርቱ የተያዙ ሰዎችን ጆሮ ያደነቁራል፤ ለምንም አይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፣ እርማት፣ እውቀታዊ ልምምድ፣ ስሜታዊ ማግባባት አይበገርም።

ዛሬም ከኑፋቄ መደብ መግባት የሚገባቸው አንዳንድ ትምህርቶች አሉ። በዚህ ምዕራፍ እነኚህን ዘመናዊ ኑፋቄዎች እናያለን። አርዕስቶቻቸውን ብቻ አይታችሁ የእናንተን ልምምድ የሚቃወም ከመሰላችሁ እንደዚያ አይደለም፣ ስለዚህ አዕምሯችሁን ሳትዘጉ እንቀጥል።

## 1. የቃል እምነት (Word-Faith)

ይህ እንቅስቃሴ ትምህርቱን የሚመሰርትበት እንደ ማርቆስ 11፥ 22-23 ባለው ጥቅስና ተመሳሳይ ጥቅሶች ላይ ነው።

> *"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። እውነት እላችኋለሁ፤ ማንም ይህን ተራራ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢለውና ይህንንም በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን ይሆንለታል።"*

ይህ የኑፋቄ ትምህርት የሚያተኩረው በተወሰኑ ቃላት ብቻ ላይ ነው። እነርሱንም ከተጠቀሱበት ትርጉም ወይም ዓውድ (context) በማውጣት ነው። ለምሳሌ በዚህ ጥቅስ "ቢለው" "ይሆንለታል" የሚሉትን ቃላት አጋጭተው የምትለውን ነገር ታገኛለህ (what you say is what you get) ብለው ያስተምራሉ።

> *"እባቦችን በእጃቸው ይይዛሉ፣ የሚገድል መርዝ እንኳን ቢጠጡ አይጎዳቸውም" ማርቆስ 16፥ 18*

የሚለውንም ጥቅስ እንዳለ ወስደው በአምልኳቸው ውስጥ እባብን እያመጡ የሚቀባበሉና መርዝም እንጠጣለን የሚሉ የዚህ ኑፋቄ ተከታዮች ብዙ ጊዜ ከሕግ አስከባሪዎች ጋር ሲጋጩ በዜና ሰምተናል።

## የትምህርቱ መልካም ጎን

እንደማገኛውም የኑፋቄ ትምህርት ይህ ትምህርትም እውነትን ተሞርኩዞ ነው የሚነሳው። እውነቱ የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት መጨበጥ ውጤት አለው የሚለው ነው። ይህንን እውነት በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ክፍሎች አይተናል።

ቃላት ኃይል እንዳላቸው ተደጋግሞ የተገለጸ እውነት ነው። ብዙ ኮንፍራንሶች ተካፍያለሁ፣ እንዳውም በብዙዎች ላይ አገልግያለሁ። የታመመ ሰው በቃል ትእዛዝ ሲፈወስ አይቻለሁ፣ ምናልባት ብዙዎቻችሁ ሰዎች በሽታቸው በጌታ ስም በሚታዘዝበት ጊዜ ለመፈወሳቸው የአይን ምስክሮች ናችሁ።

እግዚአብሔርን በሁሉ ነገር ማመስገንን መለማመድ ሌላው የመልካም ጎናቸው ምሳሌ ነው (ኤፌሶን 5፡ 20)። የእግዚአብሔርን ኃይል ለመለማመድ ቃሉን በትክክለኛ መንገድ ከምንተረጉምባቸው መንገዶች አንዱ ይህ ነው። እግዚአብሔርን ማመስገን በጣም ኃይለኛ ድርጊት ነው፤ አስተሳሰባችንን ይቀይረዋል፣ ስሜታችንን ያነሳሳውና ጥሩ ጥሩ እንዲሰማን ያደርገዋል። በተቃራኒው ደግሞ ማጉረምረማችንም ተመሳሳይ ችሎታ ስላለው እርሱም አሳባችንን ወደ መጥፎ መቀየር ይችላል። ያ ደግሞ ስሜታችንን ዝቅ ያደርገውና መደበር (depression) ውስጥ እንገባለን።

ስለራሳቸው መጥፎ ነገር መናገር ሲጀምሩ መጥፎ ነገር የሚደርስባቸው ሰዎች አጋጥመዋችሁ አታውቁም? እኔ ብዙ ምሳሌዎች ልቆጥርላችሁ እችላለሁ። በምንናገረው ቃል ውስጥ ኃይል አለ። ሟርት የሚባለው እኮ የመጥፎ ቃል ኃይል ነው። ለዚህ ነው ሰው በሚሆን ነገር ላይ አስቀድሞ መጥፎ መናገር ሲጀምር "አታሟርት" የሚባለው።

ስለልጆቻችን በቀልድም እንኳን ቢሆን ወደፊት ስለሚሆነው መጥፎ ነገር መናገር አላዋቂነት ነው፣ ለምንለው ነገር መጠንቀቅ አለብን። ስለ መሪዎቻችንም ቢሆን ዲሞክራሲያዊ መብት አለኝ ብሎ መጥፎ ነገር ለመናገር ልቅ መሆንና መንፈሳዊነት የጎደለው ባህሪ ነው። በቴሌቪዥን የሚመጡ ብዙ ሰባኪዎች መጽሕፍ ቅዱስ ቢይዙም የራሳቸው አጀንዳ ያላቸው ብዙዎች መኖራቸውን ማወቅ አስተዋይነት ነው። ስለዚህ





እርእያንታቸውን መከተል አያስፈልገንም ለማለት ነው። ዲሞክራሲያዊ መብታችን በመንግሥት ፖሊሲና የአመራር ጉድለት ላይ ተቃውሞ እንድናሰማ ያስችለናል። ነገር ግን ከዚያ አልፈን መሪዎችን ስንረግምና በመጥፎ ቃላት ስንገልጻቸው ኃይል ያለው ነገር እያደረግን መሆናችንን መገንዘብ ይገባናል።

ስለ አርባ ሁለተኛው የአሜሪካ ፕረዜዳንት ቢል ክሌንተን ስለ ድካማቸውም ሆነ ስለ ብርታታቸው ብዙዎቻችን በተለይ በእርሳቸው ዘመነ መንግሥት የነበርን ሁሉ እናውቃለን። እንኳን በአሜሪካ በኢትዮጵያውያንም ኮሜዲያኖች ብዙ ተሰቆባችዋል። አሁን አሁን እየተነሱ ያሉ አንዳንድ የታሪክ ሰዎች "የቀኝ ክንፍ ክርስቲያኖች በዚያን ያህል የጥፋት ቃል ባያጠምዷቸው ኖሮ የታሪክን ሂደት ይቀይሩ ነበር" ማለት ጀምረዋል።

በቃላችን ከእግዚአብሔር ጋር ስንስማማ ደግሞ ግሩም ድንቅ ሥራ ማከወን እንችላለን። እንዳንዴ ቅን በሆነ መንገድ የሚመጣ ትንሽ ቃል ላምጪው ባይታወቀውም እንኳን ተቀባዩን ግን ይፈውሳል። እኔ በፈረንጆቹ በ1993 መጨረሻና 1994 መግቢያ አካባቢ በአንዳንድ በአካባቢዬ በደረሱ ነገሮች በጣም ያዘንኩበትና ከሰው መገለል የጀመርኩበት ጊዜ ነበር። ምክንያቱ አንድ ብቻ ሳይሆን የተደራረበ ነገር የተከሰተ ሲሆን፣ አንድንዱ በግል ሕይወቴ አንዳንዱ ደግሞ በነበርኩበት ኅብረት ላይ የሆነ ነበር። በነገሮች አዝኜ ድብርት (depression) ውስጥ ገብቼ ነበር። አገልግሎቴ የቀነሰበት፣ መንፈሳዊ ዲስፕሊኔ የላለበት፣ ጥያቄ እየበዛብኝ መልሶች ግን ያጣሁበት ጊዜ ነበር።

በዚህ ሁኔታም ውስጥ ሆኜ የሰንበት ትምህርት ግን አስተምር ነበር። አንድ ቀን ከቤተ ክርስቲያን ስንወጣ አንዲት ስለ እኔ ሁል ጊዜ ቅን የምታስብ ወጣት "እግዚአብሔር እንዳንተ የሚወደው ሰው አላየሁም" አለችኝ። የተናገረችው ቃል በሰንበት ትምህርት ውስጥ የሰጠኋቸውን መመሪያ በመከተል ነበር። "በእግዚአብሔር ቃል የተደገፉ፣ እውነት የሆነ ቃል ሰዎችን ለማነቃቃት መናገር ተለማመዱ" ብዬ አስተምሬ ነበር። ታዲያ እንደዚያ ስትለኝ እኔ በውስጤ "ያለሁበትን ሁኔታ ብታውቂ ኖሮ እንዲህ አትይኚም ነበር" እያልኩ ተለያይተን ወደየቤታችን ሄድን። ከዚያ ያ ያለችኝ ቃል በጆሮዬ መጉላላት ጀመረ። ያ ያለችው እኮ እውነትነት አለው ብዬ

ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች

"ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው?" ሮሜ 8:35 ብሎ የጻፈላቸው ታወሰኝ።

ለመሆኑ ሕይወቴ እንዲህ የተመሰቃቀለበት ምክንያቱ ምንድነው? ብዬ ማሳብ ጀመርኩ። አቤት ስገባ ወረቀት አነሳሁና የሆነ ቦታ እንዳነበብኩት ወይም እንደሰማሁት ምክንያቶቼን ልወቃቸው ብዬ መጻፍ ጀመርኩ። ብዙ ነገር መጻፍም አላስፈለገኝም፣ በጥቂቱ አሳቤ እየጠራ መጣ። አንዳንዶቹ የተሻለ ምርጫ ብዬ በፈቃዴ ከወሰንኳቸው ውሳኔዎች የመነጩ ናቸው። አንዳንዶቹ ከእኔ ቁጥጥር ውጪ ከመሆናቸውም በላይ በውሳኔዎቹ እኔ ያልተሳተፍኩባቸው ናቸው።

ነገሮቼን ሰብስቤ ብደምር ብደማምር ባባዛም ከክርስቶስ ፍቅር እንኳን የሚለየኝ ጥሩ ኩርፊያ የሚያስኮርፈኝ ምክንያት አልነበረኝም። "በእርግጥ እግዚአብሔር እንደኔ የሚወደው ሰው ከቶ አላየሁም" ብዬ እኔም ለራሴ ነገርኩት፤ ያ ቃል ፈወሰኝ።

## የቃል እምነት ትምህርት ስህተቱ

አንድ ስለ ኑፋቄ እምነቶች የሚጽፉ ሰው የዚህን ትምህርት ስህተት ለማሳየት ይህንን እውነተኛ ታሪክ ጻፉ።

"አንዲት ታማ ሆስፒታል የተኛች ወጣት ለመጎብኘት ሄድኩ" አሉ። ወጣቷ የዚህ የቃል እምነት (Word-Faith) ተከታይ ነበረች። ስለዚህ ቢያማትም እንኳን "እሞኛል" ብላ መናገር የእምነት አፍራሽ ኑዛዜ (Negative Confession) ስለሚሆንባት፤ ስለህመሟ ምንም መልስ አትሰጥም። ነገሩ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም ሁኔታው ይሄ ነበር። አሟት ሆስፒታል ተኝታለች፣ ነገር ግን አሞኛል ብሎ መናገር እምነቷን ማጉደል ሆኖ ስላስፈራት በተቻላት መጠን ሁሉ ያልታመመች ለመምሰል ትጥራለች።

"በጣም እንዳመመሽ ታስታውቂያለሽ" አልኳት ጠጋ አልኩና ቀስ ብዬ። በድንጋጤ አይኗን አፍጥጣ አየችኝ። የካህን ልብስ የለበሰ አማኝ እንዲህ ያለ የእምነት አፍራሽ





የሆኑ ቃላት ይዞ መምጣቱ ለእርሷ ሁኔታ ግዴለሽነት ማሳየት ስለመሰላትም ፍርሀትና ንዴትም አየሁባት። እርሷም ተናዳ እኔም ጊዜ ልሰጣት ብዬ ዝም ተባብለን ለረጂም ጊዜ ቆየን። ከዚያም እጇን ያዝኩና፥

"እሞሻል ብዬ በመናገሬ ህመሙ ባሰብሽ ወይ?" ብዬ ጠየኳት። ትንሽ አሰበችና

"አልባሰብኝም" አለችኝ።

"እኔ አሞሻል ብዬ በመናገሬ እግዚአብሔር የሚቆጣና በእምነተቢስነቴ የሚቀጣሽ ይመስልሻል ወይ?" ስላት

"እኔን የሚቀጣኝ አይመስለኝም" አለች

"የአንቺ የእምነት ማነስ ሁኔታስ ይታይሻል? ታመሽ ተኝተሽ ታምሜአለሁ ብሎ መናገር እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ከመሰለሽ እኮ በእርሱ ላይ ያለሽን መተማመን ማሳነስሽ ነው፤ (positive confession) የሚባለውም ነገር ውሸትን መሸፈኛ መሆኑ ነው። ነገር ግን መታመምሽን አምነሽ 'ጌታ ሆይ እርዳታ እፈልጋለሁ' ብትዪው እርሱ ሊረዳሽ የታመነ ነው" አልኳት። ከዚያም አብረን መጸለይ ጀመርን፣ ሰሞኑንም ደጋግመን አብረን ስንጸልይ እየተሻላት መጣ፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሆስፒታል ወጣች።

ይህ እምነት ሳይሆን የሃይማኖት ሥርዓት ነው። ሰዎች ደግሞ የሃይማኖትን ሥርዓት በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል የሚዘረጋ መጋረጃ ያደርጉታል። የዚህ ኑፋቄ ተከታዮች የትምህርታቸውን ይዘት ለመጠበቅ ሲሉ ያለውን ነገር (ለምሳሌ ህመም) የለም፣ የሌለውን ነገር (ጤንነት) አለ በማለት ጭራሹኑ የባሰ ስህተት ውስጥ ገብተዋል፤ የእግዚአብሔርንም ታማኝነት ጥያቄ ፈጥረውበታል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ታማኝነት ምንጊዜም ቢሆን በእውነት ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው።

ሌላው የዚህ የቃል እምነት ትምህርት ስህተቱ ራሳቸው በራሳቸው ሁኔታ ላይ ቃል ተናግረው ያ የተናገሩት ደግሞ ትክክል ነው ብለው ማመን፣ ከዚያም ያንን የተቀበሉትን አቋም የሚደግፍ ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ በማሰባሰብ "እግዚአብሔር

እንዲህ አለኝ" ብሎ በዚያ መመራት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ኪዳኖች በሥራ ላይ ነው ብለው ይገልጹታል።

ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ያለብን አንድ ነገር የልመና ብዛትና የጥቅስ ጋጋታ የአሰራሩን ጥበብ ሊያስቀይረው አይችልም። በመንፈሳዊነታችንም ሆነ በቃላት ብዛት ልናግባባው (manipulate) አንችለም። በፈቃዱ እስካለን ድረስ እግዚአብሔር በነገራችን ላይ ነው። ለሁሉ ነገር ምክንያት አለው፣ የሚሠራውም በጥበብ ነው። ጆርጅ ማክዶላንድ ይህን አሳብ በሚመለከት የሚከተለውን አሳብ ጻፉ።

እግዚአብሔር ፈቃዱን በሰው ውስጥ ሲፈጽም ያ ሰው ደግሞ ፈቃዱን በአለም ውስጥ መፈጸም ይችላል። ብዙ ጊዜ ትኩረታችን ሁለተኛው ነጥብ ላይ ይሆናል፣ ሰው ፈቃዱን በአለም ውስጥ መፈጸሙ ላይ። ነገር ግን ቁልፉ የመጀመሪያው ነጥብ ላይ ነው፣ እግዚአብሔር ፈቃዱን በውስጣችን መፈጸሙ ላይ። ሰው ለእግዚአብሔር አላማና ፈቃድ የተሰጠ ከሆነ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር የተያዘ ከሆነ፣ በሕይወቱ ያለው አላማ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት፣ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ መፈጸም ይሆናል። የዚያን ጊዜ ችግራችንን በሚገባ መመርመር እንችላለን። ብዙ ጊዜ ራሳችንን እኮ በደንብ አናውቀውም። ሰዎች እንደሚያዩን እንኳን ራሳችንን ማየት አንችልም። ለዚህ ነው የእግዚአብሔርን ሰዎች በተለይ የበሰሉትን መጠየቅና ማማከር ያለብን። በራሳችንም ላይ ቢሆን ያለን ሥልጣን የተወሰነ ነው። በእርግጥ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሥልጣን አለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በኛ ላይ ያለው ሥልጣን ይበልጣል።

## ሚዛኑን ማግኘት

በቃል ውስጥ ኃይል አለ ብለን ተነጋግረናል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተበላሸውን ነገር ተበላሽቷል ብሎ መናገርን መፍራት ሞኝነት ነው ብለናል፤ ታዲያ በሁለቱ መካከል ሚዛኑ የት ጋ ነው?

በመጀመሪያ አጠቃላይ አመለካከታችን እንዴት ነው? ራስንም ሆነ ሁኔታን ዝቅ የሚያደርግ፣ የሚያንኳስስ ነገር መናገር ልማዳችን ነው? "የውሸት ትህትና" ከባህላችን የወረስነው ነው። ስኬትን ማድነቅ እንደነውር መታየት





የለበትም፣የአነጋገራችን ስልት መለወጥ ያስፈልገዋል። ቅንነት የሞላበት ተስፋ የሚያመጣ አነጋገር መማር ይኖርብናል። ቃላችን ኃይል አለው ብለናል፣ ታዲያ በቃላችን ምን አይነት ኃይሎችን ነው እንዲሰሩ የምናደርገው? በጌታ ስም በመናገር በሁኔታዎች ላይ ኃይልን መልቀቅ ሞኝነት መስሎ ይታያችኋል?

ሁለተኛ፣ በፀጋ ተፈተን ወይስ በህግ ተገደን ነው ያለነው? "በነፃነት እንድንኖር ክርስቶስ ነፃነት አውጥቶናል፣" ገላትያ 5፥ 1። ብሎ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያን ሰዎች ያስታወሳቸው፣ በሕግ ጎዳና ቁልቁል እየነጎዱ ሲያያቸው። ሕጋዊነት (legalism) አመለካከታችንን እንዳይወርሰው መጠንቀቅ አለብን። የምሥራች ነጋሪዎች መሆናችንን በሕግ ጠበቃነት ስንለውጥ ሳናውቀው ወደሌላ እስር እየገባን ነው። የሃይማኖት ሕጋዊነት በቀናተኛነት የተገፋፋ አለመብሰል ነው። ሕጋዊነት ራሱን እምነት አስመስሎ ቢቀርብም እምነት ግን አይደለም። እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙ ተስፋ ያደረግነው ነገር እንዲፈጸም፣እርግጠኛነት ሲሆን ህግዊነት ግን ተስፋ የለውም፣ ትኩረቱም አሁን በሚታየው ነገር ላይ ነው። ሰዎችም እምነታቸው በሕያው እግዚአብሔር ላይ መሆኑ ይቀርና በህጉ ፊደል ላይ ይሆናል።

ሚዛናዊነት ከብስለት የሚመጣ ውጤት ነው።ብስለት (maturity) ደግሞ ሂደት ነው። ብስለት በእውነተኛነት የሚወለድ፣ በትህትናና ለመማር ባለ ፈቃደኝነት የሚያድግና በልምምድ ካለፉ በኋላ የሚመጣ ክህነት ነው። ሕጋዊነት ግን ይህን የእድገት ደረጃ ይዘለዋል። ምክንያቱም ሕጋዊነት ያሳውራል። ፈሪሳውያን ድንቅ የሆነ ቃል እየሰሙ፣ ተአምራትን በዓይናቸው እያዩ ሕጋዊነታቸው ስላሳወራቸው፣ ለዘመናት የጠበቁት መሲሐቸው ሲመጣ ለመቀበል እምቢ አሉ። የሕጋዊነት ቅናታቸው (legalistic zeal) ለሞት አሳልፈው እንዲሰጡት አደረጋችው።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለ ዛሬ በድንግዝግዝ እናያለን ስለዚህም እንሳሳታለን (የእናንተን አላውቅም፣ እኔ ግን እንኳን በድንግዝግዝ ጥርት ባለ መስታወት እያየሁ ጺሜን ስላጭ ፊቴን ብዙ ጊዜ እደማዋለሁ)። ሕጋዊነት ስህተት ማድረጉን እንኳን አይቀበልም። ምክንያቱም የአንድን ነገር ሂደት መጠራጠር ራሱ እምነተቢስነት ነው ብሎ ስለሚቀበል፣ ነገር ሲበላሽ የማስተካከል ጥረት የለም። በዚህ አይነት ሁኔታ ለታመሙ ልጆቻቸው አስፈላጊው መድኃኒት እንዳይሰጥ በመከልከላቸው ልጆቻቸው

እንዲሞቱ ያደረጉ አሉ፤ ይህ ታዲያ የክርስቶስ መስቀል የፈታውን ቀንበር መልሶ በራስ ላይ ማምጣት ነው።

እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ ማድረግ አለብን። እምነታችንን በመንፈሳዊ ልምምዶች ላይ ካደረግን እነርሱን ማምለክ እንጀምራለን። እምነታችንን እኛ ለቃሉ በሰጠነው ትርጉም ብቻ ከወሰነውም የመረዳት ችሎታችንን አምልኮ አድርገነዋል ማለት ነው። እግዚአብሔር ብቻ አምላክ ነው። እምነታችን በእርሱ ላይ ብቻ መሆን አለበት። መንፈሳዊ ልምምዳችንን ሊቀበለው ይችላል ወይም ሊቃወመው ይችላል፣ እንዳውም ዞር ብሎ ሳያየው ሊተወው ይችላል። እምነታችንን በእርሱ ላይ ካደረግን ግን እምነታችንን ሁልጊዜ ያከብረዋል። ለአድገታችንም ያደርገዋል። እምነታችን በልምምዳችን ላይ ካተኮረ፣ ዛሬ የተሳካው ልምምድ ነገ አልሆን ሲል ሕይወታችንን በጣም ያዋዥቀዋል።

## 2. የብልጽግና ወንጌል (Prosperity Gospel)

መልካም የሆነን ነገር ሁሉ ሰዎች እንዲለማመዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር ቸር ነው፤ ለቸርነቱም ወርድና ስፋት የለውም። ይህንን አሳብ እንድናየው የምፈልገው ከዚህ መረዳት በመነሳት እንዲሆን እፈልጋለሁ። የድህነት ወንጌል ሰባኪ አይደለሁም ለማለት ነው።

ነገር ግን ከጥቂት አመታት ጀምሮ በምዕራባውያን (በተለይ አሜሪካ) ሰበካ የተጀመረ አሁን ደግሞ በሶስተኛው አለም መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች (በተለይ አፍሪካ) እየተስፋፋ ያለ፣ ብዙ አለመግባባትና አለመጣጣም በክርስቶስ አካል ውስጥ ያመጣ ነው ይህ የብልጽግና ትምህርት ኑፋቄ።

የዚህ ኑፋቄ ትምህርቱ የተመሰረተበት ዶክትሪን አንዳንድ ክርስቲያኖች እንዲመቻቸው አድርገው በተረጎሟቸው በሁለት ወይም ሶስት ጥቅሶች ላይ ነው። ሰውን እግዚአብሔር የፈጠረው በሀብትና በንብረት እንዲበለጽግ ነው ብለው ነው የሚያስተምሩት። ሰው ካልበለጸገ ከእምነት እኳያ የተሳሳተ ነገር አለበት ማለት ነው የሚል መረዳት ነው ያላቸው። ከዚህም የተነሳ በክርስቶስ ስላለው ዘለአለማዊ ሕይወትና ከዚህ ሕይወት በኋላ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ለማሳወቅ





ጊዜ አያባክኑም። የዚህ አይነት ትምህርት ደግሞ ለደካማው ስብእናችንና ለወደቀው እኛነታችን የሚስማማ ስለሆነ ብዙ ተከታዮች ይኖሩታል። የሚያሳዝነው ታዲያ በአለም ሐብታም የሆነችዋ አገር ይህን በመስገብገብ ላይ የተመሠረተ ትምህርት ወደ ድሀ አገሮች መላኳ ነው።

የብልጽግና ወንጌል ዶክትሪን እግዚአብሔርን የሚያቀርበው ገንዘብ እንደሚረጭ ማሽን አድርጎ ነው። ይህንን ማሽን ፕሮግራም አደራረጉን ያወቀበት ሁሉ በገንዘብ ይትረፈረፋል ይላል። ፕሮግራሙን ደግሞ እምነት ብለው ይጠሩታል። አዲስ መልክ ይዞ መጣ እንጂ የቆየ በቤተ ክርስቲያን አባቶችም የተወገዘ ነው። ኖስቲሲዝም (Gnosticism) ይባላል። በግሪክ ቃሉ እውቀት ማለት ነው። ኖስቲሲዝም ያስተማረው ዶክትሪን "ልዩ እውቀት መልካም ነገርን ያስገኛል" ይልና በዚህ መልካም ነገር ወስጥ "ድህነትንና ችግርን የመፍታት ችሎታዎች ይጠቃለላሉ" ይላል። ይህ ደግሞ ለአዕምሮ ሰዎች በጣም ተቀባይነት ያለው ትምህርት ነበር። ምክንያቱም የዕውቀት ችሎታቸው ከፍ ባለና ዝቅ ባለ ሰዎች መካከል የመደብ ልዩነት ይፈጥራል፤ ለማወቅ ፈጣን ከሆንክ ወይም ልዩ እውቀት ያለህ ከሆንክ የሰውም ሆነ የእግዚአብሔር ኃይል ለአንተ ይሠራልሃል ይላል ትምህርቱ።

በመሠረቱ የብልጽግና ወንጌል የሰውን ዝቅተኛ ተፈጥሮውን ነው የሚቀሰቅሰው፤ ትምክህት በተለይ መንፈሳዊ ትምክህት ቆሻሻ ኃጢአት ነው። (አዎን፣ ኃጢአት ሁሉ ቆሻሻ ነው፣ መንፈሳዊ ትምክህት ግን የባሰ ነው።) "ይሄ ይሄ ተሳካልኝ ስለዚህ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ስለሆነ የተሻልኩ ነኝ፣ ድሀ አይደለሁም" በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እመለካከት ይህ በጣም አላዋቂነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ማውጫ (Bible Concordance) አንሱና "ድሀ" ለሚለው ቃል መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እስቲ አጥኑት። እግዚአብሔር በእርግጥ በኃብታምና በድሀ መካከል ልዩነት ያሳየናል። ነገር ግን ልዩ በረከት ያተኮረው በደሀው ላይ ነው። መቼም ይሄ አገላለጼ ለአንዳንዶች የማይስማማ እንደሆነ ይገባኛል፣ ነገር ግን ቃሉ እውነተኛ ነው።

የብልጽግና ወንጌል ሰዎች የሚከተለውን ጥቅስ ይወስዱና በስግብግብነት ለሚደሰተው ተፈጥሮቸው ይመግቡታል።

*"ወዳጅ ሆይ፣ ነፍስህ በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳለች ሁሉ መልካም ጤንነት እንዲኖርህና በነገር ሁሉ እንዲሳካልህ እፀልይልሃለሁ"* 3 ዮሐንስ 2።

በነገር ሁሉ መሳካት ስለ ገንዘብ ብልጽግና ነው የሚናገረው ብለው ነው የሚተረጉሙት። በእርግጥ እግዚአብሔር የገንዘባችን ነገር ይገደዋል። ብዙዎቹ የጌታ የሱስ ምሳሌዎች ገንዘብን የሚመለከቱ ናቸው። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችም በአለም ዙሪያ እግዚአብሔር እንዴት በእጦታቸው ጊዜ በገንዘብ እንደደረሰላቸው አስደናቂ ምስክርነቶች አሏቸው። እኔ ራሴም በግሌና በቤተሰቤ ሕይወት ገንዘብን በሚመለከት ብዙ ታሪክ አለን። ነገር ግን ያዕቆብ 4፡3 የሚለውን እስቲ እንመልከት።

*"ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፋ ትለምናላችሁ"።*

ይህም የአዲስ ኪዳን ቃል ነው። ያ ብቻ አይደለም፣ ለብልጽግና ትምህርት የሚጠቀሰውን ቃል የጻፈው ዮሐንስ በ1ኛ መልእክቱ 3፡17 ላይ እንደጠቀሰው፤

*"ማንም ሀብት እያለው ወንድሙ ሲቸገር አይቶ ባይራራለት፣ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዴት በእርሱ ይኖራል"።*

ለብልጽግና ወንጌል ሰዎች ይህ ለመቀጥ የሚያስቸግር ነው። ምክንያቱም የሰውን መቸገር የእምነት ማነስ ጉዳይ አድርገው ነው የሚያዩት። ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ስናይ ግን የሕይወት አላማችን ገንዘብ መሰብሰብና የራስን ኀብት ማካበት ላይ ብቻ ያተኮረ ከሆነ፣ ምንም በእምነት ቃል እየተሸፈነ ቢቀርብም የሚደገፍ ተግባር አይደለም።

የብልጽግና ወንጌል በሰብአዊ ተፈጥሮ ውስጥ ላለው ደካማ ባህሪ፣ ስስትና ስግብግብነትን ለመሳሰሉት አዳማዊ ተፈጥሯችን የተስማማ ነው፤

*"ሰው አለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል?" ማቴዎስ 16፡ 26።*

ለሚለውና ተመሳሳይ ጥቅሶች ትኩረትም ቦታም የላቸውም። ሰው ለክርስቶስ ብሎ





ሕይወቱን ቢያጣ እንኳን የሚለውን ትምህርት ከግምት እንኳን ሳያስገቡ፣ ሰው በክርስቶስ ሊያተርፍ የሚችለውን ኀብትና ንብረት እያጋነኑ በመናገር ብቻ ሰው ለገንዘብ ያለውን ረሀብ ይቆሰቁሱታል።

እግዚአብሔር ልጆቹን በገንዘብና በንብረት መባረክ ይወዳል። እነኚያ በረከቶች ግን እግዚአብሔርን ስናገለግልና ራሳችንን ትተን እርሱን ስናስቀድም የሚከተሉን ናቸው እንጂ አገልገሎታችን እነርሱን ማሳደድ ብቻ መሆን አለበት ማለት አይደለም። ጌታ የሱስ በትምህርቱ መንገዱን አሳይቶናል፣

*"ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፣ የበላይ መሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን" ማቴዎስ 20፡ 26።*

ትልቅነትን `መፈለግ መልካም ነው፣ ግን እዚያ ለመድረስ እርግጠኛ የሆነው መንገድ አገልጋይነት ነው። ትልቅነት በአገልግሎት የሚመጣ ውጤት ነው እንጂ አላማ አድርገን ትኩረታችንን የምንጥልበት ግብ አይደለም። አንድ ፓስተር የሆኑ የእግዚአብሔር ሰው የሚከተለውን ቀላል ምስክርነት ጽፈው አነበብኩ።

*በ 1980 ዓ.ም መንፈሳዊ ዲሬክተር ሆነህ ለማገልገል ፈቃደኛ ከሆንክ ለ21 ቀን ጉዞ ከአሜሪካ ወደ አውሮፓ (ሮም፣ አቴናና ተመሳሳይ ታሪካዊ ቦታዎች) ዋጋውን እኛ ከፍለን ከግሩፕ ጋር አብረን ልንልክህ እንፈልጋለን የሚል ግብዣ አገኘሁ። ከዚያ እግዚአብሔርን*

*"ይህንን ግብዣ ልቀበል ወይ" ብዬ ስጠይቀው*

*"ሚስትህን ይዘህ ከሄድክ ብቻ" አለኝ።*

*ሚስቴን ይዤ ለመሄድ ዋጋውን ስጠይቅ ለአንድ ሰው $2765 ነው አሉኝ። ያ ተስፋ አስቆረጠኝ። ያለን ጊዜ ዘጠኝ ወር ስለነበር በዘጠኝ ወር ውስጥ ያን ያህል ትርፍ ገንዘብ ማጠራቀም የምንችል አልመሰለኝም። ሆኖም ያገኘናትን ትንሽም ሆነ ትልቅ ማጠራቀም ጀመርን። የሶዳ ቆርቆሮዎች እንኳን እያጠርቀምን መሸጥ ጀመርን። የሚገርመው በሌላ ጊዜ በየወሩ መክፈል የሚገባንን እዳ ከፍለን የሚተርፈን*

ገንዘብ አልነበርም። አሁን ግን ትንሽም ቢሆን ይተርፈናል። ከሰዎች ጋር ስጦታ እንለዋወጣልን፣ በዚህ ጊዜ ግን ከምንሰጠው የምንቀበለው የበለጠ ሆነ። ኮንፍራንስ ላይ ለመናገር ስጋበዝ የፍቅር ስጦታ እያሉ ይሰጡኝ ጀመር። የመሔጃው ጊዜ ወር ሲቀረው የመጨረሻውን ክፍያ ከፈልን። ቁጭ ብዬ ሳሰላስለው በዚህ ዝግጅት ስም ያገባነው ገቢ $3800 ነበር። እኛ ካቀድነው ከ $1000 በላይ ትርፍ ነበረው። ነገሩ አስገረመኝ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩና ወደ መቅደሱ ገብቼ ሂሳቡን የያዝኩበትን ወረቀት ፑልፒቱ ላይ አስቀመጥኩና

"ጌታ ሆይ! ለምን ይህን ሁሉ አደረክልን?" ብዬ መጠየቅ ጀመርኩ። ከዚያም እግዚአብሔር በአሳቤ ያናግረኝ ጀመር።

"በቤትህ ተቀብለህ አስቀምጠህ አስተናግደህ ያቋቋምካቸው ሰዎች ስንት ናቸው?" ብሎ ጠየቀኝ። ይህ የኔና የባለቤቴ የግል አገልግሎታችን ስለሆነ መልሱን በደንብ አውቀዋለሁ።

"38 ሰዎች ናቸው" ብዬ መለስኩ።

"በእያንዳንዳቸው $100 ሰጠሁህ" አለኝ።

እኔም "ጌታ ሆይ እኛ እነዚያን ሰዎች ያስተናገድነው እኮ ወሮታ ፈልገን አልነበረም" አልኩ። እርሱም "እርሱን አውቃለሁ እኔ ግን ልከፍልህ ወደድኩኝ"።

ከ $1000 በላይ የወጪ ገንዘብ ይዘን በዚያ ጉዞ ላይ ተሳተፍን። በረከቱ ግን እኛ ያደረግነው ሳይሆን ከእኛ ቁጥጥር ውጪ በሆነ መንገድ የመጣ ነው"።

ይህ ታሪክ አሳቤን ቁልጭ አድርጎ ገልጾልኛል፡ ለዚህ ነው  እንዳለ ያስቀመጥኩት። በተጨማሪም ፊት ለፊት ከቀረበው ታሪክ በስተጀርባ ያለውን የፓስተሩ ቤተሰብ በገንዘብ ላይ ያላቸውን ግንዛቤም ታስተውላላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።





## 3. የኒው ኤጅ፣ እንቅስቃሴ

የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ ብዬ ብተረጉመው ምናልባት ተቀራራቢ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። በምዕራፍ አራት ውስጥ ስለዚህ ኒው ኤጅ እንቅስቃሴ በጥቂቱ ጠቅሻለሁ። ኒው ወይም አዲስ የሚለው ቃል ግን አያሳስታችሁ። ምክንያቱም ይህ እንቅስቃሴ ያረጁ የምሥራቅ እምነቶች ዘመናዊ ካባ ደርበው ለአዲሱ ዘመን ራሳቸውን ያቀረቡበት እንቅስቃሴ ነው። ለዚህ አዲስ ዘመን አመጣሽ እንቅስቃሴ ያነበብኩትን አንድ ትርጉም ላቅርብላችሁ።

ይህ ኒው ኤጅ (አዲስ ዘመን ) እንቅስቃሴ "ምልአት ያለው (holistic) መንፈሳዊነትንና የሰውን ችሎታ ወደ ብቃት የሚያመጣ" ብሎ ራሱን ይተረጉማል። ነገር ግን ሐሰተኛ እምነት ነው። ሰው በውስጡ አምላክነት አለው ይላል። ትኩረት የሚያደርገው በሰው ውስጥ ያለ ገና ያልተደረሰበት ችሎታ አለ በማለት ሰዎችን ወደ ውስጣችሁ ጥለቁ የአምላክነታችሁን ምልአት ተለማመዱ ይላል። በሰዎች ውስጥ ያለውን መንፈሳዊ ጥማት ጊዜያዊ እርካታ ይሰጥና በመጨረሻ ግን ከነበሩበት ሁኔታ ወደ ባሰ ሁኔታ መርቶ የሚተዋቸው ነው።

ሰይጣን ከውድቀቱ ጀምሮ እግዚአብሔርን መወዳደርና እግዚአብሔር ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ በመጣር ላይ ነው። እግዚአብሔር ያደረገውን እውነተኛ ነገር የሚመስል ኮፒ በማውጣት ጥበብ በጣም የረቀቀ ነው። ምክንያቱም በዘመናት ሁሉ ያደረገው ስለሆነ ያውቅበታል።

በዚህ ዘመን የምዕራቡን ሥልጣኔ እየወረረው ያለው ይህ አዲስ ዘመን "New Age" እንቅስቃሴ በሂንዱኢዝምና በቡዲኢዝም እምነት ላይ የተመሠረተ የባእድ አምልኮ እምነት ነው። ይህን እንቅስቃሴ በተለይ ለእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አስፈሪና አስጊ የሚያደርገው ብዙዎቹ ራሳቸውን ክርስቲያኖች ነን ብለው የሚጠሩ ሁሉ ስለሚለማመዱት ነው። በልስላሴ የሚቀርብ፣ ለምሳሌ እንደ እስልምና እምነት ራሱን በኃይልም ይሁን በገሀድ ለመግለጽ ጥረት አያደርግም። በሂንዱኢዝም እምነት የየትኛውም እምነት ተከታዮች ቦታ አላቸው። የትኛውም አምላክ ተቀባይነት አለው። ስለዚህ እርሱም በየትኛውም እምነት ውስጥ ሰርጎ ለመግባት ቀላል ይሆንለታል።

እንቅስቃሴው በተለይ እምነታቸው ወደ ሀብረተሰባዊ ስራ ለሚያጋድልባቸው ክርስቲያኖች እመቺ ምርጫ ሆኖ ራሱን ያቀርባል።

መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን አይነት ልምምድ

*"የአጋንንት ትምህርት" 1 ጢሞቴዎስ 4፥ 1።*

በሌላ ቦታ ላይ ይህንን አሳብ

*"አጸያፊ ልምምድ" ዘዳግም 18፥ 12*

በሚሉ ኃይለኛ በሆኑ ቃላት ከእነኚህ ልምምዶች እንድንርቅ ያስጠንቅቀናል፤ ተካፋይ ለሚሆኑትም ውጤቱ አስከፊ እንደሚሆን ያሳያል።

*"ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቤ መካከል እንደነበሩ፣ እንዲሁም በእናንተ መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይነሳሉ። እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳን ክደው ጥፋት የሚያስከትል የስህተት ትምህርት በስውር ያስገባሉ፣ በራሳቸውም ላይ ድንገተኛ ጥፋት ያመጣሉ ... እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን እየተስገበገቡ በፈጠራ ታሪካቸው ይበዘብዟችኋል" 2 ጴጥሮስ 2፥ 1-3"*

*"የአምላካችንን ፀጋ 'ለርኩሰት የሆነ ፈቃድ' አድርገው የሚለውጡና ልዑል ገዛችንን ጌታችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው ... እነዚህ ሰዎች ግን የማያውቁትን ነገር ሁሉ ይሳደባሉ፤ አዕምሮ እንደሌላቸው እንስሳት በደመ ነፍስ በማያውቁት ነገር ይጠፋሉ.... .እነርሱ በነፋስ የሚነዱ ዝናብ የሌላቸው ደመናዎች ናቸው" ይሁዳ 4፣ 10፣ 12።*

የኒው ኤጅ እንቅስቃሴ በምዕራብ እንዲህ ቶሎ ሊስፋፋ የቻለበት አንዱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አደራዋን ትታ ትኩረቷ ሌላ ቦታ በመሆኑ ነው። ስንት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው ዛሬ በድፍረት ለምዕመኖቻቸው እንደ ጳውሎስ እንዲህ የሚሉ፣





*"ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም። ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው" 1ቆሮንቶስ 2፥ 4-5።*

ክርስትና አቋሙን ሲስት ሰዎች ወደ ሌላ ቦታ እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል። ሰይጣን ደግሞ እውነተኛውን ነገር የሚመስል የውሸት ቅጂ አዘጋጅቶ ይጠብቃል። ይህ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስን ኃይልን፤ ተአምራትን፣ ፈውስን፣ መንፈሳዊ ውጊያን፣ ከአጋንንት ኃይል መለቀቅን፣ ከሳይኮሎጂ ችግር መፈወስንና የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎችንም ለመግለጽ አይደለም የተጻፈው። ግን አንድ ነገር ላረጋግጥላችሁ፤ እውነተኛ የክርስትና እምነት አምልኮና ልምምድ ባለበት ሁሉ እነኚህ ክስተቶችም በሥራ ይገለጻሉ። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የማይሰራ የክርስትና እምነት ልምምድ ግን ውጤት የለሽ፣ ጣዕም የለሽ፣ ለውጊያ የተጋለጠ ነው።

በምዕራፍ አራት እንዳሳሰብኳችሁ ዘዳግም 18፥ 9-13 ያለውን ደጋግማችሁ እስቲ አንብቡት። በዚያ ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከሚከተሉት ነገሮች ያስጠንቅቃል።

ክታብ ማሰር (መዳፍ ማንበብ፣ ውኃ መርጨት፣ ምልክት ማየት)
ኮከብ ቆጠራ
መተት (hypnotism)
ሟርት (ሌሎችን ለመጉዳት)
ሞራ ገላጭ
ጠንቋይ
ድግምተኛ
መናፍስት ጠሪ
ሙት አናጋሪ

እነኝህ ድርጊቶች ሁሉ የኒው ኤጅ ልምምዶች ሲሆኑ በእግዚአብሔር ቃል የተወገዙ ናቸው። ምክንያቱም ጀማሪያቸው ሰይጣን ስለሆነ እኛ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ሰዎች የሰይጣን ከሆነው ጋር ምንም ግንኙነት ሊኖረን አይገባም። እዚህ ጋ ላስጠንቅቅ

የምፈልገው ነገር አለ። አንዳንድ ጊዜ አንዳንዶቹ ልምምዶች ምንም ጉዳት የሌላቸው፣ ብንሞክራቸው ምንም የማናበላሽ የሚመስሉን ነገሮች አሉ።

የእግዚአብሔር ሰዎች ሆይ! ሁል ጊዜ በጥንቃቄ መራመድ አለብን። አንዳንዴ ለእውቀት ባህሪያችን የሚስማማ ስሜታችንን የሚቀሰቅስ ነገር በጥሩ መጠቅለያ ሆኖ እንድንለማመደው ይቀርብልናል። ሁል ጊዜ መፈተኛችን የእግዚአብሔር ቃል ይሁን። መፈተኛችን "ምን አለበት" መሆን አይችልም። ፓስተሬ ዶክተር ተስፋ ወርቅነህ እንደሚለው "ይቺ ምናለበት ብዙ ነገር አለባት"። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይግባባ ከሆነ ምንም ቀላል መስሎ ቢቀርብ፣ የማይጎዳ ቢመስልም፣ ምክንያታዊ፣ ዘመናዊ መስሎ ቢቀርብም፣ ማታለል ነው፣ ይመርዛል።

## 4. በዶክትሪን መከፋፈል

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ዶክትሪን ብዙ አስተምሯል፤ የዶክትሪንንም ነገር በሚገባ የተረዳ ነበር። "ፍቅር አይወድቅም" ብሎ አስተማረ እንጂ "ዶክትሪን አይወድቅም" አላለም። እስቲ በመንደርደርያው ላይ እንደጠቀስኩት የሁለት ቃላትን ትርጉም እንይ፤ 'ዶግማ' እና 'ዶክትሪን'። ዶግማ ክርስቲያን ነን የምንል ሁሉ በዘር በቋንቋ በነገድ እና በጊዜ የምንለያይ ብንሆም አንኳን የምናምነው ነው። ዶግማ የሐዋርያት 'የእምነት ኑዛዜ' ወይም የኒቂያ ጉባኤ ባጸደቀው የእምነት ኑዛዜ ውስጥ የተጠቃለለው ሐተታ ነው። ዶግማ ስለ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ፣ ስለ ወልድ ሥጋ መልበስ፤ ስለ ደህንነት፣ ስለ መንግሥተ ሰማይና ስለ ገሃነም፣ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ መሠረታዊ እምነቶች የሚናገረው ሐተታ ነው። የብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የእምነት አንቀጽ መሠረት ነው ዶግማ።

ዶክትሪን ዶግማ በተለያዩ ንዑስ ክፍሎቹ ሲከፋፈል ነው። ክርስቲያኖችም መከፋፈል የሚጀምሩት በዶክትሪን ደረጃ ነው። ለምሳሌ ዶክትሪን ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እና ሥርዓት፣ ስለ መንፈሳዊ ልምምዶች፣ ስለ መጨረሻው ዘመን ትምህርት፣ የሚለያይ ነው። እነኚህ በዶክትሪን ደረጃ የተያዙ ትምህርቶች ሲሆኑ፣ የብዙዎችም መከፋፈል በእነኚህ ላይ ያተኮረ ነው። በዶግማ ደረጃ ልዩነት ያላቸው ግን ኑፋቄ ተብለው ይወገዛሉ።





ለብዙ ዘመናት ክርስቲያኖች በዶክትሪን አለመስማማት የተነሳ ሲከፋፈሉ፣ አንዱ ሌላውን ሲያሳድድ ጉዳት ሲያደርስ፣ ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ በሌላው ላይ ሲዘምት አውቀውም ባለማወቅም ሲጣሉ፣ ሲዋጉ፣ ሲገዳደሉም ኖረዋል። በእግዚአብሔር ቤት እየቆየንና የእግዚአብሔር ነገር እየገባን ስንሄድ ልዩ ልዩ አመለካከት የመለያየት ምክንያት ሊሆን ቢችልም፣ ልዩነት ሁሉ ግን የውጊያ ምክንያት መሆን እንደማይገባው እያወቅን እንሄዳለን። ከየት እንደሰማሁት የማላስታውሰው፣ በአዕምሮዬ ግን ተቀርጾ የቀረ ብዙ ቦታ ደጋግሜ የምናገረው አንድ የእንግሊዝኛ አባባል አለ።

On the essentials unity
On the non-essentials diversity

ይህንን አሳብ እንዳለ ለመተርጎም ሞክሬ ነበር። ነገር ግን diversity ለሚለው ቃል የሚያረካኝ ትርጉም አጣሁለት። አሳቡን ግን እንዲህ ብዬ ተረጎምኩት።
ዋና በሆኑ እውነቶች ላይ (ዶግማ) መተባበር፣ አነስተኛ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መከባበር

የፖለቲካው መከፋፈል ሕዝባችንን ግራ ባጋባበት ዘመን እኔ ነዋሪነቴ አሜሪካን አገር ነበር። በየአመቱ በጁላይ 4 አካባቢ በሰሜን አሜሪካ በኢትዮጵያውያን መካከል የሚደረገው የእግር ኳስ ውድድር ገና እንደተጀመረ አካባቢ ነበር ጊዜው። ውድድሩ መምጣቱን ለማሳወቅ የተበተነ አንድ ማስታወቂያ በአንድ የአበሻ ምግብ ቤት አግኝቼ አነበብኩ፣ እንዲህ ይላል አሳቡ ቃል በቃል ባላስታውሰውም፣ "ከሚለያዩን ነገሮች ይልቅ የሚያስማሙን ነገሮች ይበዛሉ"። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ይህ አሳብ ቢጎለምስ ኖሮ እንዴት ያለ ፈውስ ያመጣ ነበር? እያልኩ ብዙ ጊዜ ራሴን እጠይቃለሁ።

አካባቢያችንን ለክርስቶስ ለመማረክ (እየተረሳ የመጣ አገልግሎት ቢመስልም ዋናው ተልእኳችን እርሱ ነው) የእያንዳንዱ ኅብረት አቅም፣ ንብረትና የሰው ጉልበት በየአካባቢው ያስፈልጋል። ሥራው የእግዚአብሔር መሆኑን ተገንዝበን ከሰራን፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ኅብረት ለየት ያለ አገልግሎት ይሰጠዋል።

እያንዳንዱ ኅብረት በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚጫወተው የራሱ የሆነ (unique) ሚና ይኖረዋል። አንዳንድ ኅብረቶች ሰዎችን የመጋበዝና የማሰባሰብ ተሰጥኦ አላቸው፤ አንዳንዶች አገልጋዮችን በማሰልጠን፣ አንዳንዶች የወንጌልን ስርጭት በማደራጀት፣ ማቴርያልን በማዘጋጀት፣ አዋቂዎችን በመንከባከብ፣ ወጣቶችን በማደራጀት፣ የቤተሰብን ጉዳይ......ምሳሌዎች ለማቅረብ ያህል ነው። ታዲያ እነኚህ የተለያዩ ኅብረቶች ሁሉ በህብረተሰቡ ውስጥ በስጦታቸው ቢሰማሩ የሚቋቋማቸው ኃይል አይኖርም።

አንድ ዶክትሪን በሌላ ዶክትሪን ላይ ጥያቄ ይኖርዋል። ከአድቬንቲስቶች ጋር አብሬ የሠራሁበት ጊዜ ነበር። ለየት ያሉ ልምምዶች አሏችው። የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ሥርአት ቅዳሜ ቀን መሆኑ፣ ሰንበትን በተመለከተ የሚያደርጉት ጥንቃቄ፣ የምግብ ምርጫ ከእምነት ጋር መያያዙ ጥያቄ ያስጠይቀኝ ነበር። ነገር ግን ለክርስቶስ ያላቸው ፍቅርና ለእግዚአብሔር መንግሥት ያላቸው መሰጠት ከጥያቄ በላይ ስለሚያደርጋቸው ያላቸውን የዶክትሪን አቋም ከመጠየቅ ይልቅ ማክበር ተምሬአለሁ።

የዶግማንና የዶክትሪንን ልዩነት ግን አጥርተን ማወቅ አለብን። በዶግማ ከምንለያይ ሰዎች ጋር እምነትን በሚመለከት ህብረት ሊኖረን አይችልም። ምክንያቱም ዶግማ ከተነካ የእምነታችን መሠረት ተናጋ ማለት ነው። ዶክትሪን ግን የአሠራርና የአተረጓጎም ጉዳይ ነው። ለምሳሌ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው የመሆኑ እውነት የቤተ ክርስቲያን ዶግማ ነው። ይህንን እውነት የሚያናጋን ትምህርት የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ ታወግዛለች። ይህንን እውነት የማይቀበሉ ሰብሰቦችም በክርቶስ አካል ውስጥ ቦታ የላቸውም፣ እምነትንም በተመለከተ እማኞች ከነርሱ ጋር ህብረት ማድረግ አንችልም።

ሌላ ምሳሌ እንይ፤ ጥምቀት የቤተ ክርስቲያን ዶግማ ነው። ጌታ የሱስ ለቤተ ክርስቲያን ከሰጣት ስርአቶች አንዱ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ምዕመኗን ታጠምቃልች። የሥርዓቱ አፈጻጸም ግን በዶክትሪን ደረጃ የተያዘ ነው። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሕጻናትን በማጥመቅ ያምናሉ፣ ሌሎች ግን ሰው የሚያደርገውን ሲያውቅ ነው መጠመቅ ያለበት ይላሉ። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውኃ በመርጨት የጥምቀትን





ሥርዓት ያሟላሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሙሉ ሰውነት ውኃ ውስጥ መጥለቅ አለበት ይላሉ። የተለያየውን የአደራረግ ሥርዓት የሚከተሉት የተለያየ ዶክትሪን ስላላቸው ነው። ካስተዋላችሁት ግን ልዩነቱ በአሠራርና በአተረጓጎም ነው። ስለዚህ በዋናው ዶግማ ላይ አንድ ስለሆንን በዶክትሪን ደረጃ ባለን ልዩነት ከተከባብረን አብረን መሥራት የምንችልባቸው ነገሮች በጣም የበለጡ ናቸው። ይህ ከሆነ ደግሞ በልዩነታችን ላይ ፊት ለፊት ለመነጋገር እንኳን አንፈራራም።

## 5. ወሲባዊ አመንዝራነት (Sexual Idolatory)

ጥንታውያን የሆኑ ብዙ የክርስቲያን ቤተ እምነቶች (Denominations) ዛሬ ያሉት በነውጥ ውስጥ ነው። የመጀመሪያ ቀናተኝነታቸው ቀስ እያለ ተበርዞ ከዚያም አልፎ ግዴለሺ የሆኑበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። በዚህ ግዴለሽነት ደረጃ ላይ እያሉ ውስጣዊ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ፈንድቶ እንደገና ለእግዚአብሔር ስምና ሥራ ለመቆም ካልመለሳቸው ሊቀለበስ ወደማይቻል ውድቀት እንዳይገቡ ያሰጋል።

በአውሮፓ ውስጥ ታሪካዊና ጥንታውያን የሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች ወደ እስላም መስጊድነት መለወጥ እንደ ወረርሽኝ በሽታ አህጉሩን እያጥለቀለቀው ነው። ይህ ሁኔታ የተወሰኑ ቤተ እምነቶች ችግር ነው እኛን አይመለከተንም የምንል ክርስቲያኖች ካለን፣ በዶክትሪን ደረጃ ያለንን ልዩነት አጋነን ዶግማው ሲጠፋ የማይገደን ከሆነ እርቀን የማስተዋል ችሎታችን የደበዘዘ ሆኗል ማለት ነው። እነኚህ ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናት የትኛውንም ቤተ እምነት ቢወክሉ ለአጠቃላዩ የክርስቲያን ህብረተሰብ ቅርሶች ናቸው፣ ያስፈልጉናል። ውድቀታቸው ደግሞ የተቀረውንም ያናጋናል።

እንዳንድ ጥሩ ምልክቶች ግን እየታዩ ናቸው። በ 2003 (በአውሮፓውያን) ታላቅ ወንድሜ መጋቢ መርዕድ ለማ ለጉብኝት ወደ አሜሪካ መጥቶ ነበር። አንድ ቁም ነገር ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጫወተኝ። ዛሬ ቤተ ክርስቲያኒቷ ውስጥ ብዙ ሰዎች በዝግጅት ላይ ናቸው አለኝ። ከምንም የበለጠ ትኩረት በመስጠት የእግዚአብሔርን ቃል እያጠኑ ናቸው። የሚቀጥለው ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ወደአገራችን የሚመጣው በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኩል የመሰለኛል አለኝ። ከ 20 እና ከ 30 አመት በፊት በወንጌላውያን ክርስቲያኖች አመለካከት ይህ ሁኔታ

የማይታሰብ ነበር። አሁንም ቢሆን አክራሪዎችና አሳዳጆች የሉም ማለት አይደለም። ግን እዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ ደስ የሚያሰኝ ብቻ ሳይሆን ለብዙው የአገሪቷ ችግሮች መፍትሔ የሚሆን ውጤት በዚች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚነሳ እውነተኛ መንፈሳዊ እንቅቃሴ ይመጣል ብዬ እኔም በግሌ አምናለሁ።

በብዙ ታሪካዊ ቤተ እምነቶች ውስጥ የእምነት መናጋት የመጣበት አንደኛው ምክንያት የወሲብ አመንዝራዊነት ነው። አመንዝራ የሚለው ቃል አጠቃላይ ትርጉሙ ባዕድ አምልኮ ማለት ነው። ቃሉ Idolatory (idol worship) በእንግሊዝኛ Adultery ተብሎ የተተረጎመው ነው። (ይህንን ትርጉም ማስገባት ያስፈለገኝ ብዙዎቻችን አመንዝራ የሚለውን ቃል ዝሙት ብቻ እንደሆነ አድርገን ስለምንተረጉመው ነው። ዝሙት ከአመንዝራነት ልምምድ አንዱ ሲሆን አመንዝራነት ግን ከዝሙት በላይ ነው)።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ቀሳውስት የወሲባዊ አመንዝራነት ቅሌት በየጊዜው በዜና ማሰራጫዎች መታየቱ በአጠቃላይዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጥቁር ነጥብ ሆኖባታል። የወሲብ አመንዝራዊነትን በሚመለከት ሁኔታ ከአለም ጋር መመቻመች የዶክትሪን ደረጃ ብቻ ሳይሆን የዶግማ ደረጃ ስህተት ነው። ምክንያቱም መሰረታዊ የሆነውን የአምልኮ ህብረት ያበላሻል። እግዚአብሔር የራሱ የሆኑት ከእርሱ ጋር የቅርብ (intimate) የሆነ ህብረት እንዲኖራቸው ይፈልጋል። አምልኮ የሚለው የግሪኩ ቃል በገጹ ሲተረጎም 'ለመሳም መቅረብ' ማለት ነው። ስለዚህ አምልኮ የቅርብ የሆነ ግላዊ ፍቅርን የመግለጫ ስርአት ነው። ከእግዚአብሔር አብልጠን ራሳችንን ለምንም ስንሰጥ ያ አመንዝራነት ነው።

አዳምንና ሔዋንን መልካምና ክፉን ከምታሳውቀዋ ዛፍ እንዲበሉ ሰይጣን ሲፈትናቸው አላማው ምን ነበር? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ወዲያው በፈተናው ከወደቁ በኋላ አዳምና ሔዋን ያደረጉትን እንመልከት። ኃጢአታቸው እንደተጋለጠ ባወቁ ጊዜ የሸፈኑት ምናቸውን ነው? ፍሬውን ያዩበትን አይናቸውን አልነበረም፣ ፍሬውን የያዙበትንም እጃቸውን አልሸፈኑም፣ ወይም ፍሬውን የበሉበትን አፋቸውን አልነበረም። ነገር ግን ሀፍረተ ሥጋቸውን (ወሲባዊ ብልቶቻቸውን) ነበር የሸፈኑት። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ያለን መሰጠትና አምልኮ የሚገለጸው





ለወሲባዊ ብልቶቻቸን (Sexuality) በምናደርገው ጥንቃቄ ሲሆን ሰይጣንም የአመንዝራነትን ፈተና የሚያበዛው በወሲብ ፍላጎታችን በኩል ነው።

ወደ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግኙነት፣ ወደጎን ከወጣትነት የትዳር ጓደኛችን ካለን ግንኙነት ጋር የተጣመረ ነው። ከትዳር ጓደኛችን ጋር ያለንን ታማኝነት ብናጎድል፣ ወደ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንም ግንኙነት የተበላሸ ነው። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ የተባለችው ለምን ይመስላችኋል? በጋብቻ ወስጥ የሚሆን የወሲብ ግንኙነት የሰው ልጆች ግንኙነታቸውን በቅርብ የሚገልጹበት ዋናውና የመጨረሻው ደረጃ ስለሆነ ነው። (እናንተ ወንድሜ ከባሌ ይበልጥብኛል፣ ሚስቴ እናቴን አታክልብኝም የምትሉ ሁሉ የያዛችሁት የሞኝ ፈሊጥ ነውና ይህን በማለት በቤታችሁ ላይ ያስቀመጣችሁትን እርግማን እንዲያነሳላችሁ ንሰሐ ግቡ። የበረከት በራችሁንም አትዝጉ።)

አንድ ሰው ያንን ግንኙነት ከጋብቻ ውጪ በሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ሲለውጥ፣ ያ ሰው ወደ ላይ ባለው ግንኙነቱ ለእግዚአብሔር ያለውን አምልኮ በሰይጣን አመንዝራነት ለወጠ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ ወሲብ አመንዝራነት ወይም ግልሙትና (idolatry) ይባላል። ለዚህ ነው ወሲብ ሰይጣን ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔርን ሰዎች ለመበከልና ለመጣል ጠቃሚ መሳሪያ የሆነለት። እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ 23000 እስራኤላውያን እንዲሞቱ ተቆጥቶ የፈረደበት ኃጢአት የዝሙት ኃጢአት ነው።

ይህ መንገድ ለሰይጣን ዛሬም ቢሆን ያላረጀ፣ ያላፈጀ ዘዴ ነው። የእግዚአብሔርን ሰዎች በተለይ በአገልግሎታቸው የወጡትንና የሚታዩትን ለመጥለፍና ለመጣል የሚጠቀምበት ፍቱን መንገድ ነው። አንዳንዶቹን ትዳራቸውን በማፍረስ የመሪነት አቅማቸውንና የመድረክ ድምጻቸውን ሲያደክምባቸው፣ ሌሎቹን ደግሞ ለጆሮ በሚያጸይፍ ወሲባዊ ቅሌት ተጠምደው እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል። ለሰይጣን ይህ ፍቱን የሆነ የማይስትበት መንገድ ነው።

ርህራሄ ያለበት፣ ምክንያታዊ፣ በጥናት የተደገፈ፣ ለእውቀት ባሕሪያችን የሚስማማ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብ የሚያስተምረውን ግን የማይስማማ ብዙ

ወሲባዊ ትምህርት በየቦታው ይቀርባል። ይህና ተመሳሳይ ትምህርት በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖችም ወይም ክርስቲያናዊ ድርጅቶም ይቀርባል። ሰውን ለመርዳትና ለማሻሻል ተብሎ የሚቀርብ ግን በእግዚአብሔር ቃል ያልተደገፈ ይህ አይነቱ ትምህርት የቤተ ክርስቲያንን መሠረት የሚያናጋ የእምነታችንና የእግዚአብሔር ሰው የመሆናችንን ድርና ማግ የሚበጣጥስ ወደ ፍርድ የሚያፋጥነን አደገኛ ትምህርት ነው። ልንቃወመው ይገባናል። ልናሸንፈውም የምንችለው መጨረሻ በሌለው ክርክር ሳይሆን በቅድስና ኑሮና በጸሎት ኃይል ብቻ ነው። እውነተኛውን ነገር አይን ያላቸው ሁሉ እንዲያዩ የሚያስችለው የቅድስና ኑሮ ነው። አይናቸው የጠፋባቸውን ክርስቲያኖች እንዲያዩ አይናቸውን የሚከፍትላቸው ደግሞ ጸሎት ብቻ ነው።

## 6. ነጻነታዊ ትምህርተ ሃይማኖት (Liberation Theology)

ይህን እንቅስቃሴ የሚያራምዱ ግሩፖች አጀማመራቸው የህብረተሰብን ችግር አይተው ማስተካከል አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ነበር። ምንም እንኳን በችግሩ ላይ ያላቸው አመለካከት ትክክል ቢሆንም ለችግሩ መልስ ይሆናል ብለው የሚወስዱት እርምጃ ግን ከእግዚአብሔር መንገድ በጣም የራቀ ነው። በተለይ የህብረተሰብን የኢኮኖሚ፣ የዘርና የመደብ ልዩነትን ለመደምሰስና ለማሻሻል የሚደረገው ጦር ማንሳትን እና ደም መፋሰስን የሚጨምር እርምጃ የሊብሬሽን የሃይማኖት ትምህርት የሚደግፈው የሚያራምደውም ነው።

ይህ ትምህርት በብዙ የስነ መለኮት መምህራን እንኳን ሳይቀር ድጋፍ የተሰጠው ነው። ስህተትን ለማስተካከል ተብሎ ሌላ ስህተት መስራት ሁለተኛውን ስህተት ትክክል አያደርገውም። በአለም ውስጥ ፍርድ ይጓደላል፣ ፍትሕም ይጎድላል። ጉልበተኛም ደካማውን ያጠቃል። የተጠቃን ደግፎ መነሳት፣ ድምጻቸው መሰማት ለማይችል ድምጽ መሆን፣ ለደካሞች አቅም መሰጠት እንደ እግዚአብሔር ሰዎች መደረግ ያለበት ነገር ብቻ ሳይሆን የሚጠበቅብንም ነው። ሁሉን ግን እንደ እግዚአብሔር ቃል ብቻ ማድረግ አለብን። የእግዚአብሔር ቃል ለመሪዎቻችን እንድንገዛ ሲመክረን፣





መሪዎች ሁልጊዜ ትክክለኛውን ነገር ያደርጋሉ በሚል ግምት አይመስለኝም። ነገር ግን ክፉን ለመሻርና ለመለወጥ እግዚአብሔር ይችላል፣ በጊዜውም ያደርገዋል።

## በአጭሩ

ሰው ዘመናዊ ሆኖ ለመታየት የሚያስከፍለውን በሚከፍልበት በዚህ ዘመን፣ ሰው ራሱን አሳምሮ ለማቅረብ በሚጣጣርበት፣ ሌሎች ስለእርሱ ያላቸውን አመለካከት ለማስለወጥ ወይም ለማሻሻል በሚጥርበት፣ ራስን ተቀባይ ለማድረግ ብዙ ዋጋ በሚከፈልበት ጊዜ መጠንቀቅ ያስፈልገናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወይም የክርስትና ትምህርት ብቻ ተብሎ ስለቀረበ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይስማማል ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል ቃሉና መንፈሱ ሁለቱም ሲስማሙ ነው እውነተኛ መመሪያ ሊሆን የሚችለው። የአድናቂዎች ብዛት ወይም የሆታ ጭብጨባ መመሪያ ሊሆነን አይችልም፣የእግዚአብሔርንም ቃል በዚያ መለወጥ አንችልም። ምን ጊዜም ማስታወስ ያለብን መረዳት መታዘዝን ይከተላል እንጂ አይቀድምም። አሁን ደግሞ መጠራጠር ምን እንደሆነ እንይ።

# ምዕራፍ ስምንት

## መጠራጠር

አንድ ጊዜ ጌታ የሱስ አቋራጭ መንገድ እንዲሆንለት ይመስለኛል በገሊላ ባህር ላይ በእግሩ መሄድ አስፈለገው። በዚህ ጉዞው ላይ እንዳለ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ሆነው የሚሄዱበት ቦታ ደረሰ። ደቀ መዛሙርቱ ግን እርሱን በውኃ ላይ ሲራመድ ሲያዩ በጣም ተደናገጡ። ምትሐት ያዩ መሰላቸው፣ ጌታ ግን እርሱ እንደሆነ አረጋገጠላቸው። በዚህ ጊዜ ነው ቀልጣፋውና ችኩሉ ጴጥሮስ

*" ጌታ ሆይ አንተ ከሆንሀስ በውኃው ላይ እየተራመድሁ ወደ አንተ እንድመጣ አዘዘኝ"* ማቴዎስ 14፥ 28 አለ።

ጌታ ጴጥሮስን ሲጠራው ጴጥሮስ ወጥቶ በውኃው ላይ መሔድ ጀመረ። ግን ወዲያው ሰብአዊ አሳብ የገባበት ይመስላል፤ የሚያደርገውን ነገር ማድረጉን ማመን ያቃተው ይመስላል፣ ስለዚህ መስጠም ጀመረ።
ለቅፅበትም ቢሆን ጴጥሮስ አይኑን በክርስቶስ ላይ በማድረግ ማድረግ የማንችለውን ነገር እንዴት ማድረግ እንደምንችል አሳየን። በሚቀጥለው ቅጽበት ደግሞ ተቃራኒውን ድርጊት አሳየን፣ አይናችንን ከክርስቶስ ላይ ካነሳን የማይቻለውን ነገር ማድረግ አለመቻላችንን አሳየን። ጌታ የሱስ ስለተሳካው የጴጥሮስ ልምምድ ምንም አላለም፣ መስጠም ሲጀምር ግን እጁን ይዞ አዳነውና

*"... ለምን ተጠራጠርህ?" ማቴዎስ 14፥31* አለው።

ስለ መጠራጠር ማስተማር ቀላል አይደለም፤ ስለዚህ ነው ራሱን የቻለ ምዕራፍ የተሰጠው። እስቲ እንደ ልማዳችን ቃሉን በመተርጎም ይህንን ምዕራፍ እንጀምር። በአማርኛ መጠራጠር የሚለው ቃል በእንግሊዝኛው (doubt) የሚለው ሲሆን የመጣው ዲስታዞ (Distazo) ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። ዲስታዞ አስገራሚ ቃል ነው። ቃሉ በገጹ ሲታይ 'እግርን ከፍቶ መቆም' ማለት ነው። የሚያዳልጥ ቦታ ላይ እግራችንን ከፍታን ሚዛናችንን ለመጠበቅ ስንሞክር ያለውን ሁኔታ

ይገልጻል። ጴጥሮስ በአሳባችሁ ይታያችኋል? ውኃው ላይ በሁለት አሳብ ተከፋፍሎ እግሩን እንፈራጦ በአንድ በኩል ቁልቁል እየሰመጠ ሲሄድ፣ መጠራጠር ልክ እንደ ጴጥሮስ እኛንም "ሊሸከምህ የማይችል ውሀ ላይ ነው እኮ የቆምከው" ይለናል፤ ከዚያ አሳባችን መከፋፈል ይጀምራል። ጴጥሮስ እግሩ ብቻ ሳይሆን አሳቡም ነበር የተከፋፈለው። ስለሆነም ጌታ አድርግ ያለውን ማድረግ አልቻለም፤ አንድ እግሩ ና ብሎ በጠራው በጌታ ትእዛዝ ላይ ሲቆም፣ ሌላው እግሩ ደግሞ 'የምታደርገው ለሰው የማይቻል ነገር ነው' በሚለው አሳብ ላይ ቆመ መስመጥም ጀመረ። በጌታ እሰኪ.ገሰጽ ድረስ ውኃውን የአንቦጫረቀው ይመስለኛል።

ያዕቆብ በመልዕክቱ ስለ ተከፋፈለ አሳብ እንዲህ ብሎ ጽፏል፣

> *"ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፣ ለእርሱም ይሰጠዋል። ዳሩ ግን ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን። ምክንያቱም የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባህር ማዕበል ነው። ያ ሰው ከጌታ አንዳች አገኛለሁ ብሎ አያስብ። እርሱ በሁለት አሳብ የተያዘና በመንገዱ ሁሉ የሚወላውል ነው" ያዕቆብ 1፥ 5-8።*

ይህ ክፍል ትልቅ ማበረታቻና ማስጠንቀቂያም ይሰጣል። *"ሳይነቅፍ በልግስና የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን"* የሚያበረታታ ቃል ነው። ምክንያቱም *"እርሱም ይሰጠዋል"* ብሎ ነው የሚጨርሰው። በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 1 እንዳየነው እግዚአብሔር ለልጆቹ መስጠት ደስ ይለዋል። ነገር ግን ምስጢር አለው፣ *"ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን"*። ግን ያ የሚለምን ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ ማዕበል ከሆን በሁለት አሳብ የተያዘ፣ የሚያወላውል ተብሎ ነው የተገለጸው። የያዕቆብ መልዕክት አጻጻፉ ደስ ይለኛል፤ ቀጥተኛ ነው፣ ለጥያቄ ቦታ አይሰጥም፣ ማባበልና ማግባባትም አያውቅበትም። በዚህ ቦታ ላይ ስለ እምነት ሁለት ነጥቦች ያሳየናል።

ሀ. ያዕቆብ የሚለው ከእግዚአብሔር ለምንጠይቀው ነገር አሳባችንን መወሰን አለብን። በእርግጥ የምንጠይቀውን ነገር እንፈልግዋልን? አንዳንድ





ጊዜ ሰዎች በጣም ችኩሎች ስለሆንን የምንጠይቀውን ነገር አናውቅም። ሳናስብበት እንጠይቃለን፣ ያ የጠየቅነው ነገር ሌላ የሚያመጣው በጊዜው ያልታየን ጦስ እንዳለው ሳንመረምር፤ በሥጋ ግፊት፣ በአይን አምሮት፣ በአዕምሮ መስካሪነት፣ በስሜት ቀስቃሽነት መለመን እንጀምራለን።

ይህ ሁኔታ አንዳንዶቻችን በየጊዜው፣ ሌሎቻችን ደግሞ አልፎ አልፎም ቢሆን በሕይወታችን የምናልፍበት ነው። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ይሄዳል ወይ የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ በአሳባችን ቀዳሚውን ቦታ መያዝ አለበት።

አብረን የምናገለግል አንድ የእግዚአብሔር ሰው ያጫወተኝ ታሪክ ሳሰበው ያስቀኛል። "ልጅ መውለድ እፈልጋለሁና እስቲ ለልጅ ጸልይልኝ" አለችኝ አለ አንዲት ሴት ጠጋ ብላ። ሊያገለግል ተጋብዞ የሄደበት ቦታ አገልግሎቱን ከመጨረሱ በፊት ጸሎት ለሚፈልጉ እየተጸለየ ነበር። "ባልሽም ከለ ጥሪውና አብሬ ልጸልይላችሁ ስላት ተቆጣችና ባል ትፈልጋለች ያለህ ማነው? እናንተ ሰባኪዎች ደግሞ የተጠየቃችሁትን ትታችሁ ያልተጠየቃችሁትን ትቀባጥራላችሁ ብላኝ ጥላኝ ሄደች" አለ። እንግዲህ ባል ለሌላት ሴት ልጅ ስጣት ብሎ መጸለይ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ማስማማት ያስቸግራል፤ ተአምር መሥራት የማያስቸግረው እግዚአብሔር የጉዲፈቻ በር እንዲከፍት ካልሆነ በስተቀር።

አንዳንዴ ደግሞ ስሜታችን ብቻውን ከፍ ይልና የስድስት አመቱን ልጅ ጸሎት አይነት መጸለይ እንጀምራለን። የስድስት አመት ልጆችን ሰንበት ትምህርት የሚያስተምረው አስተማሪ "ዛሬ የምንማረው ስለ ጸሎት ነው፣ እንዲያውም መማር ብቻ ሳይሆን ጸሎትን እንለማመዳለን" አላቸው ተማሪዎቹን፣ "ስለዚህ እንዲሆንላችሁ የምትፈልጉትን ነገር አስቡና እንጸልይበታለን" አላቸው። አንድ የስድስት አመት ወጣት ታዲያ የጸሎት ጥያቄውን ሲያቀርብ "እያቴን ማግባት እፈልጋለሁ" አለ። አስተማሪውም ተገርሞ "ለምንድነው እያትህን የምታገባው?" ብሎ ቢጠይቀው "ሁል ጊዜ አብረን እንድንኖር" ብሎ መለሰ። እርግጠኛ ነኝ ብዙዎቻችን ይህንን

ወጣት የሚመስል ልጅ እናውቃለን። ጋብቻ በሚያሞላቅቅ እያት ተይዞ መቀማጠል በመሰለው ወጣት እንሰቅ ይሆናል። አንዳንዴ ግን የእኛም ጥያቄ ከዚያ ብዙ የተሻለ አይደለም።

የጸሎት ነገር ምስጢር ሲሆንብን እግዚአብሔር ራሱን እንዲመራን መጠየቅ ጥሩ ነው። ለአንዳንዶቻችን ጸሎት ማለት ባማረና በተቀለጠፈ ቋንቋ መቅረብ ያለበት፣ በተወሰነ ቦታ በተወሰነ መንገድ ብቻ መሆን ያለበት ይመስለንና ከዚያ ካነሰ እግዚአብሔር ጋ የማይደርስ ወይም እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ይመስለናል። የእግዚአብሔር ቃል እንዴት መጸለይ እንደሚገባን እንደማናውቅ የሚናገረው ለዚህ ነው። አንዳንዴ እንፈልጋለን ግን የምንፈልገውን እንኳን አናውቅም። የዚህ አይነት ሁኔታ አጋጥሟችሁ አያውቅም? ባለቤቴ ኤልሳቤጥ እርጉዝ የነበረች ጊዜ "ምግብ እፈልጋለሁ፣ መብላት የምፈልገውን ግን አላውቅም" ትለኝ ነበር። ታዲያ እኛም አንዳንዴ በውስጣችን የተረገዘ ነገር ስላለ ምን እንደምንፈልግ አናውቅም ግን ያቅበጠብጠናል።

ይህንን መጽሐፍ ከማዘጋጀቴ በፊት ብዙ የምጸልይባቸው ጉዳዮች ስለነበሩኝ እጸልይ ነበር። ሥራዬንና አገልግሎቴን በሚመለከት ግን ምን ብዬ እንደምለምን ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ አልነበርኩም። በውስጤ የሚያቅበጠብጠኝ ነገር እንዳለ አውቃልሁ፤ ግን ያ ነገር ምን እንደሆን አላውቅም ነበር።

ለ. ያዕቆብ ያስቀመጠው ሁለተኛው ነጥብ "በሁለት አሳብ የተያዘ የሚያወላውል" ነው የሚለው ነው። ከኤልሲ ጋር አንድ ጊዜ ለቫኬሽን ቬኑስ፣ ጣልያን ሄደን ነበር። ቬኑስ ለማታውቋት በውኃ መካከል ያለች ትንሽ ከተማ ስለሆነች በከተማዋ ውስጥ የሚደረገው ሁሉ የሚደረገው ውኃ ላይ ነው። በከተማዋ መኪና የለም። ጎንዳላ የሚባል የውኃ ላይ ታክሲ/ጀልባ ነው ወዲያ ወዲህ ለማለት የሚጠቀሙት። ሰዎች ታዲያ አንድ እግራቸውን ጀልባው ላይ አንድ እግራቸውን ደግሞ ወደ ጀልባው መረማመጃ እንዲሆን የተዘረጋው የእንጨት ርብራብ (deck) ላይ ያደርጉና ሚዛናቸውን





ጠብቀው ለመቆም ይሞክራሉ። ቀላል አይደለም፣ በዚያ ሁኔታ ሆነው እቃ እያቀብሏቸውም፣ ባጠግባቸውም ሲያልፉ እንዳይገፏቸው ተጠንቅቀው ነው። ምክንያቱም በትንሽ ነገር በሚቃወስ ሚዛን ላይ ነው የቆሙት። ያዕቆብ 'በሁለት አሳብ የተያዘና የሚያወላውል' ያለውን ስዕል ነው ሁኔታቸው የሚያሳየኝ።

እግዚአብሔር የሚያወላወል ሁኔታ ላይ ካለ ሰው ለቀረበ ጸሎት መልስ ሳይሰጥ ቢዘገይ፣ ምናልባት ቸርነቱ ግድ ብሎት ይሆናል። አንዳንዴ ለጥያቄው እነርሱ የፈለጉትን መልስ መስጠት፣ ሚዛናቸውን ስተው ተፍገምግመው እንዲወድቁ የሚያደርጋቸው ይሆናል። ለዚህ ነው ያዕቆብ "ያ ሰው ከጌታ አንዳች አገኛለሁ ብሎ አያስብ" ያለው። እስቲ ይህንን ጥያቄ ለራሳችን በታማኝነት እንመልስ። ራሳችንን የምናውቀው በውኃ ላይ እንደሄደው ጴጥሮስ ሆነን ነው ወይስ መስጠም እንደጀመረው ጴጥሮስ? መስጠም እንደጀመረው ጴጥሮስ ከሆንን አሁንም ጌታ "ለምን ተጠራጠርክ?" ብሎ ይጠይቀናል፣ አስፈላጊም ጥያቄ ነው። ይህ ደግሞ የብዙዎቻችን ልምምድ ነው። ግን እንደዚያ መሆን የለበትም። ጌታ የሱስ በዚያ ቦታ ላይ የገሰጸው የጴጥሮስን ስሜት ሳይሆን የጴጥሮስን ድርጊት ነበር። ይህ አሳብ ደግሞ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቀጥለን ወደምናየው ነጥባችን ያመጣናል።

## 1. መጠራጠር ስሜት አይደለም

ይህንን ነጥብ መገንዘብ ብቻ በዚህ መጽሐፍ ላይ ያወጣችሁትን የጊዜና የገንዘብ ተመን ይሸፍንዋል ብዬ አምናለሁ። መጠራጠር የሚሰማን ስሜት ቢመስለንም ያ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት ታላላቅ የእምነት ሰዎች ሳይቀሩ የጥርጥር ስሜት ያልነካው ሰው ያለ አይመስለኝም።

ስለ ስሜታዊነታችን (emotions) እግዚአብሔርን ማመስገን ያስፈልገናል። ስሜታዊነታችን እንደ ቀለማ ቀለም ነው። ቀለማ ቀለም ባይኖሩ የሕይወት ጣእሙ ጨው የሌለው አልጫ ስለሚሆን ለዛ የለሽ ባዶ ይሆን ነበር። ሁሉ ነገር ነጭና ጥቁር ብቻ ቢሆን ኖሮ ይሰለች ነበር። ስሜታዊናታችንም ለሕይወት አስፈላጊ ነው። የሚያም

ስሜት እንኳን ሳይቀር ለሕይወት ቅመም ነው። ጤንነትን የበለጠ ያጣፍጠዋል። ዛሬ ‘ደስ የሚል ስሜት’ በተለይ በምዕራቡ አለም እንደ አምላክ የሚመለክበት ዘመን ላይ ነው ያለነው። የሚያስወጣውን አውጥቶ፣ የሚያስከፍለውን ከፍሎ ሰው የጥቂት ጊዜ የደስታ ስሜት ለማግኘት ይጋደላል። ቀደም ብለን ያየነው የአዲስ ዘመን (New Age) እንቅስቃሴ ብዙ ተቀባይነት ያገኘው ‘ደስ የሚል ስሜት’ የሚባለውን ነገር በገፍ አቀርባለሁ በማለቱ ነው።

እኔም ጥሩ ስሜት እንዲሰማኝ እወዳለሁ፤ ያንን መከላከሌ አይደለም። ጥሩ ስሜት ግን የግሪክ ፈላስፋዎች ከዘመናት በፊት ለደስታ የሰጡትን ሐተታ ይከተላል። ስለ ደስታ ሲናገሩ፣ በቀጥታ የሚገኝ ነገር ሳይሆን ሌላ ነገር ለማድረግ በሚሆን ጥረት የሚገኝ የጎን ወጤት (byproduct) ነው። ቀደም ብለን እንዳየነው በንብረትና በገንዘብ መባረክ የራስን ነገር መሰዋዕት ከማድረግ ጋር በተዘዋዋሪ መንገድ የተያያዘ እንደሆን ማለት ነው። ጥሩ ስሜትም የሌሎች ነገሮች ውጤት እንጂ አቅደንና ጥረንበት የምናግኘው አይደለም።

“እግዚአብሔር ጥሩ እንዲሰማን አይፈልግም እንዴ?”
“በደንብ ይፈልጋል እንጂ”
“ታዲያ ለምንድነው በቀጥታ ሄደን ጥሩ ስሜትን የማንቀበለው?”
“ምክንያቱም እንደዚያ አይሠራም”
“ለምን?”
“እኔ እንጃ፣ መልሱን ሙሉ በሙሉ አላውቀውም።”

በእርግጥ ጥሩ ስሜት ለምን በቀጥታ የሚገኝ ነገር እንዳልሆነ ቀላል መልስ የለኝም። ግን እውነት ነው፣ ጥሩ ስሜት በቀጥታ አይገኝም። በደንብ ካሰባችሁበት ደግሞ ብዙዎቻችሁ ከኔ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አመለካከት ላይ ትደርሳላችሁ። “እባክህ ጌታ ሆይ ጥሩ ስሜት ስጠኝ” ብላችሁ ስንት ጊዜ ጸልያችኋል? አንድ ፍንጭ ግን ልሰጥ እችላለሁ፣ እምነት ከመጥፎም ሆነ ከጥሩ ስሜት ጋር የተያያዘ አይደለም።

እግዚአብሔር በእርሱ ጌትነት ስር ለሕይወታችን አላፊዎችና ተቆጣጣሪዎች እንድንሆን ይፈልጋል። ስሜታችን ግን ቀደም ብሎ እንዳየነው በእኛ ቁጥጥር





አይደለም። መደበር (depression) ደርሶባችሁ ያውቃል? ስለዚህ ምን እንደምል ይገባችኋል ማለት ነው። በውሳኔያችን መደበር አንፈልግም ብለን መነሳት የምንችል ቢሆን መልካም ነበር። ግን እንደዚያ አይሰራም። ከድብርት ወስጥ ለመውጣት ሌሎች ነገሮችን የማድረግ ውጤት ነው። አንዳንዶቹን ቀደም ብለን አይተናል። እግዚአብሔርን ማመስገን፣ ጠላትን መገሰጽ፣ ውስጣዊ ፈውስ ማግኘት፣ ግብረ ገብነት የጎደላቸውን ነገሮች ከሕይወታችን ማውጣት፣ የበደሉንን ይቅር ማለት፣ ጠቃሚ ያልሆነ ግንኙነትን ማቋረጥ። ሂደቱ ረጂም ወይም አጭር ሊሆን ይችላል፣ እነኚህን ነገሮች በመለማመድ እንጂ “ከአሁን ጀምሮ መደበር አልፈልግም” በማለት ግን መውጣት አንችልም።

ታዲያ በእኛ ቁጥጥር ስር የሆነው ምንድነው? ፈቃድ ነው። ልክ እምነት ወሳኔ እንደሆነ ሁሉ መጠራጠርም ውሳኔ ነው። መጠራጠር የፈቃድ ጉዳይ ነው። ሰው ለመጠራጠር ይመርጣል። ጥርጥርን ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ሌሎቹ ክፍሎቻችን ሁሉ ሊገፋፉን ይችላሉ። ስሜታችን በሁኔታዎች ተማርኮ፣ አዕምሯችን ባገኘው እውቀት ተመርቶ፣ ጥርጣሬን ወደ እኛ ሊገፋፉ ይችላሉ።ነገር ግን መጠራጠር የፈቃድ ብቻ ድርጊት ነው። ደጋግሜ እንዳልኩት ስሜታችን በቁጥጥራችን ስር አይደለም፤ ነገር ግን ስሜታችን ፈቃዳችንን አስኮብልሎ የራሱን ፍላጎት እንዳያስደርገው መግታት እንችላለን።

## 2. አለማመን ሲዘረጋጋ

ባለቤቴ ኤልሳቤጥ የምታደርገው አንድ ነገር አለ። በተለይ ትልቅ የምንለውን የቤተሰብ ውሳኔ ለመወሰን ስንነጋገር “አይሆንም አትበለኝ” ትለኛለች፣ ወይም “እምነት አፍራሽ የሆነ መልስ አትስጠኝ” ትላለች። እምነቷን የሚያጠራጥር መልስ ከምሰጣት ባልመልስላት ትመርጣለች። ትክክል ነች፣ ምክንያቱም አለማመን የመዘረጋጋት ጠባይ አለው። አለማመን ሲዘረጋጋ ብዙ ነገሮችን ይሸፍናል። የአለማመን የመዘረጋጋት ችሎታ አስደናቂ ነው። “ለምን እንደሆነ አላውቅም ግን የሚሆን የሚሆን አይመስለኝም”። “እኔ መቸም ጠንቃቃ ነኝ፣ በድፍረት እንዲህ እንዲህ ይሆናል ወይም ይህን ይህን አድርግ ለማለት አልችልም” በቤተ ክርስቲያን ብዙ ልምምድ ያላቸው ሳይቀሩ የተሸፈኑበት የአለማመን መዘረጋጋት ነው።

አለማመን ሲዘረጋ ያላሰብነው ብዙ ቦታ ስለሚደርስ፣ አለማመን መሆኑን እንኳን ለይተን ማወቅ አንችልም። ግን ችግሩ ይህ የአለማመን መዘረጋጋት ስሜታችንን ይነካል፣ ሁኔታችንን እንዲለወጥ ያደርጋል፣ አስተያይትን ይማርካል። ይህ ሁሉ ይደማመርና ፈቃዳችንን ማግባባት ይጀምራል። ልብ አድርጉ የእግዚአብሔር ግብ ፈቃዳችንን ለመድረስ ነው። በዚያው መጠን የሰይጣንም ትኩረት ፈቃዳችን ላይ ነው። ውሳኔ ሰጪ እኛነታችንን ነው ሁለቱም ለመድረስ የሚሞክሩት።

‘ነገሩ የሚሳካ አይመስለኝም’ የሚለው አባባል ኃጢአት የሚሆንበት መንገድም አለ። ጌታ የሱስ በተራራው ስብከቱ ላይ መጨነቅን ኃጢአት ብሎ ነው የጠቀሰው፣ ምክንያቱም የመጨነቅ መነሻው እግዚአብሔር አይችልም ወይም እግዚአብሔር ግድለውም የሚል ውስጣዊ አስተሳሰብና ግምት ነው። አውቃለሁ አንዳንዶቻቸን ከተፈጥሮአችን ለመጨነቅ የተሰራን ነን። የሌሎቻችን ደግሞ ከአንዳንዶቻችንም የባሰ ነው።ማንነታችን (personality) የተለያየ ነው። የባህሪ ኀልዮ (Temperamental Theory) ሁለት አይነት ሰዎችን እንድሚከተለው ያወዳድራል፣ እስቲ እንየው።





| የፍርድ ሰው<br>Judging Attitude | አስተዋይ ሰው<br>Perceiving Attitude |
|---|---|
| አከተመ/Settled | ገና/pending |
| ተወሰነ/decided | አሳብ እየተሰበሰበ/gathering more data |
| ያለቀ/Fixed | መለወጥ የሚችል/Flexible |
| አስቀድሞ ፕላን/ planning ahead | በሂደት የሚለወጥ/Adapting as you go |
| ሕይወትን መቆጣጠር/Running Life | ሕይወትን መልቀቅ/Letting Life Happen |
| መደምደሚያ/Looking For Closure | ለአስተያየት ክፍት/Open to Options |
| ውሳኔ ማድረግ/Decision-making | ተጨማሪ አሳብ/Treasure Hunting |
| ያለቀ ፕላን/Planned | መለወጥ የሚቻል/Open-ended |
| የተፈጸመ/Completed | በመካሄድ ላይ/Emerging |
| የተወሰነ/Decisive | በንድፍ ደረጃ/Tentative |
| አበቃ/Wrapping it up | ጣልቃ የሚገባ/Something will turn up |
| አስቸኳይ/Urgent | ጊዜ አለ/There's time |
| የመጨረሻ ቀን/Deadline | የመጨረሻ ቀን ለምን/Why deadline |

ከእነኚህ ሁለት አመለካከቶች የትኛው ይመስለችኋል የመጨነቅ እድሉ ከፍ ያለ? የፍርድ ሰው ነው። የፍርድ ሰው፣ ፍርሀት ያለው፣ በጣም ጠንቃቃ፣ ‘ለክፉ ቀን አስብ’ የሚል፣ ነው። እግዚአብሔር ይባርካቸው፣ እነርሱ የህብረተሰብ የማእዘን ድንጋይ

ናቸው። ያለ እነርሱ ሀብረተሰብ መቆም አይችልም። ሆኖም እንደ እነርሱ አይነት ሰዎች ናቸው ሳያውቁት በአለማመን መዘረጋጋት የሚሸፈኑት። የዚህ አይነት ሰዎች አላፊነትን ለመያዝ ብቃት ያላቸው ናቸው። በመንፈሳዊው መንገድ ግን አለማመን ጥንቃቄን መስሎ በሕይወታቸው እንዳይሰለጥን በየጊዜው ራሳቸውን መመርመር ይገባቸዋል። የድፍረት እርምጃ በፈቃዳቸው በመውሰድ የመጠራጠርን ገደል ማለፍ አለባቸው። እምነትም ጥንቃቄን የሚያልፍ ኃይል እንዳለው መገንዘብና መለማመድ ይገባቸዋል።

3 . የእውነትና የውሸት ጥርጥር

ሰው ጥርጣሬውን መጋፈጥ ያለበት ጊዜ ይመጣል፣ ልዩነቱ ጥርጣሬውን እውነተኛ በሆነ መንገድ መጋፈጡ ወይም ማስመሰሉ ላይ ነው። ሐዋርያው ቶማስ በእውነተኛ መንገድ ጥርጣሬያቸውን ለተጋፈጡ ጥሩ ምሳሌ ነው። በሙሉ ልቡ ማመን ፈልጓል፣ ነገር ግን አንድ ማረጋገጫ ካላገኘ ራሱን ወደ እምነት ማምጣት አቃተው። ጌታ የሱስ ቶማስን ስለጥርጣሬው አልቶቆጣውም ግን እንዲህ አለው።

*"ጣትህን ወደዚህ አምጣ እጆቼንም ተመልከት እጅህን ዘርጋና በጎኔ አስገባ አትጠራጠር እመን" ዮሐንስ 20፥ 27።*

የዚህ አይነት ጥርጣሬ የሚያሰቃይ ነው። ማመን እየፈለገ ፈቃዱ ግን በእውቀትና በስሜቱ የተንተተበት ሰው ችግር ነው። ነገር ግን እውነተኛ በሆነ ጥረትና ፍላጎት የሆነውን እግዚአብሔር በቸርነቱና በምህረቱ እንድሚገናኘው እምናለሁ።

የውሸት መጠራጠር ማለት ለማመን ምንም እቅድ የሌለው ሰው መጠራጠር ነው። የዚህ ሰው መጠራጠር ከማመን ይልቅ ወደ ክህደት የሚያጋድል ስለሆነ፣ ምንም ያህል ማረጋገጫ ቢሰጠውም ያ አይነቱ ተጠራጣሪ ሁልጊዜ ለመጠራጠር ሌላ ምክንያት ያገኛል። እግዚአብሔርን ማታለል ግን አይቻልም፤ ጥርጣሬው የቱ አይነት እንደሆነ እርሱ ያውቀዋል።

*ከዚያም አንዳንድ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንና ፈሪሳውያን "መምህር ሆይ ከአንተ ተአምራዊ ምልክት ማየት እንፈልጋለን" አሉት። እርሱ ግን*





*መልሶ እንዲህ አላቸው። "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይጠይቃል፣ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምልክት በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም" ማቴዎስ 12፥ 38-39።*

እነኚህ ሰዎች ብዙ ተአምራት አይተዋል፣ በብዙ ምልክትም ተነግረቸዋል። ነገር ግን ማመን አልፈለጉም።

ምናብን ለመኮርኮር 8 .

እንደ ዕብራውያን 11፥ 6 አገላለጽና ጌታ የሱስም ደቀ መዛሙርቱን ስለ አለማመናቸው የገሰጻቸውን ስንመለከት፣ በቂ እምነት ካልኖረን እግዚአብሔር በእኔም ደስ አይሰኝም ማለት ነው?

ለማመንም አላማ አልነበራቸውም። ዮናስ በአሳ ሆድ ሶስት ቀን ቆይቶ መውጣቱ፣ ለክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ምልክት እንደነበረ ለእነርሱም ለማመን በቂ ማረጋገጫ ነበር።

*ወዮልሽ ኮራዚን ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ በእናንት የተደረገው ታምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ገና ዱሮ ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ንስሐ በገቡ ነበር ማቴዎስ 11፥ 21።*

ሰው በእውነት ለማመን ከፈለገ አንዳንድ ጊዜ ማረጋገጫ ያገኛል። የማረጋገጫ አለማኖር አለማመኑን እንዲያጸናለት ብሎ የሚፈልግ ግን አያገኝም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ አመለካከት ስለሆነ ያ ሰው ኃጢአት እየሠራ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ለመፍረድ የሚያስችለው መረጃ እየፈለገ ነው ማለት ነው። ማናችንም ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ ለመፍረድ አንችልም፣ እርሱ በእኛ

ምናብን ለመኮርኮር 8.

እንደ ዕብራውያን 11፥ 6 አገላለጽና ጌታ የሱስም ደቀ መዛሙርቱን ስለ አለማመናቸው የገሰጻቸውን ስንመለከት፣ በቂ እምነት ካልኖረኝ እግዚአብሔር በእኔም ደስ አይሰኝም ማለት ነው?

ላይ ይፈርዳል እንጂ። በሌላ አነጋገር እኛ እግዚአብሔርን በርሱ መንገድ ልንገናኘው ሲገባን እርሱን በእኔ መንገድ ካልመጣህ ማለታችን ነው።

ፈሪሳውያን ጥርጣሬያቸው ለመተው የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ የውሸት ነበር። የራሳቸውን አመለካከት ለማረጋገጥ ብቻ እንጂ የእግዚአብሔርን እውነት ለማግኘት አልነበረም ጥረታቸው። ለዚህ ነው ጌታ የሱስ "ክፉና የአመንዝራ ትውልድ" ብሎ በኃይለኛ ቃል ያጋለጣቸው።

## 4. የጥርጥር ውጊያ

እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዳየነው በሰው ልጅ የሕዋሳት ክፍፍል ወስጥ መሪነቱ የመንፈስ መሆን እንደሚገባው ተነጋግረናል። መንፈስ መሪ ሲሆን ፈቃድ ደግሞ የመንፈስ ዋና ሹም ሆኖ አዕምሮንና ስሜትን ምክትል ሹማምንት አድርጎ ሥጋን ያስተዳድራል። አዕምሮ ያከማቸውን የእውቀት ስብስብ ስሜትም አስፈላጊ የሆነውን ስሜታዊነት (emotions, excitement) አምጥተው በፈቃድ ስር ይሠራሉ። ሮሜ 8 እና ገላትያ 5 ስለዚህ የሹመት ክፍፍል ያብራራሉ።

> *እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ልባቸውን (አእምሯቸውን) በሥጋ ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ። እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን ልባቸውን (አእምሯቸውን) በመንፈስ ፍላጎት ላይ ያደርጋሉ፤ የሥጋን ነገር ማሰብ ሞት ነው፣ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። ለኃጢአት የተገዛ አዕምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፣ መገዛትም አይችልም። በሥጋ ፈቃድ የሚመሩትም እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችሉም። እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ የሚኖር ከሆነ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ናችሁ" ሮሜ 8፥ 5-9።*

ከእግዚአብሔር ቃል እንድምንረዳው እንግዲህ አላፊ (responsible) መሆን ያለበት አካልም ነፍስም ሳይሆን መንፈስ መሆን አለበት።

አዕምሮ ገዢ ከሆነ የሚሰጠውን መመሪያ አስቀድሞ መረዳት አለበት። ይህ የአዕምሮ ሥነ ፍጥረት ነው፣ ሁሉን ነገር መረዳት መፈለግ እና ላልተረዳው ነገር





አለመስጠት። አዕምሮን ለገዢነት ከመረጥን ታዲያ የእምነት ነገር ሁሉ የምንረዳው ነገር ብቻ መሆን አለበት ማለት ነው። የአዕምሮ መሪነት ችግሩ በተለይ መንፈሳዊ ነገርን በሚመለከት አዕምሮ ለማወቅ ያለው ችሎታ የተወሰነ ነው፤ እውነትንም ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት አቅም የለውም።

የማምነውና የምለማመደው የተረዳሁትን ነገር ብቻ ከሆነ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወቴን ከማቀጨጩም በላይ በአገልግሎቴም እግዚአብሔር ያቀደለኝ ቦታ ለመድረስ አልችልም። ምክንያቱም የሚበልጠው እውነት ያለው ከአዕምሮ መረዳት በላይ በሆነ ደረጃ ውስጥ ነው።

ስሜት ገዢ ከሆነ ደግሞ የሚሰጡንን መመሪያዎች ሁሉ፣ ትክክል ናቸው ብለን ለመቀበል ጥሩ ስሜት የሚያመጡ ብቻ መሆን አለባቸው። የዚህ ሁኔታ ችግሩ አስቀድመን እንዳየነው ማናችንም ስሜታችንን ማዘዝና መቆጣጠር የምንችልበት ሁኔታ ላይ አይደለንም። እኔ በስሜቴ ላይ ካለኝ ቁጥጥር የበለጠ ስሜቴን የሚቆጣጠሩ ሌሎች ሁኔታዎች አሉ። ስሜቴን ካለሀበት ሁኔታ ወጥተህ ሌላ ሁኔታ ይሰማህ ለማለት አልችልም፣ ኃይልም የለኝም ስሜትም አይሰማም፤ ስትጮሁበት ብትውሉ ስሜት ከሚሰማው ነገር ንቅንቅ አይልም። ስለዚህ በድርጊቴ ላይ አላፊነት እንዲኖረኝ የስሜት ገዢነት ሊሠራ አይችልም፤ ስሜት የማይጨበጥ ከቁጥጥር ውጪ ስለሆነ ለአላፊነት አይበቃም።

ጌታ የሱስ እንግዲህ ትእዛዙንም ሆነ ምሪቱን ያተኮረው በፈቃዳችን ላይ ነው። ፈቃድ ከአዕምሮም ሆነ ከስሜት የተለየ ክፍል ነው። ይህንን ልዩነት ለማሳየት ስዕል ተጠቅመናል። ያንን ስዕል እንደገና ይህንን ምዕራፍ ከመጨረሳችን በፊት እናየዋለን። እንደገና ስዕሉን ስናየው እንደምንገነዘበው፣ ፈቃድ ከመንፈስ ክፍል ተነስቶ ወደሌላው ክፍላችን እንዴት እንድሚስፋፋ ለማሳየት ተሞክሯል። መንፈስን፣ ነፍስንና አካልንም እንደሚነካ ይታያል፤ በዚህም ለመግለጽ የተፈለገው፣ ፈቃድ አዕምሮም ሆነ ስሜት ለመቀበል የሚያስቸግራቸውን እውነት ይዞ እነርሱንም ሊሸፍናቸው እንደሚችል ማሳየት ነው።

ስለዚህ ፈቃድ በአዕምሮና በስሜት ላይ ሊሰለጥን ይችላል ማለት ነው። አንድ ነገር በእምነት ፤ለመቀበል ያ ነገር ምክንያታዊ ወይም ስሜትን የሚነካ መሆን የለበትም። ፈቃድ እምነትን ለመለማመድ የሚያስፈልገው፣ ያ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ማወቅ ብቻ ነው። ፈቃድ አንድ አሳብ የበሰለ አሳብ ነው ብሎ ማወቅ የለበትም ወይም ደስ የሚል ስሜት እንዲሰማውም መጠበቅ የለበትም፤ እምነትን ለመለማመድ መወሰን ብቻ ነው ያለበት። እንዳንዴ ሁኔታው ፈታኝ ቢሆንም ድርጊቱ እንዳዚሁ ቀላል ነው።

ጌታ ወደ መስቀል ላለመሄድ ብዙ ምክንያቶች ሊሰጥ ይችል ነበር። ጥሩ ስሜት እንዳልተሰማው ሳንጠይቅ የምንረዳው እውነት ነው። ውሳኔው የተመሠረተው በፈቃድ ላይ ብቻ ነበር፤ የእግዚአብሔር ልጅ በጌቴሴማኒ ሆኖ ያለውን ቃል አስታውሱ

*"ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይፈጸም"* ሉቃስ 22፥ 42።

ይህንን ማለት የሚችል ከመንፈስ የሆነ ፈቃድ ብቻ ነው፤ መነሻው መንፈስ የሆነ ፈቃድ ብቻ ነው ራሱንም አዕምሮንም ስሜትንም ተቃውሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ይሁን ማለት የሚችል።

ታዲያ አዕምሮና ስሜት ጠላቶች ናቸው ማለት ነው? በፍጹም አይደለም! ሁለቱም በእግዚአብሔር የተፈጠሩ የእኛነታችን ክፍሎች ናቸው። በእግዚአብሔር ሲቀደሱ ያላቸው ሙያ (በሚቀጥለው ምዕራፍ እንደምናየው) በምንም የማይተካ ነው።

ሙያቸው ግን ኢንፎርሜሽን መሰብሰብ እንጂ ስለ እምነት መወሰን አይደለም። አዕምሮና ስሜት ምክትል ሹማምንት መባል ይችላሉ፤ ባለሥልጣን ግን አይደሉም። ባለሥልጣኑ መንፈስ ሥራውን የሚሠራው በዋናው ሹሙ በፈቃድ ነው። ስለዚህ ፈቃድ በሹመት ከአዕምሮና ከስሜት በላይ ሆኖ ራሱ ግን ከመንፈስ ስር ነው። መንፈስ ከአዕምሮ፣ ከስሜትም ሆነ ከአካል ጋር ያለው ግንኙነት በፈቃድ በኩል ብቻ ነው።

በምዕራፍ ስድስት ውስጥ እንዳንዶቹ የሰው የህዋሳት ክፍሎች ለሰይጣን በቀጥታ ክፍት እንደሆኑ፣ እንዳንዶቹ ደግሞ ሰይጣን በቀጥታ የማይደርስባችው እንደሆኑ





መጥቀሳችንን ታስታውሳላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በዚያ ክፍል ባስቀመጥነው ስዕልም መንፈስንና ፈቃድን በመዝጋት ሰይጣን በቀጥታ የማይደርስባቸው መሆኑን አሳይተናል። በሌላ አባባል ሰይጣን በቀጥታ አካላችንን ሊነካ ይችላል፤ አስተሳሰባችንን በቀጥታ ሊያግባባ ይችላል፣ ስሜታችንንም በቀጥታ ሊቀሰቅስ ይችላል። ነገር ግን መንፋሳችንንም ሆነ ፈቃዳችንን በቀጥታ ሊነካ አይችልም። መንፈሳችንን ሊያውክና ፈቃዳችንን ሊያግባባ የሚችለው፣ በቀጥታ በሚደርስባቸው ክፍሎች አድርጎ ብቻ ነው።

ከሰይጣን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉት ክፍሎቻችን አካል፣ አዕምሮና ስሜት እንደሆኑ አየን። ፈቃዳችንም እምነት የጎደለው ውሳኔ እንዲወስን ለማድረግ እንዲያግባቡት ሰይጣን የሚጠቀመው እነዚህን ክፍሎች ነው። በምሳሌ ብገልጸው በፈቃድ፣ በአዕምሮና በስሜት መካከል የሚኖረው ለውውጥ ይኸን ሊመስል ይችላል።

<u>ፈቃድ</u>፥ "ጌታ ሆይ ኃጢአቴን ሁሉ ለአንተ እናዘዛለሁ፣ ይቅርታ እንድታደርግልኝም አለምንሀለሁ"

<u>አዕምሮ</u>፥ "አሁን በእርግጥ ይቅር ብሎኛል ብለህ መቼም አታምንም፣ ያንን ሁሉ ኃጢአት አድርግህ ለዛውስ መቼ የሚበቃውን ያህል ተፀፀትክና?

<u>ስሜት</u>፥ አዕምሮ ያለውን ለማረጋገጥ የሚመስል ይቅር ያለመባል ስሜትን በኩርፊያ ይገለጻል።

<u>ፈቃድ</u>፥ "እውነትም እኮ ይቅር አልተባልኩ ይሆናል፤ በልቅሶና በእንባ ሁኜ ይቅርታ ሳልጠይቅ እንዴት ይቅር እባላለሁ?"

<u>አዕምሮ</u>፥ "ግን እኮ ስሀተቱ ያንተ አይመስለኝም፣ ስለዚህ ጥፋትህ ባልሆነ ነገር ይቅርታ መጠየቅ ራሱ እኮ ማስመሰል ነው። ጊዜ ውሰድና ነገሩን በደንብ መርምር"

<u>ስሜት</u፥ ነቃ ነቃ ማለት ይጀምራል አዕምሮንም በመደገፍ ከልቅሶና ከልመና ለመገላገል ጎንበስ ቀና ማለት ይጀምራል።

<u>ፈቃድ</u>፥ " አዎን ልክ ነው፣ ለጥፋቴ እኮ የገፋፉኝ ብዙ ሁኔታዎች አሉ። እስቲ ራሴን ለመርምርና ጥፋት ከተገኘብኝ እግዚአብሔርን ተመልሼ ደጅ እጠናዋለሁ፡

የሆነው እንዲህ ነው። ፈቃድ በመጀመሪያ የእምነት ውሳኔ አደረገ። ያ ውሳኔ ግን በአዕምሮና በስሜት በኩል ውጊያ መጣበት። ያ ሲሆን ፈቃድ ውሳኔውን በመለወጥ ከአዕምሮና ከስሜት ጋር መስማማት ጀመረ።

*"ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው" 1 ዮሐንስ 1፥ 9*

የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት ከማድረግ ይልቅ ፈቃድ ወደ ሌላ ምክንያት አዘነበለ።ይህ ሰው ግን ይቅር ሳይባል ሄደ፣ ምክንያቱም መጠራጠር እምነቱን ተዋጋው። ከ 1ዮሐንስ የጠቀስነው ጥቅስ ያላለውን እስቡ "በልቅሶና በእንባ በመሬት ላይ ወድቀን ለአንድ ሰአት ብንለምነው እግዚአብሔር ምናልባት ይቅር ይለን ይሆናል" አላለም። ያለው ነገር ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ ግልጽ እውነት ነው። እውነተኛነት የስሜት ጉዳይ አይደለም፣ የውሳኔ ጉዳይ ነው። ሰው እምነትን ሲለማመድ የሚያረጋግጥለት ስሜት ሊኖረው ላይኖረውም ይችላል። ነገር ግን እምነት የፈቃድ ጉዳይ ነው። ፈቃድ አምናለሁ ብሎ በእውነተኛነት ከወሰነ፣ ስሜት በግዱ ቀስ ብሎም ቢሆን ይከተላል። እስቲ ልውውጡን በሌላ መልኩ እንየው።

<u>ፈቃድ</u>፥ "ጌታሆይኃጢአቴንሁሉለአንተእናዘዛለሁ፣ይቅርታእንድታደርግልኝም እለምንሀለሁ"

<u>አዕምሮ</u>፥ "አሁን በእርግጥ ይቅር ብሎኛል ብለህ መቼም አታምንም፣ ያንን ሁሉ ኃጢአት አድርገህ ለዛውስ መቼ የሚበቃውን ያህል ተፀፀትክና?





<u>ስሜት</u>፥ አዕምሮ ያለውን ለማረጋገጥ የሚመስል ይቅር ያለመባል ስሜትን በኩርፊያ ይገለጻል።

<u>ፈቃድ</u>፥ "ጌታ ሆይ ውጊያ አለብኝ፣ እኔ ግን ወስኛለሁ፤አሳቤና ስሜቴ ምንም ሌላ ነገር ቢነግሩኝ አንተ ግን ይቅር እንዳልከኝ ለማመን ወስኛለሁ። ምክንያቱም ቃልህ ኃጢአቴን ከተናዘዝኩ ይቅር እንደምባል ተናግሯል"።

<u>ፈቃድ</u> በወሰነው ውሳኔ ሲጸና፣ ውብ የሆነ ለውጥ በሰውዬው ሕይወት ውስጥ መካሄድ ይጀምራል፤ አዕምሮና ስሜት ከፈቃድ ጋር መስማማት ይጀምራሉ።

የእውነት - እምነት - ስሜት ባቡር

የካምፓስ ክሩሴድ መሥራችና መሪ የነበሩት ቢል ብራይት በአንድ ትራክት ላይ ያወጡት የባቡር ስዕል ነበር




እውነት የባቡሩ ሞተር ነው። ኃይል ያለው ሞተሩ ውስጥ ነው። እምነት ባቡሩን የሚያንቀሳቅሳው ነዳጅ ነው። ስሜት የባቡሩ ጭነት ነው። ብዙ ሰዎች ችግራቸው ነዳጁን(እምነትን) በጭነቱ(ስሜት) ክፍል ያደርጉታል። በጭነቱ ክፍል የተቀመጠውን ነዳጅ ሞተሩ(እውነት) ሊጠቀምበት ስለማይችል፣ ባቡሩ አይንቀሳቀስም። ትርፉ ወደኋላ እየተመለከቱ ብቻ ባሉበት መቆየት ነው። ወደ ሌላ ቦታ መድረስ ከተፈለገ ነዳጁ (እምነት) ሞተሩ ጋ መድረስ አለበት።

እንዳንዴ ቀዝቃዛ ምድጃ የሚመስለው እውነት እምነት ሲጨመርበት ሞቅ ሞቅ ማለትና መንቀሳቀስ ይጀምራል። በዚያን ጊዜ ስሜትም ምርጫ የለውም ተከትሎ

ይመጣል።እምነታችንን በስሜታችን ላይ ካዋልን ኃይል አትል ቦታ እያባከንን ነው። ይቅርታ ተደርጎልኛል ብሎ ያ ሰው ሲወስን ትንሽ ቆይቶ ይቅር እንደተባለ ይሰማዋል።

የብዙዎቻቸን ጥያቄ ታዲያ እስከመቼ የሚለው ይሆናል። እስከመቼ ነው ስሜታችን እንዲከተል፣ አዕምሯችን እንዲስማማ የምንጠብቀው? የውሳኔያችን ጥንካሬ ይፈተናል። ያ ፈተና ጊዜ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ወስነን መጽናት አለብን። ቀደም ብለን እምነትን ከጡንቻ ጋር አወዳድረነው ነበር። ጡንቻ ግፊትና ተቃውሞ በበዛበት መጠን እየጠነከረ ይሄዳል።

የብዙ ቢሊዮን ብር ኢንዱስትሪ የሆኑት የሰውነት ማጠንከሪያ ተቋሞች ሁሉ በዚህ ቲዮሪ ላይ የተመሠረተ ሥራ ነው የሚሰሩት። ከስሜታችንና ከአዕምሯችን በሚመጣብን ተቃውሞ አልፈን እምነትን እየተለማመድን ከሄድን እምነት እየጠነከረና እያደገ ይመጣል። በጊዜ ደግሞ እምነት ጠንክሮ በስሜትና በአዕምሮ ላይ ሲጎለምስ እነርሱም ድጋፋቸውን ይሰጣሉ። የሚከተለውን ካንድ የእንግሊዝኛ ዕለታዊ መንፈሳዊ ንባብ መጽሐፍ የተተረጎመ ነው። የባቡሩን ስዕል በጥሩ ሁኔታ ስለሚገልጸው ነው እዚህ ያስገባሁት።

ሶስት ሰዎች በገደል ጫፍ ላይ ይሄዳሉ  
ስሜት እምነትና እውነት ይባላሉ  
ስሜት አደናቅፎት ቁልቁል ሲንሸራተት  
እምነትም አብሮ ሲጎተት  
በጣም ስለተጠጋ ወደ ስሜት  
እርሱም ወደቀ ከፉ ውድቀት  
እውነት ግን ባለበት ሆኖ ሳይደናገጥ  
እምነትን ጎተተው ርቆ እንዳያመልጥ  
እውነትን ተደግፎ እምነት ሲነሳ  
ስሜትንም ቀስ በቀስ አወጣው ከደረሰበት አበሳ

ሚስ ቻርለስ ኢ. ካውማን፣  
(Streams in the desert Vol. 2)





እውነተኛ እምነት ጥርጣሬን ጨርሶ ያጠፋል ማለት አይደለም። በጥርጣሬም ወስጥ ግን አልፎ ይሠራል። ዎች ማን ኒ "What Shall This Man Do?" በሚለው መጽሐፋቸው የሰጡትን ገለጣ እንይ፤

*"በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስን ከያዙት አሳዳጆች እጅ ለማስለቀቅ የተደረገውን ጸሎት ማስታወስ እፈልጋለሁ። ጸሎታቸው ተመልሶ ጴጥሮስ ተፈቶ መጥቶ በሩን ሲያንኳኳ አማኞቹ እርሱ አይደለም በማለት ተከራከሩ "የእርሱ መልአክ ነው" አሉ ። በዚያ ቤት እምነት ነበር፤ እውነተኛ እምነት፣ ከእግዚአብሔር ተአምራዊ መልስ የሚያመጣ እምነት ነበር። ግን የሰዎች ደካማነትም እዚያው ቤት ነበር። ጥርጣሬ ቅርብ ነበር፣ በጊዜው እንገቱን ብቅ አደረገ። የጸሎቱ መልስ መሆኑን ከመቀበል ይልቅ ከዚያ በላይ የሆነ የሚያስመስል ጥርጣሬ ተከሰተ"።*

ሌላ የትና መቼ እንድሰማሁት ትዝ የማይለኝ አንድ እውነተኛ ታሪክ አውቃለሁ። በአንድ ከተማ ውስጥ (ኢንዶኔሽያ ይመስለኛል) ሰዎች ትንሽ ቤት ተከራይተው ጸሎት ቤት ከፈቱ። እነርሱ የተከራዩት ቤት ያለበት ግቢ ወስጥ ሌላ ባዶ ቤት ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሌሎች ሰዎች ያንን ባዶ ቤት ተከራይተው ዳንስ ቤት ከፈቱ።

የሙዚቃው ጩኸት የሰዎቹ ብዛትና ሌሎችም ዳንስ ቤትን ተከትለው የሚመጡት ባሕሪዎች የጸሎት ቤቱን ሰዎች በጣም አወኳቸው። ስለዚህ መጸለይ ጀመሩ "ጌታ ሆይ ይህንን ዳንስ ቤት ዝጋና ሌላ ከእኛ አገልግሎት ጋር የሚስማማ ነገር አምጣ" እያሉ ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩ ጀመር።

የዳንስ ቤቱ ተከራዮች ግን ስለጸሎታቸው ቢሰሙም ስቀውባቸው ሥራቸውን ቀጠሉ። አንድ ሌሊት ግን ኃይለኛ የአየር ነውጥ ሆኖ መብረቅ ወረደ። ያ መብረቅ በቀጥታ በዳንስ ቤቱ ወድቆ ሲያወድመው ጸሎት ቤቱ ግን ሳይነካ ቀረ። የዳንስ ቤቱ ተከራዮች የጸሎት ቤቱን ተከራዮች ከሰሷቸውና ፍርድ ቤት ሄዱ። የዳንስ ቤቱ ተከራዮች "ጸልየው ዳንስ ቤታችንን በመብረቅ አስመቱ" ሲሉ የጸሎት ቤቱ ተከራዮች ደግሞ "እኛ እንዲህ ያለ ነገር አላደረግንም ብለው ካዱ።" ዳኛው ሲፈርዱ "በተፈጥሮ

ኃይል ላይ ማንንም ጥፋተኛ ማድረግ አይቻልም፣ አንድ ነገር ግን አስገርሞኛል ከጸሎት ቤቱ ባለቤቶች ይልቅ የዳንስ ቤቱ ባለቤቶች የበለጠ እምነት እንዳላቸው አየሁ"።

ፈቃድ ለማመን ውሳኔ ሲያደርግ ጥርጥር ወዲያው ይጠፋል ማለት አይደለም። ይህ ሁኔታ በአፍ ሲነገር ቀላል ይመስል ይሆናል፣ በሕይወት ሲሆን ግን ትንሽ የተደበላለቀ ነው። ልብ ብለን ካየነው ትንሽ ጥርጥር የሌለበት እምነት ማግኘት ከባድ ነው። ጥርጥር እምነት ከሚፈተንባቸው ተቃውሞዎች ዋነኛው ነው። ታዲያ ጠላት ዋና መሳሪያውን በቀላሉ የሚተው ይመስላችኋል?

ያለምንም ጥያቄ እግዚአብሔር ይህንን ብሎኛል የሚላችሁ ሰው ወይ ራሱን እያታለለ ነው፣ ወይ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ሀቀኛ አይደለም። "ጨክኜ በጣም ባምን እኮ ይሠራ ይሆናል" የሚል ጭፍን እምነት በእምነት ላይ ማስቀመጥ ማለት ነው። ግን እምነታችን በእግዚአብሔር ላይ እንጂ በእምነታችን ላይ ብቻ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን።

እግዚአብሔር ሕይወታችንን በዝርዝር ያውቀዋል። ያለመረጃ ሙሉ እምነትን ለመለማመድ ያለንን አቅም ይረዳል። ታዲያ ትንሽ ጥርጣሬ እኛ የእርሱን አጋዥነት እንድንጠይቅ ያደርገናል እንጂ እርሱ ፊቱን አዙሮ እንዲመለስ አያደርገውም። ስለዚህ ሁልጊዜ ምርጫው እምነት ወይ ጥርጥር አይደለም። እግዚአብሔርን የሚያስደስተው በጥርጣሬ ፊት እንኳን እምነታችንን ይዘን መቆማችን ነው። ይህንን ስናደርግ እርሱም እኛን ወክሎ እንዲነሳ ያደርገዋል።

## 5. ቅን ጥርጣሬ

መጠራጠር ሁልጊዜ መጥፎ ነገር አይመስለኝም። ቅን የሆነ ጥርጣሬ አለ። ጥርጥር የሚጫወተው ጥሩ ሚና ሊኖረው ይችላል። ማይክ ፊሊፕስ ስል ጆርጅ ማክዶላንድ በጻፉት መጽሐፍ በዚህ አሳብ ላይ እንዲህ ብለው ጻፉ፣

ጥርጥር፣ አለማመንም እንኳን ቢሆን ነገራቸው በእግዚአብሔር እጅ እንዲሆን ለሚፈቅዱ ሁሉ ጥሩ መሳሪያ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር እምነታቸውን





እንዲጥሉ አያደርጋቸውም፣ ነገር ግን እምነታቸውን መገንቢያ አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል።

ጆርጅ ማክዶላንድ ራሳቸውም ደግሞ በዚሁ አሳብ ላይ ጽፈዋል።

> *"ጥርጣሬዎች እውነተኛ ለሆነ ሰው የሚመጡ መልዕክቶች ናቸው። ገና ላልተረዳናቸው ነገር ግን እንድንረዳቸው ለሚያስፈልጉ ነገሮች የመጀመሪያ በር አንኳኪዎች ናቸው። ጥርጣሬ ጥልቅ የሆነውን እርግጠኛነትን እንኳን ማለፍ ይችላል። ምክንያቱም ያልታወቀውን፣ ያልተጎበኘውን፣ ያልተያያዘውን ሁኔታ ቀና ብለን በምናይበት ጊዜ እርግጠኛ አለመሆናችን ብቻ ይሆናል እርግጠኝነታችን"።*

በደንብ ካሰብንበት እርግጠኛ ነኝ ሁላችንም ይህንን ልምምድ አሳልፈናል። በመጀመሪያ ጊዜ ሰው በጸሎት ተፈወስኩ ብሎ ሲናገር ስሰማ በውስጤ የነበረኝ ስሜት መጠራጠር ነበር። ጊዜው እያለፈ ሲመጣ፣ ብዙ ሰዎችም ተመሳሳይ ምስክርነት ሲሰጡ፤ በተለይ የአንዳንዶቹን ምስክርነት ላለመቀበል ምክንያት እንደሌለኝ ሳውቅ፣ "እህ" እያልኩ ማዳመጥ ጀመርኩ። ከዚያም "እስቲ ጠጋ ብዬ ልመርምረው" አልኩ። "እውነት ይመስላል" አልኩ፣ ቀጥዬም "እውነት እንደሆነ አምናለሁ" ማለት ደረጃ ደረስኩ። "ጌታ ሆይ እስቲ ለኔም ፈውስ" ብዬ መጸለይ ጀመርኩ "ዋው ጌታ ሲፈውስ" ብዬ ለመመስከር በቃሁ።

## 6. አስተሳሰብና ስሜት

እምነት ወይም ጥርጣሬ የፈቃድ ጉዳይ ነው የሚለው አነጋገር እምነትን ቀዝቃዛና ሀልውና የሌለው ሜካኒካል ድርጊት ብቻ የሚያደርገው ይመስላል። ግን እንደዚያ አይደለም። እምነት አዕምሮንና ስሜትን ይቃወማል ለማለት እንዳልሆነ አስቀድሜ እግዚአብሔር አዕምሮንም ሆነ ስሜትን እንደፈጠረ መጥቀሴን ታስታውሳላችሁ። ግን እምነት የፈቃድ ጉዳይ ነው ስንል ፈቃድ ዋናውንና የራስን ውሳኔ ያደርጋል ለማለት ነው እንጂ የአዕምሮና የስሜት ድጋፍ አያስፈልገውም ለማለት አይደለም። የአዕምሮንና የስሜትን አስተዋጽኦ መናቅ ራሱ ሞኝነት ነው።

## አዕምሮ

አዕምሮ በቀላሉ በሰይጣን ሊግባባ ይችላል ማለት ሙሉ ለሙሉ አይታመንም ማለት አይደለም።

> ምናብን ለመኮርኮር 9 .
>
> በማይታየው ስፍራ እግዚአብሔር የሚሠራውን ወይም ሊሠራ ያቀደውን እንዴት ለውቅ ችላለሁ?

መጽሐፍ ቅዱስ በአዕምሮ መንፈስ ስለመታደስ፣ አዕምሮን ስለመጠበቅ፣ የጨለማ አሳብ ስለአለማሰብ፣ የክርስቶስ አሳብ እንዲኖረን ጠንካራ በሆነ ቋንቋ አብዝቶ ይመክረናል። ይህንን ካደረገ አዕምሮ ለፈቃድ መልካም አማካሪ መሆን ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የተሞላ አዕምሮ፣ ለጌታ የሱስ ጌትነት ራሱን ካስገዛ፣ በእግዚአብሔር ግርማ የሚገረምና በእግዚአብሔር ሕልውና ደስ የሚሰኝ ከሆነ፤ ይህ አዕምሮ ፈቃድን በመምከር ታላቅ ጥቅም መስጠት ይችላል። እውነት በፈቃድና በምክንያትም ላይ መሰልጠን ይችላል፤ አንዱን ተቀብሎ ሌላውን የሚገፋ አይደለም።

አዕምሮ መንፈሳዊ የሆኑ ምክንያታዊነትንና አስተሳሰብን በማቀበል የፈቃድን የውሳኔ ኃይል ከፍ ማድረግ ይችላል። በእግዚአብሔርም ቃል ከተሞላ ፈጣን የሆነ ማስጠንቀቂያ በታቀደው ውሳኔ ላይ ማቀበል ይችላል። የተቀደሰ ምክንያታዊ አስተሳሰብ እምነትን ለመለማመድ ጠቃሚ ወዳጅ ነው።





ዛሬ በባህላችን ችግሩ ያልተቀደሰ አስተሳሰብ፣ መንፈሳዊ ጥበብን ያልተረዳ ምክንያታዊነት፣ ግትር እውቀት፣ የሥልጣኔያችን እውራ ጎዳና መሆኑ ነው። አስተሳሰብ ለስሜታችን ኃይለኛ አግባቢ ሲሆን ስሜታችን ደግሞ በተራው ለድርጊታችን ምክንያት ይሆናል። አዋቂዎች እንደሚሉት አዕምሯችን ከ 1200 ቃላት በላይ በደቂቃ አስተካክሎ ማውጣት ይችላል። ይህ ችሎታችን በባህል ተይዞ በምክንያታዊነት ታግቶ፣ ተቃውሞና መሳሳት ፈርቶ ባይያዝ ኖሮ የሚቀሰቀሰው ስሜታዊነት ለእድገት፣ ለሚዛናዊነት፣ ለጤና እና ከእግዚአብሔርም ጋር ላለን ግንኙነት እንቅፋት የሚሆን ይሆን ነበር። አዕምሯችን ግን ጌታን ሲያዳምጥ፣ መንፈስ ለገለጠው ቃሉ ሲገዛ፣ ለፈቃዱ መሪነት ሲታዘዝ፣ ያን ጊዜ የተቀደሰ ምክንያታዊነት ወይም አስተሳሰብ እያሳደግን ነው።

## ስሜት

ስሜትም ለፈቃድ በጣም ጠቃሚ የሆነ ድጋፍ መስጠት ይችላል። ራሳችንን ለእግዚአብሔር ስናስገዛ ስሜታችን ወይ ሰላም ይሰጠናል፣ ወይ የማይመች ስሜት ይሰማናል። አንዳንዴ ገና ነገሩ ሳይሆን ህሊናችን ይወቅሳናል። ብዙ ጊዜ በገጻችን የሚታየው ስሜታችን ነው። መንፈስ በውስጠኛው ክፍል መኖር የሚመርጠውን ያህል ስሜት ደግሞ ከፊት ለፊት ወጥቶ መታየት ይወዳል። ስሜታችን ከአስተሳሰባችን ጋር ቶሎ ስለሚተባበር፣ በእግዚአብሔር ቃል የተደገፈ አስተሳሰብ ለስሜትም መልካም ነው። እስቲ እንደገና ያንን ስዕል እናምጣና አንዳንድ ነገር አሻሽለን እንመልከተው።

## ምናብን ለመኮርኮር ፱.

በማይታየው ስፍራ እግዚአብሔር
የሚሠራውን ወይም ሊሠራ ያቀደውን
እንዴት ላውቅ ችላለሁ?




መንፈስ እግዚአብሔር የሚልከውን መልዕክት የምንቀበልበት ክፍላችን ነው ብለናል። ያ ከእግዚአብሔር ወደ መንፈሳችን የተላከው መልዕክት በጥቅም ላይ እንዲውል ወደ ሌሎቹ ክፍሎቻችን መተላለፍ አለበት። በስዕሉ ውስጥ የምናየው ያንን ነው። ከመንፈሳችን ወጥተው ወደ ሌሎቹ ክፍሎች የተዘረጉት ቀስቶች የሚያሳዩት ያንን ነው።

ለአዕምሯዊ ሰው እነኚህ መልእክቶች ቶሎ ወደ አዕምሮው ይመጡለታል። በስዕሉ ላይ በመንፈስና በአዕምሮ መካከል ባለው መስመር ላይ ያለችው ትንሽ ሳጥን መስኮት መሆኗ ነው። ያቺ መስኮት መኖሯንና አጠቃቀሟን ካወቅሁበት፣ መንፈስ ቅዱስ በዚያች መስኮት በኩል እውቀት ከመንፈስ ወደ አዕምሮዬ እንዲተላለፍ ያደርጋል። ይህ ማስተላለፍ ደግሞ በተለያየ ሁኔታ ሊከናወን ይችላል። ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ "የእውቀት ቃል" ወይም "የጥበብ ቃል ይለዋል።" አመጣጡ፤ ትዝ በሚለን ነገር፣ ብልጭ የሚልልን አሳብ፣ የሚታየን ስዕል ወይም ሌላ ነገር ሊሆን ይችላል። ሲመጣ ግን ለመጣለት ሰው ግልጽ ይሆናል።





በተፈጥሮ ስሜታዊ (emotional) ለሆነ ሰው ደግሞ ከመንፈስ የሚመጣው ቀስት ወደስሜቱ ለመሄድ ያደላል። እንዲህ ያለ ሰው ድንገት ጠንካራ ስሜት ሊመጣበት ይችላል። የዚህ አይነት ሰው ያ ስሜት ሲመጣበት ያውቀዋል። አሁንም ገለጻው የእውቀት ወይም የጥበብ ቃል ነው።

አንዲት የፈውስ ስጦታ ያላቸው ሴት ሲናገሩ፣ "ለበሽተኛ ልዩ የሆነ የርህራሄ መንፈስ በውስጤ ከተሰማኝ፣ ያ በሽተኛ ከጸለይኩለት እንደሚፈወስ እርግጠኛ እሆናለሁ" አሉ። አንዳንድ ሰዎች በጸሎት ላይ ሳይጠብቁትና ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ መንገድ እንባቸው ዱብ ዱብ ማለት ይጀምራል። ለረጂም ጊዜ እንዲህ አይነት ሁኔታ የሚያጋጥማቸው ሰዎች ምክንያቱን ስለማያውቁት ወይ ይደብቁታል ወይ ደግሞ ያፍሩበታል። (በተለይ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ወደ አገራችን ሲገባ፣ አልቃሻነት ክርስቲያኖች ከሚወቀሱበት ነገሮች አንዱ ነበር)። እየቆየ ሲሄድ ግን እንባ የእግዚአብሔርን ኃይል በዚያ በተጸለየለት ሰው ላይ ወይም በተጸለየበት ነገር ላይ የሚፈታ መሆኑን ይገነዘባሉ።

በተቀደሰና ባልተቀደሰ ስሜት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው ለሚለው ጥያቄ ቀላል የሆነ መልስ ቢኖረኝ ኖሮ እወድ ነበር። ግን ቀላል መልስ የለውም። ስሜት ደጋግሜ እንዳልኩት በቁጥጥራችን ስር አይደለም። ከዚህም የተነሳ ውስጣዊ ሁኔታችንን ለመግለጽ ጥሩ መለኪያ ነው። እንባቸውን መቆጣጠር እስኪያቅጣቸው ድረስ እያለቀሱ "ምነው ምን መጣ?" ሲባሉ "አይ ምንም፣ ደህና ነኝ" የሚሉ ሰዎች አጋጥመዋችሁ እያውቁም፣ እርግጠኛ ነኝ ብዙ ጊዜ አጋጥመዋችኋል። ሲከፋን አንድ የተበላሸ ነገር አለ የሚል ስሜት ስለተሰማን ነው። የምንሳሳተው ግን ሲከፋን አንድ ነገር ለመበላሸቱ ትክክለኛ የሆነ ምልክት ነው ብለን ያንን ነገር ለመለወጥ በምናደርገው ድርጊት ነው። መከፋት አንድ ነገር መበላሸቱን ሊነግረን ይችላል እንጂ ምን ማድረግ እንደሚገባን አይነግረንም።

የተቀደሰ ስሜት ከብዙ ነገሮች መገኘት የሚመጣ ነው። መንፈሳዊ እውቀት ዋናው ቁልፍ ነው። ይህም ብዙ ነገሮችን ያጠቃልላል፤ የእግዚአብሔርን ቃል አምኖ በመቀበልና እንደ ቃሉ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የቅርብ ግንኙነት በማሳደግ፣ መንፈሳዊ ውጊያን እንዴት መቋቋም እንዳለብን በመማር፣ ዲስፕሊንን

በመለማመድ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ባለን ግንኙነት በማደግ፤ እነኚህ ነገሮች በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ጤናማ ስሜትን ያመጣሉ። ስሜት በዚህ አይነት እንክብካቤ ከተያዘ ለፈቃድ አባሪ መሆን ይችላል። ሆኖም ግን የውሳኔ መሠረት መሆን አይችልም።

አንዳንድ ሰዎች ከመንፈሳቸው በቀጥታ ወደ አካላቸው የሚመጣ ምልክት ያገኛሉ። ይህ በስዕሉ ውስጥ ከመንፈስ በቀጥታ ወደ አካል በሚሄደው ቀስት ተጠቁሟል። ለአንድ ሰው ለመጸለይ ያ ሰው የት ጋ እንዳመመው ለመጠቆም በጸላዩ ተመሳሳይ አካል ላይ የህመም ስሜት መሰማት ብዙ የጸሎት አገልገሎት የሚሰጡ ሰዎች የሚመሰክሩት ነው። የሌላውን ሸክም መሸከም ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ ነው። ለዚያ ሰው ጊዜ ወስደው በሚጸልዩበት ጊዜ በራሳቸው ላይ ያለው ህመም ሲቀንስ የጸለዩለትን ሰው ሁኔታ ያሳውቃቸዋል።

## 7. ድርቀትና ጥርጥር

ድርቀትና ጥርጥር ሁላችንም በተለያዩ ጊዜያት የምናልፍበት ልምምድ ነው። አንዳንዴ ለትንሽ ጊዜ አልፎ አልፎም ለብዙ ጊዜ ህይወታችን ጋዝ እንዳለቀበት መኪና ይሆናል፤ መንቀሳቀስ ያቅተዋል። ይህ ሲሆን በጥርጥር ተይዘን ሊሆን ይችላል። በጥርጥር ምክንያት የሚመጣ መንፈሳዊ ድርቀት አለ። መረዳት መታዘዝን ይከተላል ብለን አልፈናል፤ አንዳንድ ሰዎች ግን መረዳት ካልቀደመ ብለው መታዘዝን እምቢ ይላሉ። ውጤቱ መንፈሳዊ ድርቀት ይሆናል። ማክዶላንድ እንደጻፈው "የመጣላችሁ ቃል እውነት አልመስል ካላችሁ፣ ቃሉ የጌታ ቃል አይደለም ወይም እናንተ ቃሉን ለመረዳት በቂ ሃቀኝነት የላችሁም"። ያንድ ሰው አዕምሮ መቀበል የሚችለው ቃል ያ ቃል የጌታ ቃል እንደመሆኑ መጠንና ሰውዬው ከጌታ ጋር ባለው ህብረት መጠን ነው። እውነት ያልሆነ ቃልና ህብረት ማጣት መረዳትን ይከለክላል።

ስለዚህ የያዛችሁ መንፈሳዊ ድርቀት መረዳት ካለመቻላችሁ የተነሳ ከሆነ፤ መፍትሔው የእግዚአብሔርን ቃል በሞኝነት መታዘዝ ነው። መረዳትና መንፈሳዊ ቅባትም ተከትለው ይመጣሉ።





በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንዴ ድርቀት ፈተና ነው። ያ ማለትም በድርቀት የሚመላለሰው ሰው በዚያ ሁኔታ ውስጥ ማለፉ በጥፋቱ ወይም የራሱ በሆነ ምክንያት አይደለም። እንዳውም ያ ሰው ወይም ያቺ ሴት በሚችሉት ሁሉ ታዛዦች በመሆን ሲመላለሱ ድርቀት ውስጥ ይገባሉ። ሰው ወደ በለጠ መንፈሳዊ እድገት እንዲደርስ እግዚአብሔር አንዳንዴ ድርቀትን ይጠቅማል። ታዲያ በዚያን ጊዜ የምናደርገው ምንድነው? መልሱ አሁንም ያው መታዘዝ ነው። ባለመታዘዝ ምክንያት ለመጣብን ድርቀት ማድረግ የሚገባን መታዘዝን መለማመድ ነው። ቃሉን መታዘዝ መቀጠል አለብን። በስሜታችን ለርሱ ስላለን ፍቅር ብቻ ሳይሆን ስሜታችን እምቢ ቢልም በፈቃዳችን መታዘዝን መለማመድ፣ ደግመን ደጋግመን ያንኑ ማድረግ ነው፣ ቅባቱ ይከተላል።

## 8. ፍርሀትና ጥርጣሬ

ፍርሀትን መለማመድ ሰይጣን በስሜታችን ላይ ካለው የተጽእኖ መንገዶች አንዱ ነው። የፍርሃት አላማው ደግሞ እኛ የእግዚአብሔር ከሆነው ነገር ዞር እንድንል ማድረግ ነው። በዚህ ጊዜ እምነታችን ብርታትን ይጠይቃል። ይህም ማለት የአካባቢው ሁኔታ ሳይመችም በፈቃድ እግዚአብሔርን መተማመን ማለት ነው። ብርታት፣ ሁኔታዎችና ስሜቶች አይሆንም ሲሉ በእግዚአብሔር ለመተማመን መፍቀድ ማለት ነው። እኔ ፍርሀት አልወድም፣ አጥብቄ ከምጠላቸው ነገሮች አንዱ ነው።

ነገር ግን ጌታ የሱስን መከተል ደግሞ አልፎ አልፎም ቢሆን ፍርሀት ማምጣቱ የተረጋገጠ ነው። አንዳንዴ እምነታችን የጠበቅነውን ያህል አይሰራልን ይሆናል ብለን እንፈራለን። ለምሳሌ ለፈወስ መጸለይ ያስፈራኝ ይሆናል፣ ጸሎቱ ምንም ለውጥ ላያመጣ ይሆናል የሚል ፍርሀት ይኖራል። በእኛ እምነተቢስነት ሰዎች ይጎዱ ይሆናል የሚል ፍርሃት ይመጣል። ራሳችንን በሰዎች ፊት እናቃልላለን ብለን እንፈራለን፣ ሌሎች ለምንለው ነገር ተቀባይነት አይሰጡት ይሆናል ብለን እንፈራለን።

ታውቃላችሁ እነኚህ ሁሉ እውነተኛ ፍርሀቶች ናቸው። ታላላቅ የተባሉ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን የሕይወት ታሪክ ስታነቡ፣ ከታላቁ ሐዋርያ ከጴጥሮስ ጀምሮ፣ በታላቁ ሐዋርያ በጳውሎስ በኩል አድርጎ ፍርሃትን የማይለማመድ እውነተኛ አገልጋይ

የለም። ግን ስለ ፍርሀት አንድ ሌላም ነገር ልንገራችሁ፣ ፍርሀት ሌላ ምክንያትም አለው። ፍርሀት እግዚአብሔር አንድ መልካም ነገር ለማድረግ መንሳሳቱን ማረጋገጫ ነው።

ይህ ትምህርት የሚያሳስበኝ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አለ። የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው በኢያሱ መሪነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ እስራኤላውያንን ወደ ተስፋይቱ ምድር ለማስገባት የተነሱትን ካህናት ያሳስበኛል። ማድረግ ያለባቸው አንደ ነገር ብቻ ነው፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ እግራቸውን ማስገባት፤ ከዚያ ወንዙ ይቆማል፣ሕዝቡ በደረቅ ምድር ይሻገራል። ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል? ዮርዳኖስ ወንዝ ጫፍ ላይ ቆመው ፈጣኑ የዮርዳኖስ ወንዝ ውሀው እየተጋፋ ቁልቁል በፍጥነት ሲሄድ የእናንተን አላውቅም እንጂ እኔ ግን ፍርሀት ተሰምቷቸዋል ብዬ እገምታለሁ፤ በውኃው መወሰድ አስፈራርቷቸዋል። "እነኚያ ሞኞች ካህናት" እየተባሉ መሳቂያና መሳለቂያ የሆነ ታሪክ ትተው ማለፋቸው ሳያሰጋቸው አልቀረም። አንድ እድል እንኳን ቢተርፉ ለረጂም ጊዜ የህዝቡ ሳቅ አያቋርጥ ይሆናል። ውኃው አይከፈል ይሆናል፣ ሌላው ትልቁ ፍርሀት ነው። ኢያሱ ለመሆኑ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ከእግዚአብሔር በትክክል ሰምቷል? ዳር ቆሞ አስተያየት ሰጪም ሞልቷል፣ "ይሄ ለእኔ በፍጹም ሎጂካል አይደለም" የሚል የኮሌጅ ተማሪ፣ (እሺ የቶራ ተማሪ) ወይም "እኔ አልተሰማኝም ቀፎኛል" የሚል ስሜተኛ። እምነታቸው ሙሉ አልነበረም። ነገር ግን የፈቃድ ብርታት ስለነበራቸው አንድ እግራቸውን አንቀሳቅሰው ወደፊት ተራመዱ፤ የእነርሱ እግር መንቀሳቀስ ሲጀምር እግዚአብሔር ሥራውን ሠራ።

እነኚያ ካህናት እኮ ከእኛ የተለዩ፣ ማለትም ከእኔ ከአንቺ ከአንተ የተለዩ ሰዎች አልነበሩም። ወይም የተለየ እምነታዊ ጥበብ ወይም መንፈሳዊ ብርታት ኖሯቸው አይደለም። ፍርሀት ከሌለብን መጋፈጥ የሚገባንን እላፊነታችንን እየሸሸን ራሳችንን በመሸፈን ውስጥ ነው ያለነው ማለት ነው። ፍርሀት ከሌለን ባለንበት ቆመናል ማለት ነው። ከተመቻቸንበት ሁኔታ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ባለማለት በተጠንቀቅ ቆመናል። ያ ማለትም ጠውልገናል፣ ታፍነን መሸተት ጀምሬናል፣ እድገት አይታይብንም፣ ጣፋጭነታችን አልፎ ጎምዝዘናል ማለት ነው። ሞአባውያን በነቢዩ በኤርምያስ በኩል በእግዚአብሔር ተገስጸው ነበር





*"ሞአብ በአምቡላው ላይ እንዳረፈ የወይን ጠጅ ከልጅነት ጀምሮ የተረጋጋ ነበረ፣ ከእቃ ወደእቃ አልተገለበጠም.... ቃናው እንዳለ ነው መአዛውም አልተለወጠም..... ስለዚህ እቃውን የሚገለብጡ የሚገለባብጡ ሰዎችን የምልክበት ጊዜ ይመጣል" ኤርምያስ 48፥ 11-12።*

ሞአባውያን ለውጥ ይፈሩ ነበር። ቀላል የሆነውን መንገድ ብቻ በመምረጥ ምንም ለውጥ አያደርጉም ነበር። የተቀመጡበት አምቡላ መአዛቸውን አበላሽቶታል። በተለይ የእምነት ውሳኔን በሚመለከት የሚያስፈራንን ነገር ሁልጊዜ እንጥላው። የእድገታችንና ታላቅ ነገር የመምጣቱ ምልክት ሊሆን ይችላል።

## በአጭሩ

ፒተር በፊት የታወቁት ፊላንትሮፒስት የዋረን በፊት ልጅ ናቸው። ፒተር በፊት "Life is What you make it" በሚለው መጽሐፋቸው መዝጊያ ላይ አንድ ጽሁፍ አስቀምጠዋል። እኔ ይህንን ምዕራፍ ታይፕ በማደርግበት ጊዜ ባለቤቱ ኤልሳቤጥ መጽሐፉን ታነበው ነበር። አንድ ቀን ታዲያ ቀጥሎ ያለውን ክፍል ለእኔም አነበበችልኝ። ፒተር በፊት እንዳሉት ጽሁፉን የጻፉት ጀርመናዊ ባለቅኔ ጎቴ ይባላሉ። ጽሁፉን ልተረጉመው ሞክሬአለሁ፤ ግን ለአንዳንዶቻችሁ እንግሊዝኛው የበለጠ ትርጉም የሚሰጣችሁ ስለ መሰለኝ እንግሊዝኛውንም አስቀምጬዋለሁ።

ሰው ካልተሰጠ (committed) መጠራጠር አለ ማለት ነው፣ ወደ ኋላ የማለት እድል። መንሳሳትንና መፍጠርን በተመለከተ አንድ ቀላል እውነት አለ። ይህንን እውነት አለማወቅ ከቁጥር በላይ የሆኑ አሳቦችንና ጥሩ ጥሩ ፕላኖችን ይገድላል። አንድ ሰው ለአሳቡ ወይም ለፕላኑ ራሱን በእርግጠኝነት ከሚሰጥበት ቅጽበት ጀምሮ ለዚያ ነገር አስፈላጊ የሆነ ነገር ሁሉ መከናወን ይጀምራል። በሌላ ጊዜ ፈጽሞ ሊሆኑ የማይችሉ ነገሮች ናቸው የተባሉ ሁሉ መሆን ይጀምራሉ። ከውሳኔው የተነሳ ተከታታይ የሆኑና ውሳኔውን የሚደግፉ ብዙ ጎዳዮች፣ የማይታዩ ክንውኖችና ስብሰባዎች፣ እንዲሁም የቁስና የገንዘብ እርዳታ በፍጹም ከግምት ውጪ በሆነ መንገድ ወደ እርሱ ይመጣሉ። ስለዚህ ማድረግ ያቀዳችሁትን ሁሉ፣ ወይም ራዕያችሁን ጀምሩት። ድፍረት በውስጡ ብልሀነት፣ ኃይልና ምትሀት አለው፤ አሁኑኑ ጀምሩት።

Untill one is committed; there is hesitancy, chance to draw back. Concerning all acts of initiative and creation, there is one elementary truth, the ignorance of which kills countless ideas and splendid plans: that the moment one definitely commits onself, then providence moves too. All sorts of things occur to help one that would never otherwise have occurred. A whole stream of events issues from the decision, raising in one's favor all manner of unforeseen incidents and meetings and material assistance, which no one could have dreamed would come his way. Whatever you can do, or dream you can do begin it. Boldness has genius, power, and magic in it. Begin it now.

በሚቀጥለው ምዕራፍ አንድ አርዕስት እናያለን። ይህ ሁኔታ ደግሞ የኅብረተሰባችን (በተለይ የዲያስፖራ ውጤት ሆነን በምዕራቡ ለምንኖር) ትልቅ ክፍል ስለሆነ የእምነት ጠላት ነው ብለን ለመገመት እንኳን አንገምት ይሆናል።





# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ብቸኝነት

የእምነት ጠላቶችን ስናይ የመጨረሻ ነጥብ አድርጌ ላቀርበው የፈለኩት ብቸኝነትን ነው። በምዕራቡ ኅብረተሰብ በተለይ በአሜሪካ ለብቸኞች የተለየ አድናቆት አለ። ባህሉ እራስህ በራስህ ቁም! ራስህን ቻል! ሰውዬው! ጀግናው፣ ይህ ሁሉ ብቸኞችን የሚያቆላምጥ አዳናቂ አባባል ነው። ብዙ አፈ ታሪኮችም አሏቸው፣ አዳኙ፣ የተራራው ሰው፣ ብቸኛው ከብት አርቢ (The Lone Ranger)። ሰው ያስፈልገኛል የሚል ምልክት እንኳን ካሳያችሁ ፈሪነት ይመስላል "ምነው ራስህን መቻል አቃተህ እንዴ?" በሚል የጥያቄ አመለካከት ይገላምጧችኋል።

የመቻቻል ብቃት ሁሉን በራስ ማድረግ በሆነበት በምዕራቡ ኅብረተሰብ አብሮ የሚለው ቃል ብዙ ተደናቂነት የለውም። የብቸኝነት አባዜ በጣም ስለተናወጣቸው በጋብቻ እንኳን ሐብትሽ በሐብቴ ቀርቶ ቅድመ ጋብቻ የፍቺ ስምምነት (prenuptial agreement) የተከበረ የሕግ ሐረግ ሆኗል። በውስጥ ሕይወታችን ሰው እንደሚያስፈልገን ያለን ስሜትና ጉጉት ጉልህ ቢሆንም እንኳን፣ "እጅህን አትስጥ፣ ነፃነትሽን አትሰዪ" ነው የሚሰጠን ምክር።

አንድ አፍሪካዊ ካህን ወደ አሜሪካ ተጉዘው በአንድ የሰፈር የጸሎት ፕሮግራም ላይ ተካፈሉ ይባላል። ከጸሎቱ በኋላ ከአስተባባሪው ጋር ሲጫወቱ አስተባባሪው "ስለ አሜሪካ የሚያስደንቀዎት ነገር ምንድነው?" ብዬ ጠየኳቸው አሉ። ገና ጥያቄዬን ሳልጨርሰው ከአፌ ነጥቀው "ብቸኝነታችሁ" ብለው መለሱልኝ። እኔ "ታላላቅ አውራ ጎዳኖቻችሁ፣ ረዣዥም ሕንጻዎቻችሁ" ወይ ደግሞ "እንግዳ ተቀባይነታችሁ፣ ለተቸገረ ያላችሁን ለማካፈል ያላችሁ ችሮታ" ወይም ተመሳሳይ መልሶች ነበር የጠበቅሁት፣ መልሳቸው ገርሞኝ "ምን ማለትዎ ነው?" ብዬ ጠየቅኋቸው።

Untill one is committed; there is hesitancy, chance to draw back. Concerning all acts of initiative and creation, there is one elementary truth, the ignorance of which kills countless ideas and splendid plans: that the moment one definitely commits onself, then providence moves too. All sorts of things occur to help one that would never otherwise have occurred. A whole stream of events issues from the decision, raising in one's favor all manner of unforeseen incidents and meetings and material assistance, which no one could have dreamed would come his way. Whatever you can do, or dream you can do begin it. Boldness has genius, power, and magic in it. Begin it now.

በሚቀጥለው ምዕራፍ አንድ አርዕስት እናያለን። ይህ ሁኔታ ደግሞ የኅብረተሰባችን (በተለይ የዲያስፖራ ውጤት ሆነን በምዕራቡ ለምንኖር) ትልቅ ክፍል ስለሆነ የእምነት ጠላት ነው ብለን ለመገመት እንኳን እንገምት ይሆናል።





# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ብቸኝነት

የእምነት ጠላቶችን ስናይ የመጨረሻ ነጥብ አድርጌ ላቀርበው የፈለኩት ብችኝነትን ነው። በምዕራቡ ኅብረተሰብ በተለይ በአሜሪካ ለብቸኞች የተለየ አድናቆት አለ። ባህሉ እራስህ በራስህ ቁም! ራስህን ቻል! ሰውዬው! ጀግናው፣ ይህ ሁሉ ብቸኞችን የሚያቀላምጥ አዳናቂ አባባል ነው። ብዙ አፈ ታሪኮችም አሏቸው፣ አዳኙ፣ የተራራው ሰው፣ ብቸኛው ከብት አርቢ (The Lone Ranger)። ሰው ያስፈልገኛል የሚል ምልክት እንኳን ካሳያችሁ ፈሪነት ይመስላል "ምነው ራስህን መቻል አቃተህ እንዴ?" በሚል የጥያቄ አመለካከት ይገላምጧችኋል።

የመሻሻል ብቃት ሁሉን በራስ ማድረግ በሆነበት በምዕራቡ ኅብረተሰብ አብሮ የሚለው ቃል ብዙ ተደናቂነት የለውም። የብቸኝነት አባዜ በጣም ስለተናወጣቸው በጋብቻ እንኳን ሐብትሽ በሐብቴ ቀርቶ ቅድመ ጋብቻ የፍቺ ስምምነት (prenuptial agreement) የተከበረ የሕግ ሐረግ ሆኗል። በውስጥ ሕይወታችን ሰው እንደሚያስፈልገን ያለን ስሜትና ጉጉት ጉልህ ቢሆንም እንኳን፣ "እጅህን አትስጥ፣ ነፃነትሽን አትሰዊ" ነው የሚሰጠን ምክር።

አንድ አፍሪካዊ ካህን ወደ አሜሪካ ተጉዘው በአንድ የሰፈር የጸሎት ፕሮግራም ላይ ተካፈሉ ይባላል። ከጸሎቱ በኋላ ከአስተባባሪው ጋር ሲጫወቱ አስተባባሪው "ስለ አሜሪካ የሚያስደንቀዎት ነገር ምንድነው?" ብዬ ጠየኳቸው አሉ። ገና ጥያቄዬን ሳልጨርሰው ከአፌ ነጥቀው "ብቸኝነታችሁ" ብለው መለሱልኝ። እኔ "ታላላቅ አውራ ጎዳኖቻችሁ፣ ረዣዥም ሕንጻዎቻችሁ" ወይ ደግሞ "እንግዳ ተቀባይነታችሁ፣ ለተቸገረ ያላችሁን ለማካፈል ያላችሁ ችሮታ" ወይም ተመሳሳይ መልሶች ነበር የጠበቅሁት፣ መልሳቸው ገርሞኝ "ምን ማለትዎ ነው?" ብዬ ጠየቅኋቸው።

ሲያብራሩልኝ እንዲህ አሉ፣ "በእኔ አገር ሰው ብቻውን ለመኖር በአሳቡ እንኳን አይመጣለትም። ምንም ገንዘብ ቢኖረው አፓርታማ ውስጥ እንኳን ከሌላ ጋር አብሮ ነው የሚኖረው፤ ሰው ራሱን ከቤተሰቡና ከወዳጅ ነጥሎ መኖሩ እኮ ራሱ ድህነት ነው" አሉ።

አስተባባሪው "በአሳቤ አፍሪካዊው ካህን የነገሩኝ ሁኔታ ይታየኝ ጀመር አሉ። አብሮ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ሆኖ እንደ ስዕል ታየኝ፣ ባየሁት ስዕል ደግሞ ተማረክሁ፣ እንደገና ደግሞ አስፈሪም ሆነብኝ። በውስጤ ያለ አንድ ነገር ያን አብሮ መሆንን በጣም ፈለገው፣ እንደገና በውስጤ ያለ ሌላ ነገር ያንኑ አብሮ መሆን የሚለውን አሳብ ይዋጋው ጀመር፤ የሚያመሰቃቅልና የሚያጣብብ ስሜት ፈጠረብኝ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሕይወቴ ወስጥ ጥያቄ አለብኝ፡- የቱ ነው መልካሙ አብሮ መሆን ወይስ ለብቻ መሆን? መሆን አለመሆን? ጥያቄው ያ ነው" (በትንሽ የሼክስፔር ቅኝት ነው የዘጉት)

እምነት የህብረት ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በማምንበት ጊዜ ከአመንኩት ነገር ጋር ህብረት አለኝ ማለት ነው። በእግዚአብሔር ስለማምን ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት አለኝ። የህብረቱ ጥንካሬ ደግሞ በእግዚአብሔር የተደገፈ ነው። ይህ ሁኔታ የተጀመረው ደግሞ በእምነታችን ጀማሪ በሆነው በጌታ የሱስ ነው።

> *"አብ ሲሰራ ያየውን እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፣ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና" ዮሐንስ 5፥ 19።*

ጌታ የሱስ በዚህ ቦታ በሚያደርገው ነገር ሁሉ በፍጹም በእግዚአብሔር ላይ የተደገፈ መሆኑን ነው የሚያውጀው። ከአስር ምዕራፎች በኋላ ደግሞ ይህንን ሁኔታ ከእኛ ጋር የሚያያይዘው ቃል ተናገረ።

> *"ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" ዮሐንስ 15፥ 5።*

ጌታ የሱስ ከአባቱ ጋር ባለው ግንኙነት እውነት የሆነው እኛ ከእርሱ ጋር ባለንም ግንኙነት እውነት ነው። በእግዚአብሔር ላይ መደገፍን በምሳሌነት አሳየን፣ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ዋጋ (virtue) ያለው ነገር መሆኑን ሲያሳየን ነው





*"ምንም ሊያደርግ አይችልም"* የሚለውን አባባል የተጠቀመው። በእግዚአብሔር ላይ ካለመደገፍ በስተቀር *ምንም መሥራት* እንድማንችል ነው የሚያሳየው፣ ያ ብቻ ሳይሆን ጌታ የሱስ በትምህርቱ ሁሉ ያሳየን ይህ መደጋገፍ ከላይ ወደ ታች ብቻ ሳይሆን ወደጎንም የሚሆን ነው። ከእርሱ ጋር እንደተያያዝን እርስ በርሳችንም መያያዝ እንዳለብን ነው ጌታ ያስተማረን። እንዲያውም ጌታን በሙላት ለመለማመድ የእርስ በእርስ ኅብረት አስፈላጊ ነው። ወይም አንድ የእግዚአብሔር ሰው እንዳሉት "ብቻዬን ሆኜ ስፈልገው (እግዚአብሔርን ማለታቸው ነው) እንድንዴ አውቆ የተደበቀብኝ ይመስለኛል፣ በኅብረት ውስጥ እንዳገኘው ፈልጎ ሳይሆን አይቀርም"፤ ምልክትነቱም ግልጽ ነው፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሲርቁ መጀመሪያ የሚያደርጉት ከኅብረት ራሳቸውን ማግለል ነው።

## 1. የኅብረቱ ክፍል መሆን

አንድ በፈውስ ስጦታ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያገለግሉ ሰው አንድ ቀልቤን የያዘው ነገር ጽፈው አነበብኩ።

"እግዚአብሔር የክርስትና ሕይወቴን አድሶ ይህንን አገልገሎት (የፈውስ ስጦታ ማለታቸው ነው) ከሰጠኝ ከሁለት አመት በኋላ በአመቱ በመጀመሪያው ወር አንድ ነገር ተናገረኝ" አሉ። "በዚህ አመት ብትታመም በራስህ ጸሎት አልፈውስህም" አለኝ። ከዚያም ልክ እንደቃሉ አደረገ። ትንሽ የራስ ምታት ወይ ጉንፋን በያዘኝ ቁጥር ራሴ ለራሴ ስጸልይ ምንም ለውጥ አላይም፤ ሌሎች እንዲጸልዩልኝ ስጠይቅ ግን እግዚአብሔር ወዲያው ይፈውሰኛል" አሉ።

እነኚህን ነጥቦች እስቲ እናሰላስላቸው።

- እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ያለን ህብረትና መደጋገፍ እያደገና እየቀጠለ እንዲሄድ እንጂ እንድንራራቅ ፈቃዱ አይደለም።
- እድገታችን የታቀደው አብሮ ነው እንጂ ለየብቻ አይደለም።
- እንደ እግዚአብሔው አመለካከት ሌሎች በሕይወታችን እንደሚያስፈልጉን ማወቅ የተከበረ ወይም ዋጋ ያለው ባሕሪ ነው።

አንድ ጥያቄ እዚህ ጋ ለማንሳት አስፈላጊ ቦታ ይመስላል። ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ለመግለጽ አካል የሚለውን ቃል ሲጠቀም ስዕላዊ አገላለጽ ነው ወይስ እውነተኛ ነው? በተፈጥሮአዊ አገላለጽ መቼም ስዕላዊ አገላለጽ መሆኑ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ማንኛችንም የሌላ አካል ቅጥያ አይደለንም። ነገር ግን ጳውሎስ አካል የሚለውን ቃል የተጠቀመበትን

እውነተኛ አገላለጽ ከመንፈሳዊ አንጻር ማየት መቻል አለብን። መንፈሳዊው አለም እውነተኛ መሆኑን ካመንን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እኛ የክርስቶስ እንደሆንን ነው የሚያሳየው (1 ቆሮንቶስ 12)። በመንፈሳዊ አለም ብቸኛ መሆን ተፈላጊ አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን የማይቻል ለምምድ ነው። ምክንያቱም አንድ ብልት የሌላውን ብልት አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም። ምንም ያህል አይን ጥሩ ቢሆን አይን መስማት አይችልም።

በክርስቶስ አካል ኅብረት ውስጥ የእግዚአብሔር መልካም ነገሮች የሚተላለፉ ናቸው። እውነተኛ ፍቅር በሥራ ሲገለጽ ስናይ የበለጠ ፍቅር እንድንለማመድ ይገፋፋናል። መልካም ባህሪ ያለው ሰው ስታዩ፣ የእርሱን ባህሪ ለመለማመድ ትጥራላችሁ፤ እግዚአብሔር ሁኔታውን ያቀነባበረው እንደዚያ እንዲሆን አድርጎ ነው።

የስላሴ ምስጢር የዚህ አብሮ የመሆን የኅብረት ውህደት ምሳሌ ነው። አንድ አምላክ በሶስት ህልውና መገለጹ። አንድነቱን መረዳት አስፈላጊነቱ በስላሴ ውስጥ ያለውን ውህደት ለመገንዘብ ነው። ሶስትነቱን መረዳት ደግሞ ፍቅርንና የመሳሰሉትን መለኮታዊ ባህርያት ለመረዳት ይጠቅማል። ምክንያቱም ፍቅር ከአንድ በላይ መሆንን ይጠይቃል።

ለመውደድ የሚወደድ ያስፈልጋል። ፍቅር በብቸኝነት ወስጥ ቦታ የለውም። ወዳጅ እንዲኖር ተወዳጅ መኖር አለበት፣ ፍቅር በሁለቱ መካከል በመግባት ነው ሊገለጽ የሚችለው። ስላሴ መለኮታዊ ህብረት ነው፤አብ ወዳጅ ሲሆን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ተወዳጅ፣ ወልድ ወዳጅ ሲሆን አብና መንፈስ ቅዱስ ተወዳጅ፣ መንፈስ ቅዱስ ወዳጅ ሲሆን አብና ወልድ ተወዳጅ። በአንድነታቸው ደግሞ ቃሉ እንደሚል "እግዚአብሔር





ፍቅር ነው" ስለዚህ እግዚአብሔር ህብረት ነው። ይህ መለኮታዊ ህብረት ደግሞ ለሰብአዊ ህብረት ሞዴል ነው። ሞዴል ብቻ ሳይሆን ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደሚል መነሻውም ነው።

> *"ከክፉ ምኞት የተነሳ በአለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ ከመለኮታዊ ባህሪ ተካፋዮች እንድትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነው ተስፋ ሰጥቶናል" 2ጴጥሮስ 1፥ 4።*

እግዚአብሔር የራሱ ባህሪ ተካፋዮች እንድንሆን ይፈቅዳል፣ ይጋብዘንማል። ይህ መለኮታዊ ህብረቱ ነው። ግን አንተ ብቻ ሳትሆን የተጋበዝከው እናንተ ሁላችሁም እብራችሁ ነው። የመለኮታዊውን ክብር ልናንፀባርቅ የምንችለው እንዳችን ከሌላችን ጋር በሚኖረን ፍጹም ህብረት ውስጥ ብቻ ነው።

በእምነት ማደግን በሚመለከት እንግዲህ ከሌሎች ተለይተን ብቻችንን በሆንበት ቦታ ልናድግ አንችለም። ከዚህም የተነሳ፣ በእምነት ማደግ እንዳችን ከሌላችን ጋር የምንወዳደርበትና የበለጥን ነን የምንልበት ሊሆን አይችልም። እይኔ ከጆሮዬ ጋር አይወዳደርም፤ ተወዳዳሪዎች ወይም ተቃራኒዎች ሳይሆኑ ለአንድ ግብ የሚሠሩ ናቸው። አንተ ታጋሽነትህን፣ ልምምድህን፣ እውቀትህን፣ ጥበብህን፣ አመለካከትህን፣ ስጦታህን ወደ ህብረታችን ታመጣለህ። እነኚህን የአንተን ባህርያት ከአንተ ጋር ህብረት ከሌለኝ በስተቀር ሌላ ቦታ ላገኛቸው አልችልም፤ በእምነት ለማደግ ግን በጣም ያስፈልጉኛል፣ በግልባጩ ደግሞ እኔም የራሴን ይዤ ነው የምመጣው።

በአንድነት አንተና እኔ እነኚህን ባህርያት ማምጣታችን ለህብረታችን የእምነት እድገት አስፈላጊ ነው። አንድ የእግዚአብሔር ሰው አብሮ መሆንን ሙዚቃ መፍጠር ነው በማለት የእንግሊዝኛውን ቃል በመጠቀም እንደሚከተለው አብራሩት።

M U S I C

Modeling (ምሳሌነት) እውነት በሕይወታችን እንዴት መገለጽ እንዳለበት እንዳችን ለሌላችን በማሳየት

Understanding (መረዳት) እንዳችን ለሌላችን ግልጽ ያልሆነውን እውነት ለመግለጽና ለማስረዳት በመጣር

Strength (ብርታት) በስሜታችን ዝቅ በምንልበት ጊዜ አንዳችን የሌላችንን ፈቃድ ለማበረታታትና ለማነሳሳት በመሞከር

Inspiration (ማነቃቃት) የእምነት ልምምዳችንን ለማሳደግ እንዳችን ሌላችንን በማገዝ

Correction (መተራረም) እንዳችን ለሌላችን ስህተትን በመጠቆም ለመተራረም መጣር

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሙዚቃ ለጌታ እንፈጥራለን። ያም ማለት ለጌታ የምናቀርበው ሙዚቃ ሲምፎኒ ይሆናል። እያንዳንዳችን እኛ ብቻ ልናመጣ የምንችለውን የሙዚቃ ቃና ይዘን ስንመጣ የሚጣፍጥ ሙዚቃ መንቆርቆር ይጀምራል።

ተስፋዬ ገብረአብ "የጋዜጠኛው ማስታወሻ" በሚለው መጽሐፉ ከያሬድ ጥበቡ የተጠቀሰ ብሎ ስለ ኢትዮጵያዊነት አንድ ቆንጆ ጽሁፍ ጠቅሷል። ሃሳቤን ሰብሰብ አድርጎ ስለሚገልጸው፣ ያለ ፈቃድ በዚህ ቦታ ብጠቀምበት ያሬድም ተስፋዬም ቅር እንድማይሰኙ እርግጠኛ ነኝ።

"የኦሮሞው የመለከት ድምጽ እየቀረበ ሲመጣ፣ በአማራ ዋሸንት፣ በትግሬ ከበሮ፣ በጉራጌ ዳንኪራ፣ በደቡብ እምቢልታ ታጅቦ የሚወጣው ህብረ ድምጽ፣ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አዕምሮ ሳይሆን ከውስጠ ህሊናው የሚንቆረቆር ታላቅ ሲምፎኒ እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም።"

መዘንጋት የሌለብን ነጥብ በፒያኖ ላይ ቆንጆ ሙዚቃ ለማውጣት ተጫዋቹ ነጩንም ጥቁሩንም ቁልፍ መጫን አለበት፣ ወይም ጳውሎስ እንዳለ ጌታ የሱስ በመካከላችን የጥል ግድግዳ ሆነው የሚለያዩንን ነገሮች ሁሉ አፍርሷል።





አይሁድ ወይም አረማዊ
ወንድ ወይም ሴት
ሐብታም ወይም ደሀ
ወጣት ወይም ጎልማሳ
አሠሪ ወይም ሠራተኛ
በእምነት አዲስ ወይም በእምነት የቆየ

እስቲ ከእነኚህ አስራ ሁለት ቃላት አንተን ወይም አንቺን የሚገልጹሽን ስድስቱን ቃላት አስምሩባቸው። እነኚህ ግልጽ የሆኑ የእኛነታችን ገለጻዎች ሲሆኑ ለህብረታችን ቢያንስ እነኚህን ማምጣት እንችላለን። ከፍ ብለን የገለጽናቸውን ባህርያት ታጋሽነት፣ ልምምድ፣ እውቀት፣ ጥበብ፣ አስተያየት፣ ስጦታን ከነኚህ ገለጣዎች አኳያ አስቀምጠን ጠቅለላ ድምራቸውን ስናይ፣ እያንዳንዳችን በሌላ ሊተካ የማይችል ጥቅም ለእምነት እድገት እናመጣለን። ጌታ የሱስ የአጥቢያ ቤተ ክረስቲያንን ሲያቅዳት ይህ አይነቱ ኅብረት ለአለም እንዲታይባት ለማድረግም ጭምር ነው። እስቲ በእምነት ለማደግ እንዳችን በሌላችን ልንረዳበት የምንችልባቸውን መንገዶች በሁለት ቃላት እንመልከት።

## 2. አብሮ መሥራት (Synergism)

የእንግሊዝኛው ቃል Synergism ከሁለት የግሪክ ቃል የተውጣጣ ነው። Syn ማለት አብሮ (together) ሲሆን ergos ደግሞ ሥራ ወይም መሥራት ማለት ነው። በአጠቃላይ ትርጉሙ አብረው የሚሰሩ ሲሆን በአጠቃቅም ላይ ሲውል ደግሞ ብቻ ለብቻ ከሚሰሩት የበለጠ ይሰራሉ የሚለውን አሳብ ለማጽናት ነው።

ክሪብኤጅ የሚባል አንድ የካርታ ጫወታ አለ። ሁለት አንድ አይነት ካርታዎች ካሏችሁ ሁለት ነጥብ ታገኛላችሁ፣ ሶስት አንድ አይነት ካርታዎች ካሏችሁ ስድስት ነጥብ ታገኛላችሁ፣ አራት አንድ አይነት ካርታ ካላችሁ ነጥባችሁ አስራሁለት ይሆናል። ይሄ አብሮ መሥራት (Synergism) ይባላል። ካርታዎቹ በአንድነት ሲጠራቀሙ ዋጋቸው ለብቻ ልብቻ ከሚኖራቸው በጣም የበለጠ ይሆናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ አስራ ሁለት የህብረተሰብ ቁጥር ነው ይላሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር አጥኚዎች። አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች፣ አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ለዚህ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ። የሶሺዮሎጂ ሊቃውንት ደግሞ ለመተዋወቅና አብሮ ለመሥራት አስራ አንድ ወይም አስራ ሁለት ሰዎች አብረው ቢሆኑ ቶሎ የተሻለ ውጤት ያገኛሉ ይላሉ።

አስራ ሁለት ሆነው አብረው በእግዚአብሔር ተማምነው የሚሰሩ ሰዎች የሚያመጡት ውጤት በጣም ትልቅ ነው፣ የሥራው ክንውንና ጥራት ቤተክርስቲያኑ በሙሉ ተባብሮ ከሚሠራው የተሻለ እንደሆነ ተጠንቶ ተደርሶበታል።

ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን አውቀው ሥራን አስራ ሁለት ወይም ከዚያ ላነሰ ግሩፕ በመስጠት የተሻለ ውጤት ያገኛሉ። በየቤተክርስቲያኑ እየተስፋፋ ያለው ይህ የትንንሽ ቡድን እንቅስቃሴ የመሆንና የማድረግ ነገር ነው። የጠራን እግዚአብሔርን የሚጠብቅብንን አይነት ሰዎች ለመሆን ትንንሽ ቡድን የበለጠ ይረዳናል። የእግዚአብሔርንም ነገር ለማድረግ ጥሩ ውጤት ለማምጣት አነስተኛ ግሩፕ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ አብሮ በመሥራት እድገት አለ።

አንድ አይነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች አብረው በዚያ ስጦታቸው ሲያገለግሉ ውጤቱ ብቻ ለብቻ ሆነው የሰጡት አገልግሎት ከሚያመጣው ድምር በጣም የበለጠ ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች አንድ ነገር ይሆናል ብለው ያላቸው እምነት ከፍ ያለ ከሆነ፣ አብረዋቸው የሚሠሩትም ሰዎች እምነትም ያድጋል። የማውቃቸው ሰውዬ አሉ፣ ሰው እኔ ከጸለይኩለት በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል ብለው የሚያምኑ፤ ከእሳቸው ጋር ስሆን የእኔም እምነት በዚያ ነገር ላይ ከፍ ያለ ይሆናል። ሌላ ሰውም አውቃለሁ አጋንንት ያለበትን ሰው እጄን ጭኜ ከጸለይኩለት አጋንንቱ ይወጣል ብሎ የሚያምን። ከእርሱ ጋር ስንጸልይ የእኔም እምነት ከፍ ስለሚል አጋንንት ተንጨጭተው ይወጣሉ።

> *"አንድ ሰው እንዴት ሺሁን ያሳድዳል? ሁለቱስ እንዴት አስር ሺሁን እንዲሸሹ ያደርጋሉ?" ዘዳግም 32፥ 30።*





ይህንን ቃል በገጹ አይተን ስንተረጉመው አብረው ሲሠሩ እያንዳንዳቸው የሚያመጡትም ውጤት ብቻ ለብቻ ሲሠሩ ከሚያመጡት አምስት እጥፍ የበለጠ ነው። ጥያቄው ታዲያ ከማን ጋራ እየሠራን ነው?

## 3. እርስ በእርስ (mutuality)

ይህኛው ቃል አላይ ካየነው ቃል በትንሹ የተለየ ነው። ያኛው (አብሮ መሥራት) አብሮ ሲሆኑ ኃይል እንደሚበዛ ሲሆን፣ ይህኛው ደግሞ አብሮ ሲሆኑ ሸክም እንደሚቀል ነው የሚናገረው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ሲጽፍላቸው

> *"አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፣ በዚህ ሁኔታ የክርስቶስን ሕግ ትፈጽማላችሁ" ገላትያ 6፥ 2 ነው ያላቸው።*

የክርስቶስ ሕግ ምንድነው? እርስ በርስ መዋደድ። የፍቅርን ሕግ ለማሟላት ሸክማችንን መከፋፈል በምንችልበት ኅብረት ውስጥ መሆን አለብን።

እግዚአብሔር በእንደዚያ አይነት ኅብረት ውስጥ ግሩም ድንቅ ሥራ ይሠራል። ከከበዳት ከእንዷ ላይ ቀንበሯን አንስቶ ለግሩፑ አከፋፍሎ በእነርሱ ጫንቃ ላይ አስቀምጦ እርሷን ሲያሳርፋት አይቻለሁ። በኅብረታችሁ ውስጥ የራሳቸው የባሰው ሸክም ሳይሰማቸው ለሌላው ሸክም የበለጠ የሚጨነቁና የሚጸልዩ ሰዎች አታውቁም? ባታውቋቸውም እርግጠኛ ነኝ አሉ።

ተጨንቀውስ የነበሩ ሰዎች ጭንቀታቸውን ወደ ኅብረቱ አምጥተው ምንም ነገር ሳይለወጥ እነርሱ ግን እፎይ ብለው ሲሄዱ አጋጥሟችሁ አያውቅም? ምስጢሩ የእርስ በእርስ ጉዳይ ነው። በዚህ አይነት ኅብረት ውስጥ እምነታችን ጠንካራ በሆነበት አኳያ በኅብረቱ ውስጥ ላሉ ያ ነገር ይሆንላቸዋል ብለን እናምንላቸዋለን። በድፍረት የሆነ እምነት ደግሞ ይተላለፋል። እግዚአብሔር በገንዘብ ችግር ውስጥ ልጆቹን እያስገባም ብሎ የሚያምን ገንዘብ እያጣ የሚቸገረውን ሰው ቀንበር ሊሸክምለትና በእምነት ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበው ይችላል።

**ምናብን ለመኮርኮር 10.**

**እስከመቼ ነው እና ባለማቋረጥ ዳኛውን ፍረድልኝ እያለች እንደወተወተችው መበለት በመወትወት መጸለይ የሚገባን? ወይስ ጸሎታችን መቼ ነው ባዶ ድግምት፣ እግዚአብሔርን ማግባቢያ ብቻ የሚሆነው? እምነትስ በመካከል መግባት ያለበት መቼ ነው?**

በተለይ ስሜታዊ የሆነ ችግር (emotional problem) ያለባቸው ሰዎች ለመፈወስ ሌላ ሰው ስለ እነርሱ ፈውስ እምነት እንዲኖረው ማስፈለጉን ተምሬአለሁ። በእርግጥም እምነት የፈቃድ ድርጊት እንደሆነ እምናለሁ። እግዚአብሔር ግን ባለፍንበት ስሜታዊ ችግር ተመልሰን እንድናልፍ ስለማይፈልግ፣ ፈውሳችንን በሌሎች እምነት ያደርገዋል። ያ ለእኔ የሚያምንልኝ ሰው እኔ የተሸከምኩትን ቀንበር የውስጡን ዝባዝንኬ ስለማያውቅ ሸክሙ ቀለል ያለ ይሆንለታል፤ ስለዚህ እምነትንም ለመለማመድ ይቀለዋል።

እግዚአብሔር አንዳችን ለሌላችን እንድናምን ይፈቅዳል እንዴ? አዎን ይፈቅዳል። ይህም ማለት በአንዳንድ የሕይወቴ ክፍል እኔ ራሴ የሚሠራ እምነት ላይኖረኝ ይችላል። እርስ በእርስ በምንደጋገፍ ጊዜ እኔ እምነቴ በጎደለበት በአንተ ወይም በአንቺ ውስጥ ያለው እምነት ግን በእኔ ሊሠራ ይችላል። እንዳውም በአንዳንድ ነገር ላይ በአንተ ወይም በአንቺ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር እግዚአብሔር ሙሉ እምነት አይሰጠኝም።





ስለዚህ ከእናንተ ጋር ቅርብ መሆን ያስፈልገኛል፤ ራሴን ለእናንተ ግልጽና ክፍት ማድረግ ይኖርብኛል። አለዚያ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ጉድለት ይኖረኛል።

በሕይወታችሁ ያሉት ሰዎች እምነታቸው ለእናንተ የሚያስፈልጋችሁን ያህል አለማመናቸውም የእናንተን እምነት ሊያቀጭጭ ይችላል። ይህ ለብዙዎቻችን አዲስ ትምህርት እንደሚሆን ይገባኛል። ገበናን መሸፈን፣ ጓዳን ወይም የውስጥን ለብቻ ማድረግ ለግልኝነት (privacy) መጠንቀቅ በተለይ በምዕራቡ ኅብረተሰብ ባህልም ወግ ነው። ነገር ግን አንዳንዴ መንፈሳዊ ሕይወት በሙላት እንዲሠራ ልማዱ መሰበር አለበት።

ሌሎች መጥተው የእኛን እምነት ለእነርሱ ባስቸገራቸው ነገር እንዲጠይቁን ክፍት መሆን አለብን። ማመን ቀላል የሆነላችሁ ነገር ምንድነው? እምነትንስ ለማግኘት የከበዳችሁ ነገርስ የለም? ይህ ሁኔታ ከጎረቤቶቻችሁ፣ ከቤተ ክርስቲያናችሁ አባሎች፣ ከትዳር ጓደኛችሁም እንኳን የተለየ ይሆናል።

እነኚህን ነገሮች በቅርብ እንድትመረምሯቸውና ለራሳችሁ እውነተኛ ሆናችሁ እንድትመልሷቸው ለበረታታችሁ እወዳለሁ። ምክንያቱም ክርስትና የብቸኝነት ጉዞ እንዲሆን አልታቀደም፤ እንድምታውቁት ቅድመ ክርስትና እንኳን የብቸኝነት ጉዞ አልነበረም። አንዳንድ ነገሮች ያለምንም ለውጥ ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን ተሸጋግረዋል፣ እምነት አንዱ ነው።

የሱናማዊቷ ሴት ታሪክ የእምነት እጥረት አለበኝ ብሎ የእምነት እርዳታ መጠየቅ ለሚፈልግ ሁሉ ጥሩ ምሳሌ ነው። ታሪኩ በ 2 ነገስት 4 ውስጥ ነው ያለው። ልጅ እየፈለገች ያለ ልጅ የነበረችዋ ሴት ለነቢዩ ለኤልሳ ችሮታ በማድረግ በቤቷ የእንግዳ ማረፊያ አሠርታ ለእርሱ መጠቀሚያ አዘጋጀችለት። ለእርሷ ከነበረው ውለታ (gratitude) የተነሳ ኤልሳ ደግሞ በሚቀጥለው አመት ልጅ እንደምትወልድ አምኖ ትንቢት ተናገረ፣ ትንቢቱም ተፈጸመ ታሪኩ ግን በዛ አላበቃም።

## ምናብን ለመኮርኮር 10.

እስከመቼ ነው እኛ ባለማቋረጥ ዳኛውን ፍረድልኝ እያለች እንደወተወተችው መበለት በመወትወት መጸለይ የሚገባን? ወይስ ጸሎታችን መቼ ነው ባዶ ድግምት፣ እግዚአብሔርን ማግባቢያ ብቻ የሚሆነው? እምነትስ በመካከል መግባት ያለበት መቼ ነው?

አንድ ቀን ይህ በእምነት የተወለደ ልጅ ከአባቱ ጋር በሜዳ ተሰማርቶ መሥራት የሚችልበት እድሜ ሲደርስ ራሴን ብሎ ታመመ፣ አባቱም ወደ ቤት ላከው፣ ከጥቂት ሰአት በኋላም ሞተ። እናቱ ከዚህ በኋላ ያደረገችው ጥልቅ የሆነ ትምህርት ያለበት የእምነት ምሳሌ ነው።

የልጁን አስከሬን ኤልሳዕ አልጋ ላይ አደረገችው። የልጁ አካል ከኤልሳዕ ጋር የሚገናኝበትን አንድ መንገድ ፈልጋ ያገኘችው ነው። እምነት ከተፈጥሮአዊ መነካካት ጋር የተያያዘ ነገር እንዳለው የተረዳች ይመስላል።ወደ ኤልሳዕ ወዲያውኑ ለመሄድ መዘጋጀት ጀመረች። ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ሰው እንደሆነ፣ ልጇንም ያገኘችው በኤልሳዕ የእምነት ቃል እንደሆነ ታውቅ ነበር። ይህ አስደንጋጭና አሳዛኝ ነገር ሲደርስባት በመጀመሪያ እርሱን ማሰቧ አያስደንቅም።

ችግሯንና ኃዘኗን ለማንም፣ አልገለጠችም። ለምን ወደ ነቢዩ ለመሄድ እንደፈለገች ባሏ ቢጠይቃትም እንኳን "ምንም አይደል ልሂድ" ባንድንድ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች "ግዴለም ሁሉም መልካም ነው" ነው ያለችው። ግን ሁሉ መልካም አልነበረም። በዛሬ ዘመን ሳይኮሎጂስቶች ብትመዘን "በክህደት ወስጥ" (in denial) ብለው ነበር የሚመድቧት። ከባሏም ጋር የመነጋገር ችግር ያለባት ትመስላለች። ነገር ግን ከዚያ ጠለቅ ያለ ምስጢር እየተካሄደ ነበር። በዚያ ሀዘኗ ውስጥ እያለች ሱናማዊቷ ሴት እምነት እየተለማመደች ውጤቱንም በፈቃዷ የተቀበለች ይመስለኛል። ሁሉም መልካም ሳይሆን ሁሉ መልካም እንደሆነ የሚያሳይ እምነት፤ ጌታ የሱስም አኮ ያሳየው እምነት ይህን አይነት ነበር።

*"ወዳጃችን አልአዛር ተኝቷል፤ እኔም ከእንቅልፍ ላስነሳው እሄዳለሁ" ዮሐንስ 11፣ 11።*

ጌታ የሱስንም "በክህደት ውስጥ ነው" ሳይሉት የቀሩት? እርሱ ግን የእምነቱን ውጤት እያየ ነበር የሚናገረው። ኤልሳዕ ሴትዮዋ ስትመጣ ከሩቅ ሲያያትና አገልጋዩን ግያዝን "ምነው ደህና አይደለሽምን?" ብሎ እንዲጠይቃት ሲልከው "ሁሉ ነገር ደህና ነው" ብላ ነው ለግያዝ የመለሰችው።

ከኤልሳዕም ጋር ፊት ለፊት ስትገናኝ ስለልጇ መሞት በግልጽ አላወራችም፣ ነገር ግን





ጥያቄ ብቻ ነው ያነሳችው "ጌታዬ ለመሆኑ እኔ ልጅ እንድትሰጠኝ ጠይቄህ ነበረን? አትልፋ እንዳትሰጠኝ አላልሁምን?"

ከኤልሳዕ ከራሱ በቀር ሌላ የተለወጠ ነገር ላለመቀበል ወስና ነበር። ኤልሰዕ ግያዝን "እንግዲህ ሩጥ ... በትሬንም በልጁ ፊት ላይ አድርግ" ብሎ ሊልካቸው ሲሞክር እርሷግን "ሕያው እግዚአብሔርን በሕያው ነፍስህ እምላለሁ ፈጽሞ ትቼህ አልሄድም" አለች።

ከዚያ በኋላ የታሪኩ ትኩረት ከሴትዮዋ ላይ ይነሳና በኤልሳዕ ላይ ይሆናል። እርግጠኛ ነኝ ሴትዮዋ ቤት ከደረሱ በኋላ ኤልሳዕ በሰገነቱ ላይ ባለው ክፍል ውስጥ ለልጁ ሲጸልይ እርስዋም በታችኛው ክፍል ሆና ትጸልይ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እዚያ ላይ አላተኮረም፣ ምክንያቱም የእርስዋ እምነት ከኤልሳዕ እምነት ጋር ተጣምሮ ነበር። ብቻዋን የነበራት እምነት ከኤልሳዕ ጋር እንድትገናኝ አስቻላት፤ ከኤልሳዕ ጋር አብረው ሲያምኑ ግን ማዕበሉን ቀለበሱት።

በማዕበል ውስጥ በምታልፉበት ጊዜ ለብቻ መጋፈጥ ጀብደኝነት አይደለም። የምትችሉትን ያህል አብረዋችሁ የሚቆሙ ጸላዮች ከየቦታው ቀስቅሱ። እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸውን፣ በቅባት የሚያገለግሉትን፣ በአገልግሎታቸው ከዚህ በፊት የተነካችሁባቸውን ሰዎች አብረዋችሁ እንዲቆም ቀስቅሷቸው። በማዕበል ስትያዙ ጊዜው የተራ ጸሎት ጊዜ አይደለም። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ይህን አይነቱን ጊዜ "የመንፈሳዊ ውጊያ" (Spritual Warfare) ነው የሚሉት። ለአንተም ለአንቺም በጸሎት አብረዋችሁ ለሚቆሙትም አካሉ አንድ ስለሆነ፣

*"አንድ ብልት ቢሰቃይ፣ ብልቶች ሁሉ አብረው ይሰቃያሉ"* 1 ቆሮ 12፣ 26።

የሱናማዊቷ ሴት የኤልሳዕን ተራ የሆነ አገልገሎት ብቻ አልፈለገችም። ሌላውን በእርሱ ፋንታ መላክ ለሌላ አይነት ችግር ይሠራ ይሆናል። ዛሬ ግን የእርሱ መገኘትና የእርሱ እምነት አስፈላጊ መሆኑን እውቃ ነበር፣ ስለዚህ ተሳከ።

መቼም ማንኛችንም እንደ ኤልሳዕ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ማለፍ

እንፈልግም፣ ምክንያቱም በእምነታችን ላይ ያልተጠበቀ ተጽእኖ ያመጣብናል፤ ግን እግዚአብሔር ያለ ምክንያት በእንደዚያ ያለ ሁኔታ ወስጥ እንድንሆን አያደርግም። አንዳንዴ እምነታችንን የሚጠይቁን ሰዎች በእኛ እምነት ላይ ያላቸው መተማመን የእኛን እምነት ያነሳሳዋል። ባለቤቴ ብዙ ጊዜ የምትለኝ ነገር አለ "አንተ ከጸለይክልኝ ይሳካልኛል"። ሩቅ በነበርኩበት ጊዜ ስደውልላት "አንተ መጸለይ አትርሳ" ወይም "አንተ ስለ ጸለይክ ተሳካ" ትለኝ ነበር። ያ ደግሞ እርሷ በጠየቀችኝ ነገር ላይ እምነቴን ያነሳሳዋል።

በዚህ መጽሐፍ ወስጥ በምዕራፍ 3 ያየናትን የከነአናዊቷን ሴት ታሪክ እንድናይ ያደረገው ምናልባት ለዚህ ይሆናል። ያቺ ሴት ልጇ በአጋንንት ተይዛ የመኖሯን ሁኔታ አልቀበልም አለች። መቶ አለቃውም የአገልጋዩን ወደሞት መሄድ አልቀበልም አለ። ሱናማዊቷ ሴትም የልጇን መሞት አለመቀበል ብቻ ሳይሆን ለማውራት እንኳን አልፈለገችም። አስራ ሁለት አመት ደም ሲፈሳት የነበረችዋ ሴት ለደም መፍሰስ እምቢ የሚል እምነት፣በርጤሜዎስ አይነስውርነትን አሻፈረኝ የሚል እምነት፣ ዝም በል እንኳን ሲባል እምቢ እውርነትን አልፈልግም ብሎ አመነ። የጌታን መልስ እስኪያገኝ ድረስ የዳዊት ልጅ ማረኝ እያለ ጮኸ!

ለምንድነው እምቢ ማለት የሚገባችሁ? ምን ሁኔታ ነው በሕይወታችሁ፣ በቤተሰባችሁ፣ በማኅበረሰባችሁ፣ በቤተ ክርስቲያናችሁ በቃ ከእንግዲህ ለዚህ ነገር እምቢ የሚያሰኝ እምነት እንዲኖራችሁ የሚጠይቅ?

ለዚህስ ነገር ማን እንዲተባበራችሁ፤ እምነታችሁ ከማን እምነት ጋር ቢደመር ይሠራል ብላችህ ታምናላችሁ? የማን ቅባት፣ የማን የእምነት ቃል በዚያ ነገር ላይ ያስፈልጋችኋል? እንዲህ ያሉትን ጥያቄዎችን በሕይወታችሁ ደጋግማችሁ እየጠየቃችሁ መመለስ ያስፈልጋችሁ ይሆናል። ግን ከሱናማዊቷ ሴት ታሪክ ተማሩ፤ ለማመን የሚያስፈልጋችሁንና የሚያግዛችሁን የሌላ ሰው እምነትም ፈልጉና ጸሎታችሁን ከእግዚአብሔር አስመልሱ።





## ክፍል አራት
## ጠለቅ ያሉ ጉዳዮች

እስካሁን ያየነው የዚህ መጽሐፍ ብዙው ክፍል የገለጸው ስለተራ እምነት ነው። በዚህ በመጨረሻው ክፍል ግን የእምነትን ስጦታ እናያለን። የእምነት ስጦታ ከተራውና በየእለቱ ከምንለማመደው እምነት እንዴት እንደሚለይ እናጠናለን። የእምነትንና የነፃነትን ግንኙነት እንመረምራለን፤ በመጨረሻም መጽሐፉን ለመዝጋት በእኛ ፈቃድና በእግዚአብሔር ፍቅር መካከል ስላለው ግንኙነት እንመለከታለን።

# ምዕራፍ አስር

## የእምነት ስጦታ

### 1. ሶስት አይነት ስጦታዎች

በአጠቃላይ ስለ እግዚአብሔር ስጦታዎች (የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች) በምናጠናበት ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሶስት አይነት ስጦታዎች እንደ አሉ እንመለከታለን፤ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ስጦታዎች ሁሉ በሶስት ክፍል መከፈል ይችላሉ።

ሀ. የመጀመሪያዎቹ የማነቃቂያ ስጦታዎች (Motivational Gifts) የሚባሉት ናቸው። እነኚህ ስጦታዎች በእግዚአብሔር አብ የተሰጡን ሲሆን በተፈጥሮ አብረውን የተወለዱ፣ ከአማኝነት ጋር ግንኙነት የሌላቸው፣ በጥሩም በመጥፎም ልንጠቀምባቸው የምንችል፣ ስጦታዎች ሲሆኑ በማንኛውም ሰው ሊከሰቱ የሚችሉ ናቸው። ስጦታዎቹ በሮሜ ምዕራፍ 12 ውስጥ የጠቀሱት ናቸው፤ በጥቂቱም ቢሆን በ 1ጴጥሮስ ምዕራፍ 4 ውስጥም ተጠቅሰዋል።

*"እንደተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፣ ለአንዱ የተሰጠው ጸጋ ትንቢት መናገር (ይህ ቃል በዚህ ቦታ ላይ አንዳንዴ ተመልካች 'perceiver' ተብሎ ይተረጎማል) ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን ይናገር። ማገልገል ከሆነ ያገልግል፣ ማስተማርም ከሆነ ያስተምር፣ መምከር ከሆነ ይምከር፤ ለሌላቸው መለገስ ከሆነ አብዝቶ ይለግስ፣ ማስተዳደር ከሆነ በትጋት ያስተዳድር፣ ምህረት ማድረግ ከሆነ በደስታ ይማር" ሮሜ 12፥6-8*

ለ. በሁለተኛ ቦታ ያስቀምጥኳቸው ስጦታዎች የአገልግሎት ስጦታዎች (Ministry Gifts) የሚባሉት ናቸው። እነኚህ በጌታ የሱስ ክርስቶስ አዕማድ ለሆኑ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሚሰጡ አምስት ስጦታዎች

ናቸው። ስጦታዎቹ በኤፌሶን 4 ወስጥ የተጠቀሱት ናቸው።

*" ... አንዳዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹ ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው" ኤፌሶን 4፥ 11።*

ሐ. እዚህ ሶስተኛው ቦታ ላይ ያስቀመጥኳቸው፣ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ በሰፊው የሚጠቀሱትና በሥራም የሚገለጹት የመግለጽ ወይም የገለጻ ስጦታዎች (Manifestation Gifts) የሚባሉት ናቸው። እነኚህ ስጦታዎች ለማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ ሲሆኑ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲውሉ የተሰጡ ናቸው። ስጦታዎቹ በ 1 ቆሮንቶስ 12 ውስጥ የተጠቀሱት ናቸው።

*"ለአንዱ በመንፈስ የጥበብን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታዎች ይሰጠዋል፤ ለአንዱ ታምራትን የማድረግ፣ ለሌላው ትንቢትን የመናገር፤ ለሌላው ደግሞ መናፍስትን የመለየት፣ ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፤ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ይሰጠዋል" 1 ቆሮንቶስ 12፥ 8-10።*

እምነት በስጦታ መልኩ የተገለጸው በእነኚህ በሶስተኛ ቦታ ላይ ባስቀምጥኳቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ውስጥ ነው።

## 2. የስጦታው አሰራር

የእምነት ስጦታ ሰዎች በተራ እምነት ብቻ ለማድረግ የማንችለውን ነገር ማድረግ እንድንችል ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ከፍ ያለ ስጦታ ነው። ከተፈጥሮ ኃይላችንና ችሎታችን በላይ (Supernatural) በሆነ ኃይል የምንለማመደው እምነት ነው። ተንጠራርተን ተንጠራርተን ልንደርስበት እንድማንችል እርግጠኛ የሆነውን ነገር በቀላሉ ልንይዘው ስንችል ማለት ነው። የእምነትን ስጦታ ለሚለማመዱ ሰዎች





ይህ ስጦታ ከብዙ ስጦታዎች ይልቅ በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ እግዚአብሔር እንደሚጠቀምባቸው የሚረዱበትና በቀላሉም በሕይወታቸው የሚሰራ ሆኖ ያገኙታል። ስጦታው ለመሥራት እኛን ማስፈቀድ እንኳን አይጠይቅም፣ እኛም ደግሞ ለመፍቀድ የምንደፍራውን ድፍረት ሁሉ አልፎ ይሄዳል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከላይ በሶስተኛ ቦታ ላይ ያስቀመጥኩትን ጥቅስ ሲከፍት እንዲህ ብሎ ነው።

*"መንፈስ ቅዱስን መግለጽ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው ... ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል" 1 ቆሮንቶስ 12፥ 7።*

የእምነት ስጦታ ላለው የአመነበት ጉዳይ ቶሎ ሊፈጸም ይችላል ወይም ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ለምሳሌ እምነቱ ለፈውስ ከሆነ ያ ፈውስ ወዲያው ሊከሰት ይችላል። እምነቱ ግን ለእግዚአብሔር ሥራ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ከሆነ ያ መልስ ወዲያው ሊመጣ ይችላል፣ ዘግይቶ ሊመጣ ይችላል፣ እንደ ብቻ ሆኖ ያልፍ ይሆናል፣ ወይም ደጋግሞ ሊሆን ይችላል። እስቲ የእምነትን ስጦታ ብቻውን ከማየታችን በፊት አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖረን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በአጠቃላይ እንያቸው።

መንፈሳዊ ስጦታ እግዚአብሔር ለሰዎች ራሱን ከገለጸበት ብዙ መንገዶች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ነገሮችን ራሱ በራሱ ከሚያደርግ እኛን ተጠቅሞ ያደርጋል፣ በዚሁም ከእኛ ጋር መተባበር ይወዳል። ኃይሉ ያለው እርሱ ነው ያንን ኃይሉን ግን ለሰዎች ብሎ በሰዎች ውስጥ፣ በሰዎች በኩል መጠቀም ይወዳል። ከእርሱ ለሚወጣው ኤሌክትሪክ ኃይል እኛ የኃይሉ ማስተላለፊያ የመዳብ ሽቦዎች መሆናችን ነው።

ለብዙ ሰዎች መንፈሳዊ ስጦታ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል የተፈጥሮ ችሎታቸውን ከፍ ሲያደርግ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚሰራው፣

ሀ. አስፈላጊነቱ ሲኖር

ለ. መንፈስ አገልጋዩን ሲገፋፋው

ሐ. አገልጋዩ የመንፈስ ቅዱስን ግፊት በእምነትና በድፍረት ሲከተል

አገልጋዩ በራሱ ሊያደርገው የማይችለውን በመንፈስ እርዳታ ማድረግ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የተፈጥሮውና ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ስጦታ (Natural vs Supernatural) የሚያደርገው ልዩነቱ ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ ለማየት እንኳን የእምነት አይንን መክፈት ያስፈልጋል። ጌታ በምድር በተመላለሰበትና ባስተማረበት ጊዜ ብዙዎች የመንፈስ ቅዱስን ሥራና ኃይል በአገልግሎቱ ቢያዩም፣ ማመን ግን አልቻሉም።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሚሠራበት ሰው ሕይወት ከሌሎች የተለየ የሚታይ ብዙ ነገር አይኖርም። እንዳውም የእግዚአብሔር ኃይል በውስጣቸው የሚሠራ ሰዎች የሚመሰክሩላችሁን ብትሰሙ ኃይሉ በውስጣቸው በሚሠራ ጊዜ ደካማነት እንደሚሰማቸው ነው። ለምሳሌ የፈውስ ስጦታ ያላቸው አንዳንድ ጊዜ የተፈወሰው ሰው መጥቶ ካልነገረን ወይም መረጃ ካላየን መፈወሱን እንኳን እርግጠኛ አይደለንም ይላሉ። አንድ የፈውስ ስጦታ ያላቸው ሰው "ስጦታውን እንደተቀበልኩ አካባቢ ለሰው ስጸልይ እጄን ሞቅ ካለኝ ያ ሰው እንደተፈወሰ አውቅ ነበር፤ እየቆየሁ ስሄድ ግን ያ ሞቅ የሚለው ስሜት ለቆኝ ጠፋ፣ ለካ በመጀምሪያ መንፈስ ቅዱስ ሊያበረታታኝ ፈልጎ ነው ያንን ያደረገው" አሉ።

አንድ ሰው ስጦታን መለማመዱ በስጦታው ምንነትና በአሠራሩ ላይ የተመሠረተ ነው። ለምሳሌ በእውቀት ቃል የሚያገለግሉ ብዙ ጊዜ አገልግሎታቸው ስሜታዊ ያልሆነ አዕምሯዊ ቀዝቃዛ እውነት ብቻ ይሆናል ይላሉ። ምክንያቱም የዚህ ስጦታ አገልጋዮች ስሜታቸውን የመቆጣጠር አላፊነት አለባቸው፤ በስሜት ማድረግ ከጀመሩ የእውቀትን ቃል የመቀበላቸው ችሎታ የተጋረደ ይሆናል። እንዳውም አገልግሎቱን ከጨረሱ በኋላ ነው እግዚአብሔር ያለውን እንደገና ሲያስቡት ስሜታቸው የሚቀሰቀሰው።

አንዳንዶች ደግሞ የፍርሃት ስሜት አለን ይላሉ፣ እኔ ለመንፈስ ቅዱስ መጠቀሚያ ለመሆን በቂ ስላይደለሁ ስጦታዬ በዚህ ጊዜ አይገለጥ ይሆናል የሚል ፍርሃት ይይዛቸዋል። ይህ ግን መንፈሳዊ ውጊያ ነው። ጠላት ስሜታችንን መድረስ እንደሚችል ባለፉት ምዕራፎች አይተናል፤ መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳችን መጠቀም ሲጀምር ሰይጣን ስሜታችንን ለመድረስ መሞከሩ አይቀርም። አንዳንድ ስጦታዎች





ለምሳሌ የእውቀት ቃል፣ ትንቢት፣ ልሳን፣ ተአምራት፣ አንዳንድ ፈውስም ወዲያው ልንለማመዳቸው እንችላለን። አንዳንዶቹ ግን በተለይ የማነቃቂያ የሚባሉትና በተፈጥሮ የምናገኛቸው ስጦታዎች ለምሳሌ መሪነት፣ መጋቢነት፣ አስተማሪነት፣ አስተዳደር ጊዜ የሚወስዱ ናቸው።

## እውቀት

አንዳንድ ሰዎች የእምነትን ስጦታ የሚለማመዱት በማወቅ ነው። ከተራ እምነት የበለጠ፤ ለጊዜውና ለአላማው የሚሆን ከቁጥጥራቸው በላይ የሆነ እርግጠኝነት በውስጣቸውና በላያቸው ይመጣል። አንዳንድ ጊዜ በድንገት የሚለማመዱት ሰዎች ሳይቀሩ እንዳሚደነቁና በፍርሃት እንደሚሞሉ ይመሰክራሉ። ምክንያቱም ይህ እውቀት ከምክንያትም ከተጨበጠውም እውነት ወይም ከገለጻ ውጪ ስለሚሆን ነው። "በእውቀቴ ውስጥ አውቀዋለሁ" አሉ አንድ ሰው ስለዚህ ልምምዳቸው ሲጽፉ።

## ድፍረት

ሌላው ይህንን ስጦታ የምንለማመድበት ባህሪ እንግዳና አስደናቂ የሆነ ድፍረት ነው። በድፍረት የግሳጼንም ሆን የተሰፋን ቃል ማምጣት፤ ለራስ ያላሰቡትን ነገር ድንገት በድፍረት መናገር። በተለይ ለበሽተኞችና አጋንንት ለያዛቸው ሰዎች የሚጸልዩ ይህንን ስጦታ በዚህ ድፍረት ይለማመዱታል። ወይም የሌሎችን ሸክም የሚሸከሙ የዚህ ስጦታ ያላቸው አንዳንዴ ከራሳቸው ግምት በላይ የሆነ ነገር በድፍረት ይናገራሉ። ያ የእምነት ስጦታ በውስጣቸው ሲሠራ ነው። የቤተ ክርስቲያናቸው መንጋ ሲበጠበጥና ሲከፋፈል፤ አንዳንድ መጋቢዎች ከተለመደው ጠባያቸው ውጪ በሆነ ድፍረት አዋኪዎችን ሲገስጹ አይቻለሁ። ያ የራሳቸው ድፍረት አለመሆኑን ብዙዎች ያውቁታል።

## ማበረታታት

ከአቅማችን በላይ የሆነ ተግዳሮት ሲገዳደረን፣ የእምነት ስጦታ በሚያበረታታ ሁኔታ ይገለጻል። የሌለንን ብርታት ሰጥቶ ከአቅማችን በላይ በማመን እንበረታታለን። ይህ በረከት ብዙ ጊዜ በጣም በተጣቡብንበትና መፈናፈኛ ባጣንበት ጊዜ ነው የሚገለጸው። መንገዱ ደግሞ ይለያያል፣ ብዙ ጊዜ ግን ብቻችንን ሆነን በጌታ ፊት የጥሞና ጊዜ (Meditation) በሚኖረን ጊዜ የሚመጣ ነው። በሌላ ጊዜ ደግሞ ማበረታታት በሌሎች አገልግሎት ይመጣልናል።

መስቀልኛ መንገድ ላይ ቆማችሁ ወዴት መሄድ እንደሚገባችሁ መወሰን ሲያቅታችሁ፣ ወይም እግዚአብሔር ለግላችሁ በነገራችሁ ነገር ላይ ተቃውሞ ሲበዛባችሁ፤ መልካም ከሚያስቡላችሁ ከእግዚአብሔር ሰዎች እንኳን ሳይቀር የሚመጣው ምክር ሲከብድባችሁ፣ ድንገት ካልታሰበ አቅጣጫ የሚመጣ ማበረታቻ፣ መጥቶም በፍጹም ይሆናል የሚል እምነት እንዲኖራችሁ አድርጎ አያውቅም? እኔ ብዙ ጊዜ ተለማምጀዋለሁ። ያ የእምነት ሥጦታ ለዚያን ጊዜ በዚያ ሁኔታ ላይ የመጣ ነው።

## የጉብኝት በሮች

ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው አንዳንድ ሰዎች የጉብኝት በሮች ናቸው ብለናል። በውስጣቸው ያለው ስጦታ በእኛ ውስጥ ያለውን ስጦታ የሚፈታ ሰዎች አሉ። ለምሳሌ የፈውስ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ፣ በሚያበረታቱና መንፈሳዊ ሁኔታን የሚያንቀሳቅሱ ሰዎች ባሉበት ስጦታቸው የበለጠ ይሠራል። በዚህ ጊዜ ስጦታ ያለው ሰው በውስጡ የእነኚህን ሰዎች ስጦታ ተገንዝቦ የራሱ ስጦታ ከፍ ከፍ ማለት ይጀምራል። ጥያቄው እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የእምነት ስጦታ ያለው ማን ነው? የሚለው ነው። የእምነት ስጦታ ያለው የፈውስ ስጦታ ያለው ነው። ምክንያቱም እነኚያ የመጎብኚያ በሮች የሆኑት ሰዎች የሚያደርጉት ነገር በተራ እምነታቸው ነው። ያ የእምነት ስጦታ ያስፈለገበት ጉዳይ ሲያበቃ የእምነቱ ስጦታ ሌላ ጠያቂ ጉዳይ እስኪመጣ ድረስ አይገለጥ ይሆናል።





## የቡድን እምነት

የእምነት ስጦታ በአንድ ቡድን ላይ ለጋራ የሚመጣበት የተከበሩና ውድ የሆነ ጊዜ አልፎ አልፎ ይመጣል። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በቡድኑ ውስጥ ባሉት በእያንዳንዳቸው ላይ በመፍሰስ ቅባት፣ ፈውስ፣ ንስሐ ወይም ኅብረትን ያመጣል። በዚያ ያሉት ሁሉ ደግሞ በግል መነካታቸውንና በአንድነት መሥራታቸውንም ይገነዘባሉ። ይህ አይነት ልምምድ የሚኖርበት ቦታና ጊዜ እንዲያጋጥማችሁ ተጠባበቁ፣ ካጋጠማችሁ ትባረካላችሁ። ፓስተር ሰይፉ ከበደ የፈውስ ኪዳንበተባለው መጽሐፉ ይህንን አሳብ የጉባኤ እምነት በሚል አርዕስት ስር በራሱ አገልግሎት ውስጥ በተከሰተ ጥሩ ምሳሌ ገልጸታል።

## ትንሽ ምስጢር

አንድ የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ብለው አጫወቱኝ። አንዳንዴ የእምነት ስጦታ በውስጤ እንዲሠራ ለማድረግ ራሴን አርዳታ በሚያስፈልገኝ ቦታ ከማስቀመጥ በስተቀር ሌላ ማድረግ የምችለው ነገር የለም። የእምነት ስጦታ ብዙ ጊዜ መደረግ ያለበትን ነገር ለማድረግ ወይም መረዳት ያለበትን ሰው ለመርዳት እስከወስን ድረስ በውስጤ መሥራት አይጀምርም። ብዙ ግዜ የእምነት ስጦታ እንዲሠራ በጣም ስፈልገው አይሠራም ፤ ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም። በእግዚአብሔር ዘንድ ለእኔ እንቆቅልሽ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ይሄ ነው። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ጥልቅ እየሆነ ሲሄድ፣ በቅድስና ሕይወትና በመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ስናድግና ራሳችንንም የእግዚአብሔር ኃይል በሚያስፈልግን ሁኔታ ላይ ስናስቀምጥ፤ እነኚህና የመሳሰሉት ነገሮች ለእምነት ስጦታና ለሌሎቹም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በበለጠ የተዘጋጀን ያደርጉናል።

ምናብን ለመኮርኮር 11.

ሁለት ጥያቄዎች

እምነቴ በትክክለኛ ቦታ መሆኑን እንዴት አውቃለሁ? ይህም ማለት በእግዚአብሔር ላይ መሆን አለመሆኑንስ እንዴት እለያለሁ? ለምንድነው ጌታ የቡስ ደጋግሞ "እምነታችሁ (አምላካችሁ ሳይሆን) ሙሉ አድርጓችኋል" ያለው?

እውነቱን ብነግራችሁ አንዳንዴ የዚህ አላይ የስጠሁት ሐተታ ተቃራኒው እውነት ሲሆንም አይቻለሁ። በሁኔታዬ የማይገባኝ፣ በራሴ መንገድ በምሄድበትና አንዳንዴም በኃጢአት በምመላለስበት ጊዜ እንኳን ሳይቀር የእምነት ስጦታ ሲሠራብኝ ራሴን አግኝቼዋለሁ። ተራ እምነት እንኳን ይኖረኛል ብዬ ባላሰብኩት ጊዜ የእምነት ስጦታ ሲያጥለቀልቀኝ ራሴን አገኘዋለሁ። በጣም ደክሞኝ ከማንም ልገናኝ ባልፈለኩበት ጊዜ የእግዚአብሔር ምህረት በዚህ ስጦታ አማካኝነት ይጎበኘኛል።

ብዙ ጊዜ ሥራውን የሚሠራው በእኔ ውስጥ ያለው እምነት ሳይሆን፣ ለመገልገል የመጣው ሰው እምነት ነው። እኔ እምነት በሌለኝ ጊዜ እንኳን አስደናቂ የሆኑ ፈውሶች በእኔ አገልገሎት ሲከሰቱ አይቻለሁ።

ምን ለማለት ፈልጌ መሰላችሁ፣ ይህ የእምነት ጉዳይ ትንሽ ምስጢር ነው፤ የታቀደውም ደግሞ ምስጢር እንዲሆን ነው። ከእኛ መካከል ማናችን ነን ሙሉ ለሙሉ የምንረዳውን አምላክ ማምለክ የምንፈልግ? የክርስቶስ ምስጢራዊ ጥልቀት ከግምት በላይ ነው። እውነቱን ሁሉ ተንትነን ብንጨርስ፣ መንገዱን ሁሉ ብናውቅ፣ መልሱን አስቀድመን መገመት ብንችል፣ እንደዚያ ቢሆንማ እንደ እርሱ ታላላቆች እንሆን ነበር።





## 3. የስጦታው ባለቤትነት

የእምነት ስጦታ ባለቤት ማነው? እንዳው ባጠቃላይ የመንፈስ ስጦታዎች ባለቤትነት እኛ አለን እንዴ? አይመስለኝም፣ እንዲያውም እንደዚህ ማሰብ ራሱ ስህተት ነው።

አንድ ሰው ብዙ ጊዜ በሚያገለግልበትና የእግዚአብሔርም ኃይል በእርሱ ወስጥ በሚገለጥበት ስጦታው ሊታወቅ ይችላል። ስጦታው ብዙ ጊዜ በተፈጥሮ ያለንን ችሎታ ያዳብረዋል፤ በተፈጥሮ ያለን ችሎታ ደግሞ በየጊዜው አይለዋወጥም። እንዳውም አንዳንድ ችሎታዎች ዳብረው በሰውዬው ሕይወት ውስጥ ለመገለጽ እድሜ ልክ ይወስዳሉ።

ታዲያ በመንፈሳዊ ስጦታዎች ስንነበኝ የሚሆነው ምንድነው? መንፈሳዊ ስጦታዎች እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ በዚያ ቦታ ሊያደርግ ያሰበውን ልዩ እቅድ ለማከናወን ይመጣሉ። የስጦታው ቅባት እቅዱን ካከናወነ በኋላ ወዲያው ሊቆም ይችላል፣ ወይም ሊቀጥል ይችላል። ስለዚህ የስጦታው አገልጋይ ውሳኔ ወይም ፍላጎት ስጦታውን ለማምጣት ወይም ለማቆየት አይችልም። አገልጋዩ ሊያደርግ የሚችለው ራሱን ስጦታው በሚያስፈልግበት ሁኔታ ውስጥ ማድረግ ነው። ለምሳሌ ከመንፈስ ስጦታዎች አንዱ የሆነው የእምነት ስጦታ ለአንድ በሽተኛ ፈውስ ካስፈለገ፣ ለበሽተኛው በሚደረግ የፈውስ ጸሎት መቆየት ያስፈልጋል። ስጦታውን በዚያ ሁኔታ ላይ ሊያመጣም ሆነ ሊሠራበት የሚችል መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ስለዚህ ስጦታው በመንፈስ ቅዱስ ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ስር ይቆያል። የስጦታው ዋና ግብ ደግሞ የአገልጋዩን ሕይወት መቀደስ ሳይሆን የተፈዋሹ መባረክ ነው። በሌላ አነጋገር ለታመመ ሰው የሚጸልየው አገልጋይ ለታማሚው ፈውስ ምክንያት ቢሆን በእርግጠኝነት ልንመሰክር የምንችለው የበሽተኛውን መፈወስ እንጂ ስለ አገልጋዩ የሕይወት አቋም ምንም ማለት አንችልም።

ይህን ማለት ደግሞ ስጦታው በውስጤ ሲሠራ እኔ ምንም የማገኘው የለም ለማለት አይደለም። እግዚአብሔር ሲጠቀምብኝ እኔም ብዙ እባረካለሁ። ያ እኔን ሙሉ ያደርገኛል፣ ያረካኛል፣ ደስ ያሰኘኛል፣ በእውቀቴና በመረዳቴ እድጋለሁ፣ በሕይወቴ አበረታለሁ፣ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች አማኞች ጋር ያለኝ ግንኙነት መንፈሳዊ

## ምናብን ለመኮርኮር 11.

### ሁለት ጥያቄዎች

እምነቴ በትክክለኛ ቦታ መሆኑን እንዴት አውቃለሁ? ይህም ማለት በእግዚአብሔር ላይ መሆን አለመሆኑንስ እንዴት እለያለሁ? ለምንድነው ጌታ የሱስ ደጋግሞ "እምነታችሁ (እምላካችሁ ሳይሆን) ሙሉ አድርጓችኋል" ያለው?

ምጥቀት ያገኛል። ከዚህም የተነሳ ስጦታው በውስጤ እንደገና የሚከሰትበትን ጊዜ በጉጉት እጠብቃለሁ። ስለዚህ እኔ ለስጦታው ባለቤትነት የለኝም፣ ስጦታውንም በፈለኩ ጊዜ እውጥቼ ለመጠቀምም ሆነ ቦታና ጊዜ እየመረጥሁ እዚህ ይሆናል እዚያ አይደለም ለማለት አልችለም። እንዲያውም ለእግዚአብሔር ለመመቸት ይዤ መምጣት የምችለው ባዶነቴን ብቻ ነው።

## 4. የሥጦታው አጠቃቀም

እምነት ብቻውን የሚገለጽ ሥጦታ አይደለም። በአንድ ሁኔታ ላይ የሚገለጽ ሥጦታ ነው፣ ወይም አንድ ሰው የእምነት ሥጦታ እንዲኖረው ብቻ የእምነት ሥጦታ አያገኝም። እምነት የሚኖረው ለአንድ ነገር ነው። ያ አንድ ነገር በሽታ ሊሆን ይችላል፣ ችግር፣ አስቸጋሪ ሁኔታ፣ ግራ መጋባት፣ የተበላሸ ግንኙነት፣ የገንዘብ ችግር፣ የሚያስጨንቅና የሚያጣብብ ሁኔታ ሊሆን ይችላል : : ይህ ሁኔታ ደግሞ በአካላችን፣ በአዕምሯችን ወይም በስሜታችን የሚከሰት ይሆናል፤ ያጭር ጊዜ አጣዳፊ ወይም ረዢም ጊዜ የሚወስድ አስጊ ወይም አሳሳቢ ችግር ሊሆንም ይችላል፤ ግላዊ ቤተሰባዊ፣ ኅብረተሰባዊ ከዚያም አልፎ አገራዊና ሉአላዊ ሊሆን ይችላል።

ልናደርግ የምንችለው ተራ እምነትን በመለማመድ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ብቻ ነው። የእምነት ሥጦታ መንፈስ ቅዱስ ባቀደው ጊዜ መጥቶ እንዲወርሰን መጠባበቅ ብቻ ነው።

በጸሎት መቆየት፣ በአሁኑ ጊዜ ባለን የእግዚአብሔር አሰራር መረዳት መሠረት ወደ እርሱ በጸሎት በመቅረብ እና በመቆየት የእምነት ስጦታ ሳታስቡትና ሳትጠብቁት መጥቶ ቢያጥለቀልቃችሁ አትደነቁ። አንድ ሰው እንዳሉት "ለሁለት ደቂቃ በእምነት ስጦታ ብትቆዩ የሁለት ሳምንትን መቃተትና ማቃሰት ሁሉ ይሸፍነዋል" ግን ሁልጊዜ ማስታወስ ያለብን በተራ እምነት ላይ ቆመን ነው የእምነት ስጦታን መለማመድ የምንችለው።

በሁኔታው ላይ እርምጃ ውሰድ። መውጫ ቀዳዳ አትፈልግ። ከጉዳዩም አትሽሽ፣ በፊትህ ያለውን እርምጃ ውሰድ፤ በሁኔታው ውስጥ እግዚአብሔር እንደሚመራህ፣





እንደሚጠብቅህ፣ እንደሚረዳህና፣ እንደሚያስችልህ ማወቅህን ለእግዚአብሔር ንገረው።

ማስታወሻዬ ላይ "ጌታ ሆይ! ማድረግ ስላለብህ ታደርገዋለህ፣ እኔም ይህን በመተማመን አርፋለሁ" የሚል ፀሎት አለ። መደረግ ያለበትን ነገር ሁሉ የሚያደርገው እርሱ ብቻ ነው። ለማድረግ ችሎታውና ፍላጎቱም ስላለው በእኔም ውስጥ እንኳን ይሠራዋል ብዬ አምናለሁ።

እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ከመግባታቸው በፊት የዮርዳኖስን ወንዝ ማቋረጥ ነበረባቸው። ቀደም ብለን እንዳየነው የኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ካህናት እግራቸው የዮርዳኖስን ውኃ እስኪነካ ድረስ ውኃው መቆም አልጀመረም ነበር። ውኃው ከመከፈሉ በፊት ካህናቱ ምን ያህል እምነት የነበራቸው ይመስላችኋል? ምናልባት ብዙ የሚባል ላይሆን ይችላል። ሆኖም በተራ እምነታቸው እግራቸው ውኃው ውስጥ መግባት ጀመረ፣ በዚያን ቅጽበት ደግሞ ውኃው መከፈል ጀመረ። እርግጠኛ ነኝ እንደዚያ መሆኑን ሲያዩ እምነታቸው በጣም ትልቅ መሆን ጀምሯል፤ ወንዙ መካከል ቆመው "አይዟችሁ ኑና ተሻገሩ" እያሉ ሌሎቹን ለማበረታታት የሚበቃ እምነት ሆኖላቸዋል። ተራ እምነት ያስጀምራል፣ የእምነት ስጦታ ያጥለቀልቃል አሠራሩ እንዲህ ነው።

የእምነትን ስጦታ ግን የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ራሱ ብቻ ነው፤ እኛ ስጦታውም እንኳን ቢኖረን የስጦታው ተቆጣጣሪዎች አይደለንም። ይህ ስጦታ ደግሞ በየጊዜው የሚከሰት አይደለም፤ ብዙ ጊዜ ነገሮች የሚሆኑልን በተራ እምነት ነው። በትህትናና በታዛዥነት የሚሆን ተራ እምነት ራሱ ብዙ ነገር ያደርጋል።

## 5. አዲስ አማኝ

በመጀመሪያ ጌታን እንደተቀበልን ለብዙዎቻችን እምነት በቀላሉ ይሠራልን ነበር። ከዚያም የተነሳ ብርቅና ድንቅ የሆኑ የእምነት ውጤቶች ተለማምደናል። "አዲስ ክርስቲያን የነበርኩ ጊዜ" ብለን ጀምረን ብዙ አስደናቂ ታሪኮችን እናወራለን። "የዱሮ እግዚአብሔር ቅርብ ነበር" የሚለኝ አንድ ወዳጅ አለኝ። ያኔ ያለብዙ ድካምና ጥረት እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይሰማን ነበር፣ ከዚያም የተነሳ እምነታችን

ያድግ ነበር፤ ስላምና ደስታም ያለማቋረጥ ይፈልቅልን ነበር። ነገር ግን አንድ ቦታ ላይ ስንደርስ ነገሮች እንደዚያ መሆናቸው ያበቃል። የጸሎቱ መልስ ሲያድር ሲያበልስ በእምነታችን ላይ ጥያቄ ያመጣብናል። ለምንድነው እዚህ ሁኔታ ወስጥ የምንገባው? እኛ በልጆቻቸን እድገት ከምንለማመደው ልምምድ ጋር ይመሳሰላል። ለመራመድ ሲጀምሩ እየተከተልን ከመውደቃቸው በፊት እንይዛቸው የነበረውን ለጥቂት ጊዜ ካደረግነው በኋላ እንተወዋለን። ምክንያቱም ሁል ጊዜ እየደገፍናቸው እንዲያድጉ እንፈልግም። በራሳቸው እንዲሞክሩ እንተዋቸዋለን። ያ ሙከራ ነው በእምነት የሚመስለው። መውደቃቸውን ፈልገን ሳይሆን ልጆቻችንን ዝም የምንላቸው፣ ነገር ግን ለመራመድ በዚያ ልምምድ ውስጥ ማለፍ እንዳለባቸው ስለምናውቅ ነው።

እግዚአብሔርም ደስ የሚሰኘው ሁልጊዜ እርሱ ወዲያው እያደረገልን በሚሆነው የክርስትና ደረጃ ብቻ ሳይሆን በእምነት ያደርግልናል የምንልበት ደረጃ ላይ ስንደርስ ነው። እዚያ ቦታ ላይ እንድንደርስ ስለሚፈልግ የጸሎት መልሳችንን ያዝ ያደርገዋል። ምክንያቱም

*"ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም" (ዕብራውያን 11፥ 6)።*

"ልጄ ሆይ በእምነትህ ማደግና መብሰል አለብህ" ማለቱ ነው።

ይህ ጊዜ ማለትም እግዚአብሔር ያለ እኛ ድካም ሙሉ ድጋፉን ሰጥቶን በእምነት ሳይሆን በማየት ብቻ የምንራመድበት ጊዜ ሲቆም ለብዙ ክርስቲያኖች የትልቅ ጥያቄ ጊዜ ይሆናል። እምነታቸውን ብቻ ሳይሆን የሕይወታቸውን እርግጠኝነት የሚጠይቁበት ሁኔታ ውስጥ ያስገባቸዋል። ታዲያ ብዙዎች ያን በመጀመሪያ ጌታን የተቀበሉበትንና ነገሮች ሁሉ በቀላሉ ይፈጸምላቸው የነበረበትን ሁኔታ ደግመው ለመፍጠር ይጥራሉ። ቦታውን ጊዜውን ወደ ሕይወት የመረቸውን ሰዎች እንኳን ሳይቀር መፈለግ ይጀምራሉ። ሁኔታውን መለወጥ እምቢ ሲላቸው፤ ራስን አሳንሶ ማየት፣ ራስን በኃጢአት መክሰስ፣ ፀፀት ውስጥ መግባት፣ ደህንነትንና እግዚአብሔርን ራሱን መጠራጠር እነኚህ ሁሉ የተለመዱ ስሜቶች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ ይመስለኛል ለመሪነት የሚታጩን ሰዎች





*"አዲስ ክርስቲያን ያልሆነ" 1 ጢሞቴዎስ 3፥ 6 የሚል አቀባ ያደረገበት።*

ገና አዲሶች ከሆኑ በዚህ ከማየት ልምምድና በእምነት ጸንቶ በመቆም መካከል ያለውን ከባድ ጊዜ አልተለማመዱም፣ ያሉትን የሚያድርጉ ለመሆናቸው ገና አላስመሰከሩም። ይህ ጊዜ ከባድ የመሆኑን ያህል አስፈላጊም ጊዜ ነው። ጥረት ይጠይቃል፣ ያማቅቃል፥ ነገር ግን ያነጥራል፣ ልጅን ከአዋቂ ይለያል። በዚህ ሁኔታ ላለፈ ግን ነፃነት አለ። እ፤ ነፃነት በሚቀጥለው ምዕራፍ ያንን እናያለን።

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## አ ነፃነት!

ነፃነት በእግዚአብሔር ዘንድ ጠጋ ብሎ መቆም ሲሆን የሕይወታችንን ክፍል በሙሉ የሚነካ ነው። ነፃነት መንገድም ግብም ነው፤ መድረሻችንም መረማመጃችንም ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ውብ በሆነ መንገድ ነፃነትን ሲያሳያቸው ነው ለገላትያ ሰዎች እንዲህ ያላቸው፥

*"በነፃነት እንድንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን። እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ" ገላትያ 5፥ 1።*

በእምነትና በነፃነት መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ልናያቸው የሚገቡን ሰባት ነገሮች አሉ። እነኚህን ሰባት ነገሮች በትክክል መረዳት የሚሠራ እምነት እንዲኖረን በጣም ይረዳል።

## 1. ሕግ

ሕግ ኃጢአትን ይገልጸዋል፣ ያብራራዋል፣ ግን መጠኑን አይጨምረውም ወይም አይቀንሰውም። ሕግ አስሩ ትዕዛዞች ናቸው፣ የክርስቶስ ትምህርት በተለይም የተራራው ስብከት በመባል የሚታወቀው ህግን ነው ያብራራው (የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5-7) ። ያለ ሕግ ኃጢአት ራሱ የሞተ ነው (ሮሜ 7፥ 8)። ኃጢአተኛ መሆናችሁን እርግጠኛ ካልሆናችሁ ሕግን አንብቡ፣ ኃጢአታኝነታችሁን ቁልጭ አድርጎ ያሳያችኋል። ኃጢአተኛ መሆናችሁንም ያለ ምንም ጥርጣሬ ያረጋግጥላችኋል። ሕጉን በመስጠት ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር አላማ ግን በሕጉ ውስጥ ካለብን እርግማን ነፃነት ሊሰጠን እንጂ የሕጉ እርግማን እንዲያንጸባርቅብን አይደለም።

ሕጉ የልባችንን ሁኔታ ነው የሚያሳየን፣ ክፋት እንጂ መልካም የማይገኝብን መሆኑን ነው ግልጽ የሚያደርግልን። በደለኞች፣ ራሳችንን ለማዳን አቅሙም ፍላጎቱም እንደሌለን ያሳየናል። ሕጉ እኛነታችንን ቁልጭ አድርጎ ሲያሳየን ነው አዳኝ

እንደሚያስፈልገን የምንረዳው። መታሰሩን ያላወቀ እኮ መፈታት አያምረውም፤ ግዞተኛነቱን ያወቀ ነው ነፃነት ነፃነት እያለ የሚጮኸው።

## 2. ፀጋ

ከሕግ ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጠን ስንደራደር፣ ሕግ ያለ ምንም ይሉኝታና ይቅርታ ኃጢአታችንን ያጋልጠዋል። ያን ጊዜ "እርዱኝ" ብሎ ለመጮህ ይሉኝታ አይዘንም። የዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ለመንፈሳችን ምስጢር ይነግረዋል። ክርስቶስ ያለ ኃጢአት ስለነበረ እርሱ ብቻ ነው ለኃጢአት የሚከፈለውን ለመክፈል ብቃት ያለው። በመስቀል ላይ ለስድስት ሰአት ተሰቅሎ በመዋል ለኃጢአት የተጠየቀውን እዳ ሁሉ በብቃት ከፈለው። እኔና እናንተ ግን ለስድስት አመት እንኳን በዚያ መስቀል ላይ ብንሰቀል እንኳን የአለምን ሁሉ ኃጢአት ከራሳችን ኃጢአቶች እንኳን የትንሿን ዋጋ መክፈል አንችልም ነበር።

ኃጢአተኛ ሰው የኃጢአትን ዋጋ ለመክፈል ብቃቱ የለውም። ያንን ማድረግ የሚችለው ክርስቶስ ብቻ ነበር፤ እርሱም አደረገው። ይህ ምስጢር ነው፣ የዚህ ምስጢር ስም ፀጋ ይባላል፤ የማይገባን፣ እንደሚያስፈልገን እንኳን የማናውቀው ክቡር የሆነ፣ ክርስቶስ ዋጋውን በሙላት ስለከፈለ እኛ በነጻ ያገኘነው ስጦታ ነው። ከፀጋ ስጦታዎች ሁሉ ደግሞ የመጀመሪያውና ዋነኛው ስጦታ ጽድቅ ይባላል።

## 3. ጽድቅ

ጽድቅ የክርስቶስን የማዳን ሥራ ማዕከላዊ ያደረገ የሁለት አቅጣጫ ልውውጥ ነው። ይህንን ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገልጾታል።

> *"እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን ኃጢአት የሌለበትን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው" 2ቆሮንቶስ 5፥ 21።*

የዚህን ልውውጥ ወርድና ስፋት ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት ከግምት በላይ ነው። ኃጢአት የማያውቀው፣ እንከን ያልተገኘበት ጌታ የሱስ እርሱ ራሱ ኃጢአት ሆኖ ነው ኃጢአተኞች ከኃጢአት ወጥተው የእግዚአብሔር ጽድቅ ወራሾች ለመሆን የበቁት፣





ይህ ሁኔታ በየትኛውም የሰው ግምት ትክክለኛ ፍርድ አይደለም፤ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው እንጂ።

ልውውጡ እንግዲህ እንዲህ ነው። ጌታ የሱስ የራሱ የሆነውን ጽድቅ ለእኛ ሰጠን፣ እኛ ደግሞ የራሳችን የሆነውን ኃጢአት ለእርሱ ሰጠነው። የእግዚአብሔር የጽድቅ ጥያቄ መሟላት ነበረበት፣ ያም ማለት የኃጢአት ዋጋ መከፈል ነበረበት። እግዚአብሔር መከፈል ያለበትን እዳ ዝም ብሎ ለማለፍ አይችለም፤ ቅዱስ የሆነው ባሕሪው ያንን ማድረግ አያስችለውም።

ስለዚህ ፍጹም የሆነው ፍቅሩ እዳውን ለመክፈል የሚችለውን አንድ ልጁን መስዋዕት አድርጎ እንዲሰጥ አስገደደው። ያንን የኃጢአት ዋጋ መክፈል የሚችል ሌላ ማንም ወይም ምንም አልነበረም። ስለዚህ እርሱን ብዙ አስከፈለው፣ ክፍያው ግን ለሁላችንም በቂ ነበር። ኃጢአትን አስወግዶ፤ ጌታ የሱስም ፍጹም ጻድቅነቱን ጠብቆ የአለምን ሕዝብ ሁሉ ነፃ ለማውጣት በቂ ነበር።

## 4. ፈውስ

ከጽድቅ ጋር የተያያዘውና በዚያው ልውውጥ የተገኘው ሌላው ጥቅም ፈውስ ይባላል። ኃጢአት ያበላሸውን ሁኔታ ማስተካከል ማለት ነው። ጴጥሮስ ይህንን ግንዛቤ ሲያብራራ

> *"ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ። በእርሱ ቁስል እናንተ ተፈውሳችኋል" 1 ጴጥሮስ 2፥ 24።*

ሐዋርያው ጴጥሮስ እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እላይ በሁለተኛ ቆሮንቶስ ከጠቀሰው አሳብ ጋር ተስማምቶ በልውውጡ ላይ ግን አዲስ አሳብ ይጨምርበታል። በጽድቅ ውስጥ ፈውስ አለ። ቁስል ያልነበርው ክርስቶስ ቆስሎ እኛ ከቁስላችን ተፈወስን። መሲሐዊው ትንቢት ኢሳይያስ 53 ስለዚህ እውነት የተነበየው አለ።

*“ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፣ ስለበደላችንም ደቀቀ። በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን። በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን” ቁጥር 5*

ፈውስ ነፃነት ነው። የአካል፣ የመንፈስ፣ የነፍስ፣ የግንኙነትና የሁኔታ ፈውሳችንን ሁሉ የምንለማመደው በዚሁ እምነታችን ውስጥ ነው።

## 5. ሥጋና መንፈስ

በአዲስ ኪዳን ሥጋ የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ ጥሩ የሆነ ትርጉም አለው። ነገር ግን ከመንፈስ ጋር ባለው ተግዳሮት ሲታይ ሁልጊዜ ጥሩ ያልሆነ ትርጉም ነው የሚያሳየው። ሥጋ የወደቀው ፍጥረታችን በእኛነታችን ላይ አምባገነን ሆኖ ችግር ውስጥ ሲያስገባን ነው። ሥጋ ተፈጥሮአዊው አስተሳሰባችን ነው፣ ያልተለወጠው ስሜታችን፣ የወደቅንበት ፈቃዳችን፣ ያልታደሰው መንፈሳችን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋዊ እኛነታችን ልናደርግ የምንችለውን ሲያትት በገላትያ ምዕራፍ 5 እንዲህ ነው ያለው።

*“የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው፦ይኸውም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኛነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት (ወይም አንዳንድ ትርጉሞች እንደሚያቀቡት ያልተገታ ወሲብ orgies)። ቁጥር 19-21*

ከዚያ ይቀጥልና የመንፈስ ፍሬዎች የሆኑትን ግሩምና ድንቅ ነገሮች ይዘረዝራል።

*“ፍቅር፣ ደስታ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት” ቁጥር 22-23*

ብሎ ካተተ በኋላ አሳቡን እንዴት እንደዘጋው ተመልከቱ።

*“እንደነዚህ ያሉትንም የሚከለክል ሕግ የለም” ቁጥር 23።*

የሕጉ ሥልጣን በሥጋ ሥራ ላይ ነው እንጂ በመንፈስ ፍሬ ላይ መሰልጠን አይችልም።





በሥጋ የምንመላለስ ከሆነ ሕጉ በክፉ ሥራችን ሊፈርድብን ሥልጣን አለው። ግንኙነታችን ግን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከሆነ፣ ሕጉ በእኛ ላይ ሥልጣን የለውም፤ እንኳን ሊፈርድብን ሊመረምረን እንኳን አይችልም። ከጌታ ጋር መመላለስ እስከጀመርንበት ጊዜ ድረስ ሕጉ በሄድንበት ሁሉ እየተከተለ እንደ ጥላ ያንዣብብብን ነበር። ከጌታ ጋር መመላለስ ስንጀምር ግን ከጥላው ስር ወጥተን ፀሐይ ይወጣልናል። አሁን የሚጋርደን ጥላ የለም፣ ምክንያቱም በሕግ ሥር አይደለንም። ነገር ግን ወለም ዘለም ማለት ሲመጣና በሥጋዊ መንገድ መራመድ ስንጀምር ሕጉ ሊፈርድብን ጥላውን ይጥልብናል። ይህ የሕጉ ሥራ ነው፣ ምርመራና ፍርድ ይጀምራል፣ በዚያም ወደ ንስሐ ይገፋፋናል፣ ይህ የሕግ ሥራ ነው።

## 6. እምነት

እምነት ጽድቅን ተመርኩዞ ከአለም፣ ከሥጋና ከሰይጣን ክስ ነፃ ያወጣናል። እምነት እግዚአብሔር ስለ እኛ የተነገረው እውነት መሆኑን ያረጋግጥልናል። እምነት የእግዚአብሔርን እውነት በመቃወም ሊከሰንና ሊረግመን የሚነሳውን ሁሉ ያፈርሰዋል። እምነት ራሳችንን አለምንና ሌላውንም አስፈላጊ ነገር ሁሉ የምንመለከትበት ልዩ አመለካከት ነው። በመጨረሻም እምነት በሥጋ ወይም በመንፈስ መመላለሳችንን ይወስነዋል። መጽሐፉ በሙሉ ስለ እምነት ስለሆነ በዚህ ቦታ ስለ እምነት የምጠቅሰው ይኸው ይሆናል።

## 7. ነፃነት

ነፃነት ከላይ ያየናቸው ስድስት ነጥቦች ውጤት ነው። ነፃነታችንን በሁለት መንገድ ልንጠቀምበት እንችላለን። አንደኛው የሥጋን ሥራ መርጦ በኃጢአት መውደቅ ሲሆን ሁለተኛው በመንፈስ ልምምድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሠራውን ጽድቅ በመልበስ መመላለስ ነው። በክርስቶስ ስንሆን ከቀደመው የውድቀት ክስ ነፃ ከመሆናችንም በላይ ጽድቁንና አዲሱን ሕይወት ለመለማመድም ነፃ ነን። ይህ ነፃነት ታዲያ ካንድ ነገር ነፃ መሆን ብቻ ሳይሆን ለሌላ ነገር ነፃ መሆን ነው። በክርስቶስ ከኃጢአት ክስና ካለፈው በደላችን ፀፀት ነፃ ከመሆናችንም በላይ የአዘጋጀልንንም አዲስ ሕይወት ለመውረስ ነፃ ነን።

## ፍጹም ነፃነት

እግዚአብሔርን ማገልገል ፍጹም ነፃነት ነው። በሰብአዊ አስተሳሰባችን ነፃነት ማለት የፈለጉትን ማድረግ፣ የወደዱትን መሆን ይመስለናል። ፍጹምና፣ እውነተኛ ነፃነት ግን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ስኬትና እርሱን ለማገልገል የመስጠታችን ውጤት ነው። አንድ የዱሮ የእንግሊዝኛ መዝሙር ሲተረጎም እንዲህ ይላል "አንተ ግዞኝና ያን ጊዜ ፍጹም ነፃ እሆናለሁ" ቅዱስ አውጎስጢኖስ ደግሞ በዚህ አሳብ ላይ ሲጽፍ "እግዚአብሔርን ውደድና የፈለከውን አድርግ" ብሏል። እግዚአብሔርን ከወደድን እርሱ የሚፈልገውን እናደርጋለን፣ የሚያስደንቀው ነገር ደግሞ ያንን ማድረግ እንወዳለን፣ ደስ ይለናል።

ምናብን ለመኮርኮር 12.

**እግዚአብሔር እምነትን ሽልሞ እምነተቢስነትን ይቀጣል እንዴ? ይህንንስ ካደረገ ሕጉን ማጥበቅ አይሆነም እንዴ?**

እምነት ካለንበት ሁኔታ ፈንቅሎ አውጥቶ እግዚአብሔር እንዲኖረን ወደ ከቀደልን ነፃነት ያደርሰናል። ከዚያ ሁኔታ ስንፈነቀል፣ ከፍርሃታችን እንላቀቃለን። የዚያን ጊዜ ፈቃዳችንን ትተን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመታዘዝ ነፃ እንሆናለን። መልካም የሆነውን የእግዚአብሔርን ነፃነት ለመቀበል እጃችን የተከፈተ ይሆናል። ያ ብቻ ሳይሆን ማንም ሊወስድብን ወደማይችለው ነፃነት ያሸጋግረናል። ሕይወታችንን





አጥፍተን እርሱ የሚሰጠንን ሕይወት ለመቀበል ነፃ መሆን ማለት ነው። እምነት መጋለጥ ነው። ነገር ግን ለዛ ያለው መጋለጥ፣ ራስን ለእግዚአብሔር ያለ ምንተ አፍረት መስጠት ነው። ያ እግዚአብሔርን ደስ ስለሚያሰኘው ነፍሳችንን የሚያረካ ነፃነት ያለማምደናል፡፡ ጌታ የሱስም የራሱን ነፃነት እንዲሰጠን ያስችለዋል፣ መቼም በዚች ምድር ላይ እርሱ በነበረው ነፃነት የተመላለሰ ሌላ ማንም የለም።

ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያን ሰዎች ክርስቶስ የሰጣቸውን ነፃነት በቀላሉ አሳልፈው በመስጠታቸው በኃይለ ቃል ሊያስጠነቅቃቸው የተገደደው።

> *"በነፃነት እንድንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን፣ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ"* ገላትያ 5፥ 1።

የገላትያ ሰዎች በአንዳንድ ነጻ ባልሆኑ ሰባኪያን አግባቢነት ክርስቶስ በሞቱና በትንሳኤው የሰጣቸውን ነፃነት ለውጠው ወደ ሕግ ሥርዓት እየተመለሱ ነበር። ይህ ሁኔታ ደግሞ ሐዋርያውን በጣም ነበር የረበሸው። ሕጋዊነት የአስመሰሎ እምነት ነው፤ ቁም ነገሩ ሕጋዊነትን አሽቀንጥሮ ጥሎ እውነተኛና ነፃ አገልገሎትን መያዝ ነው።

## ነፃነትና ሥልጣን

ለመረዳት ከባድ ከሆኑ መንፈሳዊ አስተምሮሆች አንዱ ይህ የነፃነትና የሥልጣን ቅንጅት ነው። ስለ ነፃነትና ሥልጣን ቢያንስ ሁለት ነገሮች ማለት ይቻላል። የመጀመሪያው ፣ በልምምድ እግዚአብሔር ሥልጣን እንዲኖረን የሚያበቃንን ነፃነትም ሊሰጠን ይችላል።

ልጆቻችንን በምናሳድግበት ጊዜ ለሥልጣን የሚያበቃቸው ነፃነት ልንሰጣቸው እንችላለን። ከሥልጣን ጋር ነፃነት ነፃ እንዲሆኑ ይጠብቃቸዋል፤ ያለሥልጣን ግን ነፃነት ራሱ ባርነት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ልጆቻችንን ስለ አላፊነት በግብርና በቃል እናስተምራቸዋለን። ጥሩ የአላፊንት ችሎታ ባሳዩን ቁጥር እኛ ደግሞ የበለጠ ውሳኔ የመወሰን ነፃነት በመስጠት እናበረታታቸዋለን።

## ምናብን ለመኮርኮር 12.

እግዚአብሔር እምነትን ሸልሞ እምነተቢስነትን ይቀጣል እንዴ? ይህንንስ ካደረገ ሕጉን ማጥበቁ አይሆንም እንዴ?

ለምሳሌ የቤት ሥራቸውን በጊዜ የመጨረስ ሃላፊነት ካሳዩን፣ እኛ ደግሞ የቤት ሥራቸውን የሚሠሩበትን ጊዜ እንዲወስኑ እንተዋቸዋለን። ሥልጣን ለነፃነት አበቃቸው ማለት ነው።

ሁለተኛ ስለ ነፃነትና ሥልጣን ቅንጅት ማለት የምንችለው ነገር በውጪ ሲታይ አላይ ያልነውን የሚቀለብስ ይመስላል። እግዚአብሔር ነፃ እስከሆንበት ሁኔታ ድረስ ሥልጣን ይሰጠናል። የየሱስ ክርስቶስን ማንነት በተረዳን ቁጥርና ለእኛ ያደረገውንም ነገር በተረዳነው መጠን፣ እግዚአብሔርም የሚያለማምደን ሥልጣን የበዛ ይሆናል። በሌላ አነጋገር ለሥልጣን ብቁ የሚያደርገን ነፃነት ነው ማለት ነው።

ወደ ሥልጣን የሚያደርስ ነፃነት ወደ ነፃነት ከሚያመጣ ሥልጣን በጣም የበለጠና የተሻለ ነው። ወንጌል የነፃነት መልዕክት ነው። ብዙ ጊዜ ሰባኪያን ልክ የገላትያን ሰዎች እንዳሳቱት ሰዎች ወንጌልን ሕጋዊ አድርገው ያቀርቡታል። መስፋፊያ ሳይሆን መታገጃ ያደርጉታል፤ ሕይወት ሰጪ ሳይሆን ሞትን አምጪ ያስመስሉታል፣ መልካም ዜና ከመሆን ለውጠው ማስፈራሪያ ያደርጉታል። ወንጌል ግን የነፃነት መልዕክት ነው።

ከሕግ ነፃነት፣ ከሥጋ ሥራዎች ነፃነት፣ ከአለም ነፃነት፣ ከሃይማኖት ሥርዓት ነፃነት፣ ከእግዚአብሔር በታች ከሆነው ከማንኛውም ነገር ሁሉ ነፃነት! አዎን "በነፃነት እንድንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን" ፦ አ1 ነፃነት እንዴት ደስ የሚል ቃል! ነፃነት ጌታን በሙላት የሚገልጸውና እግዚአብሔርም ብዙ ሥልጣን ሊሰጠው የሚመርጠው ሰው ባህሪ ነው። በጣም ኃያላን የሚሆኑት ፍጹም ነፃነት ያላቸው ናቸው። ብዙ ኃይል ቢኖራቸውም የነፃነታቸው ውጤት መሆኑን ስለሚረዱ አያሳስታቸውም።

ከዚያም በላይ ነፃነት በብዛት ያላቸው ናቸው ሥልጣንም እንደተሰጣቸው መረዳት የሚችሉ። ነፃነት ራሱ እግዚአብሔር ለእኛ የሚሰጠውን የሥልጣን ቃል የምንሰማበት ጆሮ ነው። ያንን ሥልጣን መረዳት ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይል ያለመቆጠብ በውስጣችን እንዲሠራ ይለቀዋል። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ለሥልጣኑና ለአገልግሎቱ ያለ ምንም ማመንታት በኃይል ይከራከር የነበረው።





*"ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም፤ ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው" 1ቆሮንቶስ 2፥ 4 - 5።*

*"በተናገርሁትና በአደረግሁት ነገር አሕዛብ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ ክርስቶስ በእኔ ሆኖ ከፈጸመው በቀር ሌላ ነገር ለመናገር አልደፍርም፤ ይህም የሆነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በምልክቶችና በተአምራት ነበር። በዚህም ሁኔታ ከኢየሩሳሌም እስከ እልዋሪቆን ዙሪያ ድረስ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ" ሮሜ 15፥ 18 - 19።*

*"እኔም በኃይሉ አሠራር በተሰጠኝ በእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የዚህ ወንጌል አገልጋይ ሆኛለሁ" ኤፌሶን 3፥ 7*

*"ምክንያቱም ወንጌላችን ወደ እናንተ የመጣው በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙም መረዳት እንጂ በቃል ብቻ አይደለም። ደግሞ ስለ እናንተ ስንል በመካከላችሁ እንዴት እንደኖርን እናንተ ታውቃላችሁ" 1ተሰሎንቄ 1፥5።*

ሌሎችን ሲያበረታታ ደግሞ እንዲህ አለ።

*"ይሁን እንጂ የጌታ ፈቃድ ቢሆን ፈጥኜ ወደ እናንተ እመጣለሁ፤ ከዚያም እነዚህ ትዕቢተኞች የሚናገሩትን ብቻ ሳይሆን ምን ኃይል እንዳላቸውም ማየት እሻለሁ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግሥት የወሬ ጉዳይ ሳይሆን የኃይል ጉዳይ ነው" 1ቆሮንቶስ 4፥ 19 - 20።*

ኃይል ነፃነትን ይገልጻል፣ ኃይል የኃይለኛውን ነጻነት ያረጋግጣል። ነፃነት እያደገ ሲሄድ በዚያው መጠን እኛም ወደ እግዚአብሔር እየቀረብን ነው። ነፃነትን ማሳደጊያ ዋናው ቁልፍ ደግሞ እምነት ነው። ሰው በእምነት እያደገ ሲሄድ መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው በኃይልና በሥልጣን ያሚያስታጥቅበት የነፃነት መድረክ ላይ ያደርሰዋል።

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## ፈቃድና ፍቅር

### 1. የበላይ የሆነ ፈቃድ

ችግሩ ይሄ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እስካሁን ድረስ ያየነው እምነት በፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን በመገመት ነው። የሰው ልጅ ፈቃዱ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ወደ ቀኝ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ግራ ቢያዘነብልም በአጠቃላይ ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚስማማ ነው በሚል ግምት ነው እስከዚህ የመጣነው። ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድ የማይስማማ ፈቃድስ? ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅም ሆነ ለመስማማት ጥረት የማያደርግ ፈቃድስ? ወይም ጨርሶ የእግዚአብሔር ፈቃድ ግድ የማይሰጠው ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመቀበልም ሆነ ለመከተል ብርታቱና ፍላጎቱ የሌለው ፈቃድስ? ችግሩ ይሄ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ የበላይ የሚለውን ቃል የምንጠቀመው እግዚአብሔርን ለመግለጽ ነው። አንዳንዴ ደግሞ ከእኛ በላይ ለሆነ ሥልጣን ለምሳሌ ሕገ መንግሥት፣ ባለ ሥልጣን ወይም የመሥሪያ ቤት አለቃ የበላይ ይባላል። እዚህ ግን ላመጣውና ላሳያችሁ የምፈልገው አሳብ የእያንዳንዳችንን ፈቃድ የበላይነት ነው። ፈቃዳችን የበላይነት አለው፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንድንሆን ያቀደው እንደዚያ ነው።

ፈቃዳችን የበላይ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር በትምህርት፣ በማበረታታት፣ ተስፋ በመስጠት፣ በማስጠንቀቅ በእኛ ላይ ጊዜውን አያጠፋም ነበር።ይህ ሁሉ ፈቃዳችንን ለመማረክ የተደረገ ጥረት ነው። ፈቃዳችን የበላይ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር እኛን ለመድረስ አይጥርም ነበር፤ በትዕዛዝ ብቻ ሁሉን ያከናውን ነበር፣ እኛም ምርጫ አይኖረንም ነበር።

ለምን ፈቃድ የበላይ ሆነ?

አንድ ታሪክ ከእንግሊዝኛ ተርጉሜ ላቅርብ፦

አንድ የታወቀ አሻንጉሊት ሠራተኛ በአንድ አገር ውስጥ ይኖር ነበር ይባላል። በአሻንጉሊት ሥራ ጥበብ በጣም የረቀቀ ከመሆኑ የተነሳ የሥራው ዝርዝር በጣም የጠራ ስለነበር፣ አሻንጉሊቶቹ በጣም እውን ይመስሉ ነበር። ስለዚህ በየጊዜው ብዙ አሻንጉሊቶችን ስለሚሠራ፣ ከጊዜ ብዛት በምድር ላይ ያሉ የሰው ዘሮችን ሁሉ የሚወክሉ አሻንጉሊቶቸን ሰርቶ አጠራቀመ። ከዚያም ቀኖቹን በሙሉ በእነኚህ ግሩምና ደንቅ አድርጎ በሰራቸው አሻንጉሊቶች በመጫወት ያሳልፍ ነበር። ለብዙ ዘመናት በዚህ ሁኔታ ረክቶና ደስ ብሎት ይኖር ነበር።

ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ግን ቀስ በቀስ የሐዘን ስሜት ጥላውን እያጠላበት መምጣት ጀመረ። ይህ ታልቅ ጥበበኛ አሻንጉሊት ሠራተኛ የሠራው ሥራና በጥበቡም የፈጠራቸው አሻንጉሊቶች ሁሉ ባዶና ከንቱ መሆናቸውን መገንዘብ ጀመረ። ምንም ነገር የሌለባቸው፣ በመስታወት እንደሚታይ ምስል በጣም የራቁ ባዶ መሆናቸውን እየተረዳ መጣ። ሁሉም የራሱ አዕምሮ ውጤቶች ነበሩ፤ ራሱንም ከአሻንጉሊቶቹ ጋር ዘግቶ ጊዜውን ሁሉ የጨረሰው ከእነርሱ ጋር ብቻ ስለነበር፣ ለካ በአለም ውስጥ ብቸኛ ነበር። ጥበቡና ሙያው በጣም የረቀቀ መሆኑ ራሱ ለብቸኝነቱ ዋና ምክንያት መሆኑን ባወቀ ጊዜ ብቸኝነቱ በጣም ጎለበት። ይህ ባዶነት፣ ይህ ብቸኝነት ይህ ግንዛቤ የበለጠ ጥልቅ ሐዘን ውስጥ እንዲዋጥ አደረገው።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ አንድ ቀን ራዕይ አየ። አንድ መልአካዊ ፍጡር የሕይወት ውኃ የሞላበት ጽዋ ይዞ ሊሰጠው መጣና "ከዚህ ውሀ አንድ ጠብታ የነካው ማንኛውም ነገር ሕይወት ያገኛል" አለው። ይህንንም ሲረዳ ሊሆን የሚችለው ነገር በሙሉ ገባውና ስሜቱ ገነፈለ፣ ደስታው በዛ፣ልቡ ድውድው እያለበት በመንቀጥቀጥ ጽዋውን ለመቀበል እጁን ዘረጋ። በዚያ ቅጽበት ግን አንድ ፍርሐት መጣበትና እጁን ሰብሰብ አደረገ። ይህንን ደስታውንና ስሜቱን የሚገታ አዲስ አሳብ ምን እንደሆነ መገመት ትችላላችሁ? ሕይወት እንዲህ በቀላሉ ሊሰጥ ይገባዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ መጣበት። ለአሻንጉሊቶቹ ሕይወት ከሰጣቸው ጓደኞቹ ሆነው ለመቅረታቸው ምን ማረጋገጫ አለው? እንዳሁኑ ሊታዘዙትና ሁኑ ያላቸውን ሁሉ የሚሆኑ፣ የሚወዱትና የሚከተሉት ሆነው መቆየታቸውን በምን ያውቃል? ራሳቸውን ችለው ቢሄዱስ? ጓደኞቹ ለመሆን ወይም ላለመሆን የምርጫ ነፃነት መስጠቱ አይደለም





እንዴ? ጓደኞቹ ለመሆን ባይመርጡስ? እንዳውም ጠላቶቹ ለመሆን ቢነሱስ? ስለ እርሱ ምንም አይነት አመለካከት ሳይኖራቸው እንዲያው ቢዘጉትስ? የዚህ ሁሉ አሳብ ጥላ በላዩ አጠላበት፣ ትካዜ ገባው፣ እጁን እየሰበሰበ ለራሱ እንዲህ አለ፤ "ይህንን እድል ልጠቀምበት አልችልም"።

የሰው ፈቃድ የበላይ የሆነው እግዚአብሔር ይህንን እድል ስለተጠቀመበት ነው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ፍቅር ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ባይሆን ኖሮ እኛ ብንወደው ወይም ባንወደው ግድ አይሰጠውም ነበር። ፍቅር ስለሆነ ግን እኛም ወደ እርሱ በፍቅር እንድንመለስ አጥብቆ ይፈልጋል። ያ ሊሆን የሚችለው የአሻንጉሊት ሠራተኛው ከብዙ ጥያቄ በኋላ ቀስ በቀስ እንድተረዳው ነፃነት ሲኖረን ብቻ ነው።

በግድ የሆነ ፍቅር ምን አይነት ፍቅር ነው? ሊያገባሽ የማይፈልግን ሰው አግብተሽ አብረሺው መኖር ትፈልጊያለሽ? አትፈልጊም፣ ደግሞም አይዘልቅም። ተጋብታችሁ ከኃይልና ከመሸነፍ የተነሳ መኖር ብትችይም፣ ለራስሽ ሲል ወዶሽ አግብቶሽ ብትኖሪ የበለጠ ትርጉም አለው።

ፍቅር ለተዋደዱ ነፃነት መስጠት መቻል አለበት። ፍቅር ነፃ ሲሆን ብቻ ነው በሙላት ሊሠራ ይሚችለው። እግዚአብሔር እወዳችኋለሁ ብሎ እንድንወደው ቢያስገድድን ኖሮ ያ ፍቅር አይደለም። ሌላ መንፈሳዊ ስም ይኖረው እንደሆን አላውቅም፣ ግን ፍቅር አይደለም።

ፍቅር በመጀመሪያ ነፃነት ይሰጥና ከዚያ በኋላ ተወዳጁ መልሶ እንዲወድ ያባብለዋል። እኛም ለእግዚአብሐር መልሰን የምንሰጠው ፍቅር በነፃነት ካልሆነ እውነተኛ ፍቅር ሊሆን አይችልም። በነፃነት ያልሆነ ፍቅር የሚመስል ነገር፣ አክብሮት፣ ፍርሀት፣ ወይም መታዘዝ ሊሆን ይችላል፤ ፍቅር ግን ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔርን ላለመውደድ ምርጫው ከሌለኝ ልወደውም ምርጫ የለኝም። ፍቅር ውሳኔ ነው። ስለዚህ አንዱ ሊያደርግ የሚችለው የሌላውን ፈቃድ ማባበል ነው። ምክንያቱም ፈቃድ የበላይ ነው።

ሴቷ ልጄ ሶፊ የአራት አመት ልጅ በነበረችበት ጊዜ አንድ ቀን እኔና እሷ ብቻ ቤት ውስጥ ነበርን። ገበታ ቤት ያለው ጠረጴዛ ላይ ሆኜ የሆነ ነገር እጽፍ ነበር። ትኩረቴ የምሠራው ሥራ ላይ ስለነበር እርሷ ደግሞ የኔን አሳብ ለመያዝ ትጥር ነበር። "ዳዲ ይህንን አሳየኝ" ስትለኝ "ቆይ የምሠራውን ልጨርስ" ብዬ ገፋ አደርጋታለሁ።ከዚያ ጠረጴዛው ላይ ወጥታ የምሠራውን እየነካካች አሳቤን ለማግኘት ብዙ ሞከረች። በኋላ ስታስቸግረኝ ተቆጣሁና "በይ አሁኑኑ ከጠረጴዛው ላይ ቶሎ ውረጂ አለዚያ ትቀጫለሽ" አልኳት። በዚህ ጊዜ ቅጣት ፈራችና ወርዳ ወንበር ላይ አኩርፋ ቁጭ አለች። ትንሽ ቆይታ "በውስጤ ግን አሁንም ጠረጴዛው ላይ ቆሜአለሁ" ብላ አስገረመችኝ። ፈቃዷ በእኔ ውሳኔ አልተስማማም፤ እርሷን አስፈራርቼ ማስቀመጥ ብችልም፣ ፈቃዷን ግን ማሸነፍ አልቻልኩም።

## 2. መጠን የሌለው ፍቅር

መጠን የሚለው ቃል ለማለት የፈለኩትን ሁሉ የሚገልጽ አይደለም። ግን ተቀራራቢ ሆኖ ያገኘሁት እርሱን ብቻ ነው። ለማለት የምፈልገው ግን ብዙ ቅፅሎችን የሚያጠቃልል አሳብ ነው። "የማይቀር፣ የተረጋገጠ፣ የተወሰነ፣ የተገበረ፣ የማያዳግም፣ የማይቀለበስ፣ የማይለወጥ፣ የማናመልጠው፣ ቀድሞ የሆነ ..." ፍቅሩን ለመግለጽ የሚውሉ ሆኖም እንጀት ያማያርሱ ቃላቶች ናቸው። የእግዚአብሔር ቃልም ይህንን ፍቅር በብዙ መንገድ ያስቀምጠዋል።

*"በዘለአለም ፍቅር ወድጄሻለሁ፣ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ"*
*ኤርምያስ 31፥ 3።*

*"አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ"*
*ዮሐንስ 15፥ 9።*

*"ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" ሮሜ 5፥ 8።*

*"ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላዕክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃያላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼዋለሁ"*
*ሮሜ 8፥ 38-39።*

*"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህም ፍቅርን አውቀናል" 1 ዮሐንስ 3፥ 16።*





የማይወድቅ የማይቋጭ፣ ዘለአለማዊ፣ ሰማያዊ፣ የማይገባን፣ የማይሸነፍ፣ ዋጋው የማይለካ፤ መጠን የሌለው ፍቅር። የእግዚአብሔር ፍቅር "እኔ አልሸነፍም" ይለናል። ይህንንም የሚለው ከኩራትና ከትዕቢት ተነስቶ ሳይሆን ከርህራሄ ይተነሳ ነው። ፍቅር እንዲህ ይላል "ገለል ስደረግ ልቤ ይሰበራል" ፍቅር የሚያስወጣውን አውጥቶ የተፈቃሪውን ደህንነት ይጠብቃል፤ ፍቅር የተፈቃሪውን መባረክ በጣም ስለሚፈልግ በረከቱን የሚዘጉበትን እንቅፋቶች ሁሉ ለማስወገድ ይጥራል። ፍቅር የማይታክተውና የማይመጠነው ለራሱ ብሎ ሳይሆን ለተፈቃሪው ብሎ ነው።

በ 1ቆሮንቶስ 13 የተገለጸው የፍቅር ገለጻ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያንፀባርቅ ነው

*"ፍቅር ይታገሳል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፣ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም የማይገባውን አያደርግም፤ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም በደልንም አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመጻ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሳል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል" ቁጥር 4-7።*

የእግዚአብሔር ፍቅር ይህን ይመስላል፣ በዚህም አገላለጽ መሠረት ፍቅሩ ጨዋ ነው፤ ሆኖም የእግዚአብሔር ፍቅር መጠን የሌለው ነው፤ ይህም ማለት እምቢ ብለን በመሸሽ ልናመልጠው አንችልም፣ ይከተለናል እንጂ። ይህ መጠን የሌለው ፍቅር ለመጠበቅ፣ ለመቆየት እምቢ ያለውን እያባበለ፣ እየታገሰ እሺ ለማሰኘት ይጠብቃል፥ ፍቅር ለተፈቃሪው "ከእኔ ጋር መስማማትህ፣ እኔን መቀበልህ አይቀርም፤ እስከዚያው ድረስ ግን ማደግህ ይቀጥላል" ይለዋል።

ፍቅር ኢየሱስ ነው፤ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ውስጥ ፍቅር በሚለው ቦታ ሁሉ ኢየስሱ የሚለውን እየተካችሁ ብታነቡ አሳቡ የበለጠ ትርጉም ይሰጣችኋል።

ለምሳሌ ያህል እስቲ እንዲህ ብለን እናስብ። ምርጫ በቀረበልን ጊዜ ሁሉ ፍቅር አስር ነጥብ እንድናገኝ ይጠብቅ ይሆናል (እንደ ኦሎምፒክ ጅምናስቲክ ማለት ነው)። ግን በመጀመሪያ ሙከራችን ሶስት ነጥብ እናገኝ ይሆናል እንበል።

ፍቅር አሁንም ሌላ እድል ይሰጠንና በሚቀጥለው እድል የባሰውኑ አንድ ነጥብ እናገኝ ይሆናል። ፍቅር ግን በትዕግስትና በማበረታታት አሁንም ሌላ እድል ይሰጠናል። (በነገራችን ላይ በኦሎምፒክ ጅምናስቲክ የሚሰጠው ሁለት እድል ብቻ ነው)። ፍቅር ግን አሁንም ሌላ እድል ይሰጠናል፣ በዚህ ጊዜ ምናልባት ጎብዘን ስድስት እናመጣ ይሆናል፤ ፍቅር ግን አሁንም ማበረታታቱንና እድል መስጠቱን ይቀጥላል። በዚህ ተደጋጋሚ አሳብ ወዴት እየሄድኩ እንደሆነ ሳይገባችሁ አይቀርም።

እግዚአብሔር ሌላ እድል ሊሰጠን አይሰለችም። ወደ እርሱ ተመልሰን እርሱን በሙላት እስክንለማመድ ድረስ ደግሞ ደጋግሞ ይሞክረናል። እኛን ወደ እርሱ ለማስጠጋት ያለው ፍላጎት እኛን ከእርሱ ለማራቅ የተነሱ ኃይሎች ካላቸው ውሳኔ ይበልጣል እንጂ አያንስም። የፈቃዳችንን መተባበር ብቻ ነው የሚጠብቀው። 1 ቆሮንቶስ 13ን እንደገና እናንብበው፣ በዚህ ጊዜ ግን ፍቅር በሚለው ቦታ እግዚአብሔር የሚለውን እያስገባን እናንብበው። እግዚአብሔር ይታገሳል፤ እግዚአብሔር በደልን አይቆጥርም፣ ይህም ማለት ላደረግነው ጥፋት ሁሉ ያስቀመጠው መዝገብ የለም ማለት ነው። እኛ ወደ ደህንነት እስክንመጣ ተስፋ አይቆርጥም።

እግዚአብሔር የሰው ፈቃድ የበላይ እንደሆነ ቢቆጥርም፣ ወደ እርሱ እስኪመለስ ድረስ ፈቃዳችንን ለመማረክ የሚያደርገውን ጥረት አያቋርጥም። ለዚህ ነው በየጊዜው ወደ ውሳኔ እንድንመጣ በተደጋጋሚ ዕድል የሚሰጠን።





## ፍቅር ዲሲፕሊን አለበት

ስለ ዲሲፕሊን መነጋገር ያስፈልገናል። ከኛ መካከል ማንኛችን ነን ዲሲፕሊን መደረግ የምንወድ? ብዬ ብጠይቅ ብዙዎቻችን እንገታችንን ከላይ ወደታች ሳይሆን ከጎን ወደጎን ነው የምናነቃንቀው። ነገር ግን ዲሲፕሊን ከሚወደን አባታችን ይመጣል። ምክንያቱም ዲሲፕሊን የፍቅር ባልደረባ ነው።

> *"እግዚአብሔር እንደ ልጆቹ ይዟችኋልና የተግሳጽን ምክር ታገሱ፣ ለመሆኑ*
> *አባት የማይቀጣው ልጅ ማነው? ልጆች ሁሉ በሚቀጡበት ቅጣት ተካፋይ*
> *ካልሆናችሁ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም"*
> *ዕብራውያን 12፥ 7-8።*

በዲሲፕሊን ውስጥ ቅጣት የማይቀር ነገር ነው፣ ማስታወስ ያለብን ግን የዲሲፕሊን ቅጣት የልጅነት ምልክት ነው። የዲሲፕሊን ቅጣት ለጉዳት የታቀደ ሳይሆን ጉድለትን ለማሳየት፣ ለማነቃቃትና ለማቃናት የሚደረግ ነው። አላማው ይህ ያልሆነ ቅጣት ግን ለጉዳት የታቀደ ስለሚሆን ከእግዚአብሔር አይደለም። ላጠፋነው ጥፋትና ለሠራነው በደል ሁሉ የእግዚአብሔር ቅድስና የሚጠይቀውን ፍርድ እንዴና ለዘለአለም ጌታ የሱስ ከፍሎታል። ስለዚህ እግዚአብሔር አሁን እኛን ለመቅጣት ግፊትም ፍላጎትም የለውም። ስለዚህ ፈቃዳችን ከእርሱ ፈቃድ ጋር እንዲስማማ ለማድረግ ሊያነቃንና ሊያነቃቃን ይወዳል። የእርሱ ወንድና ሴት ልጆች ሆነን ግንኙነት ለመፍጠር እንድንመርጥ ስለሚፈልግ ነው አንዳንዴ ጎነጥ የሚያደርገን፣ በማይመች ሁኔታም ወስጥ የሚተወን።

በይቅርታና በክፍያ (restitution) መካከል ያለውን ልዩነት ግልጽ ማድረግ አለብን። ይቅርታ ጌታ የሱስ በመስቀል ላይ በፈጸመው መስዋዕትነትና ድል ላይ የተመሠረተ የነፃ ስጦታ ነው። በነፃ የምንቀበለውም ነው፤ እኛም ለሌሎች በነፃ መስጠት ያለብን ነው። ክፍያ ግን በሕግ ወይም ፍትህ ላይ የተመሠረተ ላጠፋነው ወይም ላበላሸነው ምትክ የሚሆን ድጎማ ነው። ጻድቅ የሆነው አምላክ ያንን ከእኛ ይጠይቃል። ይቅርታ በኃጢአት ፀፀት ላይ ያተኮረ ሲሆን ክፍያ ግን በውጤቱ ላይ ያተኩራል።

ጌታ የሱስ እንዲህ አለ፦

*"የከሰሰህ ባላጋራህ እንዳያስፈርድብህ ዳኛውም ለአሳሪ አሳልፎ እንዳይሰጥህ በወህኒም እንዳትጣል፣ በመንገድህ ላይ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ። እውነት እልሃለሁ ከስፈረደብህ ግን የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከዚያ አትወጣም" ማቴዎስ 5፥ 25-26።*

ጌታ የሱስ የሚለን ለራሳችን ሰንል ከሌሎች ጋር ያለንን ሁኔታ ማስተካከል ይጠቅማል ነው። የቀረበብህን ክስ ቶሎ አስተካክል፣ ቅጣት ከበስተኋላ እየጠበቀህ ነው። ማድረግ የሚገባህን ቶሎ አድርገው፤ ምክንያቱም ከዚያ ማምለጥ አይቻልም። ቢያንስ ከርቸሌ ከመውረድ ትድናለህ። ፍርዱን እስከመጨረሻው አትጋፋ፣ የሚጠበቅብህን ማድረግ የማይቀር ነው፣ መደረግ አለበት፣ ከዘለአለማዊ ህጎችም ለማምለጥ መሞከር ከንቱ ልፋት ነው። እጅህን ስጥ፣ እግዚአብሔር እንዲያስገድድህ አታስገድደው።

እግዚአብሔር ያስገድዳል? ጌታ የሱስ የጠቀሰው ወህኒ የትና ምን አይነት እንደሆን አላውቅም። ግን የትም ሆን ምን በዚያ አካባቢ ዝር ላለማለት መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ያንን ነው ጌታ የሱስ እያስጠነቀቀን ያለው። መክፈል ያለብህን ለመክፈል እስቲያስገድድህ ድረስ አትጠብቅ።

ሌሎች ባንተ ላይ አለብህ የሚሉህን እዳ ቶሎ አስተካክል። የሚገባው ጊዜ አልፎ ሳይሄድ ነው መስተካከል ያለበት። መደረግ ያለበትን አድርገው። ያንን ለማድረግ ደግሞ ከአሁን የተሻለ ጊዜ የለም፤ እየቆየ ከሄደ እየባሰ ነው የሚሄደው። ለነገ ማሳደር አይጠቅምም፣ ማድረግ አለብህ! ማምለጥ አትችልም። ትንሽ ሲኦል ያለበት ገነት ወይም ትንሽ ገነት ያለበት ሲኦል የለም። የሰይጣን የሆነውን ይህን ወይም ያንን በልባችንም ሆን በአሳባችን ይዘን መቀመጥ አንችልም። ሰይጣናችን መሄድ አለበት፣ ፀጉሩም ላባውም እንኳን ሳይቀር።

እኔ እንደምገምተው መክፈል ያለበትን ላልከፈለች ነፍስ ፈውስ የላትም፤ መልሱ በመክፈል፤ እንደቃሉ በመኖር፣ ራስን በመካድ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ልጆቹን ጥሩ፣ ንጹሀንና ጽዱ ለማደረግ የወሰነ ነው። ልብ አድርጉ የምንነጋገረው ስለ ደህንነት አይደለም፣ ስለ ክርስትና ሕይወት ነው።





መክፈል ያለበት ይከፈላል፣ ያ አይቀርም፤ ለሌሎች ያለብንን ዕዳ ከተቀበልን ቶሎ ማስተካከሉ ጥሩ ነው። ጌታ ራሱ "ፈጥነህ ተስማማ" ነው ያለው። የምንነጋገረው ከእኛ ስለሚጠበቅብን ነው እንጂ እኛ ከሌሎች ከምንጠብቀው ጋር አይያያዝም። ለመሆኑ እነኝህ እዳዎች ምን ምን ይመስላሉ?

- ያልተጋደለ እውነተኛ ፍርድ
- እኛ ልናገኝ የምንፈልገውን ያህል ፍቅር መስጠት
- መተማመን
- ያልሰጠነውን ወይም የደበቅነውን ሙገሳ፣ ምስጋና መስጠት
- ልንሰጣቸው የምንችለው ግን ያለሰጠናቸው እድሎች
- ልንሰጣቸው የምንችለው ግን ያልሰጠናቸው መብቶች
- የበደልናቸውን በደል መናዘዝ
- ለፈጠርንባቸው ችግር ወይም ላደረስንባቸው ጉዳት መጸለይ
- ለጥያቄአቸው መልስ መስጠት
- የስልክ ጥሪአቸውን መመለስ
- መልካም እድልን ከልባችን መመኘት
- በደላቸውን ባይናዘዙም እንኳን ይቅር ማለት
- በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠሩ በማወቅ አክብሮት መስጠት

መክፈል የሚገባንን በመክፈል ትዕዛዙን እየጠበቅን

*"ይህም የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስክምንደርስ ነው" ኤፌሶን 4፥ 13።*

በዚህ ዲስፕሊን ውስጥ እንድናልፍ የሚያስችለንን አመለካከት የምናገኘው ከጌታ ነው። እኛም ለሌሎች ፍቅራችንን በመግለጽ፣ በትእግስትና በመቀባበል ሌሎችን በስህተታቸው ከመኮነን ወጥተን መተማመንና ተስፋን መለማመድ መማር አለብን። ይህ ሁሉ ሐተታ በቀላሉ ሲገለጽ መስጠት መቀበልን ፍጹም ያደርገዋል። የእግዚአብሔርን ፍቅር በሙላት መቀበል ለመቻል፣ ያልተወሰነ ፍቅር ለሌሎች መስጠት መቻል አለበን። ይህ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው። ምንም እንከን ያልተገኘበት ጌታ የሱስ እንኳን እግዚአብሔርን መታዘዝ ነበረበት።

*"ሁሉ ነገር ለእርሱና በእርሱ የሚኖር እግዚአብሔር ብዙ ልጆቹን ወደ ክብር ለማምጣት የድነታቸውን መሥራች በመከራ ፍጹም ሊያደርገው የተገባ ነው" ዕብራውያን 2፥10።*

መታዘዝ መረዳትን ይቀድማል የሚለውን አሳብ ለመረዳት ብዙ ጊዜ ነው የወሰደብኝ ምክንያቱም በተፈጥሮዬ በአዕምሮዬ የተረዳሁትን ነው ለማድረግ የሚቀለኝ።

## በማጣት ወስጥ ትርፍ

ይህ በማጣት ውስጥ የሚገኝ ትርፍ ፕሪንስፕል ጌታ የሱስ ያስተማረውና ሞዴል ያደረገው ነው። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እንድናልፍበት የሚያደርገን ሁኔታዎች ብዙ ያከሰረን ይመስለናል። እርሱ ግን መልካም አምላክ ነው። ለእኛም ያለው አላማ በጎና ያማረ ውጤቱ በረከት የሆነ ነው። ስለዚህ እንድናልፍበት በሚያደርግን ነገር ሁሉ ከጊዜ በኋላ ትርፍ እንዳለው ስለሚያውቅ በሁኔታችን ውስጥ እንድናለፍ ይተወናል። ነገር ግን ሁኔታችን ደግሞ እንዳያጠፋን ይጠብቀናል። በሁኔታችን ወስጥ አልፈን ስንወጣ ግን ከልምምዳችን የተነሳ በስለን አድገን ተምረን አውቀን ለራሳችንም ሆነ ለእግዚአብሔር የተሻልን ሰዎች ሆነን ነው። በማጣት ወስጥ የሚገኝ ትርፍ ማለት ይህ ነው።





# ምዕራፍ አስራ ሶስት

## የመጨረሻ ጥሪ

## ኑ! አብረን

ወደ ኃላ መለስ ብዬ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የገለጽኩዋቸውን ብዙ አሳቦች ስመለከት ልቤ የሚመኘውን አንድ ነገር ላካፍላችሁ እወዳለሁ። ልቤ ይህንን የእምነት ልምምድ በየቀኑ እንድትለማመዱት ሊያበረታታችሁ ይወዳል። ያ ብቻ አይደለም የልቤ ምኞት፤ ልቤ ኑ አብረን ይህንን የእምነት ጉዞ እንጓዝ በላቸው ይለኛል ጉዞ። ኑ አብረን የሚለው ከግሪኩ ፓራክሌሲስ (Paraklesis) የመጣ ቃል ሲሆን በእንግሊዝኛ ኤክሶርቴሽን (exhortation) ተብሎ ነው የተተረጎመው። ለማነቃቂያ ወይም ለማበረታቻ የሚውል ቃል ነው። ከባድ ግፊት ወይም አሰልቺ ጉትጎታ ወይም ጣትን ቀስሮ በማስፈራራት የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ አይደለም። ኑ አብረን፤ ጨዋነት ያለበት ቃል፤ ሰላማዊ ኅብረትን የሚያስተላልፍ አብረን እንሂድ፤ አብረን እናድርግ የሚል የደስታ ግብዣ የሚጋብዝ ነው። ኑ አብረን! የሚል ግብዣ በመጋበዝ ነው ይህን የመጨረሻውን ምዕራፍ መክፈት የምፈልገው።

እኔም ከአንተ ጋር ወይም ከአንቺ ጋር ጎን ለጎን ሆነን በዚህ የእምነት ጎዳና አብረን ብንጓዝ ራሴን እንደ እድለኛ እቆጥረዋለሁ። ይሄ ነው በመጽሐፉ መጨረሻ የማቀርብላችሁ ኤክሶርቴሽን። ብዙ ተጉዘን እዚህ መዝጊያው ላይ ስንደርስ እስቲ ተመልሼ ወደ መጀመሪያው ገጽ ልሂድና መጽሐፉን የከፈትኩበትን ጥቅስ አብረን እንድናየው ላምጣው።

*"የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?" (ሉቃስ 18፥ 8)።*

ወደ ፊት ወደዚያ ቀን በመመልከትና እንዴት ያለ ድንቅ ቀን እንደሚሆን በመገመት መጽሐፉን መዝጋት እፈልጋለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ የሚመጣበት ያ ቀን መቼ እንድሚሆን ማወቅ እንደማንችል በግልጽ ይናገራል።

*"ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ፤ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቅም" (ማቴ. 24፥ 36)።*

ያ ቀን በድንገት የሚሆን፤ ሳይጠበቅ የሚጠባ የሰርፕራይዝ ቀን ነው። ቢሆን ግን እናውቀዋለን። ጌታ የሱስንም ሁላችንም ስናየው እናውቀዋለን። ይህ የንጉሦች ንጉሥ ዘለዓለማዊና ሉአላዊ መንግሥቱን ይዞ ሲገለጥ ለማንም አጠያያቂ አይሆንም።

ጌታ የሱስን የማየቱ ሰርፕራይዝና ድንጋጤ ሲያልፍልን፤ የደስታውና የፈንጠዝያው እንፋሎት ሲሰክንልንና እያንዳንዳችን በግል ከእርሱ ጋር ቆይታ ስናደርግ ምን ይለን ይሆን?

ልጄ ሆይ እስቲ ሕይወትህን እንመልከተው፤ የአለፍክበትንም የእምነት ሕይወት አብረን እንመርምረው።

ልጄ ሆይ በማያቋርጥ እምነት እስካሁን በመኃዝህ (በመኃዝሽ) ምን ያህል ደስ እንደተሰኘሁ ልገልጽልህ (ልገልጽልሽ) እወዳለሁ። እምነትህ ሁሉን ቻይ የሆነውን እግዚአብሔርን አስደስቶታል። በተማርካቸው የእምነት እውነቶች ሁሉ በመመላለስ በእምነት ሕይወትህ ስታድግ ቆይተሀል፤ ለኔም እንደስጦታ የሆነልኝን ብዙ የተጠራቀመ የእምነትህን ታሪክ ደስ ብሎኝ ተቀብዬዋለሁ።

በተለይ ደግሞ የበለጠ የተደሰትኩበት በፈቃድህ ባደረከው ልምምድ ነው። ከተሳሳቱ የእምነት ልምምዶች ነፃ ሆነህ የፈቃድ እምነትን በመለማመድ ህዋሳትህ ሁሉ ደግሞ ከእኔ ጋር በመተባበር ምን ሚና መጫወት እንደነበረባቸው ተረድተህ ስላሳየኸው እርምጃም የበለጠ ተደስቻለሁ።

በነፃነት እምነትህን በተለያዩ ሁኔታዎች ስላሳየህና ስለተለማመድክ፤ ለአንተም የሚጠቅምህን ለየት ያሉ የእምነት ክንውኖች በሕይወትህ ስላሳየህ የእምነትህ ፍሬ ደስ አሰኝቶኛል።





በጣም ያረካኝ ልምምድህ ደግሞ የእምነትህን ጠላቶች ለይተህ አውቀህ ከመንገድህ እንዳያስቱህ ተጠንቅቀህ መኃዝህ ነው። አንተ በአለም ውስጥ እንጂ አለም ባንተ ውስጥ ሆኖ ስላላገኘሁ፤ ከዚህም ውሳኔህ የተነሳ የሚከተሉትን እነሎች ሁሉ አልፈሃል፦

- ባህላዊ የእምነት መሰናክሎችን
- ሰይጣን ያነጣጠረብህን መሳሪያዎችና ያስነሳብህን ውጊያዎች
- የተሳሳቱ መንፈሳዊና ክርስቲያን ነን የሚሉ ትምህርቶችን
- የውሸት አስተሳሰቦችንና ጥርጣሬዎችን
- ብቻዬን ልኃዝ ወይም ላድርገው የሚለውን መጥፎ ግፊት

ለነፍሴ የማያቋርጥ ደስታ የሆነልኝ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እልፎ እልፎም ቢሆን የሰጠህን የእምነት ስጦታ በድፍረት መለማመድህ ነው።

በእኔ ያለህን ነፃነት መጠበቅህንና ማሳደግህንም በደስታ አስተውያለሁ።

ሕይወትህን ወደኋላ ዞር ብዬ በምመለከትበት ጊዜ የራስህን ፈቃድ ከእኔ ፈቃድ ጋር ለማስታረቅ ያደረከውን ጥረት ሁሉ አይቻለሁ። ይህም ልቤ በጣም ደስ ካሰኛቸው ተግባርህ አንዱ ነው። ምክንያቱም ከዚያ የተነሳ ዛሬ እንዲህ ብዬ ከምጋብዛቸው አንዱ ስለሆንክ ደስ ይለኛል፤

*"እናንተ አባቴ የባረካችሁ ኑ! ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ" (ማቴ. 25፥ 34)።*

አንተ ውስጥ ተመልክቼ እምነትን ሳገኝ፤ የእኔን ባህሪያት በርዕዮትህ፤ በቅደም ተከተልህ፤ በሥራህ ወስጥ ሁሉ ማየት ችያልሁ።

አንተ ውስጥ ተመልክቼ እምነትን ሳገኝ፤ ሌሎች በአንተ እንደተረዱ፤ እንደተፈወሱ፣ ምሪት እንዳገኙ፤ እንደተማሩ፤ በጓደኝነትህም እንደተባረኩ ማየት ችያለሁ።

አንተ ውስጥ ተመልክቼ እምነትን ሳገኝ፤ ከአንተ አርአያነት የተነሣ ሌሎችም እምነትን ሲለማመዱ፤ ሲበረታቱ ማየት ችያለሁ።

አንተ ውስጥ ተመልክቼ እምነትን ሳገኝ፤ ማኅበረሰቡና ህብረተሰቡ በትለቁም በትንሹም ነገር ሲነኩና ሲበረታቱ ማየት ችያለሁ።

አንተ ውስጥ ተመልክቼ እምነትን ሳገኝ፤ የእኔ ቃል ኪዳኖች መፈጸማቸውን፤ የፍቅሬ ስጦታ የሆኑት በረከቶች መሟላታቸውን አይቻለሁ።

አብሬ መሆን የምፈልገው እንግዲህ እነኚህን ወይም እነኚህን የሚመስሉ የምስጋና ቃላት ከጌታ አፍ ልትሰማ ትችላለህ ብዬ ለማበረታታት ነው። ማመን ትችላለህ፤ አንቺም ተግባራዊ እምነት መለማመድ ትችያለሽ። ምክንያቱም እርሱ ሊረዳን ሁልጊዜ በቅርባችን ነው ያለው። እምነትህ/እምነትሽ መሆን እንደሚገባው ካልሆነ፤ እርሱ ሊረዳህ ይወዳል፤ ቢረዳሽ ደስ ይለዋል፤ ይህንን እመን፤ እግዚአብሔርን እመነው። የዚህ መጽሐፍ ዋናው ቁም ነገር ይህ ነው፤ እግዚአብሔርን የበለጠ እንድናምነው ለማድረግ። ኑ! አብረን በዚህ የእምነት ልምምድ እንሂድ… እግዚአብሔርን እንመነው።





## ዋቢ መጻሕፍት
## Sources used in this Book


Barcly, William. *The Letters to the Corinthains*. Philadelphia: The Westminister Press, 1975.

Buffett, Peter. *Life is What you make it*. Random House, Inc., New York, 2010.

Carpenter, Humphery. *The Inklings*. Boston: Houghton Mifflin Co., 1979.

Cowman, Mrs. Charles E. *Stream in the Desert Vol. 2*. Grand Rapids: Zondrvan, 1966.

DeArtega, William. *Quenching the Spirit*. Lake Mary, Fla. Creation House, 1992.

Edman V. Raymond. *They Found the Secret*. Grnad Rapids: Zondrvan, 1960.

Flynn, Mike. *The Mustard Seed Book*. Grand Rapids, Choosen Books, 1995.

Floyd, McClung. Finding Friendship with God. Ann Arbor, MI. Vine Books, 1992.

Flynn, Mike. *Holy Vulnerability*. Grand Rapids, Choosen Books, 1990.

Graham, Billy. *Just As I Am*. Harper Collins Publishers, New York, 1997.

Grubb, Norman. *Touching the Invisible*. Ft. Washington, Pa: Christian Litrature Crusade, 1978.

Lawrence, Brother. *The Practise of the Presence of God*. White Plains, NY: Peter Pauper Press Inc:, 1963.

Lewis, C.S. *Christian Reflections*. Edited by Walter Hooper. Grand Rapids: Eerdmans. 1967.

MacDonald, George. *Life Essential*. Wheaton: Harlord Shaw Publishers. 1974.

MacDonald, George. *Unspoken Sermons 3 vol*. Eureka, CA. Sunrise Books Publishers, 1989.

Meyer, Joyce. How to Hear From God. Warner Faith, Time Warner Group. USA, 2003.

Nee, Watchman. *What Shall This Man Do?* Ft. Washington, Pa.: Christian Literature Crusade, 1961.

Phillips, Michael R. *George MacDonald*. Minneapolis: Bethany House Publishers, 1987.

Shelley, L. Bruce. *Church History In Plain Language*. Woed Pulishing. Dallas, 1982.

Tittmann, George F. *What Manner of Love*. New York: Morehouse-Barlow Co. 1959.

Vine, W.E. *An Expository Dictionary of New Testament Words*. Grand Rapids Fleming H. Revell, 1966.





Williams, Charles, *War in Heaven*. Grand Rapids: Eerdmans, 1949.

*ሰይፉ ከበደ. የፈውስ ኪዳን.* Devine Power Evangelical Ministries. Riverside, CA. 2003.

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ቢኖርዎት ወይም

መጽሐፉን ለማግኘት በሚከተለው አድራሻ ሊደርሱን ይችላሉ

መንግሥቱ ለማ
3023 Becket St.
Pearland, TX. 77584
(713)436-3110
mlemma_2000@yahoo.com